# መሠረተ ሕይወት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች መማሪያ መጽሐፍ

## ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል

አዘጋጅ - ቀሲስ ሰሎሞን መሉጌታ

www.zeorthodox.org

ነሐሴ ፳፻፯ ዓ.ም

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፺ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት

## ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል

__አድራሽ፡-__
ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ

ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

**Email:- kesisolomon@gmail.com**
**Website;-www.zeorthodox.org**

*የኮምፒዩተር ሌይ አውት ዲዛይን፡- ልደት አስፋው*
*0911-350439*

## ማሳሰቢያ

www.zeorthodox.org

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል።

# መታሰቢያነቱ

ለቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም
መጥምቁ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ
ካቴድራል ካህናት፣ ዲያቆናት፣ የሰንበት
ት/ቤት አባላትና ምዕመናን ይሁንልኝ፡፡

# ምስጋና

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የአረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ፡፡ በመጨረሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም፡፡

www.zeorthodox.org

# ማውጫ


| ተ.ቁ | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| | መቅድም | I | | | |
| | መግቢያ | III | | | |
| 1. | የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የሮማ ካቶሊክ ልዩነት | 1 | | | |
| 2. | መንፈስ ቅዱስን መቀበልና በእኛ ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ | 8 | | | |
| 3. | መንፈስ ቅዱስ | 11 | | | |
| 4. | ሰማዕትነት | 16 | | | |
| 5. | የቃል ኪዳኑ ታቦት | 18 | | | |
| 6. | ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት(አንድ) | 21 | | | |
| 7. | ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት(ሁለት) | 26 | | | |
| 8. | የክብር አካል(አንድ) | 29 | | | |
| 9. | የክብር አካል(አንድ) | 33 | | | |
| 10. | እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም | 36 | | | |
| 11. | ገዳማዊ ሕይወት | 40 | | | |
| 12. | ሀልዎተ እግዚአብሔር | 44 | | | |
| 13. | የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ | 48 | | | |
| 14. | መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን | 54 | | | |
| 15. | የምሥራች | 57 | | | |
| 16. | የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ዳሰሳ(አንድ) | 59 | | | |
| 17. | የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ዳሰሳ(ሁለት) | 66 | | | |
| 18. | ቀዳም ስዑር | 72 | | | |
| 19. | ነቢዩ ዮናስና ነገረ ድኅነት | 75 | | | |
| 20. | የጾም ጥቅም (፩) | 79 | | | |
| 21. | የጾም መንፈሳዊነት(፪) | 83 | | | |
| 22. | የጾም መንፈሳዊነት(፫) | 87 | | | |
| 23. | ለከፍተኛ ትምህርት መዘጋጀት | 91 | | | |
| 24. | ቁማርተኛነት | 96 | | | |
| 25. | ወርቃማው ሕግ | 100 | | | |
| 26. | የጄሆቫ(የያህዌህ)ምስክሮች | 104 | | | |
| 27. | ሌሎችን ለክርስቶስ መማረክ | 108 | | | |


www.zeorthodox.org

| ተ.ቁ | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| 28. | ግብረ ሰዶማዊነት | 111 | | | |
| 29. | ሱሰኝነት | 115 | | | |
| 30. | የሐዋርያት ሥራ | 118 | | | |
| 31. | ክርስቲያንና የመገናኛ ብዙኃን (ሚድያ) | 122 | | | |
| 32. | ውርጃ | 126 | | | |
| 33. | ከሁሉ ጋር በሰላም መኖር | 130 | | | |
| 34. | አትፍረዱ | 134 | | | |
| 35. | ክርስቲያንና የንጽሕና ሕይወት | 138 | | | |
| 36. | ክርስቲያን እና ሥነ ልቡናዊ ጤንነቱ | 140 | | | |
| 37. | በዓላት(፩) - መግቢያ | 143 | | | |
| 38. | በዓላት(፪) - ዐበይት የጌታ በዓላት | 149 | | | |
| 39. | በዓላት(፫)- የጌታ ንዑሳን በዓላት | 155 | | | |
| 40. | በዓለ ሃምሳ በወጣቶች ሕይወት | 163 | | | |
| 41. | ማሸኮርመምና መሽኮርመም | 167 | | | |
| 42. | ወጣትነት እና ቤተሰባዊ ሕይወት | 170 | | | |
| 43. | ራስን ማክበር | 172 | | | |
| 44. | ከተቃራኒ ጾታ ጋር መቀላቀል | 175 | | | |
| 45. | ጊዜን በአግባቡ መጠቀም | 178 | | | |
| 46. | ሞርሞኒዝም | 180 | | | |
| 47. | የሕይወት አጋሬን እንዴት ልምረጥ? | 182 | | | |
| 48. | እምነትና ትዕግሥት | 185 | | | |
| 49. | ባለ ራእይ ወጣት | 187 | | | |
| 50. | የእግዚአብሔርን መንግሥት መገንባት | 190 | | | |

www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል። ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው።

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጐቱ አላቸው። ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል።

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሥራበት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ። ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ። በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ። አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ። በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው።

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር። በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ። እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ አሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት

www.zeorthodox.org

እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል፡፡

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል፡፡ በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ፡፡

ይኸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለኅትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ፡፡

***"እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል፡፡" ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪***

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ጥርት ያለውን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸው እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል፡፡ አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል፡፡

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል፡፡ በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሟያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል፡፡ ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው፡፡

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው፡፡ ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ፡፡ በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራ ኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸው መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸውም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ፡፡ በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ፡፡

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም፡፡ በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው፡፡ መምህራኑ ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣

www.zoorthodox.org

ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል፡፡ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና፡፡ ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል፡፡ በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርእሰ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኅበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጐብኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ፡፡ ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸውን ተረድተውና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

በመጨረሻም ይኽን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

www.zeorthodox.org

# የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የሮማ ካቶሊክ ልዩነት

## አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**:- ተማሪዎች በትምህርቱ መጨረሻ ስለ ሃይማኖታቸው አውቀው፤ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶና በሮማ ካቶሊክ መካከል ያለውን የሃይማኖት ልዩነት ለይተው ያብራራሉ።

**የሚጠና ጥቅስ**:- ***"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመንገድ ላይ ቁሙ፤ ተመልከቱም፥ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ፥ በእርስዋም ላይ ሂዱ፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ እነርሱ ግን፦ አንሄድባትም አሉ።"*** ኤር.፮፥፲፮

**ተጨማሪ ምንባብ**:- እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን የትኛዋ ናት? (በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ፤ ያልታተመ)

## መግቢያ

### የልዩነቱ ጥንተ ነገር

- የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን ሐዋርያት ከጌታችን እና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ባገኙት ትምህርት እና በተሰጣቸው ሰማያዊ ሥልጣን (ክህነት) ማቴ.፲፮፥፲፰-፲፱፤፲፰፥፲፰፣ ዮሐ.፳፥፳፪-፳፫ እንደመመሥረቷ፣ የተለያዩ መናብርተ ፓትርክና ተስፋፍተዋል። (መናብርተ ፓትርክና ማለትም የቤተክርስትያን አባቶች ማዕከላት ናቸው።)
- ከእነዚህም የሮም፣ የእስክንድሪያ፣ የቁስጥንጥንያ፣ የአንጾኪያ እና የኢየሩሳሌም ይጠቀሳሉ።
- በእነኚህ መናብርት የተቀመጡት አባቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ በተደረጉ ጉባኤያት ተመሳሳይ ውሳኔ እያስተላለፉ እስከ ፬፻፶፩(451) ዓ.ም ቆይተዋል።
- የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት እና ከአብ ጋር መተካከል የካደው አርዮስ በ፫፻፳፭(325) ዓ.ም በኒቅያ ጉባኤ፤ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት እና አምላክነት የካደው መቅደንዩስ በ፫፻፹፩(381) ዓ.ም በቁስጥንጥንያ ፤ ንስጥሮስ የተባለው የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ደግሞ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት ሁለት አካላት አሉት የሚለውን እና ድንግል ማርያም የወለደችው ሰው ነው የሚል የተሳሳተ ትምህርት በማስተማሩ እና ባለመታረሙም በ፬፻፴፩ (431) ዓ.ም በኤፌሶን ተወግዘዋል።

www.zeorthodox.org

- የመጨረሻው ዓለም አቀፍ ጉባኤ በኤፌሶን ከተካሄደ ከሃያ ዓመታት በኋላ የሮሙ ፓፕ ልዮን በኬልቄዶን ይህንኑ የንስጥሮስን ትምህርት መልኩን ለውጦ አስፋፍቷል፡፡ ***ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ ነው (diaphises)*** የሚል አዲስ ሐሳብ እና ሮም የጴጥሮስ መንበር ስለሆነና ጴጥሮስ ደግሞ ከሁሉም ሐዋርያት ስለሚበልጥ የሮሙ ፓፕ ከሁሉም የበላይ ነው፤የሚል ውሳኔ በኬልቄዶን አስወሰነ ፡፡
- ይህንን የተዛባ አስተሳሰብ እና የስሕተት ትምህርት ብዙዎች ቢደግፉትም ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ግን በኤፌሶን የተሸነፈው እና የተወገዘው ኑፋቄ መልኩን ለውጦ መምጣቱን በቃል እና በጽሑፍ አስረድተው ተቃውመውታል፡፡
- እግዚአብሔር በነቢዩ ከዚህ ዓይነቱ ስሕተት እንድንጠበቅ አስቀድሞ አስጠንቅቆናል፡፡ "***እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም፥ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ፥ በእርስዋም ላይ ሂዱ፥ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ እነርሱ ግን፦ አንሄድባትም አሉ፡፡"*** ኤር.፮፥፲፮፡፡
- በዛሬው ትምህርታችንም እግዚአብሔር በአንድነት፣በእውነት እና በፍቅር እንድንሄድባት የሰጠንን ቀናዋን የድኅነት መንገድ ትተው ሰዎች በራሳቸው መንገድ እና ሐሳብ በመሄዳቸው የተፈጠረውን አሳዛኝ ክሥተት የሚያመለክት አጭር ታሪክ እና የሃይማኖት ልዩነት እንማራለን፡፡

## የትምህርቱ ዋና ይዘት፡-

### የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡-

***ስያሜ***

ካቶሊካውያን የኒቅያን ጉባዔ ፫፻፳፭(325) ዓ.ም ተከትሎ ለቤተ ክርስቲያን ከተሰጣት ስም (ኦርቶዶክስ) ሌላ ካቶሊክ(የሁሉም ማለት ነው) የሚል ስም ለራሳቸው በ፬፻፶፩(451) ዓ.ም ሰጡ፡፡

***የመሠረተ እምነቱ ልዩነት***

www.zeorthodox.org

- የሮማው ፓፕ ልዮን በ፬፻፴፩(431) ዓ.ም የተወገዘውን የንስጥሮስን ኑፋቄ የሚቃወም የሚመስል ነገር ግን በአቀራረብ ያልተለየ ሐሳብ አቀረበ፡፡ ይህም ንስጥሮስ ሁለት ባሕርያት በሁለት አካላት አሉ፤ ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት ሁለት አካላት አለው፡፡ ሲል የተሳሳተውን ስሕተት ያረመ መስሎ ከሁለት አካል አንድ አካል ሆኖዋል፤ በባሕርይ ግን ሁለት ነው ብሎ አቀረበ፡፡

- በምክንያታዊ አቀራረብ እንኳዋን ብንመዝነው የተለያየ ባሕርይ ያላቸው አካላት ተዋሕደዋል ከተባለ አካል የሌለው ባሕርይ የለምና በባሕርይም ተዋሕደዋል ማለት ነበረበት ፡፡
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት አካላት(ግዙፉ የሰው አካል እና ረቂቁ የመለኮት ኣካል ተዋሕደው) አንድ አካል ካልን፤ በተመሳሳይ የሰው እና የመለኮት ባሕርያትም ከሁለትነት በተዋሕዶ አንድ ሆነዋል፡፡ ስለዚህ በክርስቶስ ሁለቱም ባሕርያት ለቅጽበተ ዓይን እንኳዋን ሳይጠፋፉ፣ሳይቀላቀሉ እና ሳይለያዩ በተዋሕዶ አሉ፡፡ልንል ይገባናል እንጂ በኤፌሶን የተወገዘውን የስሕተት ትምህርት ልንደግም አይገባም በማለት ኦርቶዶክሳውያን ተከራከሩ፡፡

## *የመለያየቱ ታሪካዊ ሒደት እና ውጤቶቹ*

- ካቶሊካውያኑም በዚህ ትምህርታቸው ዉስጥ የደበቁት የሮም የበላይነትን በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ላይ መጫን ነበር፡፡ ለዚህም ነው የጉባኤው መጨረሻ ከሁለት ባሕርይ ትምህርቱ ጋር የሮምን መንበር የበላይነት የደነገገው፡፡
- በዚህ መሠረት የሁለት ባሕርይ ትምህርታቸውን እና የሮም መንበር የበላይ ነው የሚለውን የተቀበሉላቸውን፤ የቁስጥንጥንያን እና በምሥራቅ ሮም የነበሩ በኋላም የምሥራቅ ኦርቶዶክስ የተባሉትን (በምሥራቅ አውሮጳ የሚገኙትን፡- ግሪክ፤ ሩሲያ፤ሩማኒያ…)ይዘው አንዲቱን ቤተክርስቲያን ለሁለት ከፍለው እና አስከትለው ወጡ፡፡
- እነዚህም የምድራዊውን ንጉሥ ፈቃድ (የሮም ቤተ መንግሥት ፍላጎት የነበረውን የሮም መንበር የበላይነት) ለመፈጸም በሥጋ ሐሳባቸው ተጉዘዋልና ጉባኤያቸውም ሆነ ውሳኔው በኦርቶዶክሳውያን ተቀባይነት የለውም፡፡
- የሮሙን ፖፕ ስሕተት የተቃወመው ዲዮስቆሮስም በሮማዋ ንግሥት ብርክልያ የቀረበለትን ማግባቢያ የዶግማው ስሕተት ካልታረመ እንደማይቀበለው ገለጠ፤ ምክንያቱም ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ዋነኛው ጉዳዩ ሃይማኖት ነበር፡፡ ሌሎችም ኦርየንታል ኦርቶዶክሶች(ግብጽ፤ ሶርያ፤ ሕንድ፤ አርመን፤ ኢትዮጵያ) የዲዮስቆሮስን ሐሳብ ደገፉ፡፡ ካቶሊካውያኑም በነበራቸው የሮም መንግሥት ድጋፍ አባቶታችንን አስገድደው ውሳኔያቸውን እንዲቀበሉ ለማድረግ ሞክረው ነበር፡፡
- የግብጽ ፓትርያርክ እንደነበረው እንደ ዲዮስቆሮስ ያሉት ቅዱሳን አባቶች ግን፤ ጥርሳቸው እስኪነቀል፤ ጽሕማቸውም እስኪነጭ ብዙ መከራ ተቀብለው፤ አንዲቱን፤ ሐዋርያዊቱን፤ ቅድስቲቱንና ዓለም አቀፋዊቱን ቤተክርስቲያን በምድራውያን ነገሥታት ሐሳብና ፈቃድ ሳትበረዝ ትምህርቷና ትውፊቷ ተጠብቆ እንዲኖር አድርገዋል፡፡

www.zeorthodox.org

- በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው የሮሙ ፓፕ አራፎን አልተቀበሉትም እንጂ "***የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ነንና ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የሮማን የበላይነት፣ አለቅነት ወይም ራስነት;*** እንዲቀበሉ ጥያቄ አቅርቧል። በስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ፖፕ ስቴፋን ***"እኔ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ነኝ ... በእግዚአብሔር ፈቃድ የዓለም ብርሃን ሆኜ ተልኬላችኋለሁ..."*** ብሎ ነበር።
- ይህ የበላይነት ስሜት ወደ ለየለት አምባገነንት አድጎ ኢክርስቲያናዊ ድርጊቶች እና ጦርነቶች በክርስትና ስም ይታወጁ ጀመር። በመስቀል ጦርነነት ስም የተፈጠሩ ስሕተቶችም የዚህ ስሕተት መገለጫዎች ነበሩ።

## የሮማ ካቶሊክ እና ምሥራቃውያን ኦርቶዶክሶች

እስካሁን ባየነው የሮማ ካቶሊክ እንቅስቃሴ ምሥራቃውያኑ ከሮማ ካቶሊክ ሳይለዩ ፤ እስከ አሥራ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከቆዩ በኋላ በ፲፻፶፬(1054) ዓ.ም ተለያዩ።

ለመለያየታቸውም ምክንያቶቹ የሮማ ካቶሊክ እንደገና የጨመረቻቸው ስሕተቶች እና እንግዳ ትምህርቶች ናቸው ይላሉ።እነዚህም ፦

1. ከመጽሐፍ ቅዱስ ሓሳብ (ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲያስተምር ከአብ የሚሠርጽ እያለ በተደጋጋሚ አስተማረ፤ ሐዋርያትም ይህንኑ አጽኑ እንጂ በአንድም ቦታ መንፈስ ቅዱስ ከአብ እና ከወልድ ይሠርጻል ብለው አላስተማሩም።) ካቶሊካውያን ግን ከዚህ በተቃራኒ በጸሎተ ሃይማኖት ላይ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ የሠረጸ ነው የሚል ጨመሩ።
2. " የሮም ፖፕ አይሳሳትም የሁሉም አለቃ ወይም ራስ ነው፤" ማለቷን ነው። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚያቀርቡት በማቴ.፲፮፥፲፰ ***" አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥"*** በማለት የተነገረውን ነው።

- እውነተኛ ትርጉሙ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ነው በማለት ቅዱስ ጴጥሮስ በሰጠው ምላሽ እንደተገለጠው፤ ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ መሠረትነት ላይ ትታነጻለች ማለት ነው። እነርሱ ግን በጴጥሮስ ላይ አጥንቱ ተከስክሶ ደሙ ሲፈስ ነው የተመሠረተችው በማለት በቂ ማገናዘቢያ ምንጭ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አብነት የሌለው ትምህርት ይሰጣሉ።

www.zeorthodox.org

ከዚህ በተጨማሪም የሚከተሉት ነጥቦች የካቶሊካውያኑን ሐሳብ ስሕተትነት ያስረዱናል።

- ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስን አለቃቸው አድርገው አልሾሙትም፡፡ በ፶፩(51) ዓ.ም በኢየሩሳሌም በተደረገው የሐዋርያት የመጀመሪያ ሲኖዶስ ሰብሳቢው ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ነበር፡፡ የሐ. ሥራ ፲፭፥፩-፴፩፡፡
- የቅዱስ ጴጥሮስን ሥልጣን በተመለከተ እጁን በመጫን አገልግሎቱን የፈጸመው በሮም ብቻ ሳይሆን በእስክንድርያ፤ በአንጾኪያና በሌሎችም ጭምር ነበር፡፡
- ሮማውያን ራሳቸው ቁልቁል ከሰቀሉት ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በማገናኘት ራሳቸውን የበላይ አድርገው የቆጠሩት ለሥልጣን ከነበራቸው ጥማትና ከአንዲቱ ቤተክርስቲያን አስቀድመው ከመለየታቸው የተነሣ ነው፡፡ ይህም ትምህርት በአንዲቱ ቤተክርስቲያን አስቀድሞ ያልነበረ እንግዳ ትምህርት ነው፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያት በትምህርት ገና ልጆች ሆነው ማን ታላቅ ሆኖ እንዲቆጠር (ማን ይበልጣል?) ብለው ሲከራከሩ፤ ጌታችን ጠርቶ የአሕዛብ ነገሥታትን የበላይነት መስሎ ***"እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ ነገር ግን ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ፥ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን።"*** ሉቃ.፳፪፥፳፯ እንዳለ፡፡ በቅዱሳን ፓትርያርኮችም መካከል የበላይ እና የበታች የሚባል የሥልጣን የበላይነት እና ክርክር መኖር የለበትም፡፡
- የጴጥሮስ ምትክ አይሳሳትም የሚሉትንም በተመለከተ እንኳን ምትክ የሆነው ራሱ ጴጥሮስ እንኳ ከደካማ ሐሳቡ የተነሳ በጌታችን እንደተገሠጸ፤ ቃሉንም ለመጠበቅ አለመቻሉንም መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል፡፡ ማቴ.፲፮፥፳፫፣ ማቴ.፳፮፥፴፬-፴፭፣ ማቴ.፳፮፥፷፱-፸፭፡፡ እግዚአብሔር ካላገዘው እንኳን መሬታዊው ሰው፤ ሰማያትም ንጹሐን አይደሉም፡፡ ኢዮብ.፲፭፥፲፭
- ይህ የካቶሊካውያን የተሳሳተ ከሥልጣን እና ከጥቅም ጋር የተቆራኘ አካሄድ ለሉተር መነሣት ምክንያት ሆኗል፡፡
- በሮማ ካቶሊክ ከመጻሕፍት እና ከትውፊተ ቤተ ክርስቲያን የወጣ የተሳሳተ መንገድ የተነሣ የምንለያይባቸው የእምነት መሠረቶች ወይም ትምህርቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

| ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን | የሮማ ካቶሊክ |
|---|---|
| 1. ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት አካላት አንድ አካል እንደሆነ በባሕርይም አንድ ነው ብለን እናምናለን። | 1. ክርስቶስ በአንድ አካል ሁለት ባሕርይ አለው ይላሉ። |
| 2. መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ የሠረጸ ነው ዮሐ.፲፭፥፳፮ | 2. መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ሠርጸአል ይላሉ። |
| 3. የማይሳሳተው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው ሰው ይስታል። | 3. ፖፑ አይሳሳትም፤ |
| 4. የክርስትና ማዕከል ኢየሩሳሌም ነበረች፤ ከዚያ በኋላ አልተወሰነም። | 4. ሮም የክርስትና ማዕከል ናት፤ |
| 5. የሐዋርያትን ጉባኤ እንኩዋን ጴጥሮስ አልመራውም። የሐዋ.፲፭፥፩-ፍጻሜው | 5. ቅዱስ ጴጥሮስ የሐዋርያት አለቃ ነውና የሮሙም ፖፕ የዓለም አብያተ ክርስቲያናትን በበላይነት መምራት አለበት ይላሉ። |
| 6. ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ምስጢራት የሚፈጸሙት በጳጳሳት እና በቀሳውስት ብቻ ነው። ዲያቆናቱ ካህኑን ይራዳሉ። | 6.ጥምቀት፤ ተክሊል እና ቅዱስ ቁርባን በዲያቆናት ። ሌሎቹ ምስጢራት ግን በቀሳውስትና በካርዲናሎች ይፈጸማሉ። |
| 7. ሁሉም ቅዱስ ሥጋውን እና ክቡር ደሙን ካልተቀበለ ሕይወት የለውም፡ ፡ ዮሐ.፮፥፶፬። | 7. ሥጋውና ደሙን ለቀሳውስት፣ ምእመናኑን ግን ሥጋውን ብቻ ያቆርቧቸዋል። |
| 8. ሥጋውን የሚያቀብለው ቄሱ ብቻ ነው። | 8. ቁርባኑን ለወንዱም ለሴቱም እንዲያቆርቡ ይሰጣሉ። ወንድም ሴትም ያቀብላሉ። |
| 9. በዕለት የተሠዋው መሥዋዕት አያድርም። ዘጸ. ፲፪፥፲ | 9. መሥዋዕቱን አዘጋጅተው - እያዋሉና እያሳደሩ ያቀብላሉ። |
| 10. ኦርቶዶክሳውያን መጋባት የሚችሉት ከኦርቶደክሳውያን ጋር ብቻ ነው። ነህምያ. ፲፫፥፳፯ | 10. ካቶሊካዊ ካቶሊካዊ ያልሆነን (ነችን) ሊያገባ (ልታገባ) ይችላል (ትችላለች)። |
| 11. በዝሙት ካልሆነ መፋታት አልተፈቀደም። ማቴ.፭፥፴፪። | 11. ፍቺ በዝሙትም የተነሣ ቢሆንም ፈጽሞ አይፈቀድም። |
| 12. በቀን ከአንድ ጊዜ በላይ በመንበሯ አይቀደስም። | 12. በአንድ መንበር በቀን ከአንድ ጊዜ በላይ ይቀድሳሉ። |
| 13. ቅዳሴዋ ከጥንት እንደነበረው በዓለሙ ሁሉ ተጠብቆ ይኖራልና ሳንበላ እናስቀድሳለን እንቀድሳለን። | 13. በልተው ጠጥተው ይቀድሳሉ፤ ይቆርባሉ፤ ያቆርባሉ። |
| 14. ጾም ከጥሉላት ምግብም መከልከል | 14. በጾም ወተት መጠጣት... ይቻላል። |

www.zeorthodox.org

## ምን ተማርን ?

1. በጥንታውያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት እና በካቶሊካውያን መካከል ያለውን የነገረ ሃይማኖት እና የሥርዓት ልዩነት፤
2. ቤተክርስተያን አገልግሎታችን ለራሳችን ጥቅም የምናስቀድመው ነገር መኖር የለበትም።
3. በሃይማኖት ብዙ ልንከፍል እንችላለን።

www.zeorthodox.org

# መንፈስ ቅዱስን መቀበል እና በእኛ ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

## ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ስንጠመቅ ስለተቀበልነው የመንፈስ ቅዱስ ሀብት መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል"* ፩ኛ. ዮሐ. ፪፥፳፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ግብረ ሐዋርያት ምዕ.፪ በሙሉ፡፡

### መግቢያ፡-

- ስንጠመቅ የተቀበልነው መንፈስ ቅዱስ በቅብዓተ ሜሮን ተሰጥቶናል፤ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእኛ ውስጥ ይኖራል፡፡ ስንመራበት በመንፈሳዊ ሕይወታች ን እናድጋለን፡፡
- በዛሬው ትምህርታችንም መንፈስ ቅዱስን መቼ እንደተቀበልን እንዴት እንደተሠጠን እና በውስጣችን ያለውን እርሱን በሕይወታችን መሪ ማድረግ እንደሚገባን እንማራለን፡፡

### ትምህርቱ፡-

#### በእኛ ውስጥ ያለ የመንፈስ ቅዱስ ሥራና ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት

1. **ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለን የመጀመሪያው ኅብረት የተወለድነው አዲስ ልደት (ዳግም ልደት) ነው፡፡**

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ እንዲህ ብሎታል፡፡ ***"... ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፡፡"*** ዮሐ.፫፥፭፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ***".... ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ መንፈስ ነው፡፡"*** (ዮሐ.፫፥፮) ብሎታል፡፡

ይህን አዲስ ልደት በጥምቀት እንደምናገኛውም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ገልጦልናል፡- ***"...የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን..."*** ቲቶ ፫፥፬-፭፡፡

www.zeorthodox.org

2. **በዚህ አዲስ ልደት መንፈስ ቅዱስ መታደስንና ይቅርታን ሰጥቶናል፡፡**

- ይህ ቀደም ባለው ጥቅስ ውስጥ ተገልጦአል፡፡ ቲቶ.፫፥፭ ***"በአዲስ ሕይወት.."*** (ሮሜ.፮፥፬)

ውስጥ ስለመመላለስና ስለ አሮጌው ሰዋችን የደማስቆው ሐናንያ ለጠርሴሱ ሳውል ከነገረው በኋላ እንዲህ ብሎት ነበር፦ *"አሁንስ ስለ ምን ትዘገያለህ? ተነሥና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ፣ ከኃጢአትህም ታጠብ።"* ሐዋ.፳፪፥፲፮።

❖ ቅዱስ ጴጥሮስም በበዓለ ሃምሳ ዕለት እንዲህ ብሎ ነበር። *"ንስሓ ግቡ፣ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።"* የሐዋ.ሥ.፪፥፴፰።

3. **በመቀጠልም በቅዱስ ሜሮን ምሥጢር በኩል መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ማደሩን እንመለከታለን።**

❖ ይህን ምስጢር ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ቅባት ብሎታል።*" እናንተ ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፤ሁሉንም ታውቃላችሁ።...እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል ..... ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ "* ፩ኛ ዮሐ.፪፥፳-፳፯

❖ ይህን ቅባት ስንቀባ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ሲያድር የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንሆናለን ቅዱስ ጳውሎስም፦ *"የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?"*(፩ኛ.ቆሮ.፫፥፲፮) ብሎናል። ከዚህ በተጨማሪም እንዲህ ብሎናል፦ *"ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀባላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?"* ፩ኛ ቆሮ.፮፥፲፱።

❖ ክርስቶስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር ይህ ማደሪያ ዘላቂና መጨረሻ የሌለው መሆኑን እንዲህ በማለት ገልጦአል፦ *"... ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፣ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፣ ነገር ግን ከእናንተ ጋር ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።"* ዮሐ.፲፬፥፲፮-፲፯።

❖ **እርሱም በአንድ ሰው ውስጥ ለዘላለም ስለሚኖር ምሥጢረ ሜሮን አይደገምም።**

❖ በሐዋርያት ዘመን መግቢያ ላይ የነበሩ አማኞች መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉት (የሐዋ.ሥ. ፲፱፥፮) ሲያምኑ እንደነበር ተገልጦአል።

www.zeorthodox.org

❖ የአማኞች ቁጥር እየባዛ ሲሄድ እጆችን ከመጫን ይልቅ ቅዱስ ቅብዓት መቀባት ተጀመረ።1ኛ. ዮሐ.፪፥፳-፳፯።

4. ***መንፈስ ቅዱስን መቀበላችን ብቻ በቂ ስላልሆነ ከእርሱ ጋር ኅብረት መፍጠራችን ግድ ነው።***

- እርሱ ከእኛ ጋርና በእኛ ውስጥ እንደሚሠራ እኛም ከእርሱ ጋር በመሆን በማንኛውም ዓይነት ሥራችን ሁሉ ተካፋይ እናደርገዋለን።

- በመንፈሳዊ ሕይወታችን ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለመረዳት ሁለት ነጥቦችን እንይ፡-

ሀ/ የሰው ሰብአዊ መንፈስ(ነፍስ) የሰውየውን ሥጋ ይመራል፡፡

- የመጀመሪያውን ነጥብ በማስመልከት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፡- ***"በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው ? ... " ፩ኛ ቆሮ.፪፥፲፩ "..... እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ ..."*** ፤ ***"ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፣ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው፡፡"*** ሮሜ. ፰፥፩-፯፡፡ በሌላም ቦታ፡- ***"በመንፈስ ተመላለሱ፣ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ፡፡"*** ገላ.፭፥፲፮፡፡

ለ/ የሰውን መንፈስ(ነፍስ) የሚመራው እግዚብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

ይህን ነጥብ በማስመልከትም እንዲህ ብሏል፡-***"በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና፡፡"*** ሮሜ.፰፥፲፬፡፡

ስለሆነም አንድ ሰው በሚሠራው ሥራ ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መመራቱ ግድ ነው እንላለን፣ ነውም፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስም የሰውየውን ማንኛውንም ዓይነት ሥራ ይካፈላል፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- በወልድ ውሉድ (በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጆች) ተብለናል፡፡ በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልን ሁላችን ስንጠመቅ ምስጢረ ሜሮን ተፈጽሞልናል፤ በዚህም መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል፡፡
- እርሱም ኃጢአት የማይስማማው ነውና እያሳዘንነውም አይለየንም፤ እንዲያውም መመለሳችንን እና መታዘዛችን እየጠበቀ ይታገሰናል፡፡
- በመምህራን፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች እና በመጻሕፍት እየመከረን ወደ ሕይወት መንገድ ይመራናል፡፡ በጸሎት፣ በንስሐ እና እርሱን በመታዘዝ ስንከተለውም በውስጣችን ይሠራል፡፡

## ተግባር፡-

www.zeorthodox.org

- ቅዱስ ጳውሎስ ለልጁ ለጢሞቴዎስ፤ ***"እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው እጆቼን በመጫኔ በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሣሣ አሳስብሃለሁ፡፡"*** ፪ኛ ጢሞ.፩፥፮ እንዳለው ወደ አባቶቻችን ካህናት በመቅረብ በንስሐ እና ጸሎት በመቀበል በልጅነት የተሰጠንን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንጠቀምበት፡፡

# መንፈስ ቅዱስ

# የመንፈስ ቅዱስ አሠራር በቤተ ክርስቲያን

## ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ፤ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ምስጢራት እንዴት እንደሚሠራ እና ቤተ ክርስቲያንን ለማሳደግ እና በእምነት ለመጠንከር እንዴት እንደሚያግዘን ለይተው ያብራራሉ፡፡፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይችልም፡፡"*** ዮሐ.፫÷፭

## ትምህርቱ፡-

ከዚህ በፊት እንደተማርነው፤ ሰባቱንም ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለመፈጸም ሦስት ነገሮች ያስፈልጉናል፡፡

፩. ምስጢራቱን ለመፈጸም የሚያስፈልጉ ነገሮች ለምሳሌ ውኃ ለጥምቀት.... ወዘተ

፪. ምስጢራቱን የሚፈጽሙ ካህናት /ጳጳሳት/ ፡፡

**በምስጢረ ጥምቀት፡** መንፈስ ቅዱስ የምንጠመቅበትን ውኃ በጸሎቱና በቡራኬው አማካይነት ለዳግመኛ ልደት የሚያበቃ አድርጎ ይለውጠዋል፡፡ ተጠማቂውንም ነፍሱን በማንጻትና አዲስ ሕይወት በመስጠት ይቀድሰዋል፡፡

- ***"ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን.... እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ÷ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን ፡፡ ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤው ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን ፤....ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና፡፡"*** ሮሜ.፮÷፫-፱
- ***"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይችልም፡፡"*** ዮሐ.፫÷፭

www.zeorthodox.org

- *"አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀብላችሁ.....የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።"* ሮሜ.፰፥፲፭-፲፮
- *" ያመነ የተጠመቀ ይድናል ፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።"* ማር.፲፮፥፲፮
- *"ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ፣ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፣እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም፤ያን መንፈስም በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን፣በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው።"* ቲቶ.፫፥፬-፯

**በምስጢረ ሜሮን፡-** በዚህ ምስጢር የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ስናገኝ፣በዚህም በእምነትና በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ የሚያስችለንን ኃይል እንቀበላለን፡፡ በተጨማሪም አካሎቻችንና ስሜቶቻችን ይቀደሳሉ መንፈሳዊ ዕውቀትም ይኖረናል፡፡

*"በክርስቶስ ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፣ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው።"* ፪ኛ ቆሮ.፩፥፳፩-፳፪ *"እናንተም ከቅዱስ ቅባት ተቀብላችኋል፣ ሁሉንም ታውቃላችሁ።"* ፩ኛ ዮሐ.፪፥፳

**በምስጢረ ንስሓ፡-** የሰው ልጅ ኃጢአት በመሥራት በመውደቁ እና ጥምቀት ደግሞ ሰውን የሚያድስ የማይደገምም ስለሆነ እግዚአብሔር ስንወድቅ ዳግመኛ የሚያነጻንን ምስጢረ ንስሐን በቤተክርስቲያን ሰጠን፡፡

- *"እውነት እላችኋለሁ፣ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።"* ማቴ.፲፰፥፲፰ *"ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፦ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸውም ተይዞባቸዋል አላቸው።"* ዮሐ.፳፥፳፪-፳፫

**በምስጢረ ቁርባን፡-** ካህኑ በሥርዓተ ቅዳሴው ሲጸልይ መንፈስ ቅዱስ ለሁለት ነገር ይመጣል ፡- ኅብስቱንና ወይኑን የጌታ ሥጋና ደም አድርጎ ለመለወጥ፤ እና የክርስቶስን ሥጋና ደም ለመቀበል የበቃን እንድንሆን ሊያስችለን፡፡

www.zeorthodox.org

**በምስጢረ ቀንዲል፡-** ካህኑ ሕሙሙን በቅዱሱ ቅባት (ቀንዲል) ሲቀባው በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ሥራ በሽተኛው በሥጋና በነፍስ ይድናል፡፡

***"የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል፤ ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትም ሠርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል"*** ያዕ. ፭፥፲፭ ***"ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱአቸው።"*** ማር.፮፥፲፫

**በምስጢረ ተክሊል፡-** ሁለቱ ሰዎች አንድ የሚሆኑበት ይህ ምስጢር በቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ ካለው አንድነት ጋር ተመሳሳይ ነው።

***"ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ። ሚስቶች ሆይ፣ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ።"*** ኤፌ.፭፥፳፩-፳፪ ***"ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ይሆናሉ።"*** ማቴ.፲፱፥፭ ይህ ምሉዕ የሚሆነውና የሚፈጸመውም በመንፈስ ቅዱስ ነው።ሁለቱ ሰዎች በእምነት፣በፍላጎት፣በዓላማቸውና በፍቅር አንድ ይሆናሉና።

**በምስጢረ ክህነት፡-** በቤተ ክርስቲያን ሦስት የክህነት መዓርጋት አሉ። ዲያቆን፣ ቄስ ጳጳስ፤ መንፈስ ቅዱስ በሁሉም መዓርጋት ይሠራል። እያንዳንዱ በሥራውና ለእግዚአብሔር በሚሰጠው አገልግሎትም እንዲከናወንለት ይረዳዋል።

***ዲያቆናት፡-*** በጥበብና በብቃት ሕዝቡን የሚያገለግሉበትን ጸጋና ምክር ከመንፈስ ቅዱስ ያገኛሉ።

**ካህናት(ቀሳውስት)፡-** ሕዝቡን ለማገልገል የሚያስችላቸውን መንፈሳዊ ምሪት እና ብቃትን ከመንፈስ ቅዱስ ይቀበላሉ

**ጳጳሳት፡-** አብያተ ክርስቲያናትን የመከታተልና የማስተዳደር ሓላፊነትን እንዲወጡ መንፈስ ቅዱስ ያግዛቸዋል።

***መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን ለማሳደግ ይሠራል፤*** በሐዋርያት ሥራ የመንፈስ ቅዱስን ኃይልና ሥልጣን የምናነብባቸው ታሪኮች ተጽፈዋል። የሐዋርያትን ስብከት ሲመራና ቤተ ክርስቲያንንም ሲያሳድግ እናገኛለን። የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡ። የሐዋ.፰፥፳፮-፵፣፲፥፲፯-፴፫፣፲፫፥፪-፬

**የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ምእመናን ለማሳደግ፡-** ሦስቱ አካላት (ሥላሴ) በእኛ መዳን ውስጥ ይሳተፋሉ። አብ በፍቅር፤ ወልድ በመሥዋዕትነትና በጸጋ፤ መንፈስ ቅዱስ በመምራትና በተሰጥዖ። ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ***" የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣የእግዚአብሔርም ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን"*** ያለው። ፪ኛ ቆሮ.፲፫፥፲፬

www.zeorthodox.org

በርግጥም ይሄን የሚደግፉ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እናገኛለን። ከሦስቱ (ሥላሴ) ርዳታና አሠራር ውጪ ማንም እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንና ሰማያዊ ርስት ማግኘት አይችልም።

የሚከተሉት መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ያለውን አሠራር ያሳዩናል።

**የእግዚአብሔር ልጅነት፡-** በመንፈሳዊ ልደት (ጥምቀትና ሜሮን) እና በክርስቶስ አዳኝነት ስናምን በመንፈስ ቅዱስ አሠራር የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን፡፡ ***"በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና፡፡ አባ አባት ብለን....የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀብላችሁ.....የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል፡፡" ሮሜ.*** ፰፥፲፭-፲፮

**ወደ እውነት መምራት፡-** መንፈስ ቅዱስን በውስጣቸው ያሳደሩ ሰዎች ፍላጎቶቻቸውን ይቆጣጠራሉ፡፡ እርሱም ወደ እውነት መርቶ ያደርሳቸዋል፡፡***"እኔም አብን እለምናለሁ፤ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፡፡ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ፡፡" ዮሐ.*** ፲፬፥፲፮-፲፯

***"አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤ እኔም የነገርኳችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል፡፡" ዮሐ.***፲፬፥፳፮ ***"የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤ እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ፡፡" ዮሐ.***፲፭፥፳፮

**ጥበብን መግለጥ፡-** መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው መንፈሳዊ ጥበብ እና ሰማያዊ ነገርን መግለጥ ይሰጠዋል፡፡ ***"የክብር አባት....እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ፡፡ ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንደሆነ በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤"*** ኤፌ. ፩፥፲፯-፶፱

**የመንፈስ ንቃትና ንጽሕና ይሰጠናል፡-** መንፈስ ቅዱስ ያድለናል፣ ያነጻናል እንዲሁም ጠባዮቻችን ቀስ በቀስ ያድስልናል፡፡

***"ወይስ ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን ? አትሳቱ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙትን የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡፡ ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፣ ተቀድሳችኋል፣ ጸድቃችኋል፡፡"*** ፩ኛ ቆሮ.፮፥፱-፲፩

**እንድንጸልይ ያደርገናል፡-** መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ከድካማቸው እንዲበረቱ እና ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንደሚገናኙ ያስተምራል፡፡ ለምሳሌ ስንጸልይ ፡-

www.zeorthodox.org

*"መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይናገር መቃተት ይማልድልናል (ባለማወቅና በድካም የምናደርገውን ጸሎት ተሰሚ ያደርግልናል ያርምልናልም።) ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደሆነ ያውቃል፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና። (እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲጸልዩ ያደርጋቸዋል)"* ሮሜ.፰፥፳፮-፳፯

**በመከራችን ያጸናናል፦** "አጽናኙ" (በግሪክ - ጰራቅሊጦስ) መንፈስ ቅዱስ በኃዘናችን የሚያጸናንና የሚያበረታንም ነው።*"እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል።"* ዮሐ.፲፬፥፲፯

**ምን ተማርን ?**

(1.) መንፈስ ቅዱስ በምስጢራት ይሠራልና የእግዚአብሔርን ጸጋዎች ሁሉ እንቀበላለን።

(2.) መንፈስ ቅዱስ በውስጣችሁ እየሠራ መሆኑን መርምሩ። ካልሆነ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራችሁ ለምኑ።

(3.) በመንፈሳዊ ሕይወት የመጀመሪያ ደረጃ ንስሓ ነው። መንፈስ ቅዱስም ንስሓ እንድንገባ ይረዳናል። ከዚያም እንደ ፍቅር፣ ራስን መካድ፣ ሰማያዊ አንድነት… ወዳሉት የመንፈስ ፍሬዎች ይመራናል። በዚህ ሁሉ ውስጥም ቅዱሳንን የረዳቸው እና ወደ ጥልቅ መንፈሳዊ ደረጃ ያበቃቸው መንፈስ ቅዱስ ይረዳናል። መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ እንዲሠራ በትጋት እንለምን።

www.zeorthodox.org

# ሰማዕትነት

## አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች በእምነት መጽናትን በትሕትና መሥራት የሚያስገኘውን ድል አውቀው ያስረዳሉ እነርሱም በተግባር ይገልጣሉ፡፡

**ጥቅስ፡-** "እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ድል ነሱት፤ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም፡፡"ራእ. ዮሐ.፲፪÷፲፩፡፡

### የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ፡-

#### ሀ. አሸናፊዎች እነማን ናቸው ?

- ❖ ሕይወታቸውን ለሞት አሳልፈው የሠጡ ሰማዕታት ናቸው፡፡
- ❖ እምነታቸውን ጠብቀው በወንጌል ቃል መሠረት ላይ የቆሙ፣ንስሓ የገቡ ቅዱሳን ናቸው፡፡
- ❖ የእግዚአብሔርን መስቀል የተሸከሙ መነኮሳት፣ባሕታውያን እና ሰማዕታት ናቸው፡፡
- ❖ የቅድስና ሥራ የሠሩ፣ ለዓለማዊ ነገር ባለመንበርከካቸው በየቀኑ ስቃይ የሚደርስባቸው አማኞች ናቸው፡፡
- ❖ ዓለምንና ሥጋዊ ፍላጎትን ፣ ዲያቢሎስን እና ምኞቱን ያሸነፉ ናቸው፡፡ በንጽህና በድንግልና፣ በጾም በጸሎት የተጋደሉ ናቸው፡፡
- ❖ ጥላቻ፣በቀልን ያሸነፉ ናቸው፡፡ታድያ እንዴት አሸነፉ ?

#### 1. በበጉ ደም አማካኝነት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደም፣ሰማዕታቱ የራሳቸውን ደም ስለ ክርስቶስ እስከ ማፍሰስ ኃይል ሰጣቸው፡፡ ይህም ለሚያምኑበት ሁሉ ኃይልን በመስጠት ተጋድሎአቸውን እንዲፈጽሙ የመንፈስ ጥንካሬ ሰጣቸው፡፡

www.zeorthodox.org

#### 2. ያመኑበትን በተግባር በማሳየት እና በመኖር

- የሰማዕታት አኑዋኑዋር፡- እውነተኛ ሕይወት፣ ፍቅር እና ትሕትና ነው ፡፡ የእግዚአብሔር ሰው እንዴት መኖር እንዳለበት በምስክርነት ፣ በአርአያነት የሚያሳዩበት ኑሮ ነው፡፡
- የወንጌልን ቃል በተግባር በመተርጎም እንደ ትእዛዙ እና ሥርዓቱ በመኖር አስመስክረዋል፡፡
- ይህንንም ሕይወታቸውን ለሞት አሳልፈው እስከ መስጠት ደርሰዋል፡፡ አባቶቻችን ቅዱሳን

እና ሰማዕታት በምድር ሕይወታቸውን በተጋድሎና በብዙ መከራ ጸንተው በማሳለፋቸው ደስተኛ የሆነ ሕይወት አልነበራቸውም፡፡ ይሁን እንጂ በውስጣቸው ከፍተኛ የሆነ መረጋጋት፣ ሰላም እና ደስታ ነበራቸው፡፡ በሕይወት ዘመናቸው ከዓለማዊ ምኞት ራሳቸውን ገድለዋል፡፡፡ ስለሆነም ራሳቸውን ለሰማዕትነት (ለምስክርነት) አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡

## ለ. ምሳሌዎች የሆኑ

- ቅዱስ ዮሐንስ (መጥምቀ መለኮት)፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቅዱስ መርቆሪዎስ፣ ቅድስት አርሴማ ፡፡

## ሐ. ሰማዕትነት በአሁኑ ዘመን

- ለአንዳንድ ሰዎች ይህ ዘመን የሰማዕታት ጊዜ አይደለም፡፡ ነገር ግን ራስን ከኃጢአት መጠበቅ፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በታማኝነት መጠበቅ፣ የሥጋ ምኞትን እና ፍላጎትን በመቆጣጠር የሚደርስብንን ፈተና በምስጋና መቀበል በመሳሰሉት ሁሉ መትጋት ሰማዕትነት ናቸው፡፡

## መ. ተግባር

- እንደ ሰማዕታት ለመኖር በጸሎትና በቅድስና ሕይወት ተግታችሁ ራሳችሁን በማሠልጠን እነርሱን መስሎ በመኖር ለሰዎች ምሳሌ ለመሆን ጥረት አድርጉ፡፡
- በሰማዕታት ሕይወት ላይ ጥናት በማድረግ የሰማዕታትን ሕይወት ለሌሎች አስታውቁ፡፡ ተማሪዎች የአንድ ሰማዕትን በዓል በመዘከር አክብሩ)፡፡
- የሰማዕታትን ገድል አንብቡ፡፡

www.zeorthodox.org

# የቃል ኪዳኑ ታቦት

## አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች፤ በመገናኛው ድንኳን በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የነበሩትን አውቀው፤የቃል ኪዳኑን ታቦት ትርጉም፣ አገልግሎት እና ታሪክ በሚገባ ተገንዝበው ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *" በዚያም ከአንተ ጋር እገናኛለሁ፡፡ በስርየት መክደኛውም ላይ ሆኜ እነጋገርሃለሁ፡፡ "* ዘጸ.፳፭፥፳፪፡፡

### መግቢያ፡-

- በመገናኛው ድንኳን ከነበሩት ሥፍራዎች የተለየው ቅድስተ ቅዱሳን ነው፡፡
- ቅድስተ ቅዱሳኑም ከሌሎቹ በመጋረጃ ተለይቶ በውስጡ የቃል ኪዳኑን ታቦት ብቻ ይዞ ይኖር ነበር፡፡
- የሕዝቡንም ኃጢአት ለማስተስረይ የመሥዋዕቱን ደም ሊረጭ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት የሚቻለው ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነበር፡፡ ይኸም ብቸኛ ለሆነው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት ምሳሌ ነበር፡፡

## የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ

- እስራኤል በሲና ተራራ እያሉ እግዚአብሔር ተገልጦ ዐሥር ትእዛዛት የተጻፉበትን ጽላት ለሙሴ ሰጠው፡፡

- በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ልዩ የሆነው የቃል ኪዳኑ ታቦት ነው፡፡ እርሱም የእግዚአብሔርን መኖርና ለእስራኤላውያን የገባውን ቃል ኪዳን የሚያመላክት ነበር፡፡
- የቃል ኪዳኑም ታቦት ከግራር እንጨት የተሠራ ሆኖ በውጭና በውስጥ በወርቅ የተለበጠ ነው፡፡
- በታቦቱ ውስጥም በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ ዐሥርቱ ሕግጋት የሚገኙባቸው ሁለት ጽላቶች ነበሩ፡፡
- የቃል ኪዳኑ ታቦት በስርየት መክደኛ ተሸፍኖአል፡፡ በላዩም የተዘረጋ ክንፍ ያላቸው ሁለት የኪሩብ ሥዕል አለ፡፡ ክንፉቸውም እርስ በርሱ በመነካካት የስርየት መክደኛውን ይሸፍነው

www.zeorthodox.org

ነበር፡፡ ይኸውም እግዚአብሔር ሙሴን ሲያነጋግረው ድምፁ የሚሰማበት ሥፍራ የእግዚአብሔር ዙፋን ነበር፡፡

የቃል ኪዳኑ ታቦት እስራኤላውያንን በምድረ በዳ ወደ ተስፋይቱ ምድር መርቷቸዋል፡፡ ሌዋውያኑ ይሸከሙት ነበር፡፡ ከተፈቀደላቸው ካህናት በቀር ማንም ሰው ታቦቱን ሊነካ አልተፈቀደለትም፤ ቢነካውም ይሞት ነበር፡፡

## የቃል ኪዳኑ ታቦት ታሪክና ጉዞ

- ❖ ሙሴም ሁለቱን ጽላቶች ወስዶ በታቦቱ ውስጥ አኖራቸው፡፡ በቅድስተ ቅዱሳኑም ውስጥ አስቀመጠው፡፡ ቀጥሎም የእግዚአብሔር ክብር በደመና መልክ ሥፍራውን ሁሉ ሞላው፡፡ ከሰባት ሳምንታት በኋላም ደመናው ራቀላቸውና መጓዝ ጀመሩ፡፡ ዘወትርም ደመናው በጠዋት፣ የእሳት ዐምድ ደግሞ በማታ ሲታይ፤ በአንድ ቦታ ተሰብስበው በመቆየት ወደላይ ሲመለስ ጉዞአቸውን ይቀጥሉ ነበር፡፡
- ❖ ሕዝበ እስራኤል የሲናን ተራራ ትተው ሲጓዙ፣ የዮርዳኖስን ወንዝ ሲሻገሩ እንዲሁም የኢያሪኮን ቅጥር (ግንብ) ሲዞሩ የቃል ኪዳኑ ታቦት መሪያቸው ኃይላቸውም ነበር፡፡
- ❖ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ታቦቱን ይዘው መዋጋት ፈለጉ፡፡፩ኛ ሳሙ. ፬÷፬፡፡ ነገር ግን ተሸንፈው ታቦቱ ተማረከ፡፡፩ኛ ሳሙ.፬÷፫
- ❖ ፍልስጥኤማውያን ታቦቱን ወስደው በጣዖት ቤት ዳጎን ከተባለው ጣዖት ሥር ሲያስቀምጡት ጣዖቱ ተሰባበረ፡፡ ፩ኛ.ሳሙ.፭÷፪-፯ ታቦቱን ጌት ወደ ተባለው የፍልስጥኤማውያን ከተማ ሲያዞሩት፡፡ የጌት ሰዎች በአዲስ በሽታ ተመቱ፡፡፩ኛ ሳሙ.፭÷፰-፱፡፡ በኋላም አስቀሎና ወደ ተባለው ከተማቸው አዞሩት፤ በመጨረሻም በሁለት ላሞች ላይ ተቀምጦ ወደ ዕብራውያን በቤት ሳሚስ በኩል ተመለሰ፡፡፩ኛ ሳሙ.፮÷፲፫-፲፮
- ❖ የእግዚአብሔርም ታቦት በቂርያት ይዓሪም ወደሚገኘው ወደ አሚናዳብ ቤት ተወሰደ፡፡ በዚያም ለሃያ ዓመታት ተቀመጠ፡፡ ፩ኛ ሳሙ.፯÷፩-፪ በኋላም በንጉሥ ዳዊት ዘመን ወደ ኢየሩሳሌም ተወሰደ፡፡ ፪ኛ.ሳሙ.፮÷፩ እስከ ፍፃሜ፡፡
- ❖ በመቀጠልም ንጉሥ ሰሎሞን ታላቁን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሠርቶ ታቦቱን በቤተ መቅደሱ በኢየሩሳሌም አኖሩት፡፡ ያ ታቦት ዛሬ በአገራችን በአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በክብር ተጠብቆ ይገኛል፡፡
- ❖ የቃል ኪዳኑ ታቦት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ከቦታ ቦታ መዘዋወሩ ጌታችን ሰው ሆኖ ሰውን ለማዳን ተአምራትን በማድረግ በየሥፍራው ሁሉ የመዘዋወሩ ምሳሌ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

- ❖ ውስጡ በወርቅ ተሞልቶ በውጭ በድንኳን የተሸፈነው የመገናኛው ድንኳን አምላክ ሆኖ ሳለ በፍጹም ትሕትና የባርያውንም መልክ ይዞ የተመላለሰው የጌታችን ምሳሌ ነው፡፡ ኢሳይ.፶፫፥፪-፫፡፡

ታቦቱ በወርቅ የተለበጠ ነበር፤ ወርቅ ንጹሕ እንደሆነ ድንግል ማርያምም ንጽሕት ናት፡፡

የመገናኛው ድንኳን እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝበት ሥፍራ ነበር፡፡ በታቦቱ እግዚአብሔር ይገለጥበት እንደ ነበር በእውነተኛይቱ ማደርያው በድንግል ማርያምም ክርስቶስ ተገልጦ ዓለሙን አድኖአል፡፡

## ተግባር፡-

- እግዚአብሔር በምድር ከርሱ ጋር የምንገናኝበትን ሥፍራ እንድናዘጋጅ ካዘዘን ከርሱ ጋር በአንድነት ሆኖ በተሰበሰበ ልብ ጸሎት ማድረግ ያስፈልገናል፡፡
- የመገናኛውን ድንኳን ከቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ጋር በማነጻጸር ልዩነታቸውን ግለጹ፡፡
- የቃል ኪዳኑ ታቦት በመገናኛ ድንኳን ውስጥ የተቀመጠበት ሥፍራ ምን ይባላል?
- በቃል ኪዳኑ ታቦት ውስጥ የተቀመጠው ምንድር ነበር?
- የቃል ኪዳኑ ታቦት የተከበበው ወይም የተሸፈነው በምን ነበር?
- የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣው ማን ነበር?

www.zeorthodox.org

# ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት(አንድ)

## ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የሰማያዊውን ሥልጣነ ክህነት አደራና ሓላፊነት ኦርቶዶካሳዊት ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸውን ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ለይተው ያመለክታሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***“ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት ”*** ማቴ.፲፰፥፲፯

## መግቢያ፡-

- ቅዱሳን ሐዋርያት ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተምረው መዘጋጀታቸውን፤ ከዚያም በኋላ የማሰር የመፍታት ሰማያዊ ሥልጣን እንደሰጣቸው በወንጌል ተጽፎአል። ማቴ.፲፮፥፲፮-፲፱፤፲፰፥፲፰፤ ዮሐ.፳፥፳-፳፫
- የዚህ ሐዋርያዊ ሥልጣን ወራሽ ቤተ ክርስቲያን ናት፤ ቤተ ክርስቲያንም ይህንኑ ፈለግ ተከትላ የሰማያዊውን ሥልጣነ ክህነት አደራና ሓላፊነት ለመፈጸም የሚያስችሉ አበውን የሚያፈሩ መምህራን፣ ትምህርት ቤቶች፣ ገዳማት እና አድባራት አሉዋት።
- ቤተ ክርስቲያንን የመምራት ሓላፊነት የተሰጣቸው እና የተመሰከረላቸው አባቶች በትምህርት፣ በጸሎት እና ለመንጋው ምሳሌ በመሆን ቤተ ክርስቲያንን ያስተዳድራሉ፣ ምእመናንን ይጠብቃሉ ይመራሉ። እነዚህ አባቶች በተለያየ መዓርገ ክህነት ያገለግላሉ። የመጨረሻው ማዕረግም ጵጵስና ነው። የጳጳሳት ጉባኤም ቅዱስ ሲኖዶስ ይባላል።
- ይህ ጉባኤ ዓለም አቀፋዊ እና አገራዊ ሲኖዶሳት (international and local synod) የሚባሉ ጉባኤያትን ያካሂዳል። በእነዚህ ጉባኤያትም ትምህርተ ሃይማኖት፤ ቀኖና እና የቤተ ክርስቲያን አቋማት የመጨረሻውን ውሳኔ ያገኛሉ።
- በዛሬው ትምህርታችንም ከእነዚህ ጉባኤያት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተካሄዱትን እና ቤተ ክርስቲያናችን ከምትቀበላቸው ሦስት ዓለም አቀፋዊ ጉባኤያት ስለመጀመሪያው ጉባኤ ኒቂያ እንማራለን።

www.zeorthodox.org

## ትምህርቱ፡-

- በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀዳሚና ተቀባይነት ያላቸው፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የምትቀበላቸው በኒቅያ በ፫፻፳፭(325) ዓ.ም በቆስጥንጥንያ

፫፻፹፩(381) ዓ.ም፣ በኤፌሶን በ፬፻፴፩(431) ዓ.ም የተደረጉትን ሦስት ዐበይት ጉባኤያትን ነው፡፡

## 1. ጉባኤ ኒቅያ

- ኒቅያ በጥቁር ባሕር ወደብ አካባቢ የምትገኝ ከተማ ናት፡፡ በተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ የተወገዘው አርዮስ ከአንጾኪያ ያመጣውን የክህደት ትምህርት በእስክንድርያ ለማስተዋወቅ ‹‹ታሊያ›› ማዕድ የሚሰኘውን የግጥም መጽሐፉን ተጠቅሞ ትምህርቱን ማሰራጨት ጀመረ፡፡
- ይህን የክህደት ትምህርቱን የእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስ እለእስክንድሮስ ሊያስተወው ቢሞክርም አሻፈረኝ አለ፡፡ እለእስክንድሮስም በማለቱ ወደ አንድ መቶ የሚጠጉ የሊብያንና የእስክንድሪያን ኤጲስ ቆጶሳት ሰብስቦ በ፫፻፳(320) ዓ.ም አርዮስ የኑፋቄ ትምህርቱን ማስተማር በጀመረ በሁለት ዓመቱ አውግዘው ለዩት፡፡
- አርዮስ ግን ከክህደቱ ራሱን ከማረም ይልቅ የእለእስክንድሮስን ስም ማጥፋት ጀመረ ፤ እለእስክንድሮስ የሰብአልዮስን ክህደት ያስተምራል እኔንም አውግዞ አባረረኝ አለ፡፡ የቀድሞ ጓደኛው የነበረው የኒቆሚዲያ ኤጲስ ቆጶስ አውሳቢዮስ የራሱን ተከታዮች ሰብስቦ አርዮስ ከእስክንድሪያ የተባረረው በግፍ ነውና ከውግዘቱ ፈተነዋል ብለው ተናገሩ፡፡
- ይህን ጉባኤ የመራው እራሱ አውሳብዮስ ነበረ፡፡ አርዮስም በ፫፻፳፪(322) ዓ.ም ወደ እስክንድሪያ በመመለስ እለስክንድሮስ ቢያወግዘኝ ተፈትቼ መጣሁ በማለት የክህደት ትምህርቱን ማስተማር ቀጠለ፡፡ ብዙ ተከታዮችም አፈራ፡፡
- ይህ አለመግባባት ሥር በመስደዱ ቆስጠንጢኖስ የእስፓኝን ጳጳስ ሆስዮስን ወደ እስክንድሪያ ልኮ ነገሩን እንዲያጣራ አደረገ፡፡ የእስፓኙ ጳጳስ ሆስዮስ ጠቡ የሃይማኖት እንጂ የሥልጣን አለመሆኑን በመግለጹ ቆስጠንጢኖስ ያን ጊዜ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ እንዲደረግ ዓወጀ፡፡
- ጉባኤውም በመጀመሪያ በእንቆራ ሊካሄድ ታስቦ ነበር፡፡ ሆኖም ወደ ኒቅያ ተዛወረ፡፡ በዓዋጁ መሠረት ብዙ ኤጲስ ቆጶሳት እና ሊቃውንት በኒቅያ ተሰበሰቡ፤ ከምዕራብ ከመጡት አምስት ኤጲስ ቆጶሳት ውጭ ሌሎቹ ከምሥራቅ የመጡ ናቸው፡፡ በጉባኤው ለመሳተፍ ከእስክንድሪያ ከመጡት አባቶች እለእስክንድሮስና አትናቴዎስ ከአንጾኪያ ኤዎስጣቴዎስ እንዲሁም የእንጽቢን ያዕቆብ ይገኙበታል፡፡
- በጉባኤው ላይ ‹‹ወልድ ዋሕድ›› በማለት እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ

www.zeorthodox.org

ሆነው የተገኙት፤ ፫፻፲፰(318) ሊቃውንት ብቻ ነበሩና ቤተክርስቲያን ይህን ቁጥር ተቀብላዋለች፡፡ በፍትሐዊነት በጉባኤው ብዙ የአርዮስ ደጋፊዎች ተገኝተው ነበር፡፡

- ጉባኤውን የመሩት ሊቀ ጳጳሳቱ እለእስክንድሮስና ኤዎስጣቴዎስ እንዲሁም ኤጲስ ቆጶሱ ሆስዮስ ነበሩ፡፡ ለምእመናኑ አንድነት የመሰላቸውን እንዲያደርጉ ንጉሡ ቆስጠንጢኖስ ሥልጣን ሰጣቸው፡፡ ምልክትም ይሆናቸው ዘንድ እስከ ጉባኤው ፍጻሜ ድረስ የነገሠበት ዘውዱን ቀለበቱንና ሰይፉን ለጉባኤው አስረከበ፡፡

ጉባኤው የአርዮስን ሐሳብ አደመጠ፡፡ በዚሁ መሠረት፡-

ሀ/ አርዮስ ያቀረባቸውን ጥቅሶች መረመረ

ለ/ ጥበብ የሚለውን ቃል እንዴት እንደተረጐመው አጠና፣

ሐ/ ወልድ በባሕርዩ ፍጡር ከሆነ በመዳን ምስጢር ላይ ስለሚደርሰው አደጋ ተወያየ፣

መ/ የእግዚአብሔር ቃል ለሰው ልጆች ሲል ወዶ ያደረገውን ተዋሕዶ አርዮስ የባሕርይ ተወራጅነት ቢኖርበት ነው አለ፤

ሠ/ ወልድ በባሕርይው ፍጡር ሳለ እንደሌሎች ፍጡራን በገድል በትሩፋት የአምላክነት ክብር አገኘ ስለማለቱ፡፡

- አርዮሳውያን ከግሪኮች ፍልስፍና ጋር በማዛመድ ለራሳቸው የሚመቻቸውን ጥቅስ በመጥቀስና ጥያቄ በማቅረብ "እሰጣ አገባ" ውስጥ ገቡ፡፡ እነ ቅዱስ አትናቴዎስ ግን ጌታ አዳኝ ነው፣መድኃትነቱም የባሕርይ አምላክነትን የሚያስረዳ ነው፡፡ የሚያድንም እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መልኩ ዘርዝረው ተናገሩ፡፡
- ክርስቶስ አምላክ ካልሆነ አሁን አልዳንም ማለት ነው፡፡ በእርሱ መዳናችንን ካመንን ግን ያዳነን እርሱ አምላክ መሆኑን ማወቅና ማመን አለብን፤ ፍጡር ፍጡርን አያድነውምና፡፡ ለምሳሌ የጠፋው በግ ምሳሌትን ሲያስረዳ የጠፋው በግ የሰው ዘር፣ ፈላጊው አካላዊ ቃል የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ ኢሳ.፵፫÷፳፩ ሆሴ.፲፫÷፬ ማቴ.፩÷፳፩ ሉቃ.፲፬÷፯ ፩ኛጢሞ.፩÷፩
- ‹‹ጌታ በገድል በትሩፋት አምላክ ስለሆነ አምላክ ተብሎ ሊሰገድለት ይገባዋል፡፡›› ላለው፤ አትናቴዎስ ሲመልስ፤ ፍጡር ከሆነና ለእርሱ የአምልኮ ስገድት የምንሰገድ ከሆነማ አምልኮ ባዕድ ነው ሲል ሐሳቡን ተቃውሟል፡፡ የጌታን የባሕርይ ልጅነት ሲናገር፤ ለእርሱ "አባቴ" ለእኛ ግን "አባታችሁ" አለ እንጂ ‹‹አባታችን›› አላለምና ሲጠመቅ "ወልድን" "ወልድ" ብሎ ለይቶ ጠርቶታልና›› ማቴ. ፫፡፡ ከዚህ ሁሉ ክርክርና መልስ በኋላ በጉባኤው የነበሩ አባቶች የአርዮስ ሐሳብ ሰው ሠራሽ እንጂ አምላካዊ አለመሆኑን ተረድተው፤ የሃይማኖት እንጂ

www.zeorthodox.org

የፍልስፍና ተገዥ አለመሆናቸውን በአጭር አገላለጥ ተናግረዋል፡፡

- አውሳብዮስ ዘቂሣርያና አውሳብዮስ ዘኒቆሚዲያ አርዮስን ለመደገፍ፤ ‹‹ወልድ አብን ይመስለዋል›› ቢሉም ጉባኤው ይህን አመለካከታቸውን ከአርዮስ አመለካከት ልዩ ሆኖ ስላላገኘው አልተቀበለውም፡፡
- ጉባኤው የሁለቱን ወገን ማስረጃዎች ከተመለከተ በኋላ፤ አርዮስ ወልድን ፍጡር ለማለት ያበቃው ፍልስፍና እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት አለመሆኑን እንዲረዳው ተደረገ፡፡ ሆኖም ከክህደቱ ካልተመለሰ በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ማስተማር እንደማይቻልና ወደ እስክንድርያም እንዳይመለስ ተወገዘ፡፡
- አርዮስን ካወገዙ በኋላ የቤተ ክርስቲያንን እምነት ከፍልስፍና ለይተው፤ ወልድ፣ ቃል የሚሉት የመጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር አንድ መሆኑን አብራሩ፡፡ የወልድ መገኘትም አትናቴዎስ እንዳቀረበው ‹‹ዋሕደ ባሕርይ ምስለ አብ፡- ከአብ ጋር አንድ ባሕርይ›› ነው በማለት፤ የመለኮትን አንድነት፣ የአካላት ሦስትነት፣ የወልድን የባሕርይ አምላክነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ አንቀጸ ሃይማኖታቸው አጽድቀዋል፡፡
- አሁን በቤተ ክርስቲያን የሚሠራበት የሃይማኖታችን ቀኖና ይህ ነው፡፡ ይህም ዐሥራ ሁለት አንቀጾች ያሉት ሲሆን ሰባቱ በዚህ ጉባኤ የተረቀቁ ናቸው፡፡ ሌሎቹ አምስቱ ደግሞ በሁለተኛው ጉባኤ የቀረቡ ናቸው፡፡

**በኒቅያ የቀረቡት ሰባቱ የአንቀጸ ሃይማኖት ክፍሎች፡-**

1. *" ሁሉን የፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ እናምናለን"*
2. *‹‹ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን እውነተኛ ብርሃን፤ ከአምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ፤ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፤ በባሕርይው ከአብ ጋር የሚተካከል በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን፡፡ ብቻውን ከአብ የተወለደ ሁሉ በእርሱ የሆነ፤››*
3. *"ስለ እኛ ስለሰዎች ስለመዳናችንም የወረደ ሥጋ የሆነ ሰውም የሆነ፡፡"*
4. *"ታመመ ሞተ ተቀበረ፡፡"*
5. *" በሦስተኛው ቀን የተነሣ፡፡"*
6. *"ወደ ሰማያት ዐረገ፡፡"*
7. *"ሕያዋንንና ሙታንን ይገዛ ዘንድ ዳግመኛ የሚመጣ"* የሚሉት ሲሆኑ *" በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን፡፡"* የሚለው በዚህ ጉባኤ ተጀምሮ በቁስጥንጥንያ ጉባኤ የተፈጸመ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

- ከዚህ ትምህርት ወጥተው ወልድን ከአብ ለይተው፤ ‹‹ያልነበረበት ጊዜ ነበረ›› የሚሉ

ወይም ‹‹ከመወለዱ በፊት አልነበረም›› የሚሉ ወይም ‹‹ወልደ እግዚአብሔር ከባዕድ ባሕርይ የተገኘ ነው›› የሚሉ ወይም ‹‹በባሕርይ መለወጥ አለበት›› የሚሉትን እነዚህን ሁሉ ‹‹በሁሉ ያለች ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ታወግዛቸዋለች›› ሲሉ ውሳኔያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

## ማጠቃለያ

- ለጉባኤው መሰባሰብ ዋናው ምክንያት የሆነው የአርዮስ ጉዳይ ቢሆንም፤ ሠለስቱ ምዕት እግረ መንገዳቸውን ቤተ ክርስቲያን በውጭ እና በውስጥ ስላላት የአስተዳደር ሥርዓት፣ ስለበዓላትና አጽዋማት፣ ስለ ኤጴስ ቆጶሳት መብትና ሥልጣን፣ ስለ ሀገረ ስብከት ክልል አስፈላጊነት ውሳኔ አስተላልፈዋል፡፡
- በአጠቃላይ ይህ የኒቅያ ጉባኤ የተካሔደው በ፫፻፳፭/325/ ዓ.ም ነው በዘመነ ቆስጠንጢኖስ ፫፻፲፰/318/ ሊቃውንት አባቶች በጉባኤው ተሰብስበው ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ በእለ እስክንድሮስ ሊቀመንበርነት የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል /ዮሐ. ፩፥፩-፬/ በማረጋገጥ “ወልድ ፍጡር” ሲል የሳተውን ቀንደኛ መናፍቅ አርዮስን አውግዘው ለይተውታል፡፡

## ተግባር

- ጸሎተ ሃይማኖትን በቃል አጥኑ፡፡

www.zeorthodox.org

# ዓለም አቀፍ የቤተክርስቲያን ጉባኤያት(ሁለት)

## ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸውን ዓለም አቀፍ ጉባኤያት በሚገባ አውቀው ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *" ለቤተ ክርስቲያን ንገራት "* ማቴ.፲፰፥፲፯

## መግቢያ

- ካለፈው ትምህርታችን በመቀጠል በዚህ ክፍል ጉባኤ ቁስጥንጥንያን እና ጉባኤ ኤፌሶንን እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

### 2. ጉባኤ ቁስጥንጥንያ

- ጉባኤው የተካሔደው በ፫፻፹፩/381/ ዓ.ም የታናሽ እስያ ክፍል በሆነችው በቁስጥንጥንያ ነው፡፡ ይህ ጉባኤ መቅዶንዮስ ከተባለ ከአርዮሳውያን የመናፍቃን ጉራ ወገን የሆነ፤ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ሕፁፅ ነው›› በማለት የክህደት ትምህርቱን ስላስተማረ የተጠራ ነው፡፡
- ይህ ክህደት ሲነሣ የቁስጥንጥንያ ንጉሥ የነበረው ቴዎዶስዮስ ቀዳማዊ ይህ የቤተ ክርስቲያን ችግር በጉባኤ እንዲሚፈታ ባስተላለፈው መልእክት መሠረት አንድ መቶ ሃምሳ ሊቃውንት ተሰብስበዋል፡፡
- ጉባኤውንም በየጊዜው የተለያዩ አባቶች መርተውታል፡፡ በመጀመሪያ ጎርጎርዩስ ዘእንዚናዙ ቀጥሎ ኔክታሪዎስ በመጨረሻም የእስክንድርያው ጢሞቴዎስ ጉባኤዉን በሊቀመንበርነት መርተውታል፡፡

www.zeorthodox.org

- በዚህ ጉባኤ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የተወያዩባቸው መሠረታውያን ጉዳዮችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በምስጢረ ሥላሴ ላይ ስሕተት ያስተማረውን መቅዶንዮስንና ትምህርቱን፤ ‹‹መንፈስ

ቅዱስ ሕፁፅ ነው›› የሚለውን ክህደትን ማውገዝ፡፡

2. አቡሊናርዮስንና ትምህርቱን፤ ‹‹በምስጢረ ሥጋዌ ቃለ እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ሥጋን እንጂ ነፍስን አልተዋሐደም›› የሚለውን ክህደትን ለማውገዝ፡፡
3. የእግዚአብሔር ልጅ የተዋሐደው የአዳምን ሥጋ አይደለም ሌላ በቅድምና የነበረ ሥጋ ነው እንጂ፤ የሚሉ መናፍቃንን ለማውገዝ፡፡
4. በኒቅያ ጉባኤ ላይ በተረቀቀው ጸሎተ ሃይማኖት /የሃይማኖት ቀኖና/ ላይ የተጨመሩ አምስት አንቀጾች ያሉት የሃይማኖት ቀኖና ማርቀቅ ሲሆኑ፤ የኒቅያውን ረቂቅ ንባቡን ለማስተካከል የገቡ አንዳንድ ቃላትንም ጭምር ተመልክቷል፡፡

- ጉባኤው በሎዶቅያ የተወለደውን የአቡሊናርዮስን የክህደት ትምህርትም አውግዟል፡፡ ትምህርቱም የኘላቶንን የሥጋዊ ፍልስፍና ወስዶ፤ ሰውን ለማወቅ የምትችለው ነባቢት ለባዊትና ሕያዊት ነፍስ ከመለኮት ተከፍላ የመጣች ነች፣ ቃልም ሥጋ ሲሆን የተዋሐደው ሥጋን እንጂ ነፍስን አይደለም፣ መለኮትም ለሥጋ ነፍስ ሆናት፤ ይል ነበር፡፡ በዮሐንስ ወንጌል፤፩፥፩-፲፬ ላይ ‹‹ቃል ሥጋ ሆነ›› የሚለውን ቃል በመጥቀስ በትክክል የቃልና የሥጋን ተዋሕዶ መጽሐፍ ቅዱሳዊነት ሊቃውንቱ አስረድተዋል፡፡ ከሊቃውንተ ቤተክርስቲያን መካከልም ቀዳማዊ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ /ነባቢ መለኮት/ ሰው ማለት ነፍስና ሥጋ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን እንጂ ነፍስን አልነሣም ከተባለ ያዳነው ሥጋን እንጂ ነፍስን አይደለም፤ ብሎ በመመለስ የአቡሊናርዮስን ክህደት ተናግሯል፡፡
- አቡሊናርዮስ ከግኖስቲኮች በወረሰው የክህደት ትምህርቱ ፫፻፷፪/362/ ዓ.ም በእስክንድሪያ ሲኖዶስ በ፫፻፸፱/379/ ዓ.ም በአንጾኪያ ሲኖዶስ እና በመጨረሻ በ፫፻፹፩/381/ ዓ.ም በቁስጥንጥንያ ጉባኤ ሦስት ጊዜ ተወግዟል፡፡
- በቁስጥንጥንያ ጉባኤ የሠለስቱ ምዕት ትምህርተ ሃይማኖትን አጽድቆ መናፍቃንን አውግዞ ሲለይ፤ በጉባኤ ኒቅያ አንቀጸ ሃይማኖት ከተጠቀሱት ተጨማሪ የሚከተሉትን አምስት አንቀጾች አስቀምጠዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. ‹‹በጌታ በአዳኝ ከአብ በሰረጸ እንሰግድለት እናመሰግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን፡፡››
2. ‹‹በሁሉ ባለች በሐዋርያዊት ጉባኤ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡፡››
3. ‹‹የኃጢአት ማስተሰሪያ በምትሆን በአንዲት ጥምቀት እናምናለን፡፡››
4. ‹‹የሙታንን ትንሣኤ ተስፋ እናደርጋለን፡፡››
5. ‹‹የሚመጣውን ሕይወት እንጠባበቃለን ለዘላለሙ አሜን፡፡››

www.zeorthodox.org

ከዚህ በላይ ያየነው በጉባኤ ቁስጥንጥንያ የተረቀቀው አንቀጸ ሃይማኖት በኒቅያ ጉባኤ ከተወሰነው ጋር አንድ ሆኖ ዛሬም እኛ በሐዋሪያዊት ቤተ ክርስቲያናችን ሥር የምንኖር የተዋሕዶ ልጆች የምናምነው የምንቀበለው አንቀጸ ሃይማኖት ነው፡፡

## 3. ጉባኤ ኤፌሶን፡-

- ይህ ጉባኤ ሦስተኛው ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በመባል ይታወቃል፡፡ ለጉባኤው መሰብሰብ ምክንያት የሆነው የንስጥሮስ የክህደት ትምህርት ነው፡፡
- በአንጾኪያ ትምህርት ቤት የጠርሴስ ሊቀ ጳጳስ ከሆነው ከዲያድርስ የክህደት ትምህርትን የተማረው ንስጥሮስ ይኖር የነበረው በግሪክ በሚገኝ ገዳም ነው፡፡
- ንስጥሮስ የዲያድርስን እምነትና የክህደት ትምህርት ማለትም፤ በምስጢረ ሥጋዌ ክርስቶስን በሁለት ከፍሎ አንዱን ወልደ ዳዊት ሁለተኛውን ወልደ እግዚአብሔር ነው ብሎ ያምንና ያስተምር ነበር፡፡ በእርሱ አባባል ከማርያም የተወለደው የዳዊት ልጅ ከእግዚአብሔር አብ የተወለደው ወልደ እግዚአብሔር ነው ብሏል፡፡ ስለዚህም እመቤታችን የወለደችው ሰው እንጂ አምላክ አይደለም በማለት በአደባባይ የክህደት ትምህርቱን ያስተምር ነበር፡፡
- ንስጥሮስ ለክህደት ትምህርቱ የተጠቀመበት (ዮሐ.፩÷፲፬) ‹‹ቃል ሥጋ ሆነ›› የሚለውን መለወጥን ያስከትላል፣ (ፊል.፪÷፭-፯) ‹‹ነሥዓ አርአያ ገበረ›› ያለውን፤ ቃል በሥጋ አደረ፤ ብሎ እንዲመቸው አድርጐ በመተርጐም መሪ ጥቁሱን ነበር፡፡

- ለንስጥሮስና ለክህደት ትምህርቱ በሚገባ ምላሽ የሰጠው በ፫፻፸፭/375/ ዓ.ም በእስክንድርያ የተወለደው የእስክንድሪያ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ቄርሎስ ነው፡፡ መዓርገ ዲቁናና ቅስናን ከቴዎፍሎስ ተቀብሎ፤ ቴዎፍሎስ በ፬፻፲፪/412/ ዓ.ም ሲያርፍ፤ የእስክንድርያ ሃያ አራተኛ ፓትርያርክ ሆኖ የተሾመውና የእስክንድሪያን ቤተ ክርስቲያን ለ፴፪ ዓመታት የመራው ታላቁ አባት ቅዱስ ቄርሎስ፤ የቃልና የሥጋን ተዋሕዶ በሚገባ በማስረዳት ስለውላጤና ኅድረት ተንትኖ በማብራራት ድል አድርጎአል፡፡

- የንስጥሮስን ትምህርት በመጀመሪያ የተቃወመች የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ነች፡፡ የሚባለውም በቅዱስ ቄርሎስ አማካይነት ነው፡፡

www.zoorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሦስት ታላላቅ ዓለም አቀፍ ጉባኤያትን ስታደርግ፤ የሃይማኖት ትምህርቷን፣ ሥርዓቷንና ትውፊቷን እንድትለይ እና በትክክል እንድታስተምር ያደረጋት ከምንም በላይ የምትደነቅበት ጊዜ ነው፡፡

በነዚህ ጉባኤያት ትምህርተ ሃይማኖትን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን አባቶቻችንንም በትክክል አውቀናል፡፡ በክህደታቸውና የተወገዙትንም አስተምህሮ ለይተናል ፡፡

www.zeorthodox.org

# የክብር አካል (አንድ)

## ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ስለክርስቶስ ትንሣኤና ስለተሰጠን ተስፋ አውቀው ያስረዳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው፡፡ በመበስበስ ይዘራል÷ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርድት ይዘራል÷ በክብር ይነሣል፡፡"*** ፩ኛ ቆሮ. ፲፭÷፵፪

## መግቢያ

- ይህ ክፍለ ትምህርት ሁለት ተከታታይ ክፍሎች አሉት፡፡ ከትንሣኤ በኂላ ስላለው የክርስቶስ ክቡር አካል የምንማረው የመጀመሪያው ክፍል ነው፡፡
- እንደ ክርስቶስ የክብር ትንሣኤ እንደምንነሣ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርታችን ሲሆን የጌታችን ተስፋም ተሰጥቶናል፡፡

**የሚተኮርባቸው ነጥቦች ፡-**

***ሀ.ጥያቄ፡-*** ጌታ ሲነሣ ምን ዓይነት አካል ይዞ ተነሣ? እንደ እኛ ተራ አካል ይዞ ነው የተነሣው ወይስ የክብር አካል? ክቡር አካል ይዞ ከተነሣ ***"ተቀብሎም በፊታቸው በላ"*** ሉቃ. ፳÷፵፫ ***"እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው፡፡ ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው፡፡"*** ሉቃ.፳፬÷፴፱ የሚሉት ቃላት ትርጓሜ ምንድን ነው? ክርስቶስ ሲነሣ የነበረው አካል ከድንግል ማርያም ከነሣው አካል ጋር አንድ ነው ? በክብር አካል ተወለደ ለምን አንልም?

**ለ. መልስ፡-**

1. ካለ ጥርጥር የተነሣው ክቡር አካል ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ የክብር አካል ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፡፡***"የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው፡፡ በመበስበስ ይዘራል÷ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል÷ በክብር ይነሣል፡፡ በድካም ይዘራል÷ በኃይል ይነሣል፤ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል÷ መንፈሳዊ አካል ይነሣል፡፡ ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ፡፡"*** ፩ኛ ቆሮ.፲፭÷፵፪-፵፬
2. እኛ በክብር አካል የምንነሣ ከሆነ÷የክርስቶስ ትንሣኤ ምን ያህል ይልቃል? እኛ የእርሱን ትንሣኤ መስለን በክብር ስለምንነሣበት ግልጥ ትምህርትን የጻፈልን ቅዱስ ጳውሎስ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

በፊልጵስዮስ መልእክቱ ፫÷፳፩ ላይ እንዲህ ጽፎአል፡፡ *"ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል፡፡"*

3. ታዲያ ይህ ከሆነ ክርስቶስ ከተነሣ በኋላ "በላ""አጥንትና ሥጋ" አለው፡፡ *"ዳሰሱ"* ለምን ተባለ? ቅዱስ ሉቃስ በጻፈልን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ይህ ሐሳብ እጅግ ግልጥ ሆኖ ቀርቧል፡፡

ወንጌላዊው፤ ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ራሱን ለደቀ መዛሙርቱ መግለጡን ሲጽፍ፤ ***"ነገር ግን ደነገጡና ፈሩ፤ መንፈስም ያዩ መሰላቸው፡፡ እርሱም፡- ስለምን ትደነግጣላችሁ? ስለ ምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው፡፡ ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው፡፡"*** ሉቃ. ፳፬÷፴፯-፴ በተመሳሳይ ቦታና ጊዜም ***"የተጠበሰ ዓሣ ከማር ወለላ ጋር በፊታቸው በልቷል፡፡"*** ሉቃ. ፳፬÷፴፪-፴፫

***ይህንንስ እንዴት እንገልጸዋለን?***

1. **ሐዋርያት ስለ መንፈሳዊው አካል ምንነትና ክብር አላወቁም ነበርና÷ሥጋው ከሙታን መነሣቱን ሲያረጋግጥላቸው፤** በርግጥም በመብላትና አካሉን እንዲዳስሱ በማድረግ ባያረጋግጥላቸው ኖሮ ሥጋ የሌለው መንፈስ ያዩ መስሏቸዋልና ትንሣኤውን ይጠራጠሩ ነበር፡፡
2. **በትንሣኤ በጣም አስፈላጊው ነገር የሥጋ መነሣት ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ያዩ የመሰላቸው የሥጋ ትንሣኤ ከአእምሮአቸው እጅግ የራቀ ሐሳብ ስለነበር ነው፡፡**

- ምክንያቱም መንፈስ በተፈጥሮው የማይሞት ሕያው ነው፡፡ ሥጋ የሚሞተውም ከመንፈስ ሲለይ ነው፤ ከዚያም ወደ አፈርነት ይቀየራል፤ ነገር ግን መንፈስ በመቆያ ሥፍራው (ገነት ወይም ሲኦል) ይቆያል፡፡ እንግዲህ ትንሣኤ የሥጋ መነሣትና ከመንፈስ / ነፍስ / ጋር መዋሐድ ነው፡፡
- ስለዚህም ከዚህ እምነት የራቀ አእምሮአቸውን ለማሳመንና ሌሎቹንም እንዲያሳምኑ ለማድረግ መብላት እና አካሉን እንዲዳስሱ ማድረግ አስፈልጓል፡፡
- መንፈስ ብቻውን ሙሉ የሰውን ተፈጥሮ አይወክልም፡፡ ስለዚህም ነው የሥጋን ትንሣኤ ማስረገጥ ያስፈለገው፡፡ ደቀ መዛሙርቱን ዳስሳችሁ እዩ ብሎ የፈቀደላቸውም ለዚህ ነው፡፡ (ሉቃ.፳፬÷፴፱ ዮሐ. ፳÷፳፯)

www.zeorthodox.org

3. **ይህ መንፈሳዊ ክቡር አካል ነው ወደ ሰማይ የወጣው፡፡** ሥጋ ከአየር የሚበልጥ ክብደት ስላለው ነገረ ዕርገት ከመሬት የስበት ኃይል ሕግ ጋር ላይስማማ ይችላል፡፡ ነገር ግን በክብር

ከመንፈሳዊው አካል ጋር ወደ ሰማይ ዐርጎአል፡፡ በተመሳሳይ ክብርም በአብ ቀኝ ተቀምጦአል፡፡ ተመሳሳይ የክብር አካልም ይመጣል፡፡/ማቴ.፳፰፥፴፯/

4. ይህ የክብር አካል ነው ለሳውል በጠርሴስ መንገድ ላይ የተገለጠለት፤ (የሐዋ.፱፥፫-፯)፡፡
5. የተነሣው ሥጋ ከተወለደው ጋር አንድ ነው፤ ሲለወጥ…ምን እንደሚመስል ግን በደብረ ታቦር ምሳሌሰጥቶናል፡፡ ***‹‹ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው፡፡ በፊታቸውም ተለወጠ፥››*** ማር.፱፥፪-፫ ክርስቶስ በትንሣኤ የነበረው ሥጋ ሲወለድ ከነበረው ሥጋ ጋር አንድ ነው፡፡ በክብር እና በመለወጥ ግን ሥጋውን በክቡር ባሕርዩ እና በመንፈሳዊ ኃይሉ ገልጦታል፡፡ ይህ ተመሳሳይ ነገርም በእኛ ይሆናል፡፡
6. አንዳንዶች የክርስቶስ አካል ክብርን ያገኘው ከትንሣኤው ወይም ከዕርገቱ በኋላ ነው? ብለው ይጠይቃሉ፡፡ መልሳችን የክርስቶስ አካል ያን ክብር የተላበሰው በትንሣኤው ነው፡፡ ሰውኛ ባሕርዩን ለማረጋገጥ ያደረጋቸው ልዩ ምክንያቶችም ለደቀ መዛሙርቱ ሥጋው መነሣቱን ለማሳመንና በሙሉ ልብ ወንጌልን እንዲያስፋፉ ነበር፡፡/፩ኛ ዮሐ.፩፥፩ የሐዋ.ሥ.፲፥፵፩)
   - ከዚህ ምክንያት ውጪ ግን የተነሣው የክብር አካል መብልና መጠጥ አያስፈልገውም ፡፡
   - አይራብም፥ አይጠማም፡፡ በክብር አካል ድካም የለም፣ አይታመምም፤ አይሞትምም፤ ሕያው፣ መንፈሳዊና ክቡር አካል ነውና፡፡

## ማጠቃለያ፡-

1. የተለያዩ አካላት አሉ፡፡ እጅግ አስፈላጊው አካል ከሞት ስንነሣ ይዘን የምንነሣው የክብር አካል ነው፡፡ በምድር የጽድቅ ኑሮ ከኖርን፣ ከጌታችን ጋር አንድ ሆነን (በሥጋና ደሙ) ከኖርን፥በዳግም ምጽአቱ ስናገኘውም ከክርስቶስ ጋር (ከተነሣበት ሥጋ ጋር) ተመሳሳይ የሆነ የክብር አካል ይኖረናል፡፡
2. ትንሣኤ የክርስትና ክብር ነው፡፡ ምክንያቱም መጻዒ ሕይወታችንን የደስታ አድርጎ ዘላለማዊ ሕይወትን ከእግዚአብሔር ጋር ያኖረናል፡፡

www.zeorthodox.org

# የክብር አካል (ሁለት)

## ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ክርስቶስ የክብር አካል በትንሣኤው ይዞ እንደተነሣ ተገንዝበው ያስረዳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ፣ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ...."*** ዮሐ.፳፥፲፱

## *መግቢያ፡-*

- ካለፈው ትምህርታችን ክርስቶስ የተነሣው በክብር እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ እኛም ስንነሣ የክብር አካል እንደሚኖረን፤ ***"ክቡር አካሉን እንዲመስል የተዋረደው ሥጋችንን እንደሚለውጥ፡፡"*** ፊልጵ.፫፥፲፳ አይተናል፡፡
- ባለፈው ክፍል ትምህርታችን ይሄንኑ የሚገልጡ ነጥቦች ተብራርተው የቀረቡ ሲሆን ዛሬም ስለ ክርስቶስ የክብር አካል የምንማረው ተከታታይ ትምህርት ክፍል ሁለት ነው፡፡

## ትምህርቱ

### በተዘጋ በር መግባት እና ከተዘጋ ቦታ መውጣት፤ የተነሣው አካል የክብር አካል እንደሆነ ግልጽ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡

***"ደጆቹ ተዘግተው ሳለ "*** ዮሐ.፳፥፩ እና ፳፮፤ በትንሣኤውም ከታተመ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ወጥቶአል፡፡ ሰዎች መቃብሩ ባዶ መሆኑን እንዲያዩ ድንጋዩን ያንከባለለው ከትንሣኤው በኋላ ነው፡፡ ከተዘጋ መቃብር ለመውጣቱ ምሳሌ ከሚሆኑን አንዱም ከዚያ በፊትም ከድንግል ማርያም ማሕፀን በኅቱም ድንግልና መወለዱ ነው፡፡ ይሄን ስንል አንዳንዶች ክርስቶስ እንደተነሣበት ዓይነት ክቡር አካል ይዞ ተወልዷል? ብለው ይጠይቃሉ፡፡ መልሱ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

### ክርስቶስ የተወለደው የእኛን ዓይነት አካል ይዞ ነው፡፡ ከኃጢአት በስተቀር እኛን መስሎአል፡፡

www.zeorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን የሰው ልጆችን ባሕርይ ሲወርስ፡- "የሰው ልጅ" ተብሎአል፤ በዚህም አድኖናል፡፡ "እንደኛም በሕፃንነት አድጓል" ሉቃ.፩፥፹፡፡ "ተርቧል" /ማቴ.፬፥፪/፡፡ ተጠምቷል፡፡ /ዮሐ. ፲፱፥፳፰/፡፡ ደክሞት ያውቃል (ዮሐ.፬፥፮)፡፡ "ተኝቷልም" /ማቴ. ፰፥፳፬/

### የሰዎችን ባሕርይ ባይነሣ ሕመም አይስማመውም ነበር፡፡ *ሥጋ የሚሰማውን ሕመም*

ይሰማው ነበር።

በሕመም ተሰቃይቶአል። ማለትም ተሰድቦ፣ ተገርፎ፣ ተንገላቶ፣ ተቸንክሮ ስቃይን ተቀብሏል። ይህም በመስቀል ሳለ በተደጋጋሚ ሆኖአል። የቀሬናው ሰው ስምዖን መስቀሉን በመሸከም ያገዘውም ለዚህ ነበር። የተዋሓደው ሥጋ ባሕርይ መዋቲ /ሟች/ ነበርና ስለ እኛ ሞቷል። ለእኛ ሲል ሞቶ አድኖናልም። የክብር አካል ግን አይታመምም አይሞትምም። ጌታችን ሲወለድ በታማሚ፣ሟች፣ የሚሠቃይ የሰውን ባሕርይ ይዞ ተወልዷል። በዚህ መንገድ ይህን የሰውን ባሕርይ ለብሶ ማዳንን ፈጽሞአልና ከዚያም በክብር ተነሥቷል።

**ዓለምን ከማዳኑ በፊት የነበረው የባሕርይ ክብሩ ኃጢአት የማይሰማማው ነበር።**

ጌታችን ሲወለድ፣ በተፀነሰም ጊዜ፣ በምድር ሲመላለስም በመንፈሳዊ ክብር የፈጸማቸው ነገሮች የተከናወኑት በመልካም ፈቃዱ ሲሆን ሥጋው ግን ከኃጢአት በቀር እንደእኛ ነበር። ራሱንም ባዶ አድርጎ የአገልጋዩን ባሕርይ ይዞ ተገኘ።

**ከመለኮት ጋር የነበረውም ተዋሕዶ የክብሩ አንዱ መሣሪያ ነው።**

ይህ ተዋሕዶ ሰውኛ ባሕርዩን አላስቀረውም። የሥጋን ድካም መራብ፣መጠማት፣ድካም እና ሞትም አላስወገደውም።ይህ ቢሆን መዳን አይፈጸምም፤ ዋጋውንም ያጣ ነበር። ሕማሙ የእውነት ስለነበረም ነው ማዳኑ እውነት የሆነው። ራሱን ባዶ ስላደረገም በትንሣኤው ክብር ሰጠን። ከመሞቱ በፊት ራሱን ባዶ ስላደረገ ***"አባት ሆይ ልጅህን አክብረው ልጅህ እንዳከበረህ።" "አሁንም አባት ሆይ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በነበረው ክብር አክብረኝ"*** ዮሐ.፲፯÷፩፣፭ ብሏል። ይህም ስለ ትንሣኤው የተነገረው ነው።

**ደቀ መዛሙርቱ ይህን ክብር አይተው መቋቋም አልቻሉም።**

ወንጌላዊው ዮሐንስ በራእዩ የእግዚአብሔርን ክብር አይቶ፤ ***"እንደሞተ ሰው ሆነ"*** ለምን? ***"ምክንያቱም ፊቱ እንደ ፀሐይ የበራ ዓይኖቹም የሚንበለበል እሳት ይመስሉ ነበርና"*** ነው።

**ለዚህም ነው ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ ሲገለጥ በተለያየ ደረጃና ቀስ በቀስ የትንሣኤውን ክብር ያሳያቸው።**

www.zeorthodox.org

- ለመግደላዊት ማርያም መጀመሪያ ሲገለጥ አትክልት ጠባቂ መስሏት ነበር። በመጨረሻም ራሱን ገለጠላት። /ዮሐ.፳÷፲፬፣፲፯/
- ለኤማሁስ መንገደኞች ሲገለጥም ተመሳሳይ ነገር ነው የሆነው። አብሮአቸው እየሄደ አላወቁትም። /ሉቃ.፳፬÷፲፮/
- ለደቀ መዛሙርቱም የታያቸው ተመሳሳይ እድገት ባለው አገላለጥ ነው። ይህ ባይሆን

ከትንሣኤው በኋላ ያለውን የክብር አካል ማየት ባልቻሉ ነበር፡፡

**ይህ ማለት ጌታችንን በክብሩ ሆኖ ማየት አንችልም ማለት ነው? ካየነውስ  እንዴት እና መቼ?**

የእኛ ሰውኛ ባሕርይ ከሞት ስንነሣ ይለወጣል፡፡ የክብር አካል እንዲሆንም ሥጋችን ይቀየራል፡፡ /ፊልጵ.፫÷፳፩/ እኛም እናየዋለን፡፡ ለዚህም ነው፤ ሐዋርያው ***"አሁን በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፤ያኔም ፊት ለፊት እናያለን፡፡"*** (፩ኛ.ቆሮ.፲፫÷፲፪) ያለው፡፡

***"ፊት ለፊት"*** የሚለው ቃል ትርጉም ምንድነው? እንዴትስ ይፈጸማል? ይህ ዝምታን ያስመርጣል በሙታን ትናሣኤ ግን ይሄን እናያለን፡፡

## ማጠቃለያ

1. ጌታችን እንደ እኛ ሕማምና ሞት የሚስማማው ሆኖ ተገልጾአል፡፡ መለኮቱ ከሥጋው ለቅጽበት እንኳን አልተለየም፡፡
2. በሰውኛ ባሕርዩ ከኃጢአት በቀር እኛን መስሎኣልና መዳንን ፈጽሞአል፤ ከዚያም በትንሣኤው ከብሮአል፡፡

***ይቆየን፡፡***

www.zeorthodox.org

# እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

## ዐሥረኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች፤ ስለ እመቤታችን የሥጋ ወራት የሕይወት ታሪኳን፣ ዕረፍቷን እና ዕርገቷን እንዲሁም በበዐለ አስተርእዮ ማርያም ላይ በመመርኮዝ ስለእመቤታችን መገለጥ አውቀው ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-**

- ***" ለልጅ ልጅ ሁሉ ስምሽን ያሳስባሉ"*** መዝ. ፵፬(፳)፥፲፯
- ***" እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል"*** ሉቃስ ፩፥፵፰

## መግቢያ፡-

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ትንቢት የተነገረላትና ጌታችንን ለመውለድ የተመረጠች፤ ከሴቶች ሁሉ ተለይታ የተባረከች፤ ከሰው ሁሉ ተለይታ የእግዚአብሔር ጸጋ የሞላባት መሆንዋን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ ***"ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ ጌታ ካንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ "*** ሉቃ ፩፥፳፰ እንዲል፡፡
- ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስን የማዳን ሥራ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እና በዘመናት ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሆኖ እንደሚሠራ ታስተምራለች፡፡ ‹‹***እስከ ዓለም ፍጻሜ እኔ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡›› ***፳፰፥፲፰ ብሎ ቃል በገባው መሠረት፤ በእመቤታችን ቃል ኪዳን ምልጃና መገለጥ የተፈጸሙትን መሠረት በማድረግ እመቤታችንን ታስባለች ክብር ትሰጣለች፡፡ ይሄንም ለትውልድ ሁሉ ታስተላልፋለች፡፡ ‹‹***ለልጅ ልጅ ሁሉ ስምሽን ያሳስባሉ›› ***መዝ ፵፬(፳)፥፲፯
- በዛሬው ትምህርታችንም በዚህ መሠረታዊ ሐሳብ ላይ ተመርኩዘን እመቤታችን በምድር የነበራትን ሕይወት እና ዕረፍቷን እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

# ትምህርቱ

## 1. ታሪክ

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ኢያቄም እና ሐና ከተባሉ ቅዱሳን፤ በጸሎት፣ በስእለት እና በቅድስና ኑሮም ግንቦት ፩ ቀን ፶፬፻፹፭/5485/ ዓ.ዓ (ከክርስቶስ ልደት በፊት) ተወለደች። ***" ኦ ድንግል አኮ በፍትወተ ደነስ ዘተነፀነስኪ አላ በሩካቤ ዘበሕግ እም ሐና ወኢያቄም ተወለድኪ - ድንግል ሆይ በኃጢአት ፍትወት የተፀነስሽ አይደለሽም በሕግ በሆነ ሩካቤ ከሐና ከኢያቄም ተወለድሽ እንጂ "*** (አባ ሕርያቆስ ቅዳሴ ማርያም 38) ዳዊትም ***"መሠረቶችዋ በተቀደሱ ተራሮች ነው "*** መዝ. ፹፮(፯)÷፩ ሲል ተንብዮኣል።
- ወላጆቿ በተሳሉት ስእለት መሠረትም በሦስት ዓመቷ ወደ ቤተ መቅደስ ገባች። በዚያም ዐሥራ ሁለት ዓመት ኖረች።
- በዐሥራ አምስት ዓመቷ ዘመዷ የሆነው አረጋዊው ዮሴፍ እንዲጠብቃት በአደራ ተቀብሎ ወሰዳት። በትሕትና እያገለገለችው ሳለ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ተልኮ አበሠራት።
- ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ በአክብሮት፤ ‹‹***ጸጋ የሞላብሽ ደስ ይበልሽ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው***›› አላት። ሉቃ.፩÷፳፰ እመቤታችን ግን በትሕትናና በድንጋጤ፤ ‹‹***ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?***›› አለች።
- መልአኩም በእግዚአብሔር ፊት የተወደደችና የተመረጠች መሆኗንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትወልደውም አበሠራት።
- እመቤታችን ወንድ አላውቅም፤ ስትለውም፤ ያለወንድ ዘር በመንፈስ ቅዱስ እንደሚወለድ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም፤ ብሎ አበሠራት። በዚህ ጊዜ በፍጹም ትሕትና፤ እነሆኝ የጌታ ባርያው እንደቃልህ ይሁንልኝ፤ አለች። ጌታችንንም ፀንሳ በይሁዳ ቤተልሔም በከብቶች ግርግም ወለደችው።
- እመቤታችን ጌታችንን በአርባኛው ቀን ወደ መቅደስ ስትወስደው አረጋዊው ስምዖን ከባረካቸው በኋላ እመቤታችንን ‹‹***በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል***›› አላት። ሉቃ ፪÷፴፭
- ጌታችን በተወለደ በሁለተኛው ዓመት ሄሮድስ ሊገድለው ስለፈለገ፤ እመቤታችን ልጅዋን ይዛ ከእስራኤል ወደ ግብጽ ተሰድዳለች። ጌታችንን ከወታደሮችና ከክፉ ሰዎች ሰይፍና አደጋ ለማዳን በረሓ ለበረሓ ተንከራታለች። ነፍስን የሚወጋ የሐዘን መከራዎችም አሳልፋለች።
- ስደቱ በሦስት ዓመት ከመንፈቅ ተፈጸመና ናዝሬት ተመልሰው ኖሩ።
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሠላሳ ዓመቱ ሲገለጥም በቃና ሰርግ ቤት ተአምራት የፈጸመው በእመቤታችን ጥያቄ ነበር። ዮሐ. ፪÷፩-፲፩። ጌታችን መከራ ሲቀበልና በመስቀል ሲሰቀል፤

www.zeorthodox.org

‹‹የሐዘን ሰይፍ የተወጋው የእመቤታችንን ልቧን በርኅራኄ ያየው ጌታ በመስቀል ላይ ይወደው ለነበረው ደቀ መዝሙር፤ ‹‹*እነኋት እናትህ*›› ዮሐ ፲፱፥፳፯ አለው፡፡

⌘ መንፈስ ቅዱስ ለአንድ መቶ ሃያው ቤተሰብ ሲወርድም እመቤታችን ባለችበት ነበር፡፡ የሐዋ.ሥ ፩፥፲፬ እና ፪፥፩-፪

⌘ ከጌታችን ዕርገት በኋላ እመቤታችን ወደ ጎልጎታ (የጌታ መቃብር) እየሄደች በመጸለይ ለዐሥራ ስድስት ዓመታት ኖራለች፡፡ በመጨረሻም ጌታችን ቃል ገብቶላት ከዚህ የመከራ ዓለም ጥር ፳፩ ቀን ፵፱ ዓ.ም ዐርፋለች፡፡ ‹‹*ውዴ እንዲህ ብሎ ተናገረኝ ፤ወዳጄ ሆይ ተነሽ ውበቴ ሆይ ነይ፣ እነሆ ክረምት አለፈ ዝናቡም አልፎ ሄደ (የመከራው ጊዜ አለፈ ማለት ነው)*›› መኃ. ፪፥፲-፲፩

⌘ ከዚያም በነቢዩ ዳዊት፤ ***"አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ አንተና የመቅደስህ ታቦት"*** መዝ ፻፴፩(፪)፥፰ ተብሎ የተነገረው ትንቢት እንዲፈጽም፤ ጌታ እንደተነሣ እመቤታችንም ተነሥታለች፡፡ ስልሣ አራት ዓመታት በምድር ኖራለች፡፡

## ምን እንማራለን?

- ከእመቤታችን ሕይወት በዋናነት ፍቅር፣ ታዛዥነት እና ትሕትናን እንማራለን፡፡

**ፍቅር፡-** እመቤታችን ለእግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር ነበራት ስለነበር በቤተ መቅደሱም በሙሉ ልብዋ ታገለግለው ነበር፡፡ በመከራ ሁሉ የጸናችው ከፍቅርዋ የተነሣ ነው፡፡ ዛሬም ልጆችዋን በዚህ ፍቅር ትረዳናለች፡፡

***ታዛዥነት፡-*** መልአኩ በእግዚአብሔር ስም የነገራትን ቃል ተቀብላ፤ ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም የተፈጸመም ባይሆን በፍጹም ታዛዥነት ‹‹***እንደ ቃልህ ይሁንልኝ***›› ነበር ያለቸው፡፡ እኛም በሕይወታችን ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዲፈጸምልን በቅንነት መታዘዝን ያስተምረናል፡፡

**ትሕትና፡-** እመቤታችን በንጽሕና መኖርዋን እያወቀች፤ ‹‹***እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?***›› ነበር ያለቸው፡፡ ጌታችንን ፀንሳ የእግዚአብሔር እናት ሆናም እንኳን፤ ‹‹***የባርያይቱን ውርደት ተመልክቶልና***›› ሉቃ.፩፥፵፰ በማለት በትሕትና ራሷን ዝቅ አድርጋ ኖራለች፡፡ እኛም እግዚአብሔር ሲያከብረን ትሕትናን መጎናጸፍ እንደሚገባን ያስተምረናል፡፡

www.zeorthodox.org

- እመቤታችን በማንኛውም ዘመን ቢታና አኗኗር ለክርስቲያኖች ሁሉ ምሳሌያችን ናት፡፡ **የእመቤታችን ፍቅር፣ ትሕትናና ታዛዥነት ከእናታችን ከሔዋን ጋር በማነጻጸር የሔዋንን ስሕተት እንዴት እንዳረመችው እንመልከት፡፡**
- ሔዋን የራሷን ክብር ስትፈልግ እንደ እግዚአብሔር እሆናለሁ ብላ በኃጢአት ወድቃለች፡፡ የተከለከለውን ዕፀ በእባብ ምክር ተሸንፋ በልታለች፡፡ ውጤቱም እርሷን፣ አዳምንና ልጆቻቸውን ሁሉ ወደ ሞት ጥሎአል፡፡

- የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ግን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ሲያበሥራት፤ ‹‹***እነሆ የጌታ ባርያው***›› ስትል፤ በትሕትና በቅን ታዛዥነት ቃሉን ተቀበላ፤ በትሑታን የሚያድር መንፈስ ቅዱስ አደረባት፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፀንሳ ወለደች፡፡

## አስተርእዮ ማርያም

- የማርያም መገለጥ ማለት ነው፡፡ የጌታችንን መገለጥ በምናስብበት ወራት ውስጥ ያለ በዓል ስለሆነ፤ እንዲሁም በጥር ፳፩ ቀን በሚነበበው መጽሐፈ ስንክሳር፤ እመቤታችን ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር በደብረ ማኅው የተገለጠችበትም ነው፡፡ ስለዚህ አስተርእዮ ማርያም ብለን እናከብረዋለን፡፡
- እመቤታችን ብዙ ጊዜ እየተገለጠች በግልና በማኅበር ትታያለች፤ እኛን ልጆቿን ትባርከናለች፡፡ ትራዳለችም፡፡ ለዚህም ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙኃን የዘገቡትን የእመቤታችንን መገለጥ http://www.Zeitun-eg.org/warrag.html/ ድረ ገጽ ላይ ይመልከቱ፡፡

www.zeorthodox.org

# ገዳማዊ ሕይወት

## ዐሥራ አንደኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

⌘ ተማሪዎች፤ ስለ ገዳማዊ ሕይወት አውቀው ስለ አንድ ገዳም ሥርዓት ይጽፋሉ፡፡

### የሚጠና ጥቅስ፡-

⌘ *"ራሱም ዮሐንስ የግመል ጠጕር ልብስ ነበረው፤ በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ ነበር፤ ምግቡም አንበጣና የበረሓ ማር ነበረ፡፡"* ማቴ.፫÷፬

### ተጨማሪ ምንባብ እና ምንጭ፡-

⌘ ፩ኛ ቆሮ . ፯÷፩-፵ ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት አጭር ታሪክ፡፡

### መግቢያ፡-

- ገዳም የሚለው ቃል በቁሙ ሲፈታ፤ በረሓ ጫካ ማለት ነው፡፡
- " ገዳማዊ " በተግባራዊ ዘይቤ" *የላመ ሳይቀምስ፣ የደመቀ ሳይለብስ፣ ጤዛ ልሶ፣ ድንጋይ ተንተርሶ፣ ድምፀ አራዊትን ግርማ ሌሊትን ታግሦ፣ ከዓለማዊ ኑሮ ርቆ ፣ ከሥጋዊ ሥራ እና ተድላ ደስታ ተጠብቆ፣ በዕለታዊ ኑሮው ሁሉ...፣ ራሱን በራሱ እየረዳ ዘወትር በጸምና በጸሎት፣ በገድልና ትሩፋት ተጠምዶ የሚኖር የእግዚአብሔር ሰው "* ማለት ነው ፡፡

## ትምህርቱ፡-

### አጀማመሩ፡-

www.zeorthodox.org

- ገዳማዊ ሕይወትን ኤልያስ በኮሬብ፤ዮሐንስ በዮርዳኖስ ማዶ ባለች በረሓ በመኖር አሳይተዋል፡፡ ፩ኛ ነሥት.፲፱÷፩-፳፣ ማቴ.፫÷፩-ፍጻሜው፡፡ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎአል፡፡
- በተለይም የመጥምቁ ዮሐንስ የገዳም ኑሮው በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ነበር፡፡ ከዚሁም ጋር አለባበስ እና አመጋገቡም ከዓለማዊ ምቾትና ተድላ ደስታ የራቀ የተለየም ነበር፡፡ "*ራሱም ዮሐንስ የግመል ጠጕር ልብስ ነበረው፣ በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ ነበር፤ ምግቡም አንበጣና*

***የበረሓ ማር ነበረ።"*** ማቴ.፫÷፬

- ጌታችንም የሥራውን መጀመሪያ ያደረገው በገዳመ ቆሮንቶስ ዐርባ ቀን እና ዐርባ ሌሊት በማሳለፍ ነው። ማቴ.፬÷፩-፲፩
- ይህንኑ መሠረት በማድረግ ዓለማዊ ክብርን የናቁ እና ራሳቸውን ለክርስቶስ ያጩ አባቶች እና እናቶች በገዳም ኖረዋል። የኑሮው ሥራዓት እና የገዳማቱ አመሠራረት ከላይ ባየናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ አባቶች እና በጌታችን መከራ እና ትምህርት ላይ በመመርኮዝ ነው።
- ገዳማውያን ኑሮአቸው ከሴት ርቀው (ከተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ተለይተው)፤ በበኣታቸው በጾም በጸሎት ተወስነው፣ ለማኅበር ሥርዓት ታዘው ቅዱሳት መጻሕፍትን በመመርመር ነው።
- የዚህ ዓይነቱ ገዳማዊ ሕይወት መሥራች በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ የተነሣው ግብጻዊ መናኝ አባ እንጦንስ ይባላል። የገዳማውያን ኑሮ በቀዋሚ ሕግና ሥነ ሥርዓት እንዲመራ የተደረገው ደግሞ በዚሁ ዘመን በተነሣው ግብጻዊ መናኝ አባ ጳኲሚስ ነው።
- ስለ ሆነም ገዳማዊው ሕይወትና ቀኖና(ሥርዓት) አሁን ያለው ይዘትና ቅርጽ እንዲኖረው የተደረገው በእነዚሁ ሁለት አንጋፋ አበው መሆኑ የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እምነት ነው።
- የእነዚህን ታላላቅ ታሪክ መነሻ አድርጎ መግለጽ ግዴታ ቢሆንም ከእነዚህ ገዳማውያን አበው በፊትም ***"የዋሕ ጳውሊ"*** የተባለ መናኝ እንዲህ ዓይነቱን የበረሓ ኑሮ ይኖር ነበር ።
- በገዳም ሕግና ሥርዓት ወንዶችና ሴቶች መናንያን በአንድ ገዳም ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሰጥተው መኖራቸው የክርስትናውን ዓለም ትኩረት ስለሳበ በቅጽበት እየተስፋፋ ሄደ።
- ይህን ትውፊት ከተቀበሉት የክርስትና ሀገራት አንዷ ኢትዮጵያ ናት።

## ሀ. የገዳማት አመሠራረት በኢትዮጵያ

- ኢትዮጵያ የብዙ አብያተ ክርስቲያናት ባለቤት እንደሆነች ሁሉ አያሌ ገዳማትም የሚገኙባት አገር ናት።
- የእነዚህ ገዳማት ምሥረታ ሂደት የተጀመረውም በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ከሶርያ ግብጽና ከሌላውም የግሪኮ-ሮማን ግዛት በመጡ ዘጠኝ ቅዱሳን ነው።
- በአሁኑ ጊዜ ***"ተሰዓቱ ቅዱሳን - ዘጠኙ ቅዱሳን"*** እየተባሉ የሚጠሩትም እነዚህ አበው ናቸው።
- ቅዱሳኑ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በኑፋቄ ምክንያት በአካባቢያቸው ከተፈጠረው አደገኛ ሁከት በመሸሽ ነው። ወደ ኢትዮጵያ ለመፍለስ የመረጡትም ኢትዮጵያ የኑፋቄውን ትምህርት የምትቃወም እና እንግዶች የሚያርፉባት ነጻ የክርስትና ሀገር የመሆንዋን ዜና በመስማታቸው ነበር። ከቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ማረጋገጥ እንደሚቻለውም የእነዚህ

www.zeorthodox.org

ቅዱሳን ስም፡- አባ አሌፍ፣ አባ አረጋዊ፣ አባ ሊቃኖስ፣ አባ አፍጼ፣ አባ ገሪማ፣ አባ ጉባ፣ አባ ይምዓታ፣ አባ ጰንጠሌዎን፣ አባ ጽሕማ ይባላሉ፣

⌘ ከእነዚህ ቅዱሳን በፊትና በኋላም እንደ አባ ሊባኖስ እና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ያሉ ቅዱሳን ወደ ኢትጵያ በመግባት ለገዳማዊ ሕይወት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

⌘ እነዚህ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የገዳማዊ ኑሮ መሠረት በመጣሉ በገዳማቱ መመሥረት የቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ ሕይወት ትናንት የነበረውንና ዛሬም ያለውን ስፋትና ጥልቀት እንዲያገኝ አድርጎታል፡፡

⌘ የገዳማዊ ሕይወት መጀመር በንጥቂያ፣ በግፍዕና ዓመፅ ተግባር ተሰማርተው ለነበሩ ወገኖች ሁሉ አስተማሪ ነበር፤ ነውም፡፡

⌘ በኢትዮጵያም የመጀመሪያው ገዳም ደብረ ዳሞ ሲሆን መሥራቹም ጻድቁ አቡነ አረጋዊ ናቸው፡፡

## ለ. ገዳማዊ አኗኗር በኢትዮጵያ

ገዳማዊ ኑሮ በሁለት ይከፈላል፡፡ አንደኛው ***የአንድነት ገዳም*** ሲባል፤ ***ሁለተኛው*** ደግሞ የቁሪት ገዳም ይባላል፡፡

1. **የአንድነት ገዳም** የሚባለው፤ በአንድነት ሠርቶ በአንድነት መመገብ፣ በአንድነት መጸለይና ገዳማዊ አገልግሎትን በኅብረት መፈጸም የሚቻልበት የገዳም ሥርዓት ነው፡፡

- በዚህ ዓይነቱ ገዳም ምንም ዓይነት የግል ንብረት ይዞታ አይፈቀድም፡፡ ያለ ጸሎትና ተግባር ሥራ ፈት ሆኖ መቀመጥም በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡
- ያለ በቂ ምክንያትና ከገዳሙ ማኅበር ፈቃድ ውጪ ከገዳሙ መውጣት ወደ ሌላ ቦታ መሔድ አይፈቀድም፡፡ አመጋገቡም የገዳሙ ቀኖና የሚፈቅደውን የምግብ ዓይነትና መጠን ብቻ ነው፡፡
- በሞት ለሚለይ የገዳሙ አባል ማልቀስና ማዘን፣ በሥራ መለገም፣ ስሕተትን መደበቅ፣ ሌሎችም የገዳሙ ሥርዓት የማይፈቅዳቸውን በዓለማዊ ኑሮ የሚታዩ ነገሮችን መፈጸም አይቻልም፡፡ በጠቅላላ የዓለማዊና ሥጋዊ ፍላጎት ተገዥ መሆን የገዳማዊ ሕይወት መገለጫ አይደለም፡፡
- ከመገልገል ይልቅ ለማገልገል መፋጠን የገዳማዊ ኑሮ ሌላው ግዴታ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ገዳም የሥራ እንጂ የሰነፍ ቦታ ባለመሆኑ ማንኛውም ገዳም የሚተዳደረው ገዳማውያኑ ሠርተው በሚያገኙት ገቢ ነው፡፡ አንድ ገዳም ከራሱ የልማት ሥራ እና ገቢ አልፎ በአካባቢው ለሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ የልማት አርአያ ነው፡፡
- ሥራ አለመፍታትም ራሱ የምናኔ ሕይወት ሌላው ገጽታ ነው፡፡ በእርጅና ወይም በሕመም

www.zeorthodox.org

ምክንያት ለመሥራት የማይችል አቅመ ደካማ ካልሆነ በቀር በተረጅነት እንዲኖር የሚፈቅድም ሆነ የሚፈቀድለት ገዳማዊ የለም፡፡ አቅመ ደካማ እንኳ ቢሆን ማኅበሩ ድካሙን አይቶ ከሥራ ነጻ እንዲሆን ካላደረገው በቀር እሱ ራሱ ደክሜያለሁ ልረፍ ብሎ አያርፍም፣ ልረፍ ብሎም አይጠይቅም፡፡

- የአንድነት ገዳም ከቅዱስ እስጢፋኖስ ሰማዕትነት በፊት እንደነበረችው ቤተ ክርስቲያን የአንድነት ኑሮን መኖር ማለት ነው፡፡
- ከገደማውያኑ መካከል ወደ ብቃት የደረሱ ገዳማውያን በማኅበረ ገዳሙ ፈቃድና ቡራኬ ከገዳሙ አንድነት ሳይለዩ በልዩ ቦታ ተወስነው የተባሕዎት (የብቸኝነት) ኑሮ መኖር ይችላሉ፡፡ እነዚህ መናንያን የተባሕትዎ ኑሮ የሚያስከትለውን ፈተና ሁሉ መቋቋም የሚችሉበት መንፈሳዊ ብቃት ስላላቸው ለክፉ መንፈስ የተጋለጡ አይሆኑም፡፡
- ከፍራፍሬና ከሥራ ሥር በቀር ሌላ እህል የማይቀመስባቸው ገዳማትም አሉ፡፡

2. **የቁሪት ገዳም** የሚባለው፤ ከአንድነት ገዳም የሚለየው በግል መመገብ እና የተወሰነ ንብረት መያዝ ስለሚፈቀድ ነው፡፡ ከዚህ በቀር ከአንድነት ገዳም ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

## ተባሕትዎ

- ስለ ገዳማት ስናነሣ የማይታለፍ ዓቢይ ነገር ተባሕትዎ ነው፡፡
- ከገዳማት ርቀው በሚገኙ ጫካዎችና ዋሻዎች እንደ መልከ ጼዴቅና እንደ ዮሐንስ መጥምቅ የተለየ አለባበስና አስፈሪ ግርማ ሞገስ ያላቸው ባሕታውያን የሚከሠቱበት ጊዜ አለ፡፡ እነዚህ ባሕታውያን በኅበረተሰቡ አጠራር "ግሑሳን" ይባላሉ፡፡ "ግሑስ" ማለትም "ከሰው ርቆ የሚኖር ስውር ባሕታዊ" ማለት ነው፡፡
- እነዚህ ግሑሳን ባሕታውያን ራሳቸውን ግልጽ ለማድረግ ካልፈለጉ በቀር ማንም ሰው ፈልጎ ሊያገኛቸውም ሆነ ሊያያቸው አይችልም፡፡ በሚታዩበት ጊዜም ግርማቸው አስፈሪ ነው፡፡ ኅብረተሰቡ ታዲያ ይህን ምስጢር ስለሚያውቅ ሰው በማይደርስበት በረሐም ሆነ ዋሻ የወደቀ አጽምና እንዲሁም መጽሐፍ፣መስቀል፣መቋሚያ፣ ጭራ ሌሎችም ለተመሳሳይ የብሕትውና አገልግሎት የሚውሉ ነገሮችን ሲያገኝ የእነዚህ ቅዱሳን ቅሪት ነው ብሎ በክብር ይጠብቀዋል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

⌘ ከመጻሕፍት ወይም፣ ከሊቃውንት አባቶች ወይም ከቦታው ድረስ ሔዳችሁ በመጠየቅ ስለ አንድ ገዳም ሥርዓት ጻፉ እና አቅርቡ፡፡

# ኀልዎተ እግዚአብሔር

## ዐሥራ ሁለተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

⌘ ተማሪዎች፤ ስለ እግዚአብሔር ህልውና በቂ ግንዛቤ አግኝተው በክፍል ውስጥ እና ለቤተሰባቸው ያስረዳሉ፡፡

### የሚጠና ጥቅስ፡-

⌘ ‹‹ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና፡፡›› ዕብ.፲፩፥፮

### መግቢያ

- አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ከዓለም አስቀድሞ የነበረ ዓለሙን አሳልፎ የሚኖር ዘለዓለማዊ ነው፤ የፈጠረን የሚመግበን እና የሚንከባከበን እርሱ ነው፡፡ ***‹‹የሚታዩትና የማይታዩትም፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፣ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና. . . ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፡፡ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል፡፡››*** ቆላ.፩፥፲፮-፲፯
- ከዚህ በፊት በነበረው ትምህርታችን ስለ ሃይማኖት ስንማር ስለ ዶግማ፣ ቀኖና እና ትውፊት አንሥተን፤ ዶግማ ስለ እግዚአብሔር ያለን ትክክለኛ እምነት ምንድነው የሚለውን እንደሚያሳውቀን ተምረናል፡፡
- በዛሬው ትምህርታችንም ስለ እግዚአብሔር ህልውና ወይም መኖር እንማራለን፡፡

## የትምህርቱ ዋና ትኩረት

www.zeorthodox.org

⌘ ህልዎተ እግዚአብሔር ስንል የእግዚአብሔር መኖር ማለታችን ነው፡፡ እግዚአብሔር እንዳለ እና ለሚፈልጉትም እንደሚገለጥላቸው እና ዋጋ እንደሚሰጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎአል፡፡ ***‹‹ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና፡፡››*** ዕብ.፲፩፥፮

⌘ እግዚአብሔር ራሱን በብዙ መንገድ ገልጦአል፡፡ ***‹‹ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮአል፡፡››*** ዕብ.፩፥፩

⌘ ስለምናመልከው እና ስለምንከተለው እግዚአብሔር መኖር ከሚያስረዱን የሚከተሉትን በዋናነት እንመለከታለን።

## *1. ፍጥረት፡-*

***‹‹ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፣ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን።››*** *ዕብ.፲፩፥፫*

- ሸክላ ባለሞያውን፣ሥዕል ሠዓሊውን፣ ወንበር እና ጠረጴዛ አናጺውን፣ ጽሑፍ ጸሓፊውን እንደሚያመለክቱ ፍጥረታትም አስገኚያቸውን እግዚአብሔርን ያመለክታሉ።
- ለዚህም ነው በመጽሐፈ ኢዮብ ‹‹. . . ***አሁን ግን እንስሶችን ጠይቅ፣ ያስተምሩህማል፤ የሰማይንም ወፎች ጠይቅ፣ ይነግሩህማል። ወይም ለምድር ተናገር፣ እርስዋም ታስተምርሃለች የባሕርም ዓሣዎች ይነግርሃል። የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንዳደረገ ከእነዚህ ሁሉ የማያውቅ ማን ነው?››*** ኢዮ.፲፪፥፯-፱ ሲል የገለጠውን በማጉላት፤ ነቢዩ ዳዊትም ***‹‹ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፣ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል። ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች፣ ሌሊትም ለሌሊት ዕውቀትን ትናገራለች።››*** መዝ.፲፰(፲፱)፥፩-፪ በማለት ፍጥረታት ስለ እግዚአብሔር እንደሚመሰክሩ ገልጿል።
- ምክንያት የሌለው ፍጥረትና የማያስፈልግ አካል አለመኖሩን እንዲሁም አንዱ ለሌላው የግድ አስፈላጊ ከመሆኑ ጋር የፍጥረታትን ድንቅ ነገር እናስተውላለን። ይህን መሠረት በማድረግ ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር እንዲህ እንላለን። ***‹‹የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያል፤››*** ሮሜ.፩፥፳

## *2. የልቡና ሕግ ወይም የሕሊና ዳኝነት*

***‹‹ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፣ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፣ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።››*** ሮሜ.፪፥፲፬-፲፭

www.zeorthodox.org

⌘ በየትኛውም ዓለም ያለ ሰው ከእንስሳት ተለይቶ ሲሳሳት የሚወቅሰው መልካም ሲያደርግም የሚያስደስተው ስሜት አለው። ይህንንም የሕሊና ዳኝነት ወይም በቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት በልብ የተጻፈ ሕግ እንለዋለን።

⌘ ሰዎች በዚህ ሕግ ተመርተው ፈጣሪያቸውን ማወቅ፣ ማምለክ እና ማስደሰት ይችላሉ።

⌘ ዳግመኛም እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተጠቅመው በእውነት ያወቁትን ቅዱሳን በማለት

በእግዚአብሔር ቤት እናከብራቸዋለን፡፡ በተቃራኒው ደግሞ እግዚአብሔርን ያገኙ መስሎአቸው በብዙ መንገድ የተሳሳቱንም ታሪክ እና መጽሐፍ ቅዱስ ይነግሩናል፡፡

***መምህር፡-*** የአብርሃምን እግዚአብሔርን ፍለጋ ከትውፊተ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም የልስጥራን ሰዎችን ታሪክ ከግብረ ሐዋርያት ፲፬፥፰-፲፰ ለተማሪዎች ይተርኩላቸው፡፡

### *3. ቅዱሳት መጻሕፍት፡-*

***‹‹ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፣ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቀሃል፡፡ የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡*** ፪ኛ ቆሮ.፫፥፲፮-፲፯

- እግዚአብሔርን ***በማመን፣ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡን የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን*** ስንማር እና ስናነብ ወደ እግዚአብሔር ያደርሱናል፡፡
- ምክንያቱም የተጻፉት በመንፈስ ቅዱስ ስለሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ አለባቸው እና እግዚአብሔርን ለማወቅ ይጠቅማል፡፡ ይህንን ያስረዳን ሐዋርያ በሌላ ቦታ ‹‹. . .***መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው፡፡ በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም፡፡ እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም፡፡››*** ፩ኛ ቆሮ.፩፥፲-፲፪፡፡ እና እግዚአብሔር በመንፈሱ እንዲጻፉ ባደረጋቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ራሱን ገልጦአል፡፡ ***‹‹እግዚአብሔር ለሕዝቡ፣ በውስጥዋም ለተወለዱት አለቆችዋ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል››*** መዝ.፹፯(፹፮)፥፮
- በዚህ መሠረት እግዚአብሔር ስለ እርሱ እንድናውቅ የሰጠን ቅዱሳት መጻሕፍት ስለእርሱ ይነግሩናል፡፡

## ማጠቃለያ www.zeorthodox.org

- እግዚአብሔር የነበረ ያለ እና የሚኖር ነው፡፡ በፍጥረቱ፣ በሕገ ልቦና እና በቅዱሳት መጻሕፍት ይታወቃል፡፡

## ተግባር

1. ተማሪዎች፤ እግዚአብሔርን የሚያስታውሳችሁን ነገር ለመምህር እና ለቤተሰብ አስረዱ፡፡
2. ‹‹ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና፡፡›› ዕብ.፲፩፥፮ በማመን ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ ዋጋ እናገኛለን፡፡
3. ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ ለሕይወታችን አስፈላጊ ከመሆኑም በተጨማሪ ስለ እግዚአብሔር እንድናውቅ ያስችለናል፡፡ ወጣቶች ስትተኙ እና ከእንቅልፋችሁ ስትነቁ የቻላችሁትን ያህል መጽሐፍ ቅዱስ ማንበቢያ ጊዜ ይኑራችሁ፡፡

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

## ዐሥራ ሦስተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

⌘ ተማሪዎች በትምህርቱ መጨረሻ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አውቀው ያስረዳሉ፡፡

### የሚጠና ጥቅስ፡-

⌘ ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ›› የሐዋ.ሥ. ፲÷፴፯

## መግቢያ

- ኢትዮጵያውያን በሕገ ልቦና፤ በሕገ ኦሪት እና በሕገ ወንጌል እግዚአብሔርን ሲያመልኩ የኖሩ ሕዝቦች ናቸው፡፡
- ዋናው ርእሰ ጉዳያችን ወደ ሆነው ሕገ ወንጌል የተሰጠችባትን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስንመለከት፤ ክርስትና በ፴፬(34)ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን ታሪክ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ በግብረ ሐዋርያት እንደሚከተለው ዘግቦልናል፡፡ ***‹‹የጌታም መልአክ ፊልጶስን ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደ ሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው፡፡ ተነሥቶም ሄደ፡፡ እነሆም ሕንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ፣ በገንዘቧ ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሳለም ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር፤ ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር፡፡ መንፈስም ፊልጶስን ወደዚህ ሠረገላ ቅረብና ተገናኝ አለው፤ ፊልጶስም ሮጦ*** *የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰማና የምታነበውን ታስተውለዋለህን? አለው እርሱም፡- የሚመራኝ ሳይኖር እንዴት ይቻለኛል? አለው፡፡ ወጥቶም ከእርሱ ጋር ይቀመጥ ዘንድ ለመነው፡፡ . . . እባክህ ነቢይ ይህን ስለማን ይናገራል? ስለራሱ ነውን ወይስ ስለ ሌላ አለው፡፡ ፊልጶስም አፉን ከፈተ፤ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት፡፡ በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውኃ ደረሱ ጃንደረባውም፡- እነሆ ውኃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው? አለው፡፡ ፊልጶስም በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል አለው፡፡ መልሶም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ አለ፡፡ ሰረገላውም እንዲቆም አዘዘ፤ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ አጠመቀውም፡፡››* የሐዋ.ሥራ. ፰÷፳፮-፴፰

www.zeorthodox.org

- የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎቹ አውሳብዮስ ዘቂሳርያና ሄሬኔዎስ እንዲሁም ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህ ጃንደረባ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ክርስትናን እንደሰበከ ጽፈዋል፡፡ የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በዚህ መልኩ በ፴፬(34) ዓ.ም ነበር፡፡
- ይሁን እንጂ እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ግን ክህነት አልመጣም፤ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንም /ጥምቀት፣ቁርባን፣. . ./ መፈጸም አልተጀመረም ነበር፡፡ በ፫፻፴(330) ዓ.ም በአክሱም ቤተ መንግሥት ያደገውና በትውልድ ግሪካዊ የሆነው ፍሬምናጦስ በዐሥራ ሰባተኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ አማካኝነት ጵጵስናን ተሹሞ ከመጣ በኂላ ግን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን መፈጸም ጀምረዋል፡፡
- ከዚህ በኂላ በነበሩት ዘመናት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማና የስኬት ዘመናትን እንዲሁም አሳዛኝ የውድቀትና የጥፋት ዘመናትን በማፈራረቅ አሳልፋለች፡፡ ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያለውን የቤተ ክርስቲያኒቱን ታሪክ በአጭሩ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## የትምህርቱ ዋና ይዘት

### ከ4ኛ– 6ኛ መቶ ክፍለ ዘመን

- ⌘ አባ ሰላማ (ከሣቴ ብርሃን) ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንትና መምህራን ጋር በመሆን ስብከተ ወንጌልን በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ወደ ምዕራብ እስከ ዛሬዋ ሱዳን ድረስ፣ ወደ ደቡብ እስከ ዛሬዋ ሶማልያ ድረስ ወደ ምሥራቅ እስከ ደቡብ ዐረቢያ/የዛሬዋ የመን ድረስ/ አስፋፍተዋል፡፡ በርካታ ቅዱሳት መጻሕፍትም በዚህ ዘመን ወደ ግእዝ ተተርጉመዋል፡፡
- ⌘ በ፬፻፶፩(451)ዓ.ም የተደረገውን የኬልቄዶንን ጉባኤ ባልተቀበሉ ኦርቶዶክሳውያን ላይ ካቶሊካውያን መከራ ባጸኑባቸው ጊዜ ዘጠኙ ቅዱሳን በስደት ወደ ሀገራችን ገቡ፡፡
- ⌘ እነርሱም በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ወንጌልን ሰበኩ፤ ገዳማዊ ሕይወትን አስፋፉ፣ መጻሕፍትንም ከተለያዩ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ ተረጎሙ፡፡
- ⌘ በዚሁ ዘመንም ቅዱስ ያሬድ ተነሥቶ ቤተ ክርስቲያናችን እስከ ዛሬ ድረስ የምትጠቀምበትን ዜማ እና የዜማ መጻሕፍት ደርሷል፡፡
- ⌘ ሌላው የክርስትና ፍሬ በዘመኑ ከነበረው አስተሳሰብ አንጻር በሃይማኖት የማይመስሉንን የእስልምና እምነት ስደተኞች አገራችን በእንግድነት ተቀብላቸዋለች፡፡ ጥቂቶቹ ክርስቲያን ሲሆኑ ሌሎቹ በሰላም በእንግድነታቸው ቆይተዋል፡፡ የሄዱትም በሰላም ተሸኝተዋል፡፡ ይህ መልካም ተግባር ስለ ኢትዮጵያ ክርስትና በሌላው ዓለም የነበረው ዝና እና ሕያው ክርስትና መገለጫ ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

**ከ7ኛው–10 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን**

⌘ በዚህ ዘመን ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እያበበ መጥቶ የነበረው ክርስትና በከፍተኛ ሁኔታ በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች ተዳክሟል፡፡

1. በዐረቢያ ምድር የእስልምና መነሣትና በእስልምና ኀይሎች ምክንያት የኢትዮጵያ የባሕር በሮች መዘጋት፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች የክርስትና ዓለም ጋር የነበራት ግንኙነት መዳከም፡፡
2. ዮዲት በተባለች ሴት መሪነት በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ አይሁዳውያን ተነሥተው ክርስቲያኖችን ማሳደዳቸውና መግደላቸው፣ አብያተ ክርስቲያናትንና መጻፍትንም ማውደማቸው ነው፡፡

**ከ10ኛው–15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን**

- ይህ ዘመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልእኮ እንዲሁም መንፈሳዊ አገልግሎት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ዘመን ነው፡፡
- የዛግዌ ነገሥታት (ሀርቤይ፤ ላል ይበላ፤ ነዐኩቶ ለአብ፤ ይምርሀነ ክርስቶስ) የሠሩዋቸው ድንቆቹ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት የዚህ ዘመን ፍሬዎች ናቸው፡፡ ከመሪዎቹ እስከ ሕዝቡ የነበረው የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት ከፍተኛ ነበር፡፡
- አባ ኢየሱስ ሞአ የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳምን መሥርተው በገዳሙ ውስጥ በርካታ ደቀ መዛሙርትን አስተምረዋል፡፡ ከገዳሙ የወጡ በርካታ አባቶች ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች አሰማርተው ወንጌልን ሰብከዋል፡፡ ለምሳሌ ያህልም አቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቡብ ኢትዮጵያን፣ አባ ጊዮርጊስ ቤተ አምሃራን፣ አቡነ አስተንፋሰ ክርስቶስ ዳውንትንና አካባቢውን፣ አቡነ ዜና ማርቆስ መካከለኛው ኢትዮጵያን አስተምረዋል፡፡
- እነዚህ አባቶች ደግሞ የተለያዩ ገዳማትን መሥርተው ደቀ መዛሙርትን በማፍራታቸው የእነርሱ ደቀ መዛሙርትም ወደ ተለያዩ ቦታዎች እየሄዱ ወንጌልን ሰብከዋል፤ ክርስትናን አስፋፍተዋል፡፡
- በሰሜን ክፍል አቡነ መድኃኒ እግዚእ ከዋክብት በመባል የሚታወቁት ደቀ መዛሙርታቸው በኤርትራ ጫፎች በትግራይ፤ በጎንደር እና በዛሬው አፋር አካባቢ ክርስትናን አስፋፍተዋል፤ ገደማትን መሥርተዋል፡፡
- በዚህም ምክንያት ዘመኑ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት፣ አገልግሎቷ የተስፋፋበት እና ነገሥታት ሳይቀሩ ለክህነትና ለቅድስና የበቁበት ዘመን ሊሆን ችሏል፡፡

www.zeorthodox.org

## ከ11ኛው–21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

ይህ ዘመን በተከታታይ በተፈጠሩ /በደረሱ/ ሁኔታዎች ምክንያት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መከራ የተቀበለችበትና የተዳከመችበት ዘመን ነው፡፡

### *የአክራሪ እስልምና ወረራ*

- በ፲፻፭፻(1500) ዓ.ም አካባቢ በዘመኑ ኀያል በነበረው በቱርክ መንግሥት አስታጣቂነት የዘመተው አህመድ ግራኝ በርካታ ክርስቲያኖች ገደለ፤ ብዙዎችን በግዳጅ አሰለመ፣ ካህናትን ጨፈጨፈ፣ እጅግ በጣም ብዙ ገዳማትን፣ አብያተ ክርስቲያናትን፣ መጻሕፍትን እና ንዋያተ ቅድሳትን አቃጠለ፡፡

### *የካቶሊኮች መምጣት*

- የአህመድ ግራኝ ወረራ ሌላ ችግርን ወለደ፡፡ በአህመድ ግራኝ ወረራ ጊዜ የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት ዐፄ ልብነ ድንግል ወራሪውን ለመቋቋም የሚሆን ድጋፍ ከፖርቹጋል መንግሥት ጠይቀው ነበር፡፡
- ርዳታው በተለያዩ ምክንያቶች ሲጓተት ከቆየ በኂላ የፖርቹጋል መንግሥት ወታደሮች መጥተው በእርሱ ድጋፍ ግራኝ አህመድ ድል ሆነ፡፡
- ይሁን እንጂ ከዚህ በኂላ ከፖርቹጋል መንግሥት ወታደሮች ጋር የመጡት የካቶሊክ መልእክተኞች ‹‹ካቶሊክ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ይሁን›› የሚል ጥያቄ አቀረቡ፡፡
- ጥያቄው በጊዜው ተቀባይነት ባያገኝም ከዚያ ቀጥሎ ባሉት ዘመናት ብዙ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ወደ ሀገራችን ለመምጣት አጋጣሚ ተፈጥሮላቸዋል፡፡
- ‹‹መሣሪያና ርዳታ እናስመጣላችኂለን›› በማለትም ነገሥታቱን ያባብሉ ነበር፡፡ በመጨረሻም ዐፄ ሱስንዮስ የተሰበከላቸውን የጦር መሣሪያ ርዳታ ለማግኘት ሲሉ የካቶሊክን እምነት መቀበላቸውን ዓወጁ፤ ሕዝቡም በግዴታ የካቶሊክ እምነትን እንዲቀበል ለማድረግ ሞከሩ፡፡
- በዚህም ምክንያት ጦርነት ተከፍቶ በርካታ ምእመናን በሰማዕትነት አለቁ፡፡ በመጨረሻም ዐፄ ሱስንዮስ የነገሩን አለመሳካት አይተው ‹‹የካቶሊክ ሃይማኖት ይርከስ፣ ተዋሕዶ ትመለስ›› ብለው ዓወጁ፡፡ ሥልጣናቸውንም ለልጃቸው ለዐፄ ፋሲል አስረከቡ፡፡

www.zeorthodox.org

### *ቅብዓትና ጸጋ*

- ዐፄ ፋሲል እንደነገሡ ካቶሊካውያንን ከሀገር አባረሩ፡፡ የካቶሊካውያኑ መሪ የነበረው አልፎንዙ ሜንዴዝ ግን ‹‹ቅብዓት›› እና ‹‹ጸጋ›› የሚባሉ ሁለት የስሕተት ትምህርቶችን ለሁለት ኢትዮጵያውያን አስተምሮ ወጣ፡፡ እነዚህ ሁለቱ የስሕተት ትምህርቶች ቤተ ክርስቲያንን የበለጠ አዳከሚት፡፡

***ዘመነ መሳፍንት***

- ይህ ዘመን በኢትዮጵያ ጠንካራ ማዕከላዊ አስተዳደር የጠፋበትና ሀገሪቱ ተከፋፍላ በተለያዩ መሳፍንት እጅ የወደቀችበት ዘመን ነው፡፡
- ይህ መሆኑ ቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊነት ያለው ጠንካራ አገልግሎት እንዳትፈጽምና በእስልምና ወረራ ለተጠቁት ክርስቲያኖች እንዳትደርስ ከማድረጉም በላይ ሚሲዮናውያን ወደ ሀገራችን እንዲገቡ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል፡፡

***ከዘመነ መሳፍትን በኋላ ፲፰፻፶፭-፲፱፻፶፩/1855-1951/ ዓ.ም***

- በካቶሊኮች የተረጨው የቅብዐትና የጸጋ መርዝ፤ ዐፄ ዮሐንስ በቦሩ ሜዳ እንዲካኼድ ባደረጉት ክርክር በተዋሕዶ ድል አድራጊነት ተደመደመ፡፡
- ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልዕኮዋ በመጠኑም ቢሆን ማንሠራራት ጀመረ፡፡ ሆኖም የብዙ ዘመን አረም የወረሰውን ክርስትና ለመፈለግ ቀላል አልነበረም፡፡
- ይህንኑ ችግር ቀርፎ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሐዋርያዊ ተልዕኮ ለማጠናከር በ፲፱፻፳፩(1921) ዓ.ም አራት ኢትዮጵያውያን ካይሮ ላይ ጵጵስና ተሾሙ፡፡ እነርሱም፡- አቡነ አብርሃም፣ አቡነ ይስሐቅ፣ አቡነ ጴጥሮስ እና አቡነ ሚካኤል ናቸው፡፡
- ካቶሊካውያን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ እጃቸውን መዘርጋታቸውን በጽናት ቀጠሉ፡፡
- የዚህ ማሳያ የሆነው እና በካቶሊኩ ፖፕ መሣሪያዎቹ ተባርከውለት ኢትዮጵያን ለመውረር በመጣው በጣሊያን ፋሺስት የሞሶሎኒ ጦር ከሁለት ሺሕ በላይ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፤ ካህናት መነኮሳት ተገድለዋል፡፡

***ከወረራው በኋላ***

- ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለቀው ከወጡ በኋላ በቤተ ክርስቲያን የተወሰነ የማገገም ሁኔታ ታይቷል፡፡
- በ፲፱፻፶፩(1951) ዓ.ም ቤተ ክርስቲያን የሊቀ ጵጵስናን መዓርግ ከልጆቿ አገኘች፡፡ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ተብለው ካይሮ ላይ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ ተሾሙ፡፡

www.zeorthodox.org

- የሐዋርያዊ አገልግሎት አድማስ እየሰፋ መጠነኛ እንቅስቃሴዎች ነበሩ፡፡ በካሪቢያን ደሴቶችና በአካባቢያቸው ባሉ ሀገሮች የሚገኙ ብዙ ወገኖች ወደ ቤተ ክርስቲያን መንጋ ተቀላቀሉ፡፡
- በግእዝ ብቻ የነበሩ መጻሕፍት ወደ አማርኛ እየተተረጎሙ መታተም ጀመሩ፡፡
- እስከ አሁንም በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ተተክለዋል፤ በየጊዜው አምስት ፓትርያርኮች እና ብዙ ጳጳሳት ተሹመዋል፡፡

*አዲሱ ሥሪት*

ከ፲፱፻፷፮(1966) ዓ.ም የመንግሥትን ለውጥ ተከትሎ ቤተ ክርስቲያን የነበሩዋትን የመተዳደሪያ የቦታ ይዞታዎች እና ቤት ንብረቶች አጣች። ይህንኑ ተከትሎ የሰበካ ጉባኤ፣ ሰንበት ትምህርት ቤቶች እና የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበራት መቋቋማቸው ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን እንደ ዘመኑ ቋንቋ እንድትደርስ እና በምእመናን አስተዋጽኦ እንድትተዳደር አስችሎአታል።

## ማጠቃለያ

⌘ ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝቦች፡- እውነተኛይቱን ሃይማኖት፣ መልካም ሰብእናን፣ ኪነ ጥበብን፣ ፊደልን ከነጽሑፍ ሥርዓቱ፣ ሥነ ሕንፃን ያስተማረች ታሪክን ያስተላለፈች ናት።

## ተግባር

⌘ ተማሪዎች፤ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተጻፉ መጻሕፍትን አሰባስቡ እና አንብቡ። የመወያያ ርእስ በመምረጥ በክፍል ውስጥ ተወያዩ።

www.zeorthodox.org

# መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን

## ዐሥራ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች፤ ስለ መኃልየ መኃልየ ዘሰሎመን መጽሐፍ በማጥናት መንፈሳዊ ይዘቱን ለይተው ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ‹‹ሳበን ከአንተም በኋላ እንሮጣለን፡፡›› መኃ.መኃ. ፩፥፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መጽሐፈ ሲራክ ወሰሎሞን ትርጓሜ

## መግቢያ

የሰሎሞን መዝሙር በመባል የሚጠራውን ‹‹መኃልየ መኃልየ ዘሰሎሞን›› ብዙ ሰዎች በተዛባ መንገድ ሲረዱት ማየት የተለመደ ነው፡፡

ይህም ብዙዎቻችንን በተለይም ወጣቶችን ግራ ሲያጋባ የኖረ ነው፡፡ ከፍቅር ቃላቱ ጀርባ ያለውን መንፈሳዊ ትርጉም በሚገባ መረዳት አስቀድሞ የወደደንን እግዚአብሔርን ለመውደድ ያስችላል፡፡ ፩ኛ ዮሐ.፬፥፱

## የትምህርቱ ዝርዝር

⌘ ሰሎሞን 1005 መኀልያት (መዝሙራት) ጽፎአል፡፡ (፩ኛ ነገ.፬፥፴፪) ይህ መንፈሳዊ ትርጉም ያለው ቅኔያዊ መኃልየ ግን ከሌሎቹ ተለይቶ መኀልየ መኃልይ- ከመዝሙራት የሚበልጥ ተብሎአል፡፡

⌘ ይህ መዝሙር በሰሎሞን የተደረሰ ጥንታዊ አቀራረብ ያለውና በምልልስ መልክ የተዘጋጀ ነው፡፡ በታሪክ ስንመለከተው መዝሙሩ በሰሎሞን እና በወዳጁ መካከል የተደረገ የፍቅር ምልልስ ይመስላል፡፡

⌘ በመንፈሳዊው ትርጉም ግን እስራኤል በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሙሽራ ሲሳሉ እናያለን፡፡ (ኢሳ ፶፬፥፭፤ኤር.፪፥፪፣ሕዝቅ. ፲፮፥፰-፲፬፣ ሆሴ.፪፥፲፮-፳)፡፡ በሐዲስ ኪዳንም ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ ተብላለች፡፡ (፪ኛ ቆሮ.፲፩፥፪፤ኤፌ. ፭፥፳፫-፳፭፣ራዕ.፲፱፥፯፥፱፣፳፩፥፱) መጽሐፈ መኃልየ ያለፈውን የሚናገር ስለ ወደፊቱም የሚተነብይ መጽሐፍ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

⌘ የሰው ልጆች ሰውኛ ኑሮ በወንድ እና በሴት ፍቅር የመጨረሻውን ግብ እንደሚያገኝ፤ በመንፈሳዊው ሕይወትም ሰው ብቃት ላይ የሚደርሰው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በሙሉ እና ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ያለውን ፍጹም ፍቅር ሲረዳ እና ሲያገኝ ነው፡፡

⌘ መጽሐፉ በሦስት ከያንያን የሚነገር ተውኔት ይመስላል፡፡ ሙሽራዋ(ሱላማጢስ፤ ቤተክርስቲያን እና የሰው ልጆች ነፍስ)፣ ንጉሡ ሰሎሞን፤ የእግዚአብሔር እና ቆነጃጅት የኢየሩሳሌም ልጆች፤ ነቢያት ሐዋርያት እና መላእክት

⌘ በመጽሐፉ ቅጽበታዊ የተናጋሪዎች ልውውጥ ያለው ሲሆን የተናጋሪው ማንነት በቀጥታ አልተገለጠም፡፡ ሙሽራዋ ንጉሡን ‹‹ውዴ›› ስትለው፤ እርሱም ‹‹ወዳጄ፣ ርግቤ፣ ሙሽራዬ›› ይላታል፡፡

⌘ ይህ ጥበባዊ መጽሐፍ ስምንት ምዕራፎች ሲኖሩት፤ በሚማርኩ ቃላት የጥንዶችን ፍቅር እየመሰለ መንፈሳዊውን ፍቅር ይገልጣል፡፡ የፍቅር መጀመሪያ (፩፥፩-፫) ፍቅሩ ሰፍቶም (ከ፫፥፪-፰፣፲፬) እናነባለን፡፡

## 1. የፍቅሩ መጀመሪያ (፩፥፩-፫)

- ንጉሡ በሱላማጢስ ሀገር ታላቅ የወይን እርሻ ነበረው፡፡ (፯፥፲፫፣፰፥፲፩) ሱላማጢስ በእርሻው ከወንድሞችዋ ጋር ትሠራ ነበር (፩፥፯፡፰፥፲፩-፲፪) ንጉሡ የወይኑን እርሻ ሲጎበኝ ልብዋ ተሸነፈ እርሱም ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዳት፡፡ መልክዋ ጥቁር ቢሆንም የተዋበች ናት፡፡ (፩፥፯-፰)
- ሁሉን አዘጋጅቶ የፈጠረን እና በኃጢአት ስንጠቁር መጥቶ የፈለገን፤ ወደ ገነት መንግሥተ ሰማያት (ኢየሩሳሌም ሰማያዊት) ያስገባንን የጌታችንን ዘለዓለማዊ ፍቅር የሚነግረን ክፍል ነው፡፡
- በዚያም በወይን ጠጅ ቤት ሙሽራዋ ቆይታ አድርጋለች ፩፥፪-፰፡፡ የሁለቱንም ፍቅር በአዳራሹ እናያለን፡፡ ፩፥፱፡፪፥፯
- አዳም እና ልጆቹ ወደ ገነት ገብተው ተድላ ገነትን ከአምላካቸው ጋር ያሳልፋሉ፡፡
- ሙሽራው የሚጎበኝበት የጸደይ ወራት ደረሰ፡፡ ፪፥፰-፲፯
- ሙሽራዪቱ ከውዷ በመለየትዋ እየፈለገችው ነው፡፡ ፫፥፩-፭
- ‹‹መንፈሱና ሙሽራይቱም ና ይላሉ›› ራእ.፳፪፥፲፯ እንደ ተባለ ቤተ ክርስቲያን ተስፋዋን ኢየሱስ ክርስቶስን በተስፋ ትጠብቀዋለች፡፡
- ሰርጉ ከሙሽራይቱ ቤት ወደ ሙሽራው ቤት ኢየሩሳሌም ተቀየረ፡፡ ፫፥፯-፲፩
- በምዕራፍ ፬ ንጉሡ ሙሽራዋን ከራስ ጸጉርዋ እስከ እግር ጥፍርዋ ያወድሳታል፡፡

www.zeorthodox.org

## 2. የፍቅሩ መስፋት ከ፭፥፪-፰፥፲፬

- ከሰርጉ በኋላ ሙሽራይቱ የሚረብሽ ሕልም አየች (፭፥፪) በቤትዋ ተኝታ ንጉሡ አንኳዋኩዋ እርስዋ ግን ለመክፈት ዘገየች፤
- ቆይታም ከፈተችለች፤ በዚህ ጊዜ ግን ንጉሡ ፈቀቅ ብሎ ነበር፡፡ ልትፈልገው ወጣች አላገኘችውም፤ ብቻዋን ነበረች እና ከተማይቱን የሚዞሩ ጠባቂዎች መጥተው አቆሰሉዋት፡፡
- ይህንኑ ናፍቆት እና ጉዳትዋን ለኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ካገኙት እንዲነግሩት ነገረቻቸው፡፡ ፭፥፰-፮፥፫
- በሌሊት ተመልሶ ፍቅሩን እያረጋገጠ እና እያወደሳት መጣ፡፡(፮፥፬-፯፥፲፫-፰፥፬) ጉዞው ተፈጸመ (፰፥፭-፯) ፍቅራቸውም ጥልቅ ሆነ፡፡

## ተግባር

⌘ የመጽሐፉን መንፈሳዊ ትርጉም በሚገባ ለማወቅ የትርጓሜ መጻሕፍትን አንብቡ፡፡

## ማጠቃለያ

⌘ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች እና ለቤተ ክርስቲያን ያለው ፍቅር ከማንኛውም ፍቅር መግለጫ በላይ ነው፡፡

⌘ ይህም ሆኖ ማንኛውም ሰው ይህን ፍቅር ሊገልጠው አይችልም፤ በተረዳነው የፍቅር መንገድ እንናገረዋለን እንጂ፡፡

www.zeorthodox.org

# የምሥራች

## ዐሥራ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች፤ እግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክትን እየላከ ያሰማንን የምሥራች አውቀው እምነታቸውን ያጠነክራሉ ለሌሎችም ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"የምሥራቹን የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው፡፡"* ሮሜ.፲፥፲፭

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ሉቃ.፩፥፳ - ፍጻሜ ምዕራፍ፤ ሉቃ.፪፥፲-፲፩፣ማቴ.፳፰፥፩-፯

### መግቢያ፡-

- መላእክት "***ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም***" *ዕብ.፩፥፲፬* የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸው፡፡ ስለኛ ይጸልያሉ፣ በብዙ መንገድም ይረዱናል፡፡
- *መላእክት ዛሬ ለኛ /ለሰው ልጆች በሙሉ/ መልካም ዜና ያበሠሩባቸውን ታሪኮች እንማራለን፡-*

### ትምህርቱ

**መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል** የሰው ልጆች ድኅነት ሲታወጅ የተላከ መልአክ ነው፡፡

1. በዚህ *መሠረት* መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል *መጀመሪያ* የተላከው ወደ ካህኑ ዘካርያስ ነበር፡፡
   - አባታችን ዘካርያስ እና ሚስቱ ኤልሳቤጥ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ቅዱሳን ነበሩ፡፡ ልጅ ሳይወልዱ ለረጅም ዘመናት ኖሩ፡፡
   - ከዕለታት አንድ ቀን *መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል* ካህኑ ዘካርያስ በቤተ መቅደስ እያጠነ ሳለ ተገለጠለት፡፡ *መንገድ* የሚጠርግ ልጅ እንደሚወልድ እና ስሙንም ዮሐንስ እንደሚለው አበሠረው፡፡
   - በመልአኩ ብሥራት *መሠረት* ኤልሳቤጥ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ዮሐንስ አሉት፡፡
2. *መልአኩ* ለዘካርያስ በተገለጠለት በስድስተኛው ወር ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ተገልጦ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትፀንስና እንደምትወልደው አበሠራት፡፡
   - "***ደስ ይበልሽ ! ጸጋ የምላብሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፡፡ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ" አላት፡፡*** እርስዋም ‹‹***ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው***›› ብላ አሰበች፡፡
   - መልአኩም፤ ***ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ፡፡ እነሆ***

www.zoorthodox.org

*ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ፡፡ እርሱ ታላቅ ነው፤ የልዑል ልጅም ይባላል፤ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፡፡ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል፡፡ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም፡፡* ማርያምም *ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል አለችው፡፡*

- መልአኩም፤ *መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፡፡ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡፡ እነሆ... ኤልሳቤጥ በእርጅናዋ ወራት ወንድ ልጅ ፀንሳለች ፡፡ይህ ስድስተኛ ወር ነው፡፡ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና፡፡ እርስዋም እነሆኝ የጌታ ባርያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች፡፡" ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከእርስዋ ተፀነሰ፡፡*

3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ሌሊት መላእክት ለእረኞች ልደተ ክርስቶስን አብሥረዋቸዋል፡፡

- በዚህ ጊዜ መልአኩ ተገልጦ እንዲህ ነበር ያላቸው፤ *"ዛሬ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁ፡፡ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት የሚሆን ጌታ ክርስቶስ ተወልዶላችኋልና አትፍሩ፡፡"* ጌታ ሲወለድም *"በሰማይ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን በምድር በጎ ፈቃድ ለሰው ልጆች ..."* ሲሉ ዘምረዋል፡፡

4. በትንሣኤም ታሪክ መላእክት ምን እንደሠሩ ታስታውሳላችሁ? አዎን! መላእክት የክርስቶስን ትንሣኤ ለሴቶች አብሥረዋል፡፡

- ጌታ በተቀበረበት ቦታ ኀልጎታ እያዘኑ ለተገኙት እናቶች መላእክ፤ት *"አትፍሩ እናንተስ ክርስቶስን እንድትፈልጉ አውቃለሁና ከዚህ የለም ተነሥቷል፡፡"* ነበር ያሉዋቸው፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች እንደመሆናቸው መልካሙን የምሥራች ከእግዚአብሔር ለሰው አሰምተዋል፤ ዛሬም መልካሙን ያሰሙናል፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- የእግዚአብሔርን ፍቃድ እና ማጽናናት እንደቃልህ ይደረግልኝ ብለን ማመን ይገባናል፡፡

| መዝሙር | ትርጉም |
| --- | --- |
| ወእዘ ትፌትል(2) ወረቀ ወሜላተ | እያስማማች ስትፈትል(2) ሀር እና ወርቁን |
| አስተርኣያ ገብርኤል አስተርአያ ለማርያም | ታያት ገብርኤል ማርያምን ታያት |

# የቅዱስ ጳውሎስ መልክታት ዳሰሳ (አንድ)

## ዐሥራ ስድስተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ

- ተማሪዎች፤ የሐዲስ ኪዳን አካላት የሆኑትን ዐሥራ አራቱን የቅዱስ ጳውሎስን መልእክታት እና የተጻፉበትን ምክንያት ለይተው በማወቅ ያብራራሉ፡፡

### የሚጠና ጥቅስ

- *“ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም ከሁላቸው ይልቅ ግን ደከምሁ÷ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም፡፡”* ፩ኛ ቆሮ.፲፭÷፲

### ተጨማሪ ምንባባት

- በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኛቸው ዐሥራ አራቱ መልእክታተ ጳውሎስ ፤ ትርጓሜ ጳውሎስ፡፡

### መግቢያ

ቅዱስ ጳውሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ መጻሕፍትን በመጻፍ የመጀመሪያው ነው፡፡ በእያንዳንዱ መልእክቱም በዚያን ዘመን በቤተ ክርስቲያን የነበረውን ችግር ፈትቶበታል፡፡

በመልእክታቱ ለክርስቶስ ወንጌል ጥብቅና በመቆም የተሾመበትን አገልግሎት በተግባር ሲገልጥ እናገኘዋለን፡፡ እያንዳንዱ መልእክታት የተለያየ ይዘት አላቸው፡፡

በጠቅላላው ይዘታቸው መሠረት ስንከፋፍላቸውም፡-

*ሀ. ስለ ምጽዐት የተጻፉ መልእክታት*

፩ኛ ተሰሎንቄ፡- በክርስቶስ ምጽኣት ብርሃን ውስጥ ያለ ሕይወት፤

www.zeorthodox.org

፪ኛ ተሰሎንቄ፡- የክርስቶስ መምጣት ምልክቶች፤

*ለ. ዋና መልእክታት*

፫ኛ. ሮሜ፡- እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለምን ያዳነበት ጽድቅ፡፡

፬ኛ.፩ኛ ቆሮንቶስ ፡- የክርስቶስ እና የቤተ ክርስቲያን አንድነት እና ባሕርይ፡፡

፩ኛ.፪ኛ . ቆሮንቶስ፡- የክርስቶስ ማስታረቅ፡፡

፯ኛ.ገላትያ፡- በክርስቶስ የሆነ ነጻነት (ገላ.፩÷፩)

**ሐ. የእስር ቤት መልእክታት**

፯ኛ.ኤፌሶን፡- ዓለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ የሆኑ የእግዚአብሔር ሕዝቦች፡፡

፰ኛ. ፊልጵስዩስ፡- በክርስቶስ የሚገኝ ደስታ፤

፱ኛ.ቆላስያስ፡- የክርስቶስ ሁሉን ቻይነት፡፡

፲ኛ. ፊልሞና፡- በእግዚአብሔር ሁሉም አንድ ቤተሰብ ነው፡፡

**መ. መልእክታተ ኖሎት**

፲፩.፩ኛ ጢሞቴዎስ፡- ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ የተሰጣት ማረጋጋጫ፡፡

፲፪. ፪ኛ ጢሞቴዎስ፡- በክርስቶስ መታመን፡፡

፲፫.ቲቶ፡- ክርስቶስን ለማገልገል መብቃት፡፡

፲፬. ዕብራውያን፡- ክርስትና በይሁዲነት ላይ መሠልጠንዋ፡፡

# የትምህርቱ ዋና ይዘት

## 1. ሮሜ

- የሮሜ መልእክት በቆሮንቶስ ከ፶፩-፶፯(55-57) ዓ.ም ባለው ጊዜ ተጽፎአል፡፡ በሮሜ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ችግር ለመቅረፍ የተጻፈች መልእክት አይደለችም፤ ሆኖም እንደ ትምህርት እና ማግባቢያ የተጻፈ መልእክት ነው፡፡

### ምክንያተ ጽሒፍ

**ቤተ ክርስቲያንን ከይሁዲነት መከላከል** ፡- አይሁድ ክርስቶስ በሙሴ ሕግ ላይ ያስተማረ እንጂ የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ አይደለም ይሉ ነበር፡፡ ከዚሁም ጋር ከአሕዛብ ያመኑትን ክርስትያን ለመሆን እንደ ሙሴ ሕግ ፈጽሙ ይሔንን ካላደረጋችሁም አትድኑም፤ ትንቢት የተነገረው ተስፋ የተሰጠው ለእኛ ነውና በእኛ ወግ ሂዱ ይሉ ነበር፡፡ ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስን ያመጣው የእነርሱ ጽድቅ እንዳይደለ አስተምሮዋል፡፡ ፫÷፳፩-፴፩

www.zeorthodox.org

**የአሕዛብንም ትእቢት ሊያርም ተጽፎአል፡-** ከአሕዛብ ወገን የሆኑትም እግዚአብሔር እስራኤልን ትቶ እነርሱን እንደፈለገ በማሰብ ይመኩ ስለነበር፤ **"የእነርሱ መጣል ለዓለም መታረቅ ከሆነ ከሙታን ከሚመጣ ሕይወት በቀር መመለሳቸው ምን ይሆን? በኩራቱም ቅዱስ ከሆነ ቡሆው ደግሞ**

ነው፣ሥሩም ቅዱስ ከሆነ ቅርንጫፎቹ ደግሞ ቅዱሳን ናቸው፡፡ ነገር ግን ከቅርንጫፎቹ አንዳንዱ ቢሰበር አንተም የበረሐ ወይራ የሆንህ በመካከላቸው ገብተህ ከእነርሱ ጋር የወይራ ዘይት ከሚወጣው ሥር ተካፋይ ከሆንክ በቅርንጫፎች ላይ አትመካ…" ፲፩፥፲፫-፳፪ ብሎ ሁለቱንም ሊያስተምር ጽፎታል፡፡

- በመጨረሻው ፍቃድ እና ኪዳን ላይ የተጻፈ ነው፡፡
- ወደ ዛሬዋ እስፔን ላቀደው ጉዞ የሚያስፈልገውን አገልግሎት እንዲያግዙት፤
- ተገኝቶ በማስተማሩ ምትክ እንድትሆንለት ፈልጎ ይህችን መልእክት ጽፎዋታል፡፡ቅዱስ ጳውሎስ ከአሕዛብ የሰበሰበውን ስጦታ ለማድረስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በሰማዕትነት ሊያልፍ እንደሚችል ስላሰበ ይህችን መልእክት ጽፎአታልም፤ ይላሉ፡፡ የሐዋ.ሥ.፳፩፥፰-፲፫፡፡

**የመልእክቲቱ ዋና መልእክት**

***" በቸርነቱ ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው፡፡"*** ሮሜ.፲፩፥፳፪

- ይህም በምዕ.፩፥፲፮ እና ፲፯ ተገልጦአል፡፡ የእግዚአብሔር ማዳን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ በሙሉ ነው፡፡
- ሁላችንም ወደ እግዚአብሔር የቀረብነው በእኛ ጽድቅ አይደለም፡፡ በሕይወት የምንኖረው በእግዚአብሔር ቸርነት እና ጽድቅ ነው፡፡
- በሥራ ሕግ አይጸድቅም በእምነት ሕግ እንጂ፤ በተጨማሪም ቅዱስ ጳውሎስ ለኃጢአት ከሞትን እንዴት በኃጢአት እንኖራለን ? ሲል ይጠይቃል፡፡

## 2. ፩ኛ ቆሮንቶስ

ቀዳሚት የቆሮንቶስ መልእክት በኤፌሶን ከ፶፭-፶፮(55-56)ዓ.ም ተጽፋለች፡፡ መልእክቲቱ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩትን በርካታ ችግሮች አዳርሳለች፡፡ እነርሱም፡- መለያየት እና መከፋፈል፤ የጥበብ አካሄድ፤ ሥነ ምግባራዊ ሕግጋት (በቤተ ክርስቲያን የታየ የዘመዳሞች ግቢ)፤ ለጣዖት የተሠዋን ስለመብላት፤ ጋብቻና የብቸኝነት (የምንኩስና)ኑሮ፤ በሥርዓተ አምልኮት የሴቶች ተሳትፎ፤ በጌታ ራት (ቅዱስ ቁርባን) በአግባቡ መሳተፍ፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እና ትንሣኤ ሙታንን አስመልክቶ ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

## 3. ፪ኛ ቆሮንቶስ

ሁለተኛይቱ የቆሮንቶስ መልእክት በቲቶ የተላከች ናት፡፡

ሀ. ፪ኛ ቆሮንቶስን ለመላክ ምክንያት የሆኑትም፡-

⌘ አንዳንዶች ከውጭ መጥተው የአይሁድን ትምህርት ስላስተማሩ፤

⌘ አንዳንድ የቆሮንቶስ ምእመናን ራሳቸውን ልዩ ሐዋርያት አድርገው ይቆጥሩ ነበር፡፡ ከዚያም አልፈው አርአያቸው ሙሴ ብቻ እንደሆነ ስለቆጠሩ፡፡

⌘ እነዚሁ ራሳቸውን የበላይ ሐዋርያ አድርገው የቆጠሩ የቆሮንቶስ ምእመናንን ልብ ለውጠው፤ ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስ የተገለጠለት፣ መሳጭ፣ ስብከት የሚሰብክ እና ቃላት ያሉት አይደለም ስላሉ፤

⌘ ቅዱ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ሥልጣን የለውም ብለው ስለከሰሱት፡፡

⌘ ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ እድገት እና ጥልቀት የለውም ብለው ስላስተማሩ፡፡

**ለ. በሁለተኛይቱ ቆሮንቶስ ቅዱስ ጳውሎስ ሦስት የነገረ መለኮት ትምህርቶች ላይ መልእክት አስተላልፎአል፡፡**

ও የመጀመሪያው ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በራሳቸው ፍቃድ መዘወር አይችሉም፤

ও ሁለተኛው የበላይ ነን የሚሉት ከሥጋ ብቻ ነው፡፡ (፭÷፲፯) ክርስቶስን አሁን ካለው የክፋት ዓለም ውጪ አድርገው ማየታቸው፡፡

ও ሦስተኛው ሐዋርያው የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች አዲስ አማኞች መሆናቸውን ስለተረዳ፤ ሕይወታቸውን በክርስቶስ እና ስለክርስቶስ እንጂ በራሳቸው እንዳይኖሩ ሊመክራቸው፡፡

4. ገላትያ

**የገላትያ ቤተ** ክርስቲያን፡-

ገላትያ - ዛሬ የቱርክ ዋና ከተማ አንካራ የምትገኝበት አካባቢ ነው፡፡ የገላትያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዞው የመሠረታት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡

**የመልእክቲቱ መጻፍ**

⌘ በቅዱስ ጳውሎስ ፤ በ፵፭(45) ዓ.ም ገደማ ፤ በሶርያ አንጾኪያ ተጽፋለች ፤

**ምክንያተ ጽሒፍ**

ቢጸ ሐሳውያን ቅዱስ ጳውሎስ ጌታችንን አላየውም ፤ ከሐዋርያት እኩል አይቆጠርም፡፡ በማለት ምእመናን ትምህርቱን እንዳይቀበሉ እና ወደ አይሁድ ግብር እንዲመለሱ ያደርጉ ስለነበር መልስ ለመስጠት ጽፏል፡፡

www.zeorthodox.org

**ይዘቱ**

⌘ በተግሣጽና በወቀሳ የተሰጠ የሥነ ምግባርና የሃይማኖት ትምህርት ነው፡፡

**አከፋፈሉ**

⌘ የገላትያ መልእክት ስድስት ምዕራፎች ሲኖሩት በአምስት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡

1ኛ ምዕራፍ ፩ መግቢያ ሰላምታ እና ለእግዚአብሔር የተሰጠ ምሥጋና

2ኛ ከምዕራፍ ፩-፪ ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያነቱን እያስረዳ ሐሰተኞቹን እየተቃወመ የጻፈው ትምህርት

3ኛ ከምዕራፍ ፫-፬ ስለ ሕገ ኦሪት እና ወንጌል እያነጻጸረ ስለ ክርስቶስ ያስተማረው ትምህርት፤

4ኛ ከምዕራፍ ፭-፮ የሥነ ምግባር ትምህርቶች፡፡

5ኛ ምዕራፍ ፮ ማጠቃለያ፡- የሐሰተኞች ዓላማ የቅዱስ ጳውሎስ ትምህርትና ቡራኬ

## 5. ኤፌሶን

- ኤፌሶን በታናሽ እስያ በኤጅያን ባሕር አጠገብ የምትገኝ የእስያ አውራጃ ዋና ከተማ ናት፡፡ የአርጤምስ ቤተ ጣዖትና የአይሁድ ምኩራብ ነበረበት፡፡ ዛሬ በቱርክ አገር አያሰሉን የምትባል ከተማ ናት ያን ጊዜ 350,000 ሰው የሚኖርባት ታላቅ የንግድ ከተማ ነበረች፡፡

### የኤፌሶን ቤተክርስቲያን

የዚህች ቤተ ክርስቲያን መሥራች ቅዱስ ጳውሎስ ሲሆን ፤ ሐዋርያው ሦስት ዓመት በኤፌሶን አስተ ምሯል፡፡ የሐዋ. ሥ. ፲፰፥፲፱ እና ፳፩ ይህም በሦስተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው ወቅት መሆኑ ነው ፡፡

**መልእክቲቱ የተጻፈችው**

በቅዱስ ጳውሎስ ፤ በ፷፯(67) ዓ.ም ገደማ ፤ በሮም እስር ቤት ሳለ ነው ፡፡

### የተጻፈበት ምክንያት

- ከጨለማ ሥራ እንዲለዩ ፣ በሃይማኖትና በክርስትና ሕይወት እንዲጠነክሩ አሕዛብ ቢሆኑም ከአይሁድ ጋር አንድ ሆነው በእግዚአብሔር ጸጋ መዳናቸውን ለመግለጽ ነው፡፡

### ይዘቱ

- ከወቀሳና ከተግሣጽ የተለየ ትምህርተ ሃይማኖትና የሥነ ምግባር ትምህርት ነው፡፡

### አከፋፈሉ

- የኤፌሶን መልእክት ስድስት ምዕራፎች ሲኖሩት በአራት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡

ምዕራፍ ፩ መግቢያ የቅዱስ ጳውሎስ ሰላምታ እና ለእግዚአብሔር ያቀረበው ምስጋና፤

ከምዕራፍ ፪-፫ እግዚአብሔር እንዴት እንዳዳናቸው፤

www.zeorthodox.org

ከምዕራፍ ፬-፮ ስለ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፤

ምዕራፍ ፮ ማጠቃለያ፡፡

## 6. ፊልጵስዩስ

### የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን

- ፊልጵስዩስ የመቄዶንያ ከተማ ናት፡፡ በ (358) ዓ.ዓ (ከክርስቶስ ልደት በፊት) የታላቁ እስክንድር

አባት ፊልጶስ ነግሦባት ፊልጵስዩስ ብሏታል።

- የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን መሥራች ቅዱስ ጳውሎስ ሲሆን፤ በዚህች ከተማ ልድያ ፣ የወኅኒ ቤቱ ጠባቂ እና በጥንቆላ ለጌቶችዋ ገቢ የምታስገኘው ሴት አምነዋል። የሐዋ.ሥራ. ፲፮፥፲፪-፴፬

## መልእክቲቱ

በቅዱስ ጳውሎስ፣ በ ፷፫(63) ዓ.ም በመጀመሪያ እስራቱ ጊዜ በሮም ተጽፋለች ፡፡

### ምክንያተ ጽሒፍ

ይህች መልእክት የተጻፈችበት ምክንያት ሦስት ነው ፡-

1ኛ በአፍሮዲጡ እጅ ለላኩለት ስጦታ ለማመስገን፤ ፬፥፲፰

2ኛ በመከራው ውስጥ ሳሉ ጽናታቸውን አይቶ የተሰማውን ደስታ ለመግለጽ ነው፡፡

3ኛ መለያየትን አጥፍተው እንዲስማሙ እና ከሐሰተኞች እንዲጠበቁ ለመምከር ነው፡፡ ፪፥፪

### ይዘቱ

- ደስታን እና ፍቅርን የተሞላ የሥነ ምግባር እና የሃይማኖት ትምህርት ነው ፡፡

**አከፋፈሉ፡- የፊልጵስዩስ መልእክት** አራት **ምዕራፎች ሲኖሩት** ፤ በስድስት **ዓበይት ክፍሎች** ይከፈላል፡፡

ምዕራፍ ፩ መግቢያ፤ ላኪው ለተቀባዮቹ ያስተላለፈው የፍቅር መልካም ምኞት መግለጫ እና የሰላምታ መልእክት፤

ከምዕራፍ ፩፥፲፪-፴ የነበረው ደስታ እና መታመን፤

ከምዕራፍ ፪፥፩-፲፰ በመልካም ኑሮ እንዲኖሩ የተሰጠ ምክር፤

ከምዕራፍ ፪፥፲፱-፴፬ ደቀ መዛሙርቱን (ጢሞቴዎስና አፍሮዲጡን) እንደሚልክላቸው፡፡

ምዕራፍ ፫ ከሓሰተኛ ምክር እንዲጠበቁ

## 7.ቈላስያስ

### ቈላስይስ፡-

ከኤፌሶን 100 ማይል ርቃ በስተ ምሥራቅ በፍርግያ የምትገኝ ከተማ ስትሆን ፣ በጸጉር ምርቷ የምትታወቅ ከተማ ናት ፤ የቈላስይስ ሰዎች ወንጌልን ከኤጳፍራ ተምረዋል፡፡

www.zeorthodox.org

### መልእክቲቱ

ከ፷፪-፷፬(62-64) ዓ.ም፣ በሮም የቅዱስ ጳውሎስ የመጀመሪያ እስራቱ ወቅት ነው፡፡

### ምክንያተ ጽሒፍ

1ኛ ኤጳፍራ ለቅዱስ ጳውሎስ ስለ ፍቅራቸው ስለነገረው ሊያመሠግንና ሊያበረታቸው ፲፫፥፯

2ኛ በመካከላቸው በፍልስፍና የተመሠረተ ትምህርት ነበርና ከዚያ እንዲጠነቀቁ ለማሳሰብ ነው፡፡

**ይዘቱ**

**ለመናፍቃን የተሰጠ መልስ ሲሆን ትምህርተ ሃይማኖትንና የሥነ ምግባር ትምህርትን ይዟል፡፡**

**አከፋፈሉ**

**የቈላስይስ መልእክት አራት ምዕራፎች ሲኖሩት በአምስት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡**

**1ኛ ምዕራፍ ፩ መግቢያ፤**

**2ኛ ከምዕራፍ ፩፥፲-፪፥፯ ስለ ክርስቶስ ሰው መሆን፤**

**3ኛ ከምዕራፍ ፪፥፰-፫ ሐሰተኞች እንዳይማርኳቸው የጻፈው ማሳሰቢያ፤**

**4ኛ ከምዕራፍ ፫-፬ ስለ ሥነ ምግባር፤**

**5ኛ ምዕራፍ ፬ ማጠቃለያ፡፡**

www.zeorthodox.org

# የቅዱስ ጳውሎስ መልክታት ዳሰሳ (ሁለት)

# ዐሥራ ሰባተኛ ሳምንት

## የትምህርቱ ዓላማ

❖ ወጣቶች ከትምህርቱ በኂላ፤ ስለ ቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ግንዛቤያቸውን አዳብረው ያብራራሉ፡፡

## የሚጠና ጥቅስ

❖ *" ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም ከሁላቸው ይልቅ ግን ደከምሁ፥ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም፡፡"* ፩ኛ ቆሮ.፲፭፥፲

### ተጨማሪ ምንባባት

❖ በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኛቸው ዐሥራ አራቱ መልእክታተ ጳውሎስ፤ ትርጓሜ ጳውሎስ፡፡

## መግቢያ

❖ ባለፈው ሳምንት የጀመርነውን ትምህርት ሁለተኛ ክፍል እንቀጥላለን፡፡

## ትምህርቱ

### 8. ፩ኛ ተሰሎንቄ

ተሰሎንቄ የመቄዶንያ ዋና የንግድ ከተማ ነበረች፡፡ ቀድሞ ቴርማ (ፍል ውኃ ማለት ነው፡፡) ትባል ነበር፡፡ ዛሬ የግሪክ ግዛት ናት፡፡

**የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን**

www.zeorthodox.org

❖ ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው ከሲላስ እና ጢሞቴዎስ ጋር ለሦስት ሳምንታት አስተምሮአል፡፡

**መልእክቲቱ**

በቅዱስ ጳውሎስ በ፶(50) ወይም ፶፩(51) ዓ.ም በአቴና ተጽፋለች፡፡

**ምክንያተ ጽሕፈት**

1ኛ. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ወደ ተሰሎንቄ ልኮት ነበርና እምነት እና ፍቅራቸውን ቢነግረው ደስታውን ለመግለጥ ነው፡፡

2ኛ. አንዳንድ ምእመናን ስለ ትንሣኤ ሙታን አልተረዱም ነበርና ስለሙታን ትንሣኤ እና ዳግም ምጽአት ለማስተማር ነው፡፡

**ይዘቱ እና አከፋፈሉ**

፩ኛ ተሰሎንቄ አምስት ምዕራፎች ሲኖሩት በአምስት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡

፩ኛ ምዕራፍ ፩፥፩ መግቢያ እና ሰላምታ

፪ኛ ከምዕራፍ ፩፥፪-፫፥፲፫ ሐዋርያው ስለ ተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ያለውን ፍቅር እና በእነርሱ ስላለው መልካምነት የገለጠበት፡፡

፫ኛ. ምዕራፍ ፬፥፩-፲፪ ስለ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

፬ኛ. ከምዕራፍ ፬፥፲፫-፭፥፲፩ ስለ ዳግም ምጽአት ያስተምራል

፭ኛ ልዩ ልዩ ምክሮች ፭፥፲፪-፳፰

## 9. ፪ኛ ተሰሎንቄ

**መልእክቲቱ**

❖ በ፶፩(51) ዓ.ም በሎዶቅያ ተጽፋለች፡፡

**ምክንያተ ጽሕፈት**

1ኛ. ***"የጌታ ቀን ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ…" ፩ኛ ተሰ.፭፥፪*** ብሎዋቸው ስለነበር በዘመናቸው ይመጣል ብለው ታውከው ነበርና የምጽአቱን ምልክት ለመግለጥ፡፡

2ኛ. እንዲሁም *ሥራ መሥራት* የተወ እና የሰነፉም ነበሩና ***"ሊሠራ የማይወድ አይብላ"*** ብሎ ለማስተማር ነው፡፡

**ይዘቱ እና አከፋፈሉ**

www.zeorthodox.org

❖ ፪ኛ ተሰሎንቄ ሦስት ምዕራፎች ሲኖሩት በአራት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡

ምዕራፍ.፩ ላኪው ቅዱስ ጳውሎስ ከጢሞቴዎስ እና ስልዋኖስ ጋር ያቀረበው ሰላምታ፡፡

ምዕራፍ. ፪፥፩-፲፪ ስለ ዳግም ምጽአት እና ምልክቶቹ የጻፈው ትምህርት፤

ምዕራፍ. ፪፥፲፫-፲፯ ያስተማራቸውን ወግ እና ሥርዓት እንዲጠብቁ የሰጠው ምክር፤

ምዕራፍ ፫ የማጠቃለያ ሰላምታ እና ቡራኬ

## የኖላዊነት ትምህርቶች

ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ውስጥ ትምህርተ ኖሎትን (የእረኝነት ትምህርት) የያዙ የኖላዊነት ትምህርቶች የሚባሉ ሦስት መልእክታት አሉ፡፡

## ጢሞቴዎስ

ጢሞቴዎስ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በልስጥራን ያገኘው በአባቱ ግሪካዊ በእናቱ አይሁዳዊ የነበረ ወጣት ነው፡፡ የሐዋ.ሥ.፲፮፥፩-፫ ሴት አያቱ እና እናቱ ክርስትያኖች ነበሩ፡፡ እርሱም ቅዱሳት መጻሕፍትን ተምሮአል፡፡ ፪ኛ ጢሞ.፩፥፭ እና ፫፥፲፬-፲፮ ቅዱስ ጳውሎስን ተከትሎ እግዚአብሔርን እና ቤተክርስትያኑን አገልግሎአል፡፡

## 10. ፩ኛ ጢሞቴዎስ

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመቄዶንያ ሆኖ በኤፌሶን ለነበረው ለጢሞቴዎስ የጻፈለት መልእክት ነው፡፡ ጢሞቴዎስ የሐሰት ትምህርት በሚያስተምሩ ሰዎች ምክንያት ብዙ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ስለወጡ ብዙ መከራ ተቀብሎአል፡፡

### ምክንያተ ጽሕፈት

፩ኛ. ከሐሰተኛ መምህራን (ከግኖስቲኮች) ትምህርት እንዲጠበቅ እና መንጋውን እንዲጠብቅ፡፡

እነዚህ ሐሰተኛ ትምህርቶችም ፡-

- በተረት እና በትውልዶች ታሪክ የተወሳሰበ ነበር፤ ፩፥፬ እና ፬፥፯፡፡
- ሕግን ሳይረዱ የሚያስተምሩ፤ ፩፥፯
- ጋብቻን እና ምግብን እንደ ክፉ ነገር የሚከለክሉ ናቸው፡፡፬፥፫
- ለዓለማዊ ነገር የሚመች በከንቱ እውቀት የሚከራከሩ ናቸው፡፡ ፮፥፳

www.zeorthodox.org

ይህም የአይሁድ እና ግኖስቲካውያን ትምህርት ስለሆነ ጢሞቲዎስ በአገልግሎቱ ታማኝ እንዲሆን እና ከሐሰት ትምህርት እንዲጠበቅ ቅዱስ ጳውሎስ ይመክረዋል፡፡

፪ኛ. የቤተክርስትያን አስተዳደርን እና ትምህርተ ኖሎትን እንዲያውቅ ፡፡

- *በቃል እና በኑሮ በእምነትም ለሚያምኑቱ ምሳሌ እንዲሆን እንጂ ማንም ታናሽነቱን እንዳይንቅበት* ይመክረዋል፡፡ ፬፥፲፩

- ከዚሁም ጋር ጸሎት እና ሥርዓቱ ፪፥፩ ማዕርጋተ ክህነት ፫፥፩-፲፫ የቤተ ክርስቲያንን ማንነት፣ በቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደሚኖር (፫፥፲፬-፲፯) ከምእመናን ጋር ስለሚኖረው ቀረቤታ እና አገልግሎቱ ፭፥፯ እንዲያውቅ ይጽፍለታል።

## አጠቃላይ ይዘቱ እና አከፋፈሉ

፩ኛ ጢሞቴዎስ ስድስት ምዕራፎች ሲኖሩት በአምስት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል።

ምዕራፍ ፩ ሰላምታ እና  መግቢያ፤

ምዕራፍ ፪ ሥርዓተ ጸሎት፤

ምዕራፍ ፫ እና ፭፥፩-፯፥፲፱ ሥርዓተ ኖሎት፤

ምዕራፍ ፬ ለሐሰት ትምህርቶች የተሰጠ መልስ፤ ጢሞቴዎስ ከሐሰተኛ መምህራን እንዲጠበቅ እና የቀናውን ትምህርት እንዲያስተምር።

ምዕ.፯፥፳-፳፩ ማጠቃለያ።

# 11. ፪ኛ ጢሞቴዎስ

## መልእክቲቱ

በ፷፯(66) ዓ.ም በሮም የመጨረሻ እስራቱ ተጽፋለች።

## ምክንያተ ጽሑፍ

ምእመናን አምነው በመካዳቸው፣ በመከራው ብዛት እና በቅዱስ ጳውሎስ እስራት ያዘነው ጢሞቴዎስ መከራውን ታግሶ አገልግሎቱን እንዲፈጽም፤ቅዱስ ጳውሎስ በሰማዕትነት ከማረፉ በፊት የመጨረሻውን ምክር እና ትእዛዝ ሊሰጠው እና ሊያየው ስለፈለገ፤ እንዲሁም ቅዱስ ማርቆስን እና ቅዱሳት መጻሕፍቱን ይዞለት እንዲመጣ ለማሳሰብ የጻፈው መልእክት ነው።

## ይዘቱ እና አከፋፈሉ

- ፪ኛ ጢሞቴዎስ አምስት ምዕራፎች ሲኖሩት በአራት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል።

፩ኛ ምዕራፍ ፩፥፩-፯ ሰላምታ እና መግቢያ

www.zeorthodox.org

፪ኛ ከምዕራፍ ፩፥፯-፬፥፭ የአገልግሎት ትምህርት

፫ኛ ከምዕራፍ ፬፥፯-፲፰ ቅዱስ ጳውሎስ ማረፉን ስላወቀ ከመሞቱ በፊት እንዲያየው የጻፈለት መልእክት

፬ኛ ምዕራፍ ፬፥፲፱-፳ ማጠቃለያ እና የስንብት ሰላምታ

## 12. ቲቶ

ቲቶ የቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር ነው።

**መልእክቲቱ** ፡- በ፷፫(63) ዓ.ም ገደማ በኒቆጵልዮን ተጻፈች ።

**ምክንያተ ጽሕፈት** ፡- ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እና ስለ ክህነት መመዘኛ ለማሳወቅ ፤ አስተዳደርን ለማስተማር እና ጢሞቴዎስ ወደ እርሱ እንዲመጣ ለመጥራት የተጻፈ ነው።

**ይዘቱ**፡- ባለ ሦስት ምዕራፍ የሆነችው የቲቶ መልእክት አራት ዓበይት ነገሮችን ይዛለች።

ምዕራፍ ፩ መግቢያ እና ሰላምታ፤

ከምዕራፍ ፩፥፭-፲፩ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እና አስተዳደርን የሚመለከት ትምህርት።

ከምዕራፍ ፪፥፲፩-፫፥፲፩ ስለ መዳን፤

ከምዕ.፫፥፲፪-፲፭ ሰላምታ እና ቡራኬ

## 13. ወደ ፊልሞና

**ፊልሞና**፡-ማለት ስውር ቦታ ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ፊልሞና ለተባለ ባለጸጋ ክርስቲያን በሮም እስራቱ ወቅት የጻፈው መልእክት ነው።

**ምክንያተ ጽሑፍ**፡-አናሲሞስ የተባለው ክርስቲያን ከፊልሞና ጋር በእዳ ስለተጣሉ ለማስታረቅ ። በእነ ፊልሞና ጸሎት ወደ እነሱ ለማሄድ ማሰቡንም ገልጦ ማደሪያ እንዲያዘጋጅለት ለማሳሰብ የተጻፈ ነው።

**ይዘቱ እና አከፋፈሉ**፡-ይህ መልእክት አንድ ምዕራፍ ሲኖረው በሦስት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል።

1ኛ. ከቁጥር ፩-፯ ሰላምታ

2ኛ. ከቁጥር ፰-፳፩ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ አናሲሞስ ያቀረበው ምስጋና እና ጥያቄ/

3ኛ. ከቁጥር ፳፪-፳፭ ማጠቃለያ።

www.zeorthodox.org

## 14. ወደ ዕብራውያን ሰዎች

ዕብራውያን የተባሉት በስደት የሚኖሩ ቤተ አይሁድ ሲሆኑ በአብርሃም ቅድመ አያት በኤቦር ዕብራውያን ተብለዋል።

ቅዱስ ጳውሎስ በ፷፬(64) ዓ.ም ገደማ በሮም የጻፈው መልእክት ነው።

**ምክንያተ ጽሑፍ** ጌታችን ከነቢያት፣ ከኦሪት ካህናት እና ከመላእክት እንደሚበልጥ፤ እንዲሁም አምላካቸው መሆኑን ለመግለጥ እና ከመሥዋዕተ ኦሪት መሥዋዕተ ሐዲስ እንደሚበልጥ ለማስተማር፤ በደረሰባቸው መከራ እንዲጽናኑ ለመምከር ነው።

**ይዘቱ እና አከፋፈሉ፡-**

የዕብራውያን መልእክት ሦስት ምዕራፎች ሲኖሩት በዚህ ጥናታችን በአምስት ክፍለን እናያለን።

ምዕራፍ ፩-፪ መግቢያ ሲሆን እግዚአብሔር በብዙ መንገድ እና ምሳሌ ስለ ልጁ በሥጋ መገለጥ ነግሮናል።

ምዕራፍ ፫-፬ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ የመላእክት እና የነቢያትም ጌታቸው ነው።

ምዕራፍ ፭-፲ ስለ ክርስቶስ ሊቀ ካህንነት እና አንድ ጊዜ ለዘለዓለም ስለ ፈጸመው ማስታረቅ፤

ምዕራፍ ፲፩-፲፪ በእምነት ለመጽናት በምሳሌ የቀረቡ አበው፤ ባለቤቱ ክርስቶስ እና ለተግሣጽ የሚሰጠው መከራ።

ምዕራፍ ፲፫ የሥነ ምግባር ትምህርት።

www.zeorthodox.org

# ቀዳም ስዑር

## አሥራ ስምንተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ

❖ ተማሪዎች፤ ሰሙነ ሕማማት እና ትበንሣኤ መካከል ስለምናከብረው ቀዳም ስዑር አውቀው ያብራራሉ፤ እነሱም ሰላምን ያደርጋሉ።

### የሚጠና ጥቅስ

*‹‹ገብረ ሰላመ በመስቀሉ፤በመስቀሉ ሰላምን መሠረተ››*

### መግቢያ

በየዓመቱ ከፋሲካ በፊት ያለችውን ቅዳሜን በዓመቱ ካሉት ቅዳሜ ቀናት በተለየ ሁኔታ እንጾማታለን። ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ይፈጸማሉ። በዛሬው ትምህርታችን ስለዚህችው ቅዳሜ እንማራለን።

## የትምህርቱ ዋና ይዘት

❖ ዕለተ ቅዳሜ እግዚአብሔር የሚታዩትንና የማይታዩትን፣ በእግር የሚሔዱትን እና በክንፍ የሚበሩትን በባሕር የሚዋኙትን እንስሳትን በመጨረሻም ሰውን በአርአያውና በአምሳሉ ከፈጠረ በኋላ ያረፈበት ዕለት ነች። ዘፍጥ. ፪፥፩-፫

❖ ይህች የመጀመሪያው ቅዳሜ ለእግዚአብሔር የዕረፍት ዕለተ ናት። እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን ፈጥሮ ስላረፈበት ሰንበት ዐቢይ /ታላቁ ሰንበት/ ትባላለች። ታላቋን ሰንበት እስራኤላውያን እንዲያከብሯት ታዟል። ዘጸ.፳፥፰

www.zeorthodox.org

❖ ዕለተ ቀዳሚት /ሰንበት ዐቢይ/ በዘመነ ሐዲስም የተለየ የድኅነት ሥራ ተከናውኖባታል። ጥንተ ሥነ ፍጥረትን በመፍጠር ዕረፍት እንደ ተደረገባት ሁሉ የፍጥረት ሁሉ ቁንጮ የሆነውን አዳምን ለማዳን ሕማምና ሞት የተቀበለው ቸሩ አምላክ በመቃብር ዐርፎባታል። ማቴ.፳፯፥፷፩።

❖ በዚህች ዕለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከርሰ መቃብር ዐርፎ የዋለባት ዕለት በመሆኗ ‹‹ቀዳም ስዑር፤ የተሻረችዋ ቅዳሜ›› ትሰኛለት። ስዑር ቅዳሜ የተባለችው በዓመት አንድ ቀን

ስለምትጾም ነው። ምክንያቱም እናቱ ድንግል ማርያምና ወዳጆቹ ቅዱሳን ሐዋርያት ጌታ ተላልፎ ከተሰጠበት ዕለት አንሥተው ብርሃነ ትንሣኤውን እስከሚያዩ ድረስ እህል ውኃ በአፋቸው አልዞረም። ይመኩበትና ተስፋ ያደርጉት የነበረ አምላካቸው በመቃብር ስላረፈ ዕለቱን ሞቱን በማሰብ ትንሣኤውን በመናፈቅ በጾም አክብረዋታል።

- ❖ ከቅዱሳን ሐዋርያት ሲወርድ ሲወራረድ በመጣው ትውፊት መሠረተ ቅዱሳን ሐዋርያት በማዘን፣ በመጾምና በመጸለይ ዕለቷን እንዳከበሯት የተዋሕዶ ልጆችም፤ የተቻላቸው ከዓርብ ጀምረው የሚያከፍሉ /የሚጾሙ/ ለሁለት ቀን እህል ውኃ ሳይቀምሱ ያድራሉ። ያልተቻላቸው ደግሞ ዓርብ ማታ በልተው ቅዳሜን በመጾም ትንሣኤን ያከብራሉ።
- ❖ በዚህ ዕለት ከሰኞ ከሆሣዕና ማግሥት ጀምረው እስከ ስቅለተ ዓርብ ድረስ በስግደት እና በጾም ያሳለፉ ምእመናን በዕለተ ቅዳሜ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ይሰበሰባሉ። የጠዋቱ ጸሎት ሲፈጸም ካህናቱ ‹‹**ገብረ ሰላመ በመስቀሉ፤ በመስቀሉ ሰላምን መሠረተ**›› የምስራች እያሉ በቤተ ክርስቲያን ለተሰበሰቡት ምእመናን ቄጠማ ይታደላል፤ ቄጠማው የምስራች ምልክት ነው።
- ❖ ቄጠማው የምስራች ምልክት ተደርጎ የተወሰደው በኖኅ ዘመን ከተፈጸመው ታሪክ ጋር በማቆራኘት ነው። ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን በጻድቁ ኖኅ ዘመን የነበሩ ሕዝቦች ከሕገ እግዚአብሔር ውጪ ሆነው እጅግ የሚያሳዝን ኃጢአት በሠሩ ጊዜ በንፍር ውኃ ተጥለቅልቀዋል። በወቅቱ ጻድቁ ኖኅ ወደ መርከብ ይዞአቸው ከገባው እንስሳት መካከል የውኃውን መጉደል ለመረዳት ርግብን በመርከብ መስኮት አሾልኮ ለቋታል፤ እርሷም ቄጠማ በአፍዋ ይዛ ተመልሳለች። ዘፍ. ፱፥፩-፳፱

## ማጠቃለያ

- ‹‹ቄጠማ››፣ለጥፋት ውኃ መድረቅ የምስራች መንገሪያ እንደሆነ አሁንም በክርስቶስ ሞት ሞተ ነፍስ ከሰው ልጆች ተወገደ ስትል ቤተ ክርስቲያን ለልጆቿ ቄጠማ ታድላለች። ምእመናንም የምስራች ተምሳሌት የሆነን ቄጠማ በግንባራቸው ያስሩታል።
- የክርስቶስ ተከታዮች ሁሉ ከጨለማ ወደ ብርሃን፤ ከሚያቃጥለው ዋዕየ ሲኦል/የሲኦል ቃጠሎ/ ወደ ልምላሜ ገነት ጥንተ ማኅደራቸው መመለሳቸውን፤ በዚህ አኳኋን እየገለጡ በዓለ ትንሣኤን በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያከብራሉ።

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- ገብረ ሰላም ስንል እኛም ሰላማውያን እየሆን ነውና ከተጣላናቸው ጋር በመታረቅ ሰላምን እናድርግ፡፡ ማቴ.፭፥፳፫-፳፮
- በኃጢአት ከእግዚአብሔር ተጣልተን የምንኖርም ሰላምን በንስሐ የምናደርግበት ዘመን ነው፡፡

www.zeorthodox.org

# ነቢዩ ዮናስና ነገረ ድኅነት

## ዐሥራ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ ፡-**

- ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ በነቢዩ ዮናስ ታሪክ ምሳሌት የእግዚአብሔርን ምሕረትና የማዳን ሥራ አውቀው ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ ፡-**

- ***"አቤቱ ማዳንህን ናፈቅሁ፤ሕግህም ተድላዬ ነው፡፡"*** መዝ.፻፲፰(፻፲፱)÷፻፷፬

**ተጨማሪ ምንባባት ፡-**

- ትንቢተ ዮናስና ትርጓሜው

## መግቢያ፡-

- ከዘመናት በፊት ሰዎች ከእግዚአብሔር ራቁ፤ራሳቸውን እና አምላካቸውን እግዚአብሔርን ረስተው በኃጢአት ወደቁ፡፡ እግዚአብሔር ግን አልረሳቸውም፡፡
- ሁሉም ሰዎች በሙሉ እንዲድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ እንዲደርሱ ካለው ፈቃድ የተነሣ ከጎናቸው አልራቀም፡፡ ነቢያቱን እየላከ ምርጦቹን እስራኤልንና ሌሎችን ሕዝቦች ከጣዖታት አምልኮ እና ን ባለማወቅ ከመኖር እንዲወጡ ጠራቸው፡፡
- እስራኤልን ሲጠራም በወገንተኝነት አልነበረም፤ እርሱን ያወቀውና የተባረከው የአብርሃም ዘር ስለነበሩ እንጂ፡፡
- እስራኤል ግን እግዚአብሔር እንደጠራቸው መሆን አልቻሉም፡፡ ጣዖት በማምለክ እና በአሕዛብ ልማድ ረከሱ፡፡
- ከተያዙበት የኃጢአት ወጥመድ እንዲሁም እግዚአብሔር አምላክን በመካድ ከጣዖታት ባዕድ አምልኮ መላቀቅ ያቃታቸው ሕዝበ እስራኤል እና ነቢያቶቻቸው አዳኛቸውን እግዚአብሔርን ተስፋ ከማድረግ የተሻለ አማራጭ አልነበራቸውም፡፡
- ይህም ሆኖ የሰዎች መከራ ሲበዛና ሕዝቡም ከእግዚአብሔር በራቁ መጠን በጉስቁልናቸው ሊተው ያልፈቀደው የሠራቸው እግዚአብሔር ሊያድናቸው ፈቀደ፡፡ ለእነርሱ ያለው ፍቅርም ብርቱ ሆኖ ቀጠለ፤ክንዱም አዳኛቸው ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

## የትምህርቱ ይዘት ፡-

ሀ. እግዚአብሔር ዮናስን አዳነው።

❖ ይህ ነቢይ የዋህ እና የእምነት ልብ ያለው ነበር። እንደ ሌሎቹ ሕዝቦች የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰማ ሸሽቶአል።

❖ ይህም ***"ድምፅህን ሰምቼ ሸሽሁ እርቃኔንም ስለሆንኩ ተደበቅሁ"*** ዘፍ.፫÷፲ የተባለውን ቃል ያስታውሰናል። እንደ አይሁድ ነቢይነቱ ከሌሎቹ የበለጠ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይጠበቅበታል፤

❖ ዮናስ ለርሱ የሚሆን ሰላም በተርሴስ ወይም በመርከቡ ውስጥ የሚገኝ መስሎታል:: ***"ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ?"*** የሚለውን የዳዊት ቃል (መዝ.፻፴፱÷፯) ያነበበ፤ የሚያውቀው ዮናስ ግን ሰላም ወደሌለበት ሸሸ።

ለ . እግዚአብሔር ዮናስን እንዴት አዳነው?

☙ እግዚአብሔር አምላክ ዮናስ የታዘዘውን በመፈጸም እንዲድን የሚከተሉትን ተጠቅሟል።

1. ***ምቾት መንሣት***፡- የባሕር ሞገድ፣ የቅሊቱ መጥፋት(በዚህም እግዚአብሔር መልእክቱን በምልዓት እንዲረዳ አደረገው)
2. ***በመለማመድ***፡- እግዚአብሔር የዮናስን ሕይወት ባሕር ሰጥሞ ከመሞት እና ከዓሣ ነባሪ ሲያድናት ምሕረቱን አሳይቶታል። በተግባራዊ ትምህርትም ምሳሌ ሰጥቶታል። (ቅሊቱ ተልእኮውን እንዲፈጽም እና ሐዘኔታ እንዲኖረውም ረድታዋለች።)
3. **የተፈጥሮ ኃይል** ፡- ትምህርትነቱ ለዮናስ ነበር።

### ሀ. በመታዘዝ ፡-

❖ አውሎ ንፋሱ ለጌታ ሲታዘዝ የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመፈጸም ነበር።

❖ ዓሣ ነባሪውም እንደ መርከብ ሆኖ ዮናስ መገኘት ከአለበት ቦታ አድርሶታል።

❖ ትሉም ዛፉን በመብላት ታዝዞአል።

www.zeorthodox.org

### ለ. የእግዚአብሔርን ችሎታ እና ኃይል በማሳየት ፡-

☙እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ ይችላል፤ሁሉም ፍጥረታትም ይታዘዙታል።

☙የሰው ልጅ ግን ለመታዘዝም ሆነ ለእንቢታ ነጻ ፈቃድ አለው።

ሐ. እግዚአብሔር መርከበኞቹንም አድኖአል፡-

ከአሕዛብ ወገን የሆኑት መርከበኞች ከሸሸው ነቢይ ተሽለዋል፡፡ እንዴት?

1. ወደ አማልክቶቻቸው ጸልየዋል፡፡
2. በጓደኝነት መንፈስ ጸልየዋል፡፡
3. አለመረጋጋቱ ከእነርሱ መካከል በተሠራ ኃጢአት መሆኑን አምነዋል፡፡(ተአምኖ ኃጣውእ ነበራቸው፡፡)
4. በአክራሪነት መንፈስ ሳይታወሩ ዮናስ እንዲጸልይ ለምነውታል::
5. ሩኅሩኅ እና ጠንቃቃ አስተሳሰብ ነበራቸው፡፡ ብዙ ንብረታቸውን ከጣሉ በኋላ ዮናስን ሞት የሚገባው መሆኑን እያወቁም ተጠንቅቀዋል፡፡
6. ዮናስን ወደ ባሕር ከመጣላቸው በፊት ምሕረትና ቸርነትን እየለመኑ፤ ***"ንጹሕም ደም በእኛ ላይ እንዳታደርግ እንለምንሃለን፡፡"*** እያሉ ጸልየዋል፡፡
7. ከዚህ መንገድም ፍትሕ እና ምሕረትን የተሞላ ልብን እናያለን፡፡
8. በእግዚአብሔር ተአምራዊ ኃይል ያምኑ ነበር፡፡

መ. እግዚአብሔር ነነዌን አዳነ፡-

- በመጨረሻም እግዚአብሔር ነነዌን የሚያድንበትን መልእክት የሚያደርስለት ሰው አገኘ፡፡ ልጆቹን እንደሚወድ አባት ይጠነቀቅላቸው ነበርና፡፡
- እግዚአብሔር ሊቀጣቸውና ሊያጠፋቸው ቢፈልግም ከቁጣው የሚመለስ ቸር የምሕረት አምላክ እንደመሆኑ ታገሳቸው፡፡ ዮናስ ወደነዚህ ክፉ ሕዝቦች ለመሄድ አልፈለገም ነበር፡፡
- እግዚአብሔር ግን ንስሐቸውን ሊቀበል ፈቀደ፡፡ ታግሷቸውማል፡፡ ኢአማንያን እና ኃጢአተኞች ቢሆኑም ፈጣሪያቸው አልተዋቸውም፡፡ እግዚአብሔር ልጆቹ ምንም ቢበድሉትም አይተዋቸውም፡፡
- የነዚህ (የነነዌ ሰዎች) ንስሓም የእውነት ነበር፡፡ዮናስ የተናገራቸውን ቃል ሰምተው እግዚአብሔርን በመፍራት አለቀሱ፡፡ ንጉሡም ማቅ ለብሶ በአመድ ላይ ተኛ፡፡ ሕዝቡም በጾምና ራሳቸውን በማዋረድ ንስሐ ገቡ፡፡ እንስሳቱም ጾሙ፡፡ እግዚአብሔር እውነተኛ ንስሐን እና የተሰበረን ልብ ይቀበላል፡፡

www.zeorthodox.org

ሠ. ዮናስ የክርስቶስ ምሳሌ ነው ፡-

- እግዚአብሔር ዮናስን ወደ ነነዌ ሰዎች ላከው፤ የነነዌ ሰዎችም ንስሐ ገብተው ዳኑ፡፡ በተመሳሳይም እግዚአብሔር ከፍቅሩ የተነሳ አንድያ ልጁን ላከ ፤ ጌታችን ሥጋን ተዋሕዶ ሰው ሆነ፤ስለ ዓለም ሞቶ ተነሣ፤ ላመኑበትም የዘላለም ሕይወት ሰጠ፡፡

- ዮናስን ወደ ባሕሩ መጣል መርከበኞቹን በሙሉ ከሞት ጥፋት አድኗል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሰቀል ለዓለም ሁሉ ከዘላለም ሞት መዳንን አድሏል፡፡
- ዮናስ በዓሣ ነባሪው ሆድ ሦስት ቀንና ሌሊት አድሮ በመውጣት በሕይወት ኖሯል፡፡ አሁንም በተመሳሳይ ሁኔታ ጌታችን በመስቀል ላይ ሞቶ ሦስት ቀንና ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ከሙታን ተነሥቷል፡፡ ሕያው ሆኖ የዘላለምን ሕይወት ሰጥቶናል፡፡
- በዮናስ ጸሎት የሞትን ድል መነሳትና ዳግም ልደትን የሚያስተምር ግልጽ መልእክት አለ፡፡ ***"በሲኦልም ሆድ ውስጥ ሆኜ ጮኽሁ÷ቃሌንም አዳመጥህ...በምድርና በመወርወሪያዎችዋ ለዘላለም ተዘጋሁ፤አንተ ግን አቤቱ አምላኬ÷ሕይወቴን ከጉድጓዱ አወጣህ፡፡"*** ዮና.፩÷፪-፯ ይህንንም ከጌታችን ሞት እና ትንሣኤ ጋራ በማነጻጸር ለቅዱሳን ሐዋርያቱ ያላቸውን ማስተዋል ይገባል፡፡ ***"...የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች አልፎ ይሰጣል÷የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል÷ ለአሕዛብም አሳልፈው ይሰጡታል÷ ይዘብቱማል÷ ይተፉበትማል÷ ይገርፉትማል÷ ይገድሉትማል÷ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል አላቸው፡፡"*** ማር.፲÷፴፫-፴፬

## ማጠቃለያ፡-

- እግዚአብሔር የሰው ልጆችን በነቢያት ቃል እያዘጋጀ ነበር፡፡ በተጨማሪም ብዙ ምልክቶች እና ትንቢቶችን በመግለጥ የዓለምን ድኅነት እንዲጠብቁ አድርጓል፡፡ የትንቢቱን መፈጸም (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን) የተጠባበቁና ያመኑም ድነዋል፡፡

## ተግባር፡-

1. በእኛ ያለ መንፈስ ቅዱስን ፈቃድ እና የእኛን ተግባር አስተውለን ለመታረም ጥረት ማድረግ አለብን፡፡
2. ***"መገሠጽስ እግዚአብሔር ገሠጸኝ÷ለሞት ግን አልሰጠኝም፡፡"*** መዝ.፻፲፯(፻፲፰)÷፲፰. ይህን ቃል ከነብዩ ዮናስ ታሪክ ጋር አነጻጽሩት፡፡
3. ተስፋ መቁረጥን ከእናንተ አርቁ፤ በዚህም ስሕተታችሁን በማረም የቀና ሕይወት ትጓዛላችሁ፡፡
4. እግዚአብሔር እንደፍቃዱ ሕይወታችንን እንዲመራው እና እንዲያርመን እንጸልይ፡፡
5. እግዚአብሔር ለድኅነታችን ያዘናልና፤እግዚአብሔር ለሚያዘን ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ ልብ ሊኖረን ይገባል፡፡
6. እግዚአብሔር ቀጥቷቸው መልካምን ያገኙና የዳኑ ቅዱሳንን ታሪክ አስረዱ፡፡
7. እግዚአብሔር ምሕረቱን እና ትዕግሥቱን ለሰዎች ከሚያሳይባቸው ሁኔታዎች የተወሰኑትን ግለጡ፡፡

www.zeorthodox.org

# የጾም ጥቅም (፩)

## ሃያኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ** ፦ ተማሪዎች ስለ መንፈሳዊ ጾም እና ጸሎት ምንነትና ጥቅም አውቀው ከቤተሰቦቻው እና ከጓደኞቻቸው ጋር ይወያያሉ፤ የጾምና የጸሎት ሕይወታቸውን ቀስ በቀስ ለማሳደግ ይለማመዳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፦** *"አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ።"* ማቴ ፬÷፩-፪

## መግቢያ

ይህ ትምህርት ስለ ጾም መንፈሳዊነት እና ጥቅም ለተከታታይ ሦስት ሳምንታት የምንማረው ሲሆን፤ በዛሬው የመጀመሪያው ክፍል ትምህርታችንም የጾምን ጥቅም እናያለን።

**የጾም ትርጉም**

- ጾመ ተከለከለ ማለት ሲሆን፤ ከምግብና መጠጥ ለተወሰነ ሰዓታት እንዲሁም ከቅባት(ጽሉላት) ምግቦች (ሥጋ፣ወተት፣ቅቤ) ደግሞ በጾም ወቅት ፈጽሞ መከልከል ነው።
- በተጨማሪም ክርስቲያኖች ሁል ጊዜም መጾም ያለባቸው ክፉት፣ ኃጢአትና ክፉ ምኞቶችም አሉ።
- ጾም የሥጋ ፍላጎቶችን በማዳከም የነፍስን ፍቃድ ለመፈጸም የምንችልበት ነው።

ጾም የመንፈሳዊ እድገት መንገድ ነው። ከመንፈሳዊ እድገት ጋር ያልሆነ ጾም የምግብ ለውጥ ብቻ ነው።

## የሚተኮርባቸው ነጥቦች

**ጾም ቀዳሚው ሕገ እግዚአብሔር ነው።**

www.zeorthodox.org

- እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠው የመጀመሪያው ሕግ ከአንድ የዛፍ ዓይነት እንዳይበላ መከልከል ነበር። /ዘፍጥ. ፪÷፲፮-፲፯/
- በዚህም እግዚአብሔር አዳምን ሊያስተምረው የፈለገው የሥጋን ፍላጎት በሙሉ መፈጸም እንደማይገባና ራስን መግዛትን ነው።
- በምድራዊና ቁሳዊ ነገሮች ላይ ያለውንም መልካምነትና ደረጃ ለማስተማር ነው።

- አዳም በፈተናው ተሸነፈ፤ በዚህም አዳም ከነፍሱ ይልቅ ለሥጋው ማስቀደሙን እናስተውላለን፡፡
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሥራው መጀመሪያ ያደረገው ጾምን ነው፡፡ *"ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፡፡ አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ፡፡"* ማቴ ፬÷፩-፪

## *የዘመነ ብሉይ ነቢያት ጾመዋል*

- መዝሙረ ዳዊት መዝ ፴፬(፴፫)÷፲፫፣፷፰(፷፱)÷፲፣ ፻፲፰/፻፲፱/÷፳፬፤ ትንቢተ ዳንኤል ዳን. ፲÷፫
- የመጥመቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርትም ይጾሙ ነበር፡፡ *"እኛና ፈሪሳውያን ብዙ ጊዜ የምንጾመው ደቀ መዛሙርትህ ግን የማይጾሙት ስለምንድን ነው? አሉት፡፡"* ማቴ ፱÷፲፬
- ጌታችንም ሐዋርያት እንደሚጾሙና የጾምንም አስፈላጊነት በጥያቄያቸው ላይ ተመሥርቶ አስተምሮአል፡፡ *"ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን ሙሽራው /ክርስቶስ/ ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል (በሞት፣ በእርገት) በዚያን ጊዜም ይጾማሉ፡፡"* ማቴ ፱÷፲፭ በዚህም መሠረት ሐዋርያት ጾመዋል፡፡

## *ሐዋርያት ጾመዋል*

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ጾመ፣ ሐዋርያትም ጾመዋል፡፡
- <u>ቅዱስ ጴጥሮስ</u> *"በስድስት ሰዓት ያህል ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራው ወጣ፡፡ ተርቦም ሊበላ ወደደ"* የሐዋ.፲÷፱-፲
- <u>ቅዱስ ጳውሎስ</u> *"በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን… በመጾም፣ በንጽሕና፣ በዕውቀት ፪ኛ ቆሮ.፮÷፬-፲፩ "በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፣ በረኃብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም ነበርሁ፡፡" ፩ኛ ቆሮ.፲፩÷፳፯*
- <u>ሐዋርያት በአንድነት</u> *"እነዚህ ጌታን ሲያመልኩና ሲጾሙ መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ፡፡ በዚያን ጊዜም ከጾሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው፡፡"* ዮሐ.ሥ.፲፫÷፪
- የጽድቅ መምህራችን መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስም የጾምን ኃይል፤ *"ይህ ዓይነት ግን (ጋኔን) ከጸሎትና ከጾም በቀር አይወጣም አላቸው፡፡"*ማቴ ፲፯÷፳፩

www.zeorthodox.org

## *የዓዋጅ ጾም በጉባኤ ሁሉም የሚጾመው ጾም ነው*

- የነነዌ ሰዎች እንዲጾሙ ታውጆ ጾመዋል፤ ጌታም የንስሐና የዓዋጅ ጾማቸውን ተቀብሎ ምሮአቸዋል፡፡ ዮና.፫÷፫-፮

- አይሁድ ጾመው አስቴር በንጉሡ ፊት እንድትቆምና ሕዝቡን እንድታድን ረድቶአታል፡፡ አስቴ. ፬፥፲፫-፲፯
- ስለዚህም ነው ነብዩ፤ *"ጾሙን ቀድሱ ጉባኤውንም አወጁ፡፡"* ኢዩ ፪፥፲፭ ያለው፡፡

## *የሕግ አጽዋማት*

- የጾም ሕግን መሥራት ያስተማረ እግዚአብሔር ነው፡፡(ዘፍ. ፪፥፲፮-፲፯)
- በሕግ የተወሰኑ የጾም ቀናት እንደነበሩም ተጽፎአል፡፡ *"በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጾማለሁ"* ሉቃ.፲፰፥፲፪
- በዚህና ከላይ በተገለጡት መሠረት ቤተ ክርስቲያን በዓመት ሰባት አጽዋማትን በሕገ ቤተ ክርስቲያን ደንግጋለች፡፡

***እነርሱም፦*** ዐቢይ ጾም፣ ጾመ ነነዌ፣ ጾመ ነቢያት፣ ጾመ ሐዋርያት፣ ጾመ ፍልሰታ፣ጾመ ድኅነት/ረቡዕና አርብ/ እና ገሀድ ናቸው፡፡

### ጾም ከመንፈሳዊ በረከቶች ቀድሞ የሚፈጸም ነው፡፡

- የእግዚአብሔርን በረከቶች በመንፈሳዊ ብቃት ለመቀበል በጾም መዘጋጀት አለብን
- ስለዚህም ነው ከቤተ ክርስቲያን በዓላት ሁሉ በፊት ያለው፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት እንደ ልደት፣ጥምቀት፣ትንሣኤ የመሳሰሉትን ዐበይት በዓላት ከማክበራችን በፊት ጾምን እየጾምን እንቆያለን፡፡
- ከመቁረባችን በፊት ለ፲፰ ሰዓታት የምንጾመውም ለዚህ ነው፡፡

### ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጾምን በማስቀደም ይፈጸማሉ፡፡

- መጾም ለማይችሉ ሕሙማን ቀንዲል ሲፈጸም ካልሆነ፤ ምስጢራት ሁሉ ጾምን በማስቀደምና ከጾም ጋር ይፈጸማሉ፡፡

### እግዚአብሔርን ለማገልገል ከመውጣት በፊት ጾም ይቀድማል፡፡

- ጌታችን ያስተማረን ይህንኑ ነው፡፡/ማቴ.፬፥፩-፲፩/
- ሐዋርያትም ለማስተማር ከመውጣታቸውና ማቲያስን በይሁዳ ከመተካታቸው በፊት ጾመዋል፤ /የሐዋ.ሥ.፩፥፩-፳፯/
- ጳውሎስና በርናባስም ለሐዋርያዊ ተልዕኮ ከመውጣታቸው በፊት ጾመዋል፡፡/የሐዋ.ሥ.፲፫፥፪-፫/

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

- ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትምህርትና ሐዋርያዊ ትውፊት ላይ ተመርኩዛ ለጾም ልዩ ትኩረት ትሰጣለች፡፡ ይህም በሌሎች እየቀረ የመጣ መንፈሳዊ ኃይልና ትውፊት ነው፡፡
- የሥጋ ፍላጎታችን ድርጊቶቻችንን ሁሉ ይቆጣጠራል፡፡ የሥጋ ፍላጎታችንን ሁሉ በአግባቡ መቆጣጠርና መግታት ካልቻልን በመንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ስለዚህ በጾምና ጸሎት የሥጋ ፍላጎቶታችንን መቆጣጠር እንችላለን፡፡
- ጾም ለመንፈሳዊ እድገት አስፈላጊው መንገድ ነው፡፡

## ተግባር

- የጾምና ጸሎት ሕይወትን ቀስ በቀስ እያዳበሩ ማሳደግ ይቻላል፡፡ ተማሪዎች የጾምና የጸሎት ሕይወታችሁን ለማሳደግ ከትንሽ ወደ ብዙ ሰዓታት ቀስ በቀስ ለማሳደግ ተለማመዱ፡፡
- ዐቢይ ጾምን ከነፍስ አባታችሁ ጋር ምክር በመቀበል ጀምሩት፡፡
- ከቤተሰብና ከጓደኞቻችሁ ጋር ስለጾም ጥቅምና መንፈሳዊ ነገር በመወያየት ትርፍ ጊዜያችሁን መልካም ነገር በማድረግ አሳልፉ፡፡

### *መዝሙር*

ንጹም ጾመ ወናፍቅር ቢጸነ
ወንትፋቀር(5) በበይናቲነ

**ትርጉም**

ጾምን እንጹም ወንድሞቻችንንም እናፍቅር
እርስ በርሳችንም እንዋደድ

www.zeorthodox.org

# የጾም መንፈሳዊነት /ሁለት/

# ጾምና ሥጋዊ አካል

# ሃያ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ ጾም ከሥጋዊ አካላችን ጋር ስለአለው አንድነትና ለመንፈሳዊ እድገት ስለሚሰጠን ጥቅም አውቀው ያስረዳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" ዳንኤልም በንጉሡ መብልና መጠጥ እንዳይረክስ በልቡ አሰበ፡፡"*** ትን.ዳን ፩÷፰

ተጨማሪ ምንባባት፡- ዳንኤል ፩

## የሚተኮርበት ነጥብ

- በትንቢተ ዳንኤል ተጽፎ እንደምናጠናው ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ በንጉሡ ከሚቀርበው መብልና ጠጅ ይልቅ በጾምና ጸሎት ተወስነው ጥራጥሬን ይመገቡ ነበር፡፡ በዚህም ከሌሎቹ ይልቅ ፊታቸው አምሮ ሥጋቸው ወፍሮ ታይተዋል፡፡ ትንቢተ ዳንኤል ፩÷፩-፲፮
- ከዚህም ዓለም ምኞት፣ ከሥጋ ፈቃድ ምግብና መጠጥ ይልቅ የነፍስና ፈቃዶቿን መፈጸም አስፈላጊ መሆኑን ከእግዚአብሔር ጋር በአንድነት እንደሚጠብቀን እንረዳለን፡፡ በእግዚአብሔር የማያምነው ንጉሥ ለዳንኤልና ለሠለስቱ ደቂቅ ለጤቸውና ለአካላቸው ብቃት የተሻለ ነው ብሎ ያቀረበላቸው ምርጥ ምግብ ብቻ ነበር፡፡ ይህን ያደረገው ሰው ሥጋዊ ብቻ ነው ብሎ ስለአሰበም ነው፡፡ በተቃራኒው እግዚአብሔርን በእውነት የሚያመለኩት፣ ሰው ከሥጋ ብቻ እንዳልተፈጠረና ቁሳዊ ምግብ ብቻ የሚያስፈልገው እንዳልሆነ ይረዳሉ፡፡ ስለዚህ ዳንኤልና ጓደኞቹ ግን ከሥጋ ፍላጎትና መብልና መጠጥ ይልቅ ነፍስና ፈቃዶችዋ ዋናው አስፈላጊ ነገሮች መሆናቸውን ተረድተው÷ ለሥጋቸው የሚያስፈልጋቸውን መብልና መጠጥ ተቆጣጠሩት፡፡
- የዳንኤልና የጓደኞቹ ጾም ምን ውጤት አስገኘ? ከሌሎቹ በተሻለ ጤነኞች፣ ጠንካሮች እና በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም በጥልቀት ያደጉ ሆኑ፡፡

www.zoorthodox.org

## ትርጉም ከሥጋ አንጻር

❖ የጾምን መንፈሳዊ ትርጉም በሚቀጥለው ትምህርታችን እናየዋለን፡፡ ከሥጋ አንጻር ግን በዛሬው ትምህርታችን ሁለት ነጥቦችን እናያለን፡፡

፩. ከምግብ መጠጥ ለተወሰኑ ጊዚያት /ሰዓታት/ ተከልክሎ መቆየት፡፡

፪. ከጥሉላት ምግቦች (ማለትም ከሥጋና ከወተት ውጤቶች) በጾም ወራት መከልከል ነው፡፡ ቀጥሎ እነዚህን ሁለት ነጥቦች እንወያያለን፡፡

1. **ከምግብና መጠጥ ተከልክሎ መቆየት፡-** በጾም ወቅት ከማንኛውም መብልና መጠጥ ተከልክሎ መቆየት የግድ ነው፡፡ አትክልቶችን ብቻ እየበሉ ከመብልና መጠጥ ሳይከለከሉ መቆየት ይቻላል፡፡ ሆኖም ይህን ማድረግ አትክልት ብቻ በሊታነት (Vegetarian) እንጂ ጾም አይደለም፡፡

- ከመብልና መጠጥ መጾም ከሰውየው መንፈሳዊ ሕይወት ደረጃ አንፃር፤ ከዕድሜው፤ ከጤናውና፤ ከሥራው ዓይነትና ከሌሎችም ጉዳዮች አንጻር እየታየ በተለይ ከአንድ ክርስቲያን ምእመን ከንስሐ አባቱ ጋር በመነጋገር የሚፈጸም ነው፡፡
- ይህም ሆኖ ግን እያንዳንዱ እንደየአቅሙ የሚጠበቅበት አነስተኛ ደረጃ አለ፡፡ ይህም ከንሰሐ አባት ጋር በመመካር ይፈጸማል፡፡ መራብ በጾም አንዱ የሚፈለግ ነገር ነው፡፡ ይሄንንም በሚከተሉት ምሳሌዎች ማየት እንችላለን፡-
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *"አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጾመ በኋላ ተራበ፡፡"* ማቴ.፬÷፪
- ቅዱስ ጴጥሮስ" ***ጴጥሮስም በስድስት ሰዓት ያህል ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራው ወጣ፡፡ ተርቦም ሊበላ ወደደ፤ ሲያዘጋጁለት ሳሉም ተመስጦ መጣበት፤..."*** የሐዋ.ሥ.፲፣፱-፲
- ቅዱስ ጳውሎስ ***"መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፤ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብን ተምሬአለሁ፡፡ ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ፡፡"*** ፊልጵ. ፬÷፲፪
- ***" በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጾም፣ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ፡፡"*** ፩ኛ ቆሮ.፲፩÷፳፯
- በጾም ወቅት በረኃብ ሆነን በምንጸልየው ጸሎት መንፈሳዊ ደረጃ ላይ እንደርስበታለን፡፡ በዚህም የተራቡትን በማሰብና በመመጽወት ታላቅ በረከት እንቀበልበታለን፡፡

www.zeorthodox.org

2. **ከጥሉላት መከልከል፡-** እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ሊበላ ያዘዘው አትክልትና አዝርዕት ብቻ ነበር፡፡ ***" እግዚአብሔርም አለ፡- እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በምድር ፊት ሁሉ ላይ ዘሩ በእርሱ ያለውን ሐመልማል ሁሉ የዛፍን ፍሬ የሚያፈራውንና ዘር ያለውንም ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ፤"*** ዘፍ ፩÷፳፱ እንስሳትም እንዲሁ ነበሩ፡፡ ዘፍ፩÷፴

- ከአዳም ውድቀት በኋላ ተከታዮቹ ከኖኅ መርከብ ከወጡ በኋላ ነው *ሥጋ* ብሉ የተባሉት፡፡ (ዘፍ.፱÷፩-፫)
- እግዚአብሔር ሕዝቡን አርባ ዓመት በበረሐ ሲመራቸው÷መብል እንዲሆናቸው የሰጣቸው ***"የድንብላል ዘር የሚመስል÷ እንደማርም የሚጣፍጥ ነበር"*** ዘጸ.፲፮÷፴፩ ***ሥጋ ሲሰጣቸው ግን ከቁጣ ጋር ነበር፡፡*** (ዘኁል.፲፩÷፴፫-፴፬)
- *ዳንኤልና ሠለስቱ ደቂቅ ሲጾሙም* ***'በጥራጥሬ ነበር'*** (ዳን. ፩÷፰-፲፪፣፲÷፫)
- ሕዝቅኤል እንዲበላ የታዘዘው አዝርዕትን ነበር፡፡ (ሕዝቅ. ፬÷፱) ነብዩና
- *ንጉሥ ዳዊትም* በጾሙ ቅቤና *ሥጋ* አልበላሁም ብሏል፡፡*መዝ*.፻፰ (፻፱) ÷፳፬
- አትክልትና አዝርዕት ምግቦች ለሰውነታችን ቀላል ናቸው፤ እንድንተጋም ያደርጉናል፡፡

## ጾም ለሥጋችን የሚያስገኘው ጥቅም

- ለሰውነታችን ዋና ዋና አካላት የዕረፍት ጊዜ ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ ጉበት፣ ልብ.... ኮሌስትሮል ይቀንሰላቸዋል፡፡
- ክብደት መቀነስ፤ ይህም ለልብና ለጠቅላላ ጤናችን ተመራጭና ተፈላጊ ነው፡፡ ንቁና ቀልጣፋም ያደርገናል፡፡
- የጾም ምግቦች የአንድን ሰው ጤንነት ያጠናክራሉ (ይጠብቃሉ፡፡) ሕመም የሚያመጡትም ከባድ ምግቦች እና ስቦች ናቸው፡፡

## ጾም ከሥጋ ይልቅ ለነፍስ የበለጠ ይቀርባል፣ ይጠቅማልም፡፡

- በሥጋችን ስንጾም ለነፍሳችን መንፈሳዊ ተግባር ማዘጋጀታችን ነው፡፡ በዚህም ጾም የሥጋ መራብ ብቻ ሳይሆን የነፍስ ብልፅግና መንገድም ነው፡፡ ለዚህም ነው የጾም ወቅት የሥጋና የነፍስ መንፈሳዊ ተግባር መተባበር ነው የሚባለው፡፡

## ቅድሚያ ለነፍስ መስጠት

- ***" ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል፡፡"*** ማቴ. ፬÷፬
- ***"እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና÷ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ፡፡"*** ሮሜ ፰÷፭

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

1. ስንጾም የሥጋችን ጤና ይጠበቃል፣ ይሻሻላል እንጂ አይጎዳም፡፡
2. ጠቃሚው ነጥብ ደግሞ ፣ ስንጾም ለመንፈሰዊ እድገት ራሳችንን እናዘጋጃለን፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ ስንሆንም ዲያብሎስን በጾምና ጸሎት ማሸነፍ እንችላለን፡፡
3. በጾም ራስን መግዛት እናገኛለን፡፡ ራስን በመግዛትም የተሻለ ስብዕና እንዲኖረን ያደርገናል፡፡ ራሱን የገዛ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ጠንካራ ነው፡፡ የሚናገረውን፣ የሚያየውንና የሚሠራውን የሚያውቅና በአግባብ የሚፈጽም ነው፡፡ ስለዚህ እንጹም፡፡

www.zeorthodox.org

# የጾም መንፈሳዊነት (ሦስት)

## ጾምን መቀደስ

## ሃያ ሁለተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ

❖ ተማሪዎች ጾምን ስለመቀደስ ትርጉሙንና አፈጻጸሙን ለይተው ያብራራሉ፡፡

### የሚጠና ጥቅስ

❖ ***"ጾምን ቀድሱ÷ጉባኤውንም ዓውጁ"*** ኢዮኤል ፪÷፲፭

### መግቢያ

ይህ በሦስት ተከታታይ ክፍሎች ስለጾም መንፈሳዊነት ያቀረብነው ትምህርት የመጨረሻው ክፍል ነው፡፡

### የትምህርቱ ትኩረት

ጾምን መቀደስ ማለት፤ ልዩ ማድረግ፣ ማንጻት፣ ማክበር ማለት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ጾማችን ለእግዚአብሔር የተለየ መሆን አለበት፡፡ ጾም በንጽሕና ሆነን እግዚአብሔርን በማክበር የምንፈጽመው ነው፡፡

የጾም ቀናት የተቀደሱ ናቸው፡፡ ለእግዚአብሔር ለይተን የምንጾመው ቤተ ክርስቲያን የጾም ወቅት ብላ ስለወሰነች ብቻ ነው፡፡ እያንዳንዳችን ደግሞ የራሳችን ዓላማና ግቦች በጾም ወቅት ሊኖረን ይገባል፡፡ በጾም ወቅት የሚኖረን የተመረጠ ዓላማ ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር የሚመነጭና ወደ እርሱም መቅረቢያ ነው፡፡

ስንጾም ነፍሳችን ወደ እግዚአብሔር ትቀርባለች የሥጋ ፍላጎቶቻችንንም በመግዛት መሆን አለበት፡፡

www.zeorthodox.org

ስለዚህም ጾም በሰውና በምግብ መካከል ብቻ የተመሠረተ ግንኙነት ሳይሆን መንፈሳዊ ዓላማ ያለው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለ አንድነት ነው፡፡

### ጾም እንዴት ይቀደሳል?

## 1. ጾምን ከንስሐ ጋር በመፈጸም

ንስሐ ዕለታዊ ተግባር ቢሆንም፤ንስሐ ገብተን መጾም ጾማችንን ይቀድስልናል፡፡

ጾም ግፍንና በሌሎች ላይ የሚፈጸም በደልን በመተውና መካስ መሆን አለበት፡፡ የተቀደሰ ጾም፤ ***"እኔስ የመረጥሁት ጾምይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ÷ ቀንበርንስ ትለቅቁ ዘንድ የተገፉትንስ አርነት ትሰድዱ ዘንድ÷ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን?"*** ኢሳ. ፶፰÷፮

## 2. አብዝቶ በመጸለይ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ***"የዚህ ዓይነቱ አብሮ አደግ ሰይጣን በጾምና ጸሎት ካልሆነ በቀር አይወጣም፡፡"*** ማቴ.፲፯÷፳፩ ብሎ አስተምሮናል፡፡ ይህም በዲያብሎስ ፈተና ላይ ድል ለመቀዳጀት፤ በአሸናፊነት ለመኖር የጾምና የጸሎት ተያያዥነት እና አስፈላጊነትን ያመለክተናል፡፡

በተለይም በጾም ወቅት አብዝቶ መጸለይ ይገባል፡፡ ለዚህም ነው በቤተ ክርስቲያን ረጃጅም ጸሎቶች በተለይ በጾም ወራት የሚፈጽሙት፡፡

ከጸሎት የተለየን ጾም በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አናገኝም፡፡ አይፈጸምም፡፡ ***ሳይታክቱ ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው.... እግዚአብሔር ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለሚታገሳቸውም ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን? እላችኋለሁ÷ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል፡፡ "ሉቃ.፩-፰***

## 3. የብቻችን ጊዜ በመስጠትም ጾማችንን እንቀድሳለን፡

- ጌታችን በተግባር ያስተማረንም ይሄንኑ ነው፡፡ አርባ ቀንና ሌሊት ብቻውን ነበር፡፡ ማቴ. ፬÷፩-፲፩ በተጨማሪም፤ ***"በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ÷ ሌሊቱንም ሁሉ ሲጸልይ አደረ፡፡"*** ሉቃ.፮÷፲፪
- እኛም በመንፈሳዊ ሕይወታችን ጥልቀት እንዲኖረን ጸጥታንና የብቸኝነት ጊዜን ልንለማመድ ያስፈልገናል፡፡ ይህም በተለምዶ በጾም ወቅት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ **ለምሳሌ፡-**በፊልም፣ ጌም፣፣ በቀልድና በጨዋታ የምናሳለፈውን ሰዓት በዚህ የጾም ወቅት ለእግዚአብሔር ብንሰጥ ጾማችንን እየቀደስን ነው፡፡

## 4. በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎትና መርሐ ግብሮች በብዛት በመሳተፍ፡

www.zeorthodox.org

- ቤተ ክርስቲያን በጾም ወቅት ከሌላው ጊዜ የበለጠ የቅዳሴ፣ የመዝሙር፣ የስብከት፣ ሌሊት በሰዓታት አገልግሎት ትሰጣለች፡፡
- እኛም ከትምህርትና ጥናታችን ውጪ እነዚህን አገልግሎቶች ብንሳተፍ ራሳችንን የምናንጽበት የተቀደሰ ጾም ይሆንልናል፡፡

## *የማይገቡ አጽዋማት*

- **የፈሪሳውያን የግብዝነት ጾም፤** (ሉቃ. ፲፰÷፱-፲፬) ይህም በንቀት የተሞላ፣ ለመታየት የሚፈጸም ነው፡፡ ማቴ.፮÷፲፮-፲፰
- **ሌላውን ለመጉዳት ተማምሎመጾም** ቅዱስ ጳውሎስን ለመግደል የጾሙ ሰዎች ነበሩ፡፡ የሐዋ. ሥራ ፳፫÷፲፪-፲፫
- በኤርምያስ ዘመን የነበሩ ሰዎችም እንዲሁ እግዚአብሔር የማይወደውን ጾም ይጾሙ ነበር፡፡ (ኤር. ፲፬÷፲፩-፲፪)

## ማጠቃለያ

ጾም የመንፈሳዊ እድገት ደረጃ እና መገለጫ ነው፡፡ ይሄን መንፈሳዊ እድገት ለማሳካትም ጾምን መቀደስ አለብን፡፡

ጾም ከንስሐ /ከመጸጸት ጋር/ አብዝቶ በመጸለይና ራስን ለመንፈሳዊ ሕይወት ከማያስፈልጉ ነገሮች በመቆጠብ ይፈጸማል፡፡

## ተግባር

ተማሪዎች በጾም ወቅት መንፈሳዊ ኃይልን ለማግኘት የሚከተሉትን መንፈሳዊ ተግባራት ተለማመዱ መንፈሳዊ ትርፍ ታገኛላችሁ፡፡

(1) ብዙ ጊዜ ንስሐ የገባችሁበትን፤ የተዋችሁትን እና ብዙ ጊዜ የጣላችሁን ኃጢአት በተለይ በጾም ወቅት ታገሉት፣ ፈጽማችሁም ተውት፡፡

(2) ከመዝሙረ ዳዊት በተለይም ለሕይወታችሁ በጎ ተፅዕኖ ያለውን መርጣችሁ መርጣችሁ በየቀኑ ጸልዩ፡፡

(3) መጽሐፍ ቅዱስ በየቀኑ ማንበብ፡፡ በክፍል /በምዕራፍ/ ከፋፍላችሁ፣ በማሰላሰልና በመጸለይ በየቀኑ አንብቡ፡፡

(4) የሕሊና ጸሎትን ማድረግ መለማመድ፡፡ በሥራ፣ በመንገድም ሆነ በማንኛውም ሰዓት ፈጣሪን ማሰብና የተማራችሁትን ማሰላሰል፡፡

www.zeorthodox.org

(5) እነዚህን ጸሎቶች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችና መዝሙራት ስትጸልዩ፤ በሕይወታችሁ በጥልቀት ለመረዳት እንድትችሉ አሰላስሉአቸው፡፡

(6)መንፈሳዊ ምንባብ አዳብሩ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በተከታታይነት ማንበብ፤ የቅዱሳንን ሕይወት ታሪክ ማንበብ፤ ወይም ሌሎች መንፈሳዊ መጻሕፍትን ማንበብ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ማድረግ ጥሩ አንባቢ እንድትሆኑ ይረዳችኋል ፡፡

(7) በጾመ ሁዳዴ የጾም መዝሙራትንና የሕማማት ምንባባትን አጥኑ፣ ተለማመዱ ዘምሩም ደጋግሟቸውም። ይህን ማድረግም ከዘፈን እና ከሌሎችም አልባሌ ድርጊቶች እንድትጠበቁ ይደርጋችኋል ።

(8) ስትጾሙ በተለያዩ ደረጃዎችና ሁኔታዎች ለመፈጸም፤ ከንስሐ አባታችሁ እና ቤተሰብ ጋር በመመካከር አድርጉት። ቁርስን መመጽወት፣ የነግህ ኪዳን ማድረስ፣ የጾም ሰዓትን ማሻሻል (ከስድስት ወደ ዘጠኝ ሰዓት ወዘተ...)

(9) ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ልንፈጽማቸው የሚገባን በርካታ ተግባራትም አሉ። **ለምሳሌ፡-** ጨዋነት፣ ትዕግሥት፣ የሌሎችን ድክመት መሸከም፣ ቁጣን መቆጣጠር፣ የምሥጋናና ማበረታቻ ቃላት መጠቀም ሌሎችን ማገልገልና መርዳት፣ ደግነት ዕርቅና ሰላም የመሳሰሉት ናቸው ።

(10) ሌላው ተግባር የልብ ንጽሕና ነው ። የልብ ንጽሕናን የሚጠብቁልንን ትሕትና ፣ ውሳጣዊ የመንፈስ ሰላም፣ እግዚአብሔርን መውደድ ፣ አለማማረርና ባለን ነገር መደሰት፣ ከረብሻኝነት የተለየ ውስጣዊ ጸጥታ፣ አለመቀየም እምነት እና ተስፋ የመሳሰሉት ናቸው። ከዳዊትም ጋር ***"ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝ "*** ብለን በጾማችን እንጸልይ።

www.zeorthodox.org

# ለከፍተኛ ትምህርት መዘጋጀት

## ሃያ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በትምህርታቸው ስኬታማ የሚሆኑበትንና ለከፍተኛ ትምህርት እንዴት መዘጋጀት እንዳለባቸው በቂ ዕውቀት ጨብጠው አስፈላጊውን ዝግጅት ያደርጋሉ፣ ለጓደኞቻቸው ልምዳቸውን ያካፍላሉ፣ ያስረዳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ተዘጋጅታችሁ ኑሩ" ማቴ. ፳፬÷፵፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

❖ ለከፍተኛ ትምህርት የሚያዘጋጁ እና መረጃ የሚሰጡ መጻሕፍትን አንብቡ

## መግቢያ፡-

- ወጣቶች በሚከተሉት አርእስተ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ መምህሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡-
- ወጣቶች ለምንድነው መማር ያስፈለጋችሁ? ባልማር ምን ልሆን እችላለሁ? ብላችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ?
- በትምህርታችሁ እና በተማሪነት ሕይወታችሁ ደስተኛ ናችሁ?
- የትምህርት ዝንባሌያችሁን ለይታችሁ ታውቃላችሁ?
- በትምህርታችሁ ስኬታማ ነኝ ብላችሁ ታምናላችሁ? ካልሆናችሁ ለምን እንዳልሆናችሁ ምክንያታችሁን ጻፉ፡፡
- ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት ምን ዓይነት ዝግጅት እያደረጋችሁ ነው? ስለ ከፍተኛ ትምህርት በቂ መረጃ ወይም ግንዛቤ አላችሁ?

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በዚህ በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዓለማችን ላይ የምናያቸው ከፍተኛ እድገትና ፈጣን ለውጦች መሠረታቸው ትምህርት ነው፡፡ ብዙ ሀገራት በዓመት ከፍተኛ ገንዘብ የሚመድቡት ለትምህርት፣ ለጥናት እና ምርምር ነው፡፡ ወላጆች የልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ለመምረጥ ጊዜ

ሰጥተው ያስባሉ፤ ልጆቻቸውን ለማስተማር ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን መሥዋዕት ያደርጋሉ፡፡ የተለያዩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ትምህርትን ለእያንዳንዱ ሰው ለማዳረስ እና ድንቁርናን እንዲሁም መሐይምነትን ለማጥፋት ተግተው ይሠራሉ፡፡ ስለዚህ ያለምንም ማጋነን ትምህርት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ትልቁን ሥፍራ እንደያዘ እንመለከታለን፡፡

መጽሐፍ ቅዱስም የሚነግረን እውነት ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ የትምህርቱን አስፈላጊነት ከትምህርት የሚገኘውን ጥበብ እና ዕውቀትን የሰው ልጅ ሁሉ እንዲያገኝ መጽሐፍ ቅዱስ ደጋግሞ ይሰብካል፡፡ ነቢያት በበረሐ ትምህርት ቤቶች ነበሩአቸው፡፡ ሐዋርያት ከጌታ እግር ሥር ቁጭ ብለው ተምረዋል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የገማልያል ደቀ መዝሙር ነበር፡፡ "ከመጠምጠም መማር ይቅደም" የሚለው የሀገራችን አባባል ትምህርት የሁሉ ነገር ቀዳሚ እና መሠረት መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ከማስተማር መማር፣ ከመናገር መስማት፣ ከማሳመን ማመን ይቀድማል፡፡ ወጣቶች በኅሊናችን ስለትምህርት ሊኖረን የሚገባው ግንዛቤ እና ሥዕል ይህ ነው፡፡ አንዳንድ ሰነፎች ከሚናገሩት "የተማሩት የት ደረሱ" የተሳሳተ አባባል፤ ራሳችሁን መጠበቅ አለባችሁ፡፡

ከዚህ በመቀጠል ወጣቶች በትምርታችሁ ስኬታማ እንድትሆኑ የሚያስችሉአችሁን ነገሮች እና ለከፍተኛ ትምህርት እንዴት መዘጋጀት እንዳለባችሁ በቅደም ተከተል እናያለን፡፡

**በትምህርት ስኬታማ ለመሆን የሚያስችሉን ነገሮች ምንድ ናቸው?**

## ሀ. የትምህርትን ጥቅም መገንዘብ፡-

የሰው ልጅን ከጎዱት ጦርነቶች እና የተፈጥሮ አደጋዎች በላይ አለማወቅ ወይም ድንቁርና የጎዳው ይበልጣል፡፡ ትምህርት ይህን ያለማወቅ ጨለማ ከላያችን ላይ የሚገፍ እና አእምሮአችንን በዕውቀት እንዲሁም በጥበብ ብርሃን የሚያበራ ስለሆነ ለትምህርት በጎ የሆነ ግንዛቤና ክብር ሊኖረን ይገባል፡፡ ይህ በጎ የሆነ ግንዛቤ በውስጣችን ከፍተኛ የሆነ የመማር ፍላጎት እንዲኖረን ከማድረጉም በላይ ለትምህርት ያለንን ዝንባሌ እና የማወቅ ጉጉታችን እንዲጨምር ይረዳናል፡፡ በዚህ የተነሣ በማንኛውም የትምህርት ዓይነት ስኬታማ ለመሆን ቀዳሚው ነገር ለትምህርት ያለን በጎ አመለካከት፣ ለመማር የተዘጋጀ ኅሊና እንዲሁም የማወቅ ጉጉት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ትምህርት ጨለማችንን እና ድንቁርናችንን ከመግፈፉም በላይ በሕይወታችን የተሻለ የሥራ ዕድል እንዲኖረን እና ጥሩ ክፍያ (ደመወዝ) እንዲከፈለን የሚያስችለን መንገድ ነው፡፡ በተማርነው ትምህርት የበለጠ ማኅበረሰቡን የምናገለግልበትን ዕድል እናገኛለን፡፡ እንዲሁም በቀሪው የሕይወት ዘመናችን የማንወደውን ሥራ እየሠራን መራራ ኑሮን እንዳንገነጭ ይጠብቀናል፡፡ በአጠቃላይ ትምህርት ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሥነ ልቡናዊ፣ ፖለቲካዊ፣ መንፈሳዊ . . . ወዘተ. ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች

www.zeorthodox.org

ያሉት መሆኑን ተገንዝበን፤ ስለትምህርት የነበረንን የተሳሳተ ፍልስፍና በመቀየር ውጤታማ ተማሪ ለመሆን ጠንክረን መሥራት ይገባናል።

## ለ. በዓላማ በመማር፡-

ለምን እንደሚማር እና ተምሮ ምን እንደሚሆን የማያውቅ ተማሪ፤ ውኃ ላይ እንደሚንሳፈፍ እና መድረሻውን እንደማያውቅ የውሃ ላይ ኩበት ነው። አንዳንድ ተማሪዎች ለምን እንደሚማሩ እና ተምረው ምን ደረጃ እንደሚደርሱ ራእይ ስለሌላቸው ያገኙትን ትልቅ የትምህርት ዕድል በዋዛ ፈዛዛ ሲያባክኑ ይስተዋላል። አንዳንዶቹም መሔጃ ስለሌላቸው ሌሎች ደግሞ ጊዜ ለማሳለፊያ እና በዘልማድ ትምህርት ቤት የሚመላለሱ ብዙ ናቸው። ስለዚህ ወጣቶች ነገ መሆን የምትመኙትንና የምትፈልጉትን ዛሬ ላይ ሆናችሁ በማየት ዓላማና ራእይ ኖሮአችሁ መማር አለባችሁ።

## ሐ. ወደፊት ለመሆን ያሰብነውን መልካም ነገር ለማሳካት፣

ራስን በመግዛት ሕልማችን እውን እንዲሆን እና ዓላማችን ግቡን እንዲመታ ከወዲሁ የዓላማ ጽናትና ራስን መግዛትን ልንለማመድ ይገባል። አለበለዚያ ሕልማችን ቅዠት ዓላማችን የማይጨበጥ ደመና ሆኖ ይቀራል። ስለዚህ ተማሪዎች ብዙ ጊዜያችንን ለትምህርት እና ለጥናት ልንሰጥ ይገባል። ሰነፍና ጎበዝ ተማሪዎችን የሚለያቸው የጊዜ አጠቃቀማቸው እና ለትምህርታቸው የሚኖራቸው የዓላማ ጽናት ነው። ስኬታማ ተማሪዎች ራሳቸውን ለትምህርት የሰጡ ናቸው። የጊዜ አጠቃቀማቸው ዘመናዊ እና በጣም የተጠበቀ ነው። ከመምህሮቻቸው ጋር መልካም ግንኙነት አላቸው። በጣም ከአቅማቸው በላይ ካልሆነ በስተቀር ከትምህርት ቤት አይቀሩም። ክፍል ውስጥ ከመምህራቸው ፊት ለፊት ነው የሚቀመጡት። ያልገባቸውን ማንኛውንም ጥያቄ እፍረት ሳይሰማቸው ይጠይቃሉ። ከጓደኞቻቸው ጎጂ ተጽዕኖ እና ከተለያዩ ብርቅርቅ ነገሮች ራሳቸውን ይጠብቃሉ። የቤት ሥራዎቻቸውንና ጥናታቸውን በአግባቡ እና በጊዜው ያከናውናሉ፤ በትምህርታቸው በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ አስቀድመው በጥንቃቄ ይዘጋጃሉ።

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን የስኬታማ ተማሪዎች ፈለግ የምንከተል ከሆነ እኛም ስኬታማ የማንሆንበት ምንም የተለየ ምስጢር የለም። በትምህርት ስኬተማ የመሆን ምስጢሩ ከምንም ነገር መጀመሪያ ትምህርትን ማስቀደም፣ መዘጋጀትና ለትምህርት ራስን ማስገዛት ነው።

www.zeorthodox.org

### 2. በትምህርት ስኬታማ እንዳንሆን የሚያደርጉን ነገሮች ምንድን ናቸው

- የትምህርት ፍላጎት ማነስ።
- ከትምህርት ቤት ያለ በቂ ምክንያት መቅረት።

- ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም፡፡
- መምህሩ ሲያስረድ በአግባቡ አለመከታተል፡፡
- ስልታዊ የጥናት ዘዴ አለመጠቀም ለነገ ማለት እና ባለቀ ሰዓት ለማጥናት መሞከር፡፡
- ያለአግባብ ኢንተርኔት፣ ፊልም፣ ቴሌቪዥን፣ ጨዋታ እና መዝናናትን ማብዛት፡፡
- ራስን አለመግዛት፣ ከሰነፍ ተማሪዎች ጋር ማዘውተር . . . ወዘተ፡፡

### 3. ለከፍተኛ ትምህርት እንዴት እንዘጋጅ፡-

ወታደሮች ለጦርነት፣ ስፖርተኞች ለውድድር፣ እጮኛሞች ወይም አዲስ ተጋቢዎች ለጋብቻ . . . ወዘተ ራሳቸውን አስቀድመው እንደሚያዘጋጁ ሁሉ፤ ወጣቶችም ራሳቸውን ለከፍተኛ ትምህርት የሚያዘጋጁት አሥራ ሁለተኛ ክፍልን ሲጨርሱ መሆን የለበትም፡፡ አትሌቶች ራሳቸውን ለሩጫ ውድድር የሚያዘጋጁት የሩጫው ዕለት አይደለም፡፡ በቂ ጊዜ ወስደው የአካል ብቃት እና የሥነ ልቡና ዝግጅት ለረዥም ጊዜ ያደረጋሉ፡፡ እንደዚሁ ሁሉ ለከፍተኛ ትምህርት ዝግጅት ወጣቶች ማድረግ ያለባቸው ረዘም ላለ ጊዜ ነው፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ከጀመሩ ጀምሮ ለከፍተኛ ትምህርት መሠረት የሚሆናቸውን ዕውቀትና ትምህርት መቅሰም አለባቸው፡፡ ከክፍል ወደ ክፍል በተዘዋወሩ ቁጥር፣ የአጠናን ዘዴያቸው፣ ማጥኚያ ጊዜያቸው እና የንባብ ልምዳቸው እየጨመረ መምጣት አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወጣቶች የበለጠ ሓላፊነት እና ተጠያቂነት የሚሰማቸውን ራሳቸው፣ የገዙ እና የዓላማ ጽናት ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡

ከወላጆቻቸው እና ከመምህሮቻቸው ጋር በመመካከር የትምህርት ዝንባሌያቸውን ለይተው ማወቅ አለባቸው፡፡ ስለ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቂ ዕውቀትና ግንዛቤ መያዝ እንዲሁም ምን ዓይነት ትምህርት እንደሚያጠኑ ከወዲሁ አስቀድመው መለየትና ማቀድ ይገባቸዋል፡፡ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሚያስተምሩ መምህራን፣ ትምህርታቸውን ጨርሰው በሥራ ላይ ከሚገኙ ሰዎችና ትምህርታቸውን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እየተከታተሉ ካሉ ተማሪዎች ልምድ መቅሰም፤ ወጣቶች የሚፈልጉትን ነገር አጥርተው እንዲያውቁ እና ትክክለኛ ውሳኔ እንዲወስኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለዚህ ወጣቶች የከፍተኛ ትምህርት ዝግጅት በቂ ጊዜ እና ጥልቅ ማስተዋል እንደሚፈልግ አውቃችሁ ከወዲሁ በቂ ዝግጅት አድርጉ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

ትምህርት እራሳችንን እና አካባቢያችንን የምንለውጥበት መሣሪያ ነው፡፡ ትምህርት በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ያለውን ቁልፍ ሚና ተምረናል፡፡ በትምህርት ስኬታማ የምንሆንበትን ምስጢር፣ ለከፍተኛ ትምህርት እንዴትና መቼ መዘጋጀት እንዳለብን አውቀናል፡፡ ስለዚህ ወጣቶች በትምህርት

ራሳችሁን፣ ቤተሰባችሁን፣ ሃገራችሁን እንዲሁም ዓለምን መቀየር እንደምትችሉ ተገንዝባችሁ፤ በእግዚአብሔር በመተማመን በዓላማና በራእይ ታታሪ ልትሆኑ ይገባል። ስኬታማ ተማሪዎች በመሆናችሁ ራሳችሁ፣ ቤተሰቦቻችሁ እና እግዚአብሔር በእናንተ ሕይወት እንደሚከብር ስሙም ከፍ እንደሚል አውቃችሁ ለመማር ለመመራመር ትጉሃን ሁኑ።

## ተግባር፡-

መምህሩ ስኬታማ ተማሪዎች ለጓደኞቻቸው ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ያድርግ።

መምህር በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እና በትምህርታቸው የተመሰከረላቸውን ሰዎች ጋብዘው ለወጣቶች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ያድርጓቸው።

ስለ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወጣቶች ልምድ እንዲቀስሙ የተለያዩ መምህራንን፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን የመሳሰሉትን በመጋበዝ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን ያመቻቹላቸው።

www.zeorthodox.org

# ቁማርተኛነት

## ሃያ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**፡- ተማሪዎች፤ ቁማር በመንፈሳዊ እና በማኅበራዊ ሕይወታቸው ላይ የሚያመጣውን ከፍተኛ ጉዳት ተገንዝበው ራሳቸውን ከቁማር ይጠብቃሉ፤ ቁማር ስለሚያስከትለው ጉዳት ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ**፡- "ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም" ማቴ. ፮÷፳፬

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- ማቴ. ፮÷፳፬፣ የሐዋ/ሥራ. ፫÷፩-፲፩፣ ፩ጢሞ. ፮÷፲፣ ዕብ. ፲፫÷፫፣ ማቴ. ፬÷፪-፲፣ ሉቃ. ፲፮÷፱-፲፩

### መግቢያ፡-

- መምህሩ ወጣቶችን ስለ ቁማርተኛነት በቂ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ የጽሑፍ እና የምስል መረጃዎችን ያሳዩዋቸው፡፡
- ወጣቶች ስለ ቁማር የሚያውቁትን ነገር እና በከተማችን ያሉትን የቁማር ዓይነቶች እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡
- ወጣቶች በአካባቢያቸው የሚያውቁትን ቁማርተኛ እንዲሁም ሕይወቱን ለጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ ያድርጉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አንዳንድ ሰዎች ሀብታም የመሆን ሕልማቸውን እውን ለማድረግ እና በአቋራጭ ለመክበር ቁማርን ቀላል እና አቋራጭ መንገድ አድርገው ሲያዘወትሩ ይታያል፡፡ በእርግጥ ቁማር ሀብታም የመሆን ሕልማችንን እውን የሚያደርግ አቋራጭ መንገድ ነው? ስንቱንስ ሀብታም አድርጓል? የሚሉት ጥያቄዎች የዚህ ትምህርት ዋና መወያያ ይሆናሉ፡፡

www.zeorthodox.org

### 1. ቁማር ምንድን ነው?

ቁማር ሰዎች በውስጣቸው ያለውን ከፍተኛ የገንዘብ ፍቅር እና ባለጸጋ የመሆን ሕልም

በአቋራጭ ለማሳካት የፈለሰፉት እና የፈጠሩት ነገር (ጨዋታ) ነው፡፡  የራስ ያልሆነን ገንዘብ ብዙ ድካምና ጥረት ሳያደርጉ በቀላሉ በአጭር ጊዜ የሌሎችን ገንዘብ ለማግኘት የሚደረግ በሞራልም በሃይማኖትም ተገቢ ያልሆነ ሕገ ወጥ መንገድ ነው፡፡ ቁማር ብዙ ድካምና ልምምድ የሚያስፈልገው አይደለም፡፡ በቀላሉ መልመድ የሚቻል ነገር በመሆኑ አንዳንድ ሰዎች ገንዘብን ሠርተውና ደክመው ከማግኘት ይልቅ በአቋራጭ የመክበርና የመበልጸግ ሕልማቸውን ለማሳካት የሚመርጡት ሕገ ወጥ ዘዴ ነው፡፡  እነዚህ ሰዎች የተለያዩ አሳሳች ስልቶችን እና የብልጠት መንገዶችን በመጠቀም ከሥራ ይልቅ ቁማርን ምርጫቸው አድርገው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ በዚህ የተነሣ ቁማር የብዙ ሰዎችን ቀልብ መግዛት የቻለ ሲሆን ኅብረተሰቡ የሚቀበላቸው እና በተለያየ ስያሜ የሚጠራቸው የቁማር ዓይነቶች አሉ፡፡ ሎተሪ፣ ቢንጎ፣ ፑል፣ ኳስ፣ ካርታ፣ ከረንቡላ . . . በመሳሰሉት ጨዋታዎች ገንዘብ በማስያዝና በማወራረድ የሚፈጸሙ የቁማር አይነቶች ናቸው፡፡

ቁማር መጀመሪያው የሚያጓጓ ሲሆን መጨረሻው ግን አሳዛኝ ነው፡፡ መጀመሪያው ድል ተስፋ ቢሆንም መጨረሻው ግን ሽንፈትና ተስፋ መቁረጥን የሚያመጣ ነው፡፡ ቁማር መጀመሪያ አትራፊዎች የሚያደርገን ቢመስለንም በኋላ ግን የማንወጣው የቁማር ሱሰኛ ከማድረጉም በላይ ጊዜያችንን፣ ሀብትና ንብረታችንን እያባከነ ለከፍተኛ ክስረት እና ድህነት የሚዳርገን ነገር ነው፡፡ በተለያዩ ብዙኃን መገናኛ ቁማር እንደ ጥሩ ነገር ስሙን ቀይሮ ስለሚሰበክና በየቀኑ ስለሚቀነቀን ብዙ ሰዎች ስለ ቁማር ያላቸው ግንዛቤ የተዛባ ሊሆን ይችላል፡፡ ዛሬ ዛሬ የኢንተርኔት የመረጃ መረብም ቁማርን በሀገር ውስጥ ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከማንኛውም ሰው ጋር በተመቸንና በመረጥነው መልኩ የቤታችንን ወንበር ሳንለቅ ሊያጫውተን የሚያስችል አማራጭ ይዞልን ቀርቧል፡፡ ነገር ግን በብዙዎች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጤናቸው፣ በማኅበራዊ ግንኙነታቸው፣ በጊዜያቸውና በገንዘባቸው ላይ ጉዳት እያስከተለ ነው፡፡

## 2. ቁማር የሚያሳድራቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች፡-

ቁማር በአንድ ሰው ላይ የሚያሳድራቸው መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነ ልቡናዊ ብዙ አሉታዊ ተጽዕኖዎች፤ በዚህ ትምህርት ጥቂቶቹን ዐቢይ ተጽዕኖዎች ለማየት እንሞክራለን፡፡

www.zeorthodox.org

### 2.1. መንፈሳዊ ክስረት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ሰው ለሁለት ጌቶች መገዛት እንደማይችል፤ ልገዛ ቢል እንኳን አንዱን ሲያስደስት ሌላውን እንደሚያስከፋ፤ በግልጽ በራሱ ሕይወትና በወንጌል አስተምሯል፡፡ ማቴ. ፮÷፳-፲ "ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም

ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።" ማቴ. ፮÷፳፬

ቁማር ሲጀመር በቀልድና በደስታ ቢሆንም እያደረ ግን በቀላሉ ለመተው በማንችልበት ሱሰኝነት ውስጥ ይከተናል። በመጨረሻም የቁማር ሱስ ተገዢ እንሆናለን፤ ቁማር በእኛ ላይ ይሠለጥናል ማለት ነው። ለመንፈሳዊ ሕይወት የምንሰጠው በቁማር ስለሚያዝ የእግዚአብሔርን ቃል የምንሰማበትና ለመንፈሳዊ አገልግሎት የምንተጋበት ጊዜ እያደር ይመነምናል። በእግዚአብሔር በመታመን ለሥራ ከመትጋት ይልቅ በቁማር መታመን ስለምንጀምር ሕልማችን ሁሉ ገንዘብ ይሆናል። የቁማር ሱስ ተገዢ ስለምንሆን ለእግዚአብሔር እና ለቃሉ መገዛትና ታማኝ መሆንን እንተዋለን። ይህ ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ኪሳራ ውስጥ ይከተዋል።

## 2.2. ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ፡-

ከመንፈሳዊ ክስረት በተጨማሪ ቁማር በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለንን ተቀባይነት እና ተአማኒነት ያሳጣናል። "ቁማርተኛ" በሚለው አዲስ መጠሪያ ስማችን እንታወቃለን። በተጨማሪም በሓላፊነት በተለይ ከገንዘብ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች አመኔታ ስለማይጣልብን እና ለአደራ ስለማንበቃ ከሕብረተሰቡ እንድንገለል ያደርገናል። በቁማር የተነሣ ትዳራቸው የተፈታ፣ ልጆቻቸውን የበተኑና ከፍተኛ ብድር ውስጥ የተዘፈቁ ሰዎች ብዙዎች ሲሆኑ የማኅበረሰቡ ዕዳዎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ቁማርተኛ እኔ ላሸንፍ፣ ልበልጽግ በሚል ስሜት የግለኝነት መንፈስ ያድርበታል። ሌላው በቁማር ጨዋታው ሲሸነፍ ይደሰታል። ይህ አመለካከት በልቡ ስለሠረፀ እና ሽንፈቱን መቀበል ስለሚሳነው ለሐሰት፣ ለስርቆት፣ ለድብድብ ለተለያዩ ወንጀሎች ይጋለጣል፤ እንዲሁም ለእስር ይዳረጋል። በዚህም ለተለያዩ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች እራሱን እና ቤተሰቡን ያጋልጣል።

## 2.3. ሥነ-ልቡናዊ ቀውስ፡-

የቁማር መዘዝ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች የሚያቆም አይደለም። ሥነ-ልቡናዊ ቀውሶችንም ያስከትላል። አንድ ቁማርተኛና ሕሊናው በቁማር በሚገኝ በጣም ብዙ ብር ስለሚያዝ እና ቀንና ሌሊት ቁማር ተጫውቶ የሚያገኘውን ገንዘብ ብቻ ስለሚያስብ ሙሉ በሙሉ የቁማር ጥገኛ ይሆናል። ሌላ አማራጭ የሚያይበት የሚያስተውልበት ዓይነ ኅሊናው በቁማር ስለሚታወር በጎ ዕድሎች ያመልጡታል። የሚፈልገውን ሁሉ በተግባር ለማግኘት ስለማይችል እንዲማረር ያደርገዋል። በመጨረሻም ተስፋ ያደረገው ቁማር ሁሉን እንዳሳጣው ሲረዳ የመኖር ሕልሙ ስለሚጨልም ራሱን ለማጥፋት ገመድ ይዞ ይነሣል። በቁማር አንገታቸውን ለገመድ ሰጥተው ወደ መቃብር የወረዱ፣ የተበደሩትን መክፈል ተስኖአቸው ለእስር ቤት የተዳረጉ፣ ለዘመናት የደከሙበትን

www.zeorthodox.org

እና ያፈሩትን ሀብት ሀብትና ንብረት በአንድ ምሽት ቁማር የተነጠቁ ብዙ ናቸው። እነዚህ ሁሉ ቁማር የሚያመጣቸውን መጠነ ሰፊ መዘዞችና ቀውሶች የምናይባቸው ማስረጃዎቻችን ናቸው።

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች ጥሩ ቤትና፣ መኪና፣ የተደላደለ ኑሮ . . . ወዘተ መመኘት በራሱ ክፉ ነገር አይደለም። ገንዘብ ለዚህ ዓለም ኑሮአችን አስፈላጊ መሆኑም እውነት ነው። ነገር ግን ፍላጎታችንን ለማሟላት ከሥራ ይልቅ ከመልካም ሥነ ምግባር እና ከሕግ ውጪ ቁማርን እንደአማራጭ ወስደን ቁማርተኛ መሆን ግን ከስሕተት ሁሉ የከፋ ስሕተት ነው። ቁማር ለምን ይህን ያህል አጠያያቂ ሆነ ? ወጣቶች እናንተስ ቁማር ተጫውታችሁ ታውቃላችሁ? ወይስ ለመጫወት ትፈልጋላችሁ? ቁማር ጊዜያችንን፣ ገንዘባችን፣ ጤናና ሰላማችንን ሁሉ የሚነጥቀን ክፉ ነገር ነው። ስለዚህ ወጣቶች ራሳችንን ከዚህ ክፉ ተግባር ልንጠብቅ እና በሥራ የሚያምን ማንነት ሊኖረን ይገባል።

## ተግባር፡-

- መምህሩ ወጣቶች በቁማር እና በሚያስከትላቸው ክፉ መዘዞቹ ላይ መጠነኛ ጥናት እና ምርም እንዲያደርጉ የቤት ሥራ ይስጣቸው።
- በቁማር ሱስ የተያዙ ወጣቶች ካሉ መንፈሳዊ ምክርና የሥነ-ልቡና ርዳታ እንዲያገኙ መምህሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።
- ወጣቶች በቁማር እና በመዘዞቹ ላይ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የተለያዩ ጥናቶችን እና መጻሕፍትን እዲያነቡ ይጠቁሙአቸው።

www.zeorthodox.org

# ወርቃማው ሕግ

## ሃያ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ከትምህርቱ በኋላ፤ ስለፍቅር ምንነት እንዲሁም ሌሎችን እንዴት ማፍቀር፣ ይቅር ማለት፣ መቀበል እና ማበረታታት እንዳለባቸው ተገንዝበው ለጓደኞቻቸው በክፍል ውስጥ ያብራራሉ፤ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ተግባራዊ ልምምድ ያደርጋሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፣ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና" ማቴ. ፯÷፲፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ ፮÷፴፩፣ ማቴ. ፳÷ ፵፫-፵፰፣ ሮሜ. ፲፪÷ ፱-፳፩

### መግቢያ፡-

- መምህሩ ወጣቶችን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከትምህርቱ በፊት ይጠይቋቸው፡፡
- ወጣቶች ሌሎች ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትና የምትወዱት ነገር ምንድነው?
- በእናንተም ሆነ በሌሎች ሰዎች በተለይ በምትወዷቸው ሰዎች ላይ እንዲደረግ የማትፈልጉት ነገር ምንድነው?
- መምህሩ ወጣቶች የጥያቄዎቹን መልሶች በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ለየብቻ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

ዕለት ዕለት ከሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ብዙ ነገሮች ይገጥሙናል፡፡ በብዙ ነገሮች የበሰሉ፣ የሰከኑ እና የተረጋጋ ሕይወትን የሚመሩ ሰዎች እንደሚገጥሙን ሁሉ፤ ገና በአመለካከታቸው ያልበሰሉ፣ ራሳቸውን እና ስሜታቸውን ያልገዙ፣ ችኩል ሰዎችም ይገጥሙናል፡፡ በዚህ የተነሣ ከሰዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነትም በብዙ ገጠመኞች የተሞላ ነው፡፡ እጅግ ጥንቁቅ፣ ታታሪ ሠራተኛ እና ባለራእይ ሰዎችን ባየንበት ዓይናችን፤ ዝርክርኮችን፣ ሰነፎችን እና ወሬ ወዳጆችን ደግሞ እናያለን፡፡ ሰው አክባሪዎችን፣ ትሑታንን እና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች አይተን አድንቀን ሳንጨርስ፤

www.zeorthodox.org

ሰውን የሚንቁና የሚያንቋሽሹ፣ በትዕቢት ልባቸው ያበጠ፣ ከመነጋገርና ከመወያየት ይልቅ ዱላ የሚቀናቸው፣ በጭንቅላታቸው ሳይሆን በጉልበታቸው የሚያስቡ ሰዎችን ደግሞ እንታዘባለን።

የተጣሉትን የሚያስታርቁ በበጎ ነገሮች እና ሰላምን በመስበክ የተጠመዱ እንዳሉ ሁሉ፤ በአሉባልታና በሐሜት ሰዎችን ሲያጋጩ፣ ጓደኛሞችን ሲያበጣብጡ እና የሰው ትዳር ሲያፋቱ የሚኖሩ ዘመናቸውን በወሬ እና በአሉባልታ የሚያባክኑ ብዙ ሰዎች አሉ።

ጤነኛ አእምሮ እና ንጹሕ ሕሊና ያለው ሰው መወደድ፣ መከበር፣ መፈቀር፣ ይቅርታ ማግኘት እና በሰላም መኖርን ይፈልጋል። መጠላት፣ መዋረድ፣ መናቅ፣ መንቋሸሽ፣ መታማት፣ መዘረፍ ወዘተ በአጠቃላይ ክፉ ነገሮች ሁሉ በእርሱ ላይ እንዲደርሱበት አይፈልግም። ለዚህ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም የምንኖርበትን ምስጢር በወንጌል የነገረን።

**እንግዲህ “ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና” ማቴ. ፯÷፲፪** በተባለው መሠረት ሁላችንም ቃሉን ወደተግባር ለመለወጥ እንጣር።

ወጣቶች በትምህርቱ መግቢያ ላይ ሰዎች ምን እንዲያደርጉላችሁ ትፈልጋላችሁ? ተብላችሁ ተጠይቃችሁ ነበር። ሰዎች እንዲወዷችሁ፣ ፍቅር እንዲሰጥዋችሁ፣ እንዲያከብሯችሁ፣ እንዲንከባከቡዋችሁ፣ ይቅር እንዲሏችሁ፣ መልካምና በጎ ነገር እንዲያደርጉላችሁ . . . ወዘተ ትፈልጋላችሁ? እናንተስ ሌሎችን የሚወድና የሚያፈቅር እንዲሁም ይቅር የሚል ልብ አላችሁ? ሌሎች ስሕተቶቻችንን፣ ውድቀቶቻችንን፣ ነውራችንን እንዲሁም ደካማ ጎናችንን . . . ወዘተ እንዲሸፍኑልንና እንዲሸከሙልን፣ ይቅርታ እንዲያደርጉልንና ሁለተኛ ዕድል እንዲሰጡን እንፈልጋለን። እኛስ ሌሎችን የመሸከም፣ ምስጢራቸውን የመጠበቅ፣ ከስሕተታቸው እንዲማሩ በማድረግ ዕድል እንሰጣቸዋለን? እነዚህ ጥያቄዎች ሁላችንንም የሚመለከቱ ናቸው። በቅን ልቡና ከመለስናቸው ደግሞ ከሰዎች ጋር ከዚህ በኋላ የሚኖረን ግንኙነት ከዚህ ቀደሙ የተለየ መልካም ይሆናል። ከሰዎች ጋር በሰላም እና በፍቅር እንዴት መኖር እንደምንችል ጥበቡ እና ምስጢሩ ይገለጥልናል። ሌሎችን ስናከብር እንከበራለን፣ ስንወድ እንወደዳለን፣ ይቅር ስንል ይቅር እንባላለን፣ ሌሎችን ከነደካማ ጎናቸው ማፍቀር እና መሸከም ስንጀምር እኛንም ይሸከሙናል፣ የሌሎችን መብት ስናከብር የእኛ መብት ይጠበቃል . . . ወዘተ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌሎች ፍላጎቶቻችንን እንዲያሟሉልን፣ ስሜታችንን እንዲሁም የውስጣችንን መሻት እንዲያውቁልን እኛን እንዲረዱን መፈለግ ብቻ በቂ ስላልሆነ እናንተም ይህን አድርጉ ብሎ አስተማረን።

www.zeorthodox.org

## 1. ሌሎችን ማፍቀር፡-

የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን እንዲፈስ እና በኑሮአችን እንዲታይ ሌሎችን ማፍቀር መልመድ እንዲሁም መማር አለብን፡፡ ጌታችን ኢየሱሱ ክርስቶስም ይህን አጽንኦት ሰጥቶ አስተምሯል፡፡

"እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፣ እኔ እንደወደድኋችሁ እናንተም እንዲሁ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፡፡ እርስ በርሳችሁም ብትዋደዱ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ በዚህ ሁሉ ያውቋችኋል፡፡" ዮሐ. ፲፫÷ ፴፬-፴፭

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ እኛም የእግዚአብሔር የሆኑትን ሁሉ በመውደድና በማፍቀር ውስጥ የእግዚአብሔርን ፍቅር እናያለን፡፡ በተቃራኒው ሰዎችን ሳንወድና ሳናፈቅር የእግዚአብሔርን ፍቅር ማየት አንችልም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክረው እውነትም ይህ ነው፡፡

"ማንም፡- እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፣ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችና፡፡" ፩ዮሐ. ፬÷፳-፳፩

በሥጋዊ ዓይናችን የምናያቸውን ሰዎች ስንወድና ስናፈቅር የማይታየውን አምላክ ፍቅር በመንፈሳዊ ዓይን ማየት እንችላለን፡፡ በክርስትና ሕይወታችን ውስጥ ፍቅር ትልቁን ስፍራ ይይዛል፡፡ ይህም ማለት ያለ ፍቅር የምንኖረው ኑሮ፣ የምናገለግለው አገልግሎትና አምልኮአችን በአጠቃላይ ከንቱ ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ፍቅር በመንፈሳዊ ሕይወታችን ውስጥ ያለውን ትልቅ ሥፍራ እንድንገነዘብ በመልእክቱ መክሮናል፡፡

"በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሽው ጸናጽል ሆኛለሁ፡፡" ፩ቆሮ. ፲፫÷ ፩-፲፫

ወጣቶች ሰዎች የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንደሆንን እንዲያውቁ፤ እንዲሁም በእኛ እርስ በእርስ መዋደድ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዲያዩ፤ አገልግሎታችንና አምልኮአችን የሰመረ እንዲሆን፤ ሌሎችን ማፍቀርን መማር አለብን፡፡ ሌሎችን ማፍቀርን ስንለማመድ ፍቅር ሌሎችን መርዳት የምንችልበት አቅም እና የመንፈስ ትስስር እንዲሁም ሕብረት እንዲኖረን ያደርጋል፤ ልባችን በደስታ ይሞላል የእግዚአብሔርንም ፍቅር በጥልቀት ሌሎችን በመውደድ ውስጥ እናያለን፡፡

www.zeorthodox.org

## 2. ይቅርታ፡-

በየቀኑ ከሰዎች ጋር በሚኖረን መስተጋብር ከሰዎች ጋር ልንጣላ እና ልንጋጭ የምንችልባቸው

አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ ሰዎች ሊበድሉን፣ ሊያስቀይሙን፣ ቃላቸውን ሊያጥፉ፣ ሊክዱን እና ልብ የሚሰብር ክፉ ቃል ሊናገሩን . . . ወዘተ ይችላሉ፡፡ እኛም በጊዜው ስሜታዊ ልንሆንና ብዙ ሐሳቦችን ልናስብ፤ ክፉ በክፉ የሚሸነፍ መስሎን የሰደቡንን ለመስደብ፣ የረገሙንን ለመርገም፣ የገፉንን ለመግፋት፣ የደበደቡንን ለመደብደብ. . . ወዘተ እንዘጋጅ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በተረጋጋ አእምሮ እና በሰከነ ኅሊና ማሰብ ስንጀምር ይህ ስሕተት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ምክንያቱም የሰደቡንን ስንሰድብ መልሰን እንሰደባለን፡፡ ክፉ ላደረጉብን ክፉ ለማድረግ እና ለመበቀል ስንነሣ ክፉ ነገር ይጠብቀናል፡፡ ስለዚህ ክፋት ክፋትን እየወለደ እንጂ መቼም ሰላም አይመጣም፡፡ ለዚህ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክፉ ነገሮች የሚሸነፉበትን እና የሚቆሙበትን ምስጢር ያስተማረን፡፡ የጥል ግድግዳ የሚፈርሰው፤ ጦርና ጎራዴ በሰላማዊ ነገር ወደ ማረሻነት የሚቀየረው፣ የክፋት፣ የእርግማን እና የበቀል ምንጭ የሚደርቀው በይቅርታ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ጠላቶቹን ወዶ፣ ክፋውን በመልካም አሸንፎ፣ እና ለሰቀሉት ይቅርታ ለምኖ፤ እኛም ክፋውን በመልካም እንድናሸንፍ፣ እንዲሁም በይቅርታ እጅ ለእጅ ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ ልብ ለልብ እንድንጨባበጥ አስተምሮናል፡፡ የሚከተሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎችን ይህን እውነት የሚገልጹ በመሆናቸው ወጣቶች በጸሎት እና በተመስጠ አንብቧቸው፡፡ (ማቴ.፶፬÷፫-፵፰፣ ማቴ. ፲፰÷፳፩-፴፭፣ መዝ. ፴፩(፴፪)÷፩-፪ ሉቃ. ፲፭÷፲፩-፳፬፣ ኤፌ. ፬÷ ፴፩-፴፪፣ ሮሜ. ፲፪÷ ፲፬-፳፩)

## ማጠቃለያ፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌሎችን እንዴት ማፍቀር፣ ማክበር፣ መቀበል እና ይቅር ማለት እንደምንችል በሕይወቱ አስተምሮናል፡፡ ይህን እውነት መቀበል እና በኑሮአችን ክርስቶስን መምሰል ደግሞ የእያንዳንዳችን ሓላፊነት እና ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ ወጣቶች ወርቃማውን ሕግ የሕይወታችሁ መርሕ በማድረግ በኑሮአችሁ እና በየዕለት ተዕለት እንቅስቃሴአችሁ የሰላም ሰባኪዎች እና የሰላም አምባሳደሮች ሁኑ፡፡

## ተግባር፡-

- መምህሩ ወጣቶች ወርቃማውን ሕግ በየዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው እንዴት መተግበር እንደሚችሉ ተግባራዊ ምሳሌዎችን ከሰጡ በኋላ ወጣቶች እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡

www.zeorthodox.org

# የጂሆቫ (የይሆዋ) ምስክሮች

## ሃያ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ከትምህርቱ በኋላ፤ የጂሆቫ ምስክሮችን እምነትና አስተምህሮ እና የቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት ተገንዝበው ልዩነታቸውን ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እኔ እና አብ አንድ ነን፡፡" ዮሐ. ፲÷፴

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መምህሩ ወጣቶች ስለ ጂሆቫ ምስክሮች እምነት መረጃ የሚሰጡ መጻሕፍትን እንዲያነቡ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

### መግቢያ፡-

- የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚነግረን ሰዎች በክርስቶስ ላይ የሐሰት እና የክህደት ትምህርትን የጀመሩት ዛሬ በዚህ ዘመን ሳይሆን በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ዘመን ነበር፡፡ ሐዋርያት እውነትን ሲሰብኩ እና በክርስቶስ ኢየሱስ የሙታንን ትንሣኤ ሲያውጁ፤ ሐሰትን የሚሰብኩ፣ ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ፣ ልዩ ልዩ የሆነ እንግዳ ትምህርትን የሚያስተምሩ መናፍቃን ነበሩ፡፡ በዚህ የተነሣ ቅዱሳን ሐዋርያት ክርስቲያኖች በእውነት እንዲቆሙ፣ በሃይማኖት እንዲጸኑ፣ በቃልና በጽሑፍ ይመክሯቸው እና ደጋግመው ያሳስቧቸው ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክረውም እውነት ይህ ነው፡፡
- "ወዳጆች ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም መጥተዋልና፤" ፩ዮሐ. ፬÷ ፩-፪
- "ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛው ማን ነው? አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው፡፡ ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም፡፡ በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው፡፡" ፩ ዮሐ. ፪÷ ፳፪-፳፫
- "የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ እንጂ፡፡ ነገር

www.zeorthodox.org

ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።" ገላትያ ፩÷ ፯-፱

- ወጣቶች እነዚህ ከላይ የምትመለከቷቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች፤ መጽሐፍ ቅዱስን እና ወንጌልን ማጣመም ዛሬ የተጀመረ ሳይሆን በሐዋርያትም ዘመን የነበረ መሆኑን የምንረዳባቸው ማስረጃዎቻችን ናቸው። ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን በብዙ የሐሰት እና የክህደት ፍልስፍናዎች ስትፈተን ቆይታለች። መሠረቷ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነም እውነተኛውን ሃይማኖት እየሰበከች እና ምእመናንን ከሐሰት ትምህርት እየጠበቀች እዚህ ዘመን ላይ ደርሳለች። ዛሬም ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እና ከሐዋርያት ትምህርት ውጪ ወንጌልን ለራሳቸው ፍላጎት የሚያጣምሙ፣ እንደገዛ ምኞታቸው የሚተረጉሙና ልዩ ልዩ የሆነ እንግዳ ትምህርትን የሚያስተምሩ መናፍቃን በምድራችን በዝተዋል። ነገር ግን በዚህ ሳንደናገጥ እና ግራ ሳንጋባ እንደ አባቶቻችን እውነተኛውን ሃይማኖት እየመሰከርን ምእመናንን ከሐሰት ትምህርት እየጠበቅን ልንጓዝ ይገባናል። በዚህ ትምህርት የጄሆቫ ምስክሮችን የሐሰት አስተምህሮ እንማራለን።

## የሳምንቱ ትምህርት

የጄሆቫ ምስክሮች ሃይማኖት በ፲፰፻፸፪(1872) እ.ኤ.አ በአሜሪካን ሀገር በቻርለስ ራስል ተመሠረተ። ቻርለስ ራስል ፌብርዋሪ ፲፮ ቀን ፲፰፻፶፪ እ.ኤ.አ በፔንስልቫኒያ የተወለደ ሲሆን በጋዜጠኝነት ሞያ ሀገሩን እያገለገለ ነበር። በ፲፰፻፸፭(1875) እ.ኤ.አ ሲያገለግልበት የነበረውን የኮንግሪጌሽናል ቤተ ክርስቲያን ትቶ ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ማኅበር መሪ ሆነ። መሥራቹ ቻርለስ ራስል የተነሣበት ዓላማ፤ ‹‹መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ መነሻ በማድረግ በሌሎች ሳይመራ አንድ ሰው ራሱ አንብቦ፣ አጥንቶ እና ተመራምሮ ትክክለኛው ውሳኔ ላይ መድረስ ይችላል›› የሚል ነበር። በዚህ መሠረት ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ማኅበር ተቋቁሞ ጥናቱ ተጀመረ። ጄሆቫ የሚለውን ስም ይዘው በመነሣት እግዚአብሔር ስለሠራቸው ሥራዎች አማኞቹ በምስክርነት እንደሚናገሩ ያስተምራሉ።

www.zeorthodox.org

1. ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የሚለዩባቸው የሐሰት ትምህርቶች፤

ሀ. ምስጢረ ሥላሴን አይቀበሉም።

ይህም አብ የሁሉ ፈጣሪ መንፈስ እንደሆነ፤ መንፈስ ቅዱስም የአብ ኃይል ሲሆን፤ ወልድ ግን

መጀመሪያ ማለትም ከአዳም በፊት በአብ የተፈጠረ መንፈስ ነው ሲሉ ያምናሉ፤ ያስተምራሉ። ይህ ትምህርታቸው ከአርዮስ ትምህርት ጋር ተመሳሳይ ነው።

**ለ. ስለ ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ያላቸው እምነትና ትምህርት የተዛባ ነው።**

የጄሆቫ ምስክሮች ሰው ከነአካሉ ነፍስ ይባላል እንጂ ነፍስ ከሥጋ ውጪ አይደለችም ብለው ያምናሉ። ሰው ሲሞትም ነፍስ ሞተች ይላሉ። ትንሣኤ እንዳለ ቢያምኑም ነፍስ ይህን ሥጋ ሳይሆን ሌላ ተመሳሳይ አካል ለብሳ እንደምትነሣ፤ ደግ የሠሩ ነፍሳት እና ባለማወቅ ክፉ የሠሩ ነፍሳት ትንሣኤ ሲኖራቸው፤ ኃጢአተኛ ሰዎች ግን እንደሞቱ እንደሚቀሩ ያምናሉ ያስተምራሉ። መንግሥተ ሰማያትን የሚወርሷት 144,000 ሰዎች ብቻ ናቸው ብለው የሚያምኑ ሲሆን ከፍርድ በኋላ ክርስቶስ ሥልጣኑን ለአብ ያስረክባል ይላሉ። የክርስቶስን ትንሣኤ ቢቀበሉም እርገቱን ግን አይቀበሉም።

**ሐ. ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን አይቀበሉም፡-**

ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ክቡር ስለሆነ ለመስቀል ክብር እና የጸጋ ስግደትን ትሰግዳለች። ነገር ግን የጄሆቫ ምስክሮች ለመስቀል ያላቸውን ጥላቻ እና ንቀት ደጋግመው ይገልጻሉ። ለእነርሱ የዛሬው መስቀል ቅርጽም ሆነ ትርጉም ተቀባይነት የለውም። ሌላው መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ዛሬም እንደሚሠራ አያምኑም። በአጠቃላይ በምስጢረ ክህነት፣ በምስጢረ ጥምቀት፣ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና በቅዱሳን አማላጅነት አያምኑም። እመቤታችን ሌሎች ልጆች እንዳሉአት፤ ሔዋን ለሰው ልጆች ውድቀት ምክንያት ስለሆነች እግዚአብሔር ከሴቶች ጋር እንደማያወራ ያምናሉ ያስተምራሉ።

## ማጠቃለያ፡-

የጂሆቫ ምስክሮችን እምነት እና አስተምህሮ በጥልቀት ስንመረምረው ፍጹም ከእውነት የራቀና ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ያፈነገጠ መሆኑን እንገነዘባለን። መጽሐፍ ቅዱስ እምነት ከመስማት እንደሆነ እና የሰባኪን አስፈላጊነት ይመሰክራል። ቻርለስ ራስል ግን ማንኛውም ሰው ራሱ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ፣ አጥንቶ እና ተመራምሮ ትክክለኛ እምነት ላይ መድረስ እንደሚችል በድፍረት ያስተምራል። የሚከተሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች ግን ይህን የድፍረት አስተምህሮ ውድቅ የሚያደርጉ እና የቻርለስ ራስልን ፍልስፍና በዜሮ የሚያባዙ ሆነው እናገኛቸዋለን።

www.zeorthodox.org

“እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?” ሮሜ. ፲÷፲፬

"ሕይወትም የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ እንደገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ፡፡ እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ፡፡" ፪ ጢሞ ፬÷፫-፬

"ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጒም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ፡፡" ፪ጴጥ ፩÷፳-፳፩

ቻርለስ ራስል በመጀመሪያ ማወቅ የነበረበት መጽሐፍ ቅዱስ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጒመው እንደማይችልና እንዳልተፈቀደ ነበር፡፡ ነገር ግን አምላካዊ ቃል እርሱና ተከታዮቹ ባለመታዘዛቸው ከላይ በዝርዝር ለተማርናቸው የሐሰት እና የክህደት ትምህርቶች ሰለባ ሆነዋል፡፡ ስለዚህ ወጣቶች የጀሆቫ ምስክሮች እምነት እና አስተምህሮ በመሥራቹ በነቻርለስ ራስል ፈቃድ ላይ የተመሠረተ የሐሰት እና የምንፍቅና አስተምህሮ መሆኑን ተገንዝባችሁ ራሳችሁን እና ሌሎችን ከዚህ የክህደት ትምህርት ጠብቁ፡፡ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን መልእክት ዘወትር አስታውሱ፡- "የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፤ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለም ያው ነው፡፡ ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ፡፡" ዕብ. ፲፫÷፯-፱

## ተግባር

መምህሩ ወጣቶች የጀሆቫ ምስክሮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋት የሚጠቀሙባቸውን ስልቶችና መንገዶች እንዲያውቁና ራሳቸውን እንዲጠብቁ በተግባራዊ ምሳሌዎች የተደገፈ ገለጻ እና ውይይትም እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሌሎችን ለክርስቶስ መማረክ

## ሃያ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በትምህርቱ መጨረሻ በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎችን አስተምሮ እና ወንጌልን ሰብኮ የክርስቶስ ማድረግ የሁሉንም ሓላፊነት እና ግዴታ መሆኑን አውቀው እንዴት በተግባር መግለጽ እንዳለባቸው በክፍል ውስጥ ውይይት ያስረዳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፡፡" ዮሐ. ፲÷፲፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፳፰÷፲፱-፳፣ ማር.፲፮÷፲፭፣ ሉቃ. ፬÷፲፯-፲፱፣ ሮሜ. ፲÷፱-፲፫

### መግቢያ፡-

- ወጣቶች አንድ ሰው ክርስቶስን አለማወቁ እና አለመዳኑ ያስጨንቃችኋል?
- በአገኛችሁት አጋጣሚ እምነታችሁን ለማያምኑ ሰዎች ትመሰክራላችሁ?
- እስካሁን ስንት ሰዎችን ክርስቶስን አምነው እንዲከተሉ አድርጋችኋል?
- ያላመኑና ያልተጠመቁ ጓደኞች አሉዋችሁ? እስካሁን በክርስቶስ እንዲያምኑ እና እንዲማረኩ ያደረጋችሁት ጥረት ምንድነው?

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

www.zoorthodox.org

ያላመኑ በክርስቶስ እንዲያምኑ፣ ያልተጠመቁ እንዲጠመቁ እና የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ፣ የራቁት እንዲቀርቡና በክርስቶስ ፍቅር እንዲማረኩ ቤተ ክርስቲያን ያለመታከትና ያለመሰልቸት ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ መስበክ አለባት፡፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚነግረን ቤተ ክርስቲያን ራሷን ከስደት እንዲሁም እውነተኛ እምነቷን ከመናፍቃን እየተከላከለች ጎን ለጎንም የክርስቶስን መንግሥት በማስፋፋት ዕለት ዕለት ነፍሳትን ለክርስቶስ ትማርክ ነበር፡፡ የሐዋ/ሥራ. ፪÷፴፯

ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ዳግመኛ ለፍርድ እስኪመጣ ድረስ የአመኑት በሃይማኖት በምግባር እንዲጸኑ፣ ያላመኑ ደግሞ እንዲያምኑና እንዲጠመቁ ታደርጋለች፡፡ በትጋት በማገልገል ለፍጥረት ሁሉ ወንጌልን መስበክ በክርስቶስ የተቀበለችው ትልቅ አደራ እና ሥራዋ ነው፡፡ ይህን የክርስቶስን ሥራ ሐዋርያት ተከታዮችቻቸው እና በየዘመናቱ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች እየሠሩ አልፈው የሥራቸው ፍሬ ዛሬ ላይ ሊደርስ ችሏል፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው እያንዳንዳችን ሌሎችን ለክርስቶስ የመማረክ ሓላፊነት እንዲሁም ግዴታ አለብን፡፡

**ወንጌላዊነት፡-**

ወንጌል ማለት የምሥራች ማለት ሲሆን፤ ወንጌላዊ ደግሞ ይህን የምሥራች ለሰዎች የሚነግር የሚመሰክር ማለት ነው፡፡ ይህን የምሥራቹን ቃል መመስከር እና ማገልገል ደግሞ ወንጌላዊነት ይባላል፡፡ ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደው፣ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነውና ሞትን ድል አድርጎ በኃይሉና በሥልጣኑ ስለተነሣው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መመስከር፣ ማስተማር ማለት ነው፡፡ ወንጌላዊ፤ ክርስቶስ የእግዚአብሔር፣ ልጅ እግዚአብሔር የፈጣሪ ልጅ ፈጣሪ፣ የአምላክ ልጅ አምላክ፣ እንደሆነ የሚሰብክ ሞትን ድል አድርጎ እንደተነሣ የሚመሰክር ማለት ነው፡፡ እያንዳንዱ ክርስቲያን ይህን እውነት አምኖ የማሳመን፣ ተቀብሎ የማቀበል፣ ተረድቶ የማስረዳት እና ጠብቆ የማስጠበቅ ሃይማኖታዊ ግዴታ አለበት፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን በመመስከር መንግሥቱን ማስፋት የእያንዳንዳችን ሓላፊነት እና ግዴታ መሆኑን በወንጌል በተራራው ስብከት አጽንኦት ሰጥቶ አስተምሯል፡፡ (ማቴ. ፳፰÷፲፰-፳)

በአንድ ሀገር ስንኖር እንደ አንድ ዜጋ ሰው በደል ሲደርስበት እና ሲገደል አይተን ዝም ብለን አልፈን መሔድ የለብንም፡፡ እያንዳንዱ ዜጋ ለሚመለከተው አካል የመጠቆም እና ወንጀለኞችን ለፍርድ የማቅረብ ሓላፊነት እና ግዴታ አለበት፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ሰው አደጋ ደርሶበት ወድቆ ርዳታ እየጠየቀ አይተን ዝም ብለን አናልፈውም፤ የሕክምናም ሆነ ሌላ አስፈላጊ ርዳታ እንዲያገኝ እናደርጋለን፡፡ ልክ እንደዚህ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን (የመንግሥተ ሰማያት) ዜጋ የሆንን ክርስቲያኖች፤ እውነትን ሳያውቁ በጨለማ ሕይወት ለሚኖሩ ሰዎች እውነትን በመመስከር ወደብርሃን ማውጣት ሃይማኖታዊ ግዴታ አለብን፡፡ ምክንያቱም እምነታችን እዚህ ዘመን የደረሰው የቀደሙ አባቶች እምነታቸውን ያለማቋረጥ ስለመሰከሩ ወንጌልን ሰብከው የማያምኑትን ለክርስቶስ መማረክ ስለቻሉ ነው፡፡ (ዕብ.፲፪÷፩-፫፣ የሐዋ/ሥራ. ፬÷፳) ስለዚህ ዘላለማዊ እውነት የሆነውን የክርስቶስን መንግሥት የመመስከር ሥራ ሥራችን በማድረግ ክርስቶስን እና ቤተ ክርስቲያንን ልናገለግል ይገባል፡፡ (፪ጢሞ. ፬÷፭) ወንጌላዊነት እግዚአብሔር እኛን ተጠቅሞ በሌሎች ሕይወት

www.zeorthodox.org

ውስጥ ትልቅ ሥራ የሚሠራበት አገልግሎት ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በዓለም ሁሉ እንዲስፋፋ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ይሠራል፤ የተለያዩ የጸጋ ስጦታዎችን ያድላል፡፡ እነዚህን የጸጋ ሰጦታዎች የተቀበልን ሁላችን እንደታማኙ አገልጋይ ልንጠቀምባቸው እና ሌሎችን ለክርስቶስ ልናተርፍበት ይገባል፡፡ (ማቴ.፳፭÷፳፩-፳፯) እግዚአብሔር ሥራ እንድንሠራለት ሲመርጠን ወደኂላ ማለት የለብንም እንደሰነፍ አገልጋይም መፍራት የለብንም፡፡ እንደ ዮናስ ወደተርሴስ መኮብለል ከእኛ የሚጠበቅ ተግባርም አይደለም፡፡ ጌታ ቅዱስ ጳውሎስን እንዴት ለአገልግሎት እንደመረጠ፤ ሐዋርያው ጳውሎስም ለጥሪው ታማኝ በመሆን እንዴት ወንጌልን ለአሕዛብ በብዙ ድካም እንዳገለገለ አውቀን እኛም በትጋት ልናገለግል ይገባናል፡፡

2. የወንጌል አገልግሎት እንቅፋቶች፡-

የወንጌል አገልግሎት የከበረ አገልግሎት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን እውነት ለሰዎች በመመስከር ነፍሳትን ለክርስቶስ የምንማርክበት ትልቅ የእግዚአብሔር ሥራ ነው፡፡ የምንመሰክረው በብልሃት የተፈጠረ ተረት ሳይሆን የእግዚአብሔርን እውነት ነው፡፡ የሰው አጀንዳ ሳይሆን መለኮታዊ አጀንዳ ነው፤ የሰው ፍቃድና ሐሳብ ሳይሆን መለኮታዊ ፈቃድ ነው፡፡ እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ይህን ባለመገንዘብ እና አንዳንዴም የአዋቂ አጥፊ በመሆን ሰዎች የወንጌልን አገልግሎት ለራሳቸው ክብር፣ መታወቂያ እና የራሳቸውን አጀንዳ ማስፈጸሚያ ሲያደርጉት ይስተዋላል፡፡ እነዚህ የወንጌል አገልግሎት እንቀፋቶች ናቸው፡፡ የሲሞንን ክፉ ግብር እንዳንከተል ራሳችንን መጠበቅ እና እግዚአብሔር የሚከብርበትን አገልግሎት ለመፈጸም መትጋት አለብን፡፡ (የሐዋ/ሥራ. ፰÷፲፰-፳፬)

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች የወንጌል አገልግሎት አንገታችሁን የምትደፉበት እና የምታፍሩበት አገልግሎት አይደለም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "በወንጌል አላፍርም" እንዳለ (ሮሜ.፩÷፲፮) እናንተም ላላመኑና ላልተጠመቁ ሰዎች ሳታፍሩ እና ሳትሸማቀቁ ሃይማኖታችሁን ስበኩ፣ እውነትን መስክሩ፣ የምሥራቹን ወንጌል ተናገሩ፡፡ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ትጉ፤ ነፍሳትን ለክርስቶስ ማርኩ፡፡ ይህን በማድረጋችሁ እግዚአብሔር አገልጋዮቹን በባረከበት በረከት ይባርካችኋል፤ በአገልግሎታችሁም እግዚአብሔር ይከብራል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- ወጣቶች በዚህ ዘመን ነፍሳትን እንዴት ለክርስቶስ መማረክ እንደሚችሉ እና ወንጌልን መስበክ ሥራቸው እንዲያደርጉት መምህሩ ያወያያቸው፡፡

# ግብረ ሰዶማዊነት

## ሃያ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምርቱ ዓላማ**፡- ወጣቶች እግዚአብሔር ግብረ ሰዶማዊነትን እንደማይፈቅድ እና እንደሚጸየፍ አውቀው ከዚህ ክፉ ግብር ራሳቸውን ይጠብቃሉ፤ ለሌሎችም ያስረዳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ**፡- "ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ" ሮሜ. ፩÷፳፪

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- ዘፍ. ፲፱÷፩-፪፣ ሮሜ. ፩÷ ፲፰-፴፪

- ❖ አባ ሳሙኤል ሰዶማውያንና የኃጢአት ደሞዝ ፲፱፻፺፰(1998) ዓ.ም አዲስ አበባ፡፡
- ❖ መምህሩ ወጣቶች በጉዳዩ በቂ መረጃ የሚያገኙባቸውን ምንጮች ይጠቀሚቸው፡፡

### መግቢያ፡-

- ❖ ወጣቶች ስለ ሰዶማዊነት (Homosexuality) ምን ያህል ታውቃላችሁ?
- ❖ ወንድ ለወንድ እና ሴት ለሴት ጋብቻን የፈቀዱ ሀገራት እነማን ናቸው?
- ❖ ራሳችሁን ከዚህ ክፉ ግብር እንዴት ትጠብቃላችሁ?

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

በዚህ ዘመን ግብረ ሰዶማዊነት እንደ ጥሩ ነገር እየታየ በመምጣቱ ጠዋትና ማታ በተለያዩ ማስ ሚዲያዎች፣ ድረ ገጾች፣ ፊልሞች፣ ጋዜጦች እና መጽሔቶች ይቀነቀናል፤ ይሰበካልም፡፡ አንዳንዶችም ከሰው ልጅ ሥልጣኔ ጋር አብሮ የመጣ አድርገው ሲመለከቱት እና ሲያናፍሱት እናስተውላለን፡፡ በሰለጠነው ዓለም በወንድና በወንድ መካከል ያለው የግብረ ሰዶማዊ ግንኙነት (Gays) በሴትና በሴት መካከል ያለው የግብረ ሰዶማዊ ግንኙነት (Lesbians) እንደ ጥሩ ነገር እየታየ መምጣቱ ብቻ ሳይሆን ሕጋዊነት እያገኘ መጥቷል፡፡

www.zeorthodox.org

በርካታ ሀገሮች የወንድ ለወንድ እና የሴት ለሴት ጋብቻን ከፈቀዱ ሰንብተዋል፤ በሒደት ላይ ያሉም ብዙ ናቸው፡፡ በአሜሪካና በአውሮፓ የሚገኙ አንዳንድ የእምነት ተቋማትም ከመሪዎቻቸው

ጀምሮ በዚህ ግብረ ሰዶማዊ ግብር ስለቆሸሹ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ግብረ ሰዶማዊነትን ደግፈው ሲሰብኩ እንዲሁም ወንድ ለወንድ ሲያጋቡ ታዝበናል፡፡ ይህ አስደንጋጭ እና አሳፋሪ ክስተት ብዙዎቻችንን ሊያስደነግጠን ቢችልም መጽሐፍ ቅዱስ ግብረ ሰዶማዊነት ዛሬ የተጀመረ ክፉ ግብር ሳይሆን ጥንትም የነበረ ብዙዎችን ያረከሰ ነውር እና አስጸያፊ ተግባር መሆኑን ይመሰክራል፡፡

## 1. ግብረ ሰዶማዊነት በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን፡-

**መጽሐፍ ቅዱስ፡-** የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ መጽሐፍ በሆነው በኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ስለ ግብረ ሰዶማዊነት ይናገራል፡፡ የሰዶምና የገሞራ ሰዎች ግብረ ሰዶማውያን ነበሩ፡፡ ሰዶምና ገሞራ በዮርዳኖስ ሸለቆ የተቆረቆሩ ከተሞች ነበሩ፡፡ በእነዚህ ሁለት ከተሞች ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ግብረ ሰዶማውያን ማለትም ወንድ ከወንድ፣ ሴት ከሴት ጋር ዝሙት የሚያደርጉ ይህ ኃጢአትም በእነርሱ ይበዛ ስለነበር ስያሜው የቦታውን ስም በመያዝ ግብረ ሰዶም ተባለ፡፡ በዘመናት ሁሉ ይህን ኃጢአት የሚሠሩ መጠሪያ ሆኖ አገለገለ፡፡ ዛሬም በግብር የሚመስሉአቸው ሰዎች ግብረ ሰዶማዊ ወይም ሰዶማውያን እየተባሉ ይጠሩበታል፡፡

የሰዶምና የገሞራ ሰዎች ወንድ ከወንድ፣ ሴት ከሴት ጋር የሚፈጽሙት ዝሙት አጸያፊ ስለነበር እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው ወሰነ፡፡ (ዘፍ. ፲፰÷፳፣ ዘፍ.፲፱÷፭-፱)፡፡ ሁለት መላእክትን ወደ ሰዶም ላከ፡፡ ሁለቱ መላእክት የእግዚአብሔር ሰው እና ከሰዶማዊነት ግብር ንጹሕ የነበረውን ሎጥን ከከተማው እንዲወጡ ካደረጉ በኋላ እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን በእሳትና በዲን አጠፋ፡፡ (ዘፍ.፲፱÷፲-፳፮) ሰዶምና ገሞራ አሁን በጨው ባሕር እንደተሸፈኑ የሥነ-ምድር ተመራማሪዎች ይናገራሉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ሰዶምና ገሞራ የክፋት ሁሉ የፍርድም ምሳሌ በመሆን ተጠቅሰዋል፡፡ (ኢሳ. ፩÷፱-፲፣ ኢሳ. ፫÷፱፣ ኤር. ፳፫÷፲፬፣ ሰ.ኤ.፬÷፮፡፣ ሕዝ. ፲፮-፵፮፣ ማቴ.፲÷፲፭፣ ራዕ. ፲፩÷፰)

### 1.1. ሰዶማዊነት ነውር ነው፡-

መጽሐፍ ቅዱስ ግብረ ሰዶማዊነት ነውር እና አጸያፊ እንደሆነ ይመሰክራል፡፡ ነውር የሆነበትም ምክንያት ይህ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ሀ. እግዚአብሔር የመሠረተውን የጋብቻ ሥርዓት ማለትም አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት የሚለውን ሕግ የሚያፈርስ በመሆኑ፤

ለ. በሁለት ተቃራኒ ጾታ ማለትም በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚደረገውን ተፈጥሮአዊ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያቆሽሽ አዲስ ልምድ ስለሆነ፤

ሐ. የሰው ልጅ ዘሩን የመተካት ከፊጣሪ የተሰጠውን መብቱን የሚገፋ (የሚያሳጣ) ተግባር በመሆኑ፤

መ. ሰዶማዊነት በአንድ ወንድ ወይም በአንዲት ሴት ብቻ የሚቆም ግብር ስላልሆነ፤ ወንዱ ብዙ ወንዶችን ሴቷ ብዙ ሴቶችን ሲለምዱ ለተለያዩ በሽታዎች ስለሚያጋልጥ፤

ሠ. ሰዎች ስለ ፍቅር ትክክለኛ ሥዕል እንዳይኖራቸው እና በስሜት የሚነዱ ራስ ወዳዶች እና ሓላፊነት የማይሰማቸው ዜጎችን ስለሚፈጥር፤

ረ. የተለያዩ አካላዊ፣ ሥነ ልቡናዊ እና መንፈሳዊ ክስተቶችን ስለሚያስከትል በእግዚአብሔር የተናቀ እንዲሁም የተጠላ ግብር ነው፡፡ ከተፈጥሮ ሥርዓትና ሕግ ውጪ በመሆኑ በኅብረተሰቡም ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ማኅበራዊ መገለልን የሚያስከትል ክፉ ተግባር ነው፡፡ ይህ ክፉ ግብር ወንድ ከወንድ ሴት ከሴት ጋር ብቻ ሳይሆን ከእንስሳትም ጋር ግንኙነት እንዲፈጽሙ በር የሚከፍት ነውረኛ ሕይወት ነው፡፡

"ማናቸውም ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ጸያፍ ነገር አድርገዋል፤ ፈጽመው ይገደሉ፤ ደማቸው በላያቸው ነው፡፡" (ዘሌ. ፳፥፲፫)

"የሰዶም ሰዎች ግን ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኃጢአተኞች ነበሩ፡፡" (ዘፍ. ፲፫፥፲፫)

"እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸው የነበሩ ከተማዎችም በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል፡፡" (ይሁዳ. ቁ. ፯)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በሮሜና በቆሮንቶስ መልእክቱ ግብረ ሰዶማዊነትን "አስነዋሪ"፣ "ለባሕርይ የማይገባ"፣ እንዲሁም "ከተፈጥሮ ሕግና ሥርዓት ውጪ" እንደሆነ አጽንኦት ሰጥቶ ያስተምራል፡፡ በዚህ ሰዶማዊ ግብር ኃጢአት የሠሩት ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችም እንደሆኑ ይናገራል፡፡

" . . . ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርድ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኵስነት አሳልፎ ሰጣቸው . . ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶች መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ፡፡" (ሮሜ. ፩፥፳፬-፳፯)

www.zeorthodox.org

". . . ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣኦትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚያደርጉ . . . የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡፡" (ቆሮ. ፮፥፱-፲)

ወጣቶች "ቀላጭ" ማለት ወንዳገረድ ለጾታው የማይገባ ዝሙትን ለመፈጸም እንደ ሴት ሆኖና ከወንድ ዘርን የሚቀበል ማለት ነው፡፡ እንደዚሁም ሴት ከወንዳ ወንድ ሴት ጋር ዝሙት ስትፈጽም ‹‹ቀላጭ›› ትባላለች፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች ግብረ ሰዶማዊነት በእግዚአብሔር የተጠላ ክፉ ግብር መሆኑን ተገንዝባችሁ ራሳችሁን ከዚህ ክፉ ተግባር ጠብቁ፡፡ ብዙ ንጹሐን ሰዎች በእነዚህ ክፉ ሰዎች እንዳይበላሹና ሰዶማውያን እንዳይሆኑ እውነታውን ማስተማር ግንዛቤ መፍጠር የሁላችሁም ሓላፊነት መሆኑን አትዘንጉ፡፡

## ተግባር፡-

- መምህሩ ወጣቶች ግብረ ሰዶማዊነት የሚያስከትለውን አካላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነ-ልቡናዊና መንፈሳዊ ቀውስ እንዲወያዩበት ግንዛቤያቸውንም እንዲያሰፉ ያድርጓቸው፡፡
- በግብረ ሰዶማውያን ክፉ ሥራ ላይ ጥልቅ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ሰዎችን በመጋበዝ ወጣቶች ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ በመስጠት ወጣቶች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሱሰኝነት

## ሃያ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ራሳቸውን ከተለያዩ ሱሶች እንዲጠብቁ የሚያስችላቸውን በቂ ዕውቀት ጨብጠው ለሌሎችም ያስረዳሉ፤ ራሳቸውንም ይጠብቃሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም" ፩ ቆሮ. ፮÷፲፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

- ☒ መምህሩ ወጣቶች ስለ ተለያዩ ሱሶች ምንነት እንዲሁም የሚያስከትሉትን ጉዳት በጥልቀት እንዲረዱ በጉዳዩ ዙሪያ የተጻፉ መጻሕፍትን እንዲያነቡ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

### መግቢያ፡-

- ☒ ወጣቶች ሱስ የሚያሲዙ ነገሮች ምንድን ናቸው?
- ☒ ሰዎች እንዴት ሱሰኛ ይሆናሉ?
- ☒ ለተለያዩ ሱሶች ተገዢ የሆኑ ሰዎች የሚያሳዩአቸው ጠባያት ምን ምን ናቸው?

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

አንድ ሰው ራሱን የመግዛትና የመቆጣጠር አቅሙን ሲያጣ ለተለያዩ ደባል ልማዶች መገዛት ይጀምራል፡፡ ያለእነዚህ ነገሮች መኖር አልችልም የሚል አመለካከት ሲያዳብር ሱሰኛ ሆኗል ይባላል፡፡ ብዙ ሰዎችን የሱስ ተገዢ ከሚያደርጉ ነገሮች መካከል አልኮል መጠጥ፣ አደንዛዥ ዕፆች፣ ጫት፣ ሲጋራ፣ ቡና፣ ሻይ . . . ወዘተ ይገኙበታል፡፡

www.zeorthodox.org

እነዚህ ከላይ በዝርዝር የተመለከትናቸው አንድን ሰው ለሱስ ተገዢ የማድረግ አቅማቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ አልኮል መጠጥ፣ እንደ ሐሺሽ፣ ጫት፣ ሲጋራ ያሉ አደንዛዥ ዕፆች አጥብቀን ልንርቃቸው የሚገባ በጤናችን፣ በአእምሮአችን (ሥነ ልቦና)፣ በገንዘባችን፣ በሥራና ትምህርት ጊዜያችን፣ በማኅበራዊ ግንኙታችን ወዘተ ላይ ክፉ ጉዳት የሚያስከትሉ ሱስ አስያዥ ነገሮች ናቸው፡፡ እንደ ቡና፣ ሻይ የመሳሰሉት ደግሞ በመጠኑ ራሳችንን በመቆጣጠርና በመግዛት ካልተጠቀምናቸው

የማንወጣው የሱሰኝነት ሕይወት ውስጥ ቀስ በቀስ ይከቱናል፡፡ ለምሳሌ ቡና እና ሻይ መጠጣት በሀገራችን የተለመደ ነገር ነው፡፡ በሃይማኖታችንም የተከለከሉ ነገሮች አይደሉም፡፡ ነገር ግን የእነርሱ ተገዢ ሱሰኛ ካደረጉን ግን ችግሩ እዚህ ላይ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ቡና ካልጠጡ ያማቸዋል፣ ይጨናነቃሉ፣ ሥራቸውንም በአግባቡ አይሠሩም፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም የነፍሳቸውን ስንቅ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይሰንቁ፣ በጾም ጊዜ እንዳይጾሙና ለጸሎት እንዳይተጉ የቡና፣የሻይ ሱሰኛ መሆናቸው እንቅፋት ይሆንባቸዋል፡፡

## 1. ሰዎች ሱሰኛ የሚሆኑባቸው ምክንያቶች፡-

ሰዎች ለተለያዩ ሱሶች ተገዢ የሚሆኑባቸው በርካታ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን በዛሬው ትምህርታችን ጥቂቶቹን ለማየት እንሞክራለን፡፡

1.1. የባዶነት፣ የብቸኝነት ስሜት
1.2. የግንዛቤ እጥረት
1.3. ከችግር ለመሸሽ
1.4. ከጭንቀት ለመራቅ
1.5. በጓደኞቻችን ተጽእኖ
1.6. መጠጥና አደንዛዥ ዕፆችን እንደመዝናኛ መቁጠር . . . ወዘተ

## 2. ሱሰኝነት የሚያስከትላቸው ችግሮች፡-

ብዙ ሰዎች መጠጥን፣ ሲጋራን፣ ጫትና አደንዛዥ ዕፆችን የጀመሩት ለመዝናናት በሚል እሳቤ ነበር፡፡ ነገር ግን ቀስ በቀስ የሱስ ተገዢ ከመሆን አልፈው ሱሰኝነት የሚያመጣቸውን በርካታ ችግሮችን መቀበል ግድ ሆኖባቸዋል፡፡ ሱሰኝነት ከሚያስከትላቸው በርካታ ቀውሶች እና ችግሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

2.1. ለሱሰኝነት የሚያጋልጡት እንደ አልኮል መጠጥ፣ አደንዛዥ ዕፆች፣ ጫት፣ ሲጋራ የመሳሰሉትን ነገሮች ለመጠቀም ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ ይጠይቃሉ፡፡ በርካታ ገንዘብ ሱሰኛ ለሆንበት ነገር ስለሚባክን ለኢኮኖሚያዊ ቀውስ የመጋለጥ ዕድላችን ሰፊ ነው፡፡
2.2. ሱሰኝነት ለሥራና ለልማት የሚኖረንን ተነሳሽነት፣ ፍላጎትና ቅልጥፍና ይቀንሳል፡፡
2.3. በሕብረተሰቡ ዘንድ አለመታመንን እና ንቀትን ያስከትላል፡፡
2.4. ቀድሞ የነበረንን ጥሩ ስምና ሰብእናችንን ያበላሻል፡፡

www.zeorthodox.org

2.5. ለተለያዩ በሽታዎች እንደ ጉበት፣ ኩላሊት፣ ሳንባ፣ ካንሰር . . .ወዘተ በሽታዎች ከማጋለጡም በላይ ለአእምሮ መታወክ፣ የማስታወስ ችሎታ መቀነስና ለዓይነ ስውርነት ወዘተ መጥፋት ምክንያት ይሆናል፡፡

2.6. ከሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ፌዘኛና ለቁም ነገር የማንበቃ ያደርገናል፡፡

2.7. ለትዳራችን መፈታት፣ ለልጆቻችን መበታተን ምክንያት ይሆናል፡፡ እንዲሁም ለቤተሰብ ያለን ፍቅር እንዲቀዘቅዝ ያደርጋል፡፡ ለተለያዩ የወንጀልና ሕገ ወጥ ሥራዎች ያጋልጠናል፡፡

2.8. በራሳችን የመተማመን ስሜታችንን ይቀንሳል፡፡ በማኅበራዊ ግንኙነታችን መገለልን ያስከትላል፡፡

2.9. በመንፈሳዊ ሕይወታችን ክስረትን ያመጣል፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች ከዚህ ትምህርት ሰዎች እንዴት ወደ ሱሰኝነት ሕይወት እንደሚገቡና ሱሰኝነት በአንድ ሰው ሕይወት ላይ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነልቡናዊ፣ አካላዊና መንፈሳዊ ችግሮችን እንደሚያስከትል ተምራችኋል፡፡ በተለይም ሱሰኝነት የእግዚአብሔርን መንግሥት እና ዘላለማዊ ሕይወትን የሚያሳጣን የኃጢአት ባሪያ የሚያደርገን ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ ለቤዛ ቀን የታተምንበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዳናሳዝንና የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆነውን ሰውነታችን እንዳናቆሽሽ ከሱሰኝነት ሕይወት ልንርቅ ይገባል፡፡

## ተግባር፡-

- ☒ ሱሰኝነት እንዴት የጤና ቀውስ እንደሚያስከትል አንድ የሕክምና ባለሙያ በመምህሩ አማካኝት ተጋብዞ ለወጣቶች ገለፃ ያድርግላቸው፡፡
- ☒ መምህር ከዚህ በፊት በተለያዩ ሱሶች ተይዘው የነበሩ እና ከዚያ ሱስ የተላቀቁ ወጣቶችን በመጋበዝ ልምዳቸውን ለጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ ያደርጓቸው፡፡
- ☒ ወጣቶች ራሳቸውን እና ሌሎችን እንዴት ከተለያዩ ሱሶች እንደሚጠብቁ ያወያዩአቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የሐዋርያት ሥራ

## ሠላሳኛ ሳምንት

**የትምህርት ዓላማ፡-** ወጣቶች ከትምህርቱ በኋላ፤ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ዓላማ በጥልቀት ተረድተው የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጥንካሬ በመገንዘብ ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትበላላችሁ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ፡፡" የሐዋ/ሥራ ፩÷፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

- የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ
- የሐዋርያት ሥራ የትርጓሜ መጽሐፍ

## መግቢያ፡-

የሐዋርያት ሥራ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት በኋላ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮም እስከገባበት ጊዜ ያለውን የመጀመሪያይቱን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚናገር መጽሐፍ ነው፡፡ ስለሆነም የሐዲስ ኪዳን የታሪክ መጽሐፍ በመባል ይታወቃል (ይጠራል)፡፡ ይህ የሐዲስ ኪዳን የታሪክ መጽሐፍ ከ፴፬/34/ ዓ.ም እስከ ፷፬/64/ ዓ.ም ያለውን የሠላሳ ዓመት የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ይተርካል፡፡ የቤተ ክርስቲያንን አመሠራረት፣ መስፋፋትና የሐዋርያትን አገልግሎትም ይገልጣል፡፡ ጠለ ምሕረት (የሐዋርያት ሥራ) ጸሓፊ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ነው፡፡ ሉቃስ ወንጌሉን ቴዎፍሎስ ለሚባል ሰው እንደተጻፈ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍንም ለዚሁ ሰው ደግሞ ጽፏል፡፡ (የሐዋ ሥራ ፩÷፩-፲፪) የሐዋርያት ሥራን ሉቃስ በግሪክ ቋንቋ በሮም ሀገር በ፷፬/64/ ዓ.ም መጨረሻ ወይም በ፷፭/65/ ዓ.ም መጀመሪያ እንደጻፈውይታመናል፡፡

www.zeorthodox.org

# የሳምንቱ ትምህርት፡-

## 1. የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ዓላማ፡-

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ዓላማ የክርስቶስ ወንጌል በሐዋርያት አማካኝነት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በቅርብና በሩቅ ባሉ ሃገሮች እንዴት እንደተሰበከ እና ክርስትና እንዴት እንደተስፋፋ መግለጥ ነው።

## 2. የሐዋርያት ሥራ አጠቃላይ ይዘት፡-

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የሐዲስ ኪዳን የታሪክ መጽሐፍ እንደመሆኑ ሐዋርያት በሀገሩ እየተዘዋወሩ፣ ወንጌልን እየሰበኩ እና ተአምራትን እያደረጉ ብዙዎችን ለክርስቶስ እንደማረኩ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው።

በተለይ ሐዋርያት በየሀገሩ ያስተማሯቸው ትምህርቶች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተመዝግበው ይገኛሉ። እነርሱም፡-

ሀ. በበዓለ ሃምሳ ዕለት ቅዱስ ጴጥሮስ የሰጠው ትምህርት። (የሐዋ/ሥራ ፪÷፲፬-፴፮)

ለ. ቅዱስ ጴጥሮስ በመቅደስ ከሽባው መፈወስ በኋላ የሰጠው ትምህርት (የሐዋ/ሥራ ፫÷፲፩-፳፮)

ሐ. እስጢፋኖስ የሰጠው ሰፊ ትምህርት (የሐዋ/ሥራ ፯÷፩-፶፫) ቅዱስ ጳውሎስ በምኩራብ ውስጥ ያስተማረው ትምህርት። (የሐዋ/ሥራ ፲፫÷፲፮-፵፩)

ሠ. ቅዱስ ጳውሎስ በአቴና ውስጥ በአርዮስፋጎስ አደባባይ ቆሞ ያስተማረው ትምህርት (የሐዋ/ሥራ ፲፯÷፳፪-፴፩)

ረ. ቅዱስ ጳውሎስ በማሉጢን ለኤፌሶን ሽማግሌዎች (ቀሳውስት) የሰጠው ትምህርት (የሐዋ/ሥራ ፳÷፲፯-፴፭)

## 3. የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ አከፋፈል፡-

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሃያ ስምንት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን መጽሐፉ በሦስት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል።

www.zeorthodox.org

### 3.1. መግቢያ፡-

የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አንድ ከቁጥር አንድ እስከ ዐሥራ ዐራት ያለው ክፍል የመጽሐፉ መግቢያ ነው። ይህም የመጽሐፉ ጸሐፊ ቅዱስ ሉቃስ መጀመሪያ ለቴዎፍሎስ ከጻፈለት ወንጌል ቀጥሎ ይህን የሐዋርያት ሥራን እንደጻፈለት፣ ሐዋርያት ጌታን በዐይናቸው እያዩት እንዳረገና ዓሥራ አንዱ ሐዋርያት ከእመቤታችን ጋር ለጸሎት ይተጉ እንደነበር ይተርካል።

### 3.2. የሐዋርያት ምስክርነት በኢየሩሳሌም፤ (የሐዋ.ሥራ ፩-፰)፡-

በእነዚህ ስምንት ምዕራፎች ውስጥ ሐዋርያት በአስቆሮቱ ይሁዳ ምትክ ማትያስን እንደመረጡ፤ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የወረደላቸው ዕለት ቅዱስ ጴጥሮስ በሰጠው ምስክርነት ሦስት ሺሕ ሰዎች እንዳመኑ፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ ከዐርባ ዓመት በላይ ሽባ ሆኖ ይኖር የነበረውን ሰው በመፈወሳቸው አምስት ሺሕ ሰዎች እንዳመኑ፤ የመጀመሪያይቱ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የኅብረት አኗኗር፤ ሐዋርያት በአንድነት መከራ እየተቀበሉ በኢየሩሳሌም እንደሰበኩና የሰባቱን ዲያቆናት ምርጫና የእስጢፋኖስን እና የፊልጶስን አገልግሎት ይዘረዝራል።

### 3.3. የሐዋርያት ምስክርነት በይሁዳና በሰማርያ፤ (የሐዋ/ሥራ ፰-፲፪)፡-

በእስጢፋኖስ ሞት የተበተኑ ክርስቲያኖች ክርስትናን በይሁዳና በሰማርያ እንዳስፋፉ፤ የሳሙኤልን መጠራት ጴጥሮስ በልዳ፣ በኢዮኤልና በቂሳርያ ወንጌልን እንዳገለገሉ፤ ስለ አንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መመሥረትና ማደግ፤ ሄሮድስ ሐዋርያው ያዕቆብን እንዳስገደለው እና ጴጥሮስን እንዳሰረው ይናገራል።

### 3.4. የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞ፤(የሐዋ/ሥራ. ፲፫-፳፰)፡-

እነዚህ ምዕራፎች ሐዋርያው ጳውሎስ በአንደኛ ሐዋርያዊ ጉዞው የሠራቸውን ሥራዎች፤ በኢየሩሳሌም የተደረገውን የሐዋርያት ጉባኤ፤ የጳውሎስን ሁለተኛውን ሐዋርያዊ ጉዞ፤ የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን ሦስተኛውን ሐዋርያዊ ጉዞ፤ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ከተያዘ በኋላ በቂሳርያ ሁለት ዓመት እንደታሰረ በኋላም ይግባኝ በጠየቀው መሠረት ወደ ሮም እንደተወሰደ፤ በሮም በነጻነት ክርስቶስን እንደሰበከ ይተርካል።

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች የሐዋርያት ሥራን ቅዱስ ሉቃስ እንደጻፈው፣ የመጀመሪያውን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሕይወት እና አገልግሎት ምን እንደሚመስል ተምራችኋል። እናንተም እንደ አባቶቻችሁ ቅዱሳን ሐዋርያት በእምነታችሁ ለመጽናት በዚህ ዘመን የክርስቶስ ምስክሮች ሆናችሁ በእግዚአብሔር የተወደደውን አገልግሎት እያገለገላችሁ ነፍሳትን ለክርስቶስ ማርኩ።

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- ወጣቶች የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን በጥልቀት እንዲያነቡና መልእክቱን እንዲረዱ በመምህሩ እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- ወጣቶች መጽሐፍን ካነበቡ በኋላ ትርጓሜውንም ጨምረው የሚያነቡበት ዕድል እንዲፈጠር፣ ጥያቄዎቻቸው እንዲመለሱላቸውና ቅዱሳት መጻሕፍትን የመመርመር ፍላጎታቸውን እንዲጨምር መምህሩ የተቻላቸውን ሁሉ ያድርጉላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ክርስቲያን እና መገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ)

## ሠላሳ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ሚዲያ በስብእናቸው ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ መሆኑን ተረድተው በአግባቡ እንዲጠቀሙበት መርዳት ነው፡፡

**በቃልና የሚጠና ቅጥስ፡-** "ሁሉ ተፈቅዶልናል፤ ሁሉ ግን አይጠቅምም" ፩ ቆሮ ፮÷፲፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ቆሮ ፮÷፲፪-፲፰፣ ፪ ቆሮ. ፮÷፲፬-፲፮

### መግቢያ፡-

- ወጣቶች ስለ ሚዲያ (መገናኛ ብዙኃን) ያላችሁ ግንዛቤና የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም ባህላችሁ ምን ይመስላል?
- መገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ) በሕይወታችሁ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ? መልሳችሁ አዎን ከሆነ እንዴት?

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሰው ልጅ የፈጠራ ችሎታ ጎልቶ የወጣበት ምድራችን በተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከመቼውም ጊዜ በላይ መጠቀም የቻለችበት ዘመን ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ብዙኃኑ የዓለማችን ኅብረተሰብ በእነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እየተገለገለም ይገኛል፡፡ የዘመኑን ቴክኖሎጂ በመጠቀም መረጃዎችን ማግኘት፣ መለዋወጥና ሕይወትን በቀላሉ መምራትም ተችሏል፡፡ በዚህም የተነሣ ዓለማችን በፈጣን የለውጥ ጉዞ ላይ ስትሆን የሰው ልጅ ፈጠራ የሆኑትን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በማስተዋወቅ እና መረጃዎችን በፍጥነት ለማኅበረሰቡ በማድረስ ትልቁን ሚና እየተጫወተ ያለው ደግሞ መገናኛ ብዙኃን (ማስሚዲያ) ነው፡፡ መገናኛ ብዙኅን (ማስ ሚዲያ) በአንድ ጊዜ በተለያዩ ቦታዎችና በስፋት የሚገኘውን ብዙኃኑን ሕዝብ የመድረስ እና የማገናኘት አቅም ያለው ዘዴ እና መሣሪያ ነው፡፡ ድረ ገጾች፣ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ጋዜጣ መጽሔት፣ መጽሐፍ፣ ፊልም ወዘተ የሚያጠቃልል እና በብዙ መረጃዎች የበለጸገ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ዓለማችን እና በውስጧ የሚኖሩ የሰው ልጆች በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን (ማስ ሚዲያ) ተጽዕኖ ሥር መሆናቸው ከማናችንም ያልተሰወረ ሐቅ ነው፡፡ ክርስቲያኖች የተለያዩ ሚዲያ መጠቀማችን ወይም እነዚህ ሚዲያ እቤታችን በመገኘታቸው በራሱ ችግር የለውም፤ ስሕተትም አይደለም፡፡ ክርስቲያኖች ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ ያለባቸው በእነዚህ መገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ) የሚተላለፉትን የተለያዩ መረጃዎች መርጠው መጠቀም መቻላቸው ላይ ነው፡፡ ክርስቲያኖች የሚሰሙትን፣ የሚያነቡትንና የሚያዩትን መምረጥ መቻል አለባቸው፡፡

በተለይ በክርስትና ሕይወታቸው ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖ ተገንዝበው ጤናማ እና በሥነ ምግባር በታነጸ ሰብእና የመገናኛ ብዙኃን ውጤቶችን (ሚዲያ)ን መጠቀም አለባቸው፡፡

## 1. የመገናኛ ብዙኃን (ማስ ሚዲያ) ተጽዕኖዎች (The Influences of Media)

መገናኛ ብዙኃን (ማስ ሚዲያ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሰብእናችን እና በዘወትር እንቅስቃሴያችን ላይ በጎም ይሁን ክፉ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሲሆን ጥቂቶቹን በዚህ ትምህርት ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡

### 1.1. መንፈሳዊ ሕይወትን ይረብሻል

በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን (ማስ ሚዲያ) የሚተላለፉ መረጃዎችን ወጣቶች እንደወረደ በቀጥታ የሚቀበሉ ከሆነና መርጦ አጣርቶ የመጠቀም ባህል ከሌላቸው መንፈሳዊ ሕይወታቸው ይረበሻል፡፡ ወጣቶች የተለያዩ ቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ድራማ፣ ፊልም፣ ስፖርት . . . . ወዘተ አዘውትረው ሊመለከቱ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ሙሉ ጊዜያቸውን በዚያ ላይ የሚያውሉ ከሆነ የትምህርት፣ የጥናት፣ የሥራ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ወዘተ ውድና ወርቃማ ጊዜያቸው በእነዚህ ፕሮግራሞች ይባክናል፡፡ ስለዚህ ወጣቶች ለትምህርት፣ ለጥናት፣ ለሥራ፣ ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው፣ ለጓደኞቻቸው እና ለቤተሰባቸው የሚሰጡት ጊዜ እየቀነሰና እየተወሰደ አጠቃላይ እንቅስቃሴያቸው የተረበሸ ይሆናል፡፡ በተለይም በመገናኛ ብዙኃን (በማስ ሚዲያ) በአብዛኛው የሚተላለፉት ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የሚጣላ አስተምህሮን የሚያራምዱ፣ ከመልካም ሥነ-ምግባር የሚቃረኑ ድርጊቶችን እንደጥሩ ነገር የሚሰብኩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ወጣቶች በእነዚህ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር በሚቃረኑ እና ኢ-ክርስቲያናዊ በሆኑ ፍልስፍናዎች የመመሰጥ ዝንባሌ ስለሚያድርባቸው የነበራቸውን በጎ ነገር ሳያውቁት እየተነጠቁ ይመጣሉ፡፡ እምነታቸውም ቀስ በቀስ ይሸረሸራል፡፡

www.zeorthodox.org

### 1.2. ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ቀውሶችን ያመጣል፡፡

ዕለት ዕለት በምናያቸው እና በምንሰማቸው አዳዲስ የአኗኗር ዘይቤዎች ለማኅበራዊ ሕይወት የነበረን በጎ ነገር እያደር እየተሸረሸረ ስለሚሄድ ከዚህ በፊት ያልተለመዱ ነገሮችን ከመልካም ባህልና ሥነ ምግባር እንዲሁም ከክርስቲያናዊ እምነትና ሥርዓት ጋር የሚጋጭ ነገር ስንናገር ስንሠራ እንገኛለን፡፡ የሌሎችን በሥልጣኔና በዘመናዊነት ሽፋን በተለይም በምዕራቡ ዓለም ባህል ሳናውቀው በሚዲያ አማካኝነት ስለምንላበስ የራሳችንን መልካም ባህል እና ማንነት አውልቀን እንጥላለን፡፡ ለሀገራዊ ፍቅር ያለው ስሜት መሳሳት፣ ለትዳር ያለው መልካም አመለካከት እየተለወጠ መምጣት፣ የተለያዩ አደንዛዥ ዕፆችን እና የአልኮል መጠጦችን ማዘውተር፣ ከመንፈሳዊ ሥርዓትና ከመልካም ባህል ውጪ እያፈነገጠ የመጣ የጠባይ፣ የአኗኗር ሁኔታ፣ አለባበሳችን መቀየሩና የተደበላለቀ ቋንቋ መናገራችን ሚዲያው የፈጠረብን ተጽዕኖ ነው፡፡

በተለይ በቴሌቪዥን መስኮት የምንመለከታቸው የጦርነት፣ የተለያዩ ወንጀሎች፣ የዝሙት፣ የዘፈንና የዳንኪራ ፊልሞች በማንነታችን ላይ የሚያሳድሩት ሥነ ልቡናዊ ተጽዕኖ ጉዳት ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአብዛኛው በልጆች እና በወጣቶች የሚፈጸሙ ከመልካም ሥነ-ምግባር ያፈነገጡ ድርጊቶች እና ወንጀሎች መንሥኤያቸው ዘወትር ከሚመለከቷቸው ልዩ ልዩ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችና ፊልሞች እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡ ስለዚህ ወላጆች ለልጆች የሚመለከቱትን የቴሌቪዥን ፕሮግራም፣ የሚያነቡትን መጽሐፍና የሚጠቀሙትን ድረ ገጽ ሊመርጡላቸው፣ ሊከታተሉአቸው እና የመገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ) ውጤቶች አጠቃቀም ሥነ-ምግባር ሊያስተምሯቸው ይገባል፡፡

## 2. የመገናኛ ብዙኃን ተጽዕኖዎችን እንዴት ማሸነፍ ይቻላል?

በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉትን ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ተግባራት መቆጣጠርና ማስቆም ባይቻለንም ራሳችንን ከእነዚህ ክፉ ተግባራት መካከል እንዲሁም በእምነት ጸንተን ክፉውን በመቃወም ከሞት አስተምህሮ መጠበቅ ግን እንችላለን፡፡ የሚዲያን ተጽዕኖዎች ከምንከላከልባቸው መንገዶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

www.zoorthodox.org

### 2.1. በመንፈሳዊ ሕይወት መርካት፣

ጠቢቡ ሰሎሞን "የጠገበች ነፍስ የማር ወለላ ትረግጣለች ለተራበች ነፍስ ግን የመረረ ነገር ሁሉ ይጣፍጣታል" ምሳሌ. ፳፯፥፯ ይላል፡፡ ወጣቶች ሕይወታችሁ ወይም ነፍሳችሁ የመንፈሳዊ ነገሮች ራብተኛ ከሆነች በመገናኛ ብዙኃን(ሚዲያ) የሚተላለፉ መራራ የኃጢአት ትዕይንቶች ሁሉ

ይጣፍጡአታል፡፡ ነፍሳችን በክርስቶስ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፣ በቅዱሳን ታሪክ ፣ በዝማሬና በመንፈሳዊ አገልግሎት ከረካች ግን የመገናኛ ብዙኃኑን (የማስ ሚዲያውን) ጎጂ ተጽዕኖ በድል አድራጊነት ማሸነፍ እንችላለን፡፡

**2.2. በማንነታችን እና በባህላችን በመኲራት፡-**

ኢትዮጵያውያን እንደመሆናችን በሀገራችን፣ በሕዝባችን፣ በባህላችንና በቋንቋችን ልንኮራ እና ራሳችንን ልናከብር ይገባል፡፡ ከሌሎች ሥልጣኔን፣ ዕውቀትንና መልካም ነገሮችን እንጂ ከእኛ ማንነት እንዲሁም ባህል ጋር የሚጣረሱ ነገሮችን መውሰድ የለብንም፡፡ ስለዚህ ራሳችንን በሚገባ ልናከብር በባህላችንና በቋንቋችን በመኲራት የመገናኛ ብዙኃንን (ሚዲያ) ጎጂ ተጽዕኖን ማሸነፍ ይቻላል፡፡

**2.3. በጎ ነገሮችን ብቻ በመምረጥ፡-**

ሁለንተናችንን ለክርስቶስ ስናስገዛ እና እንደ ቃሉ መኖር ስንጀምር በጎ ኅሊና ይኖረናል፡፡ በጎ ሐሳብም ከልባችን ስለሚመነጭ በጎ መጻሕፍትን፣ ጋዜጦችን፣ ጓደኞችን . . . ወዘተ የመምረጥ ፍላጎትና ችሎታችን ጠንክሮ ከፍተኛ ዐቅም እናገኛለን፡፡ በዚህም ከመገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ) ተጽዕኖዎች ነጻ መሆን እንችላለን፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች በዚህ ትምህርት የመገናኛ ብዙኃን (ማስ ሚዲያን) በጎ ገጽታዎች እና በማንነታችን ላይ የሚፈጥሩትን አሉታዊ ተጽዕኖዎች በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ በመገናኛ ብዙኃን (ማስ ሚዲያ) የሚተላለፉትን የተለያዩ ፕሮግራሞችን እና መረጃዎችን መምረጥ የሁላችንም ሓላፊነት መሆኑን አውቃችሁ፤ መገናኛ ብዙኃን (ማስ ሚዲያን) በሥነ-ሥርዓት ለበጎ ሥራ የመጠቀም ባህልን አዳብሩ፡፡

## ተግባር፡-

- መምህሩ ወጣቶች ስለ መገናኛ ብዙኃን (ማስ ሚዲያ) እና ተዛማጅ ጉዳዮች ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያግዛቸውን መረጃ እንዲያገኙ ያድርጉ፡፡
- ወጣቶች በማስ ሚዲያ (መገናኛ ብዙኃን) ጥቅምና ጉዳት ላይ ክርክር እንዲሁም ውይይት እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ውርጃ (Abortion)

## ሠላሳ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ውርጃ ምንነት እና የሚያስከትለውን አካላዊና መንፈሳዊ ጉዳቶች አውቀው ያስረዳሉ፤ ራሳቸውንም ይጠብቃሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ ይፈሳል፡፡" ዘፍ. ፱÷፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መዝ. ፻፴፰(፻፴፱)÷፲፫-፲፬፣ ኤር. ፩÷፬-፭፣ ኢሳ.፵፬÷፳፬፣ ኢዮ. ፴፩÷፲፭

- የሞት ደወል፣ የትውልድ ድምፅ በኢትዮጵያ ፅንስና የማሕፀን ሐኪሞች ማኅበር የተዘጋጀ መጽሐፍ መስከረም ፲፱፻፺፮ ዓ.ም
- መምህሩ ስለ ውርጃ የተጻፉ መጻሕፍትን ወጣቶች እንዲያነቡ የመጻሕፍቱን ዝርዝር ይንገሯቸው፡፡

### መግቢያ፡-

- ወጣቶች ስለ ውርጃ ያላችሁን አመለካከት ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- በአካባቢያችሁ ስላሉ በውርጃ የታወቁ ባህላዊ ሐኪሞችንና ሆስፒታሎችን ለመምህራችሁና ለጓደኞቻችሁ ትዝብታችሁን አካፍሉ፡፡
- በውርጃ ጊዜ ሕይወታቸው ያለፈ ሴቶችን አስታውሱና የምታውቁት እውነተኛ ታሪክ ካለ ለክፍሉ ተናገሩ፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

www.zeorthodox.org

በአንደኛውና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከፈሰሰው የሰው ልጅ ደም በላይ ዛሬ በዓለማችን በውርጃ ምክንያት የሚፈሰው የሕፃናት ደም ምድራችንን የደም መሬት (አኬልዳማ) አድርጓታል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በዓለማችን በየዓመቱ እስከ ሃምሳ ሚሊዮን የሚደርስ ሕጋዊ ውርጃ ይካሔዳል፡፡ ሲሆን በአጠቃላይ ውርጃ በሕግ ከተፈቀደ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በውርጃ የሞቱት

ሕፃናት ቁጥር ከአንድ ቢሊዮን በላይ ይሆናል ተብሎ ይገመታል። ሆን ተብሎ የሚፈጸም ውርጃ እና በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሠት ውርጃ መጨንገፍ ተብሎ በሁለት ይከፈላል።

## 1. ሆን ተብሎ የሚፈጸም ውርጃ

የውርጃ ደጋፊዎች እና አራማጆች ዘወትር ስለ ውርጃ ጠቃሚነት በአገኙት አጋጣሚ ሲሰብኩና ተጽእኖ ሲፈጥሩ ይታያሉ። በዚህ የተነሣ በአደጉት ሀገሮች ውርጃ ሕጋዊ ሆኖ በሕገ መንግሥታቸው ከተፈቀደ ዓመታት አስቆጥሯል። እነዚህ የውርጃ ደጋፊዎች ውርጃን ከሴቶች መብት ጋር በማገናኘት የመብት ጥያቄ አድርገው ይከራከራሉ። በዚህ የተነሣ ውርጃን የሚያበረታቱ ሴቶች (I have a right over my body) ‹‹በራሴ ሰውነት ላይ መብት አለኝ›› ሲሉ ይደመጣሉ። ከዚሁ ጎን ለጎን ውርጃን የሚደግፉ ሰዎች በማሕፀን ውስጥ ያለውን ሕፃን ግማሽ ሰው (Sub-Human) እንደሆነ፣ ሕይወትም እንደሌለውና የሰው ልጅ እንዳልሆነ ያምናሉ ያስተምራሉ።

## 2. በተለያዩ ተፈጥሮአዊና ተፈጥሮአዊ ባልሆኑ ነገሮች የሚከሠት መጨንገፍ (miscarriage)

አንድ በእናቱ ማሕፀን ውስጥ ያለ ሕፃን ተፈጥሮአዊና ተፈጥሮአዊ ባልሆኑ ምክንያቶች ለማደግ የማይችልባቸው ሁኔታዎች ስለሚፈጠሩ የመጨንገፍ ዕድል ይገጥመዋል። ከማሕፀን ውጪ አንድ ሴት ስትፀንስ፣ የእናትየዋና የሕፃኑ ደም ሳይጣጣም ሲቀር፣ በተለያዩ የጤና እክሎችና ልዩ ልዩ አደጋዎች የእናትየዋ ሕይወት አስጊ ሁኔታ ላይ ሲወድቅ ፅንስ ሊጨነግፍ ይችላል። ይህ ዓይነቱ መጨንገፍ ሆን ተብሎ ታስቦበት ታቅዶ የሚደረግ ስላልሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ አያደርገንም።

## 3. በማሕፀን ውስጥ ስላለው ፅንስ ማወቅ የሚገባን እውነታ፤

በማሕፀን ውስጥ ያለው ሕፃን ፍፁም ሰው ነው። የውርጃ ደጋፊዎች እንደሚሰብኩት ሕይወት የሌለውና ግማሽ ሰውም አይደለም። በማሕፀን ውስጥ ያለው ፅንስ ሰው ካልሆነ ምንድን ነው? የሰው ልጅ ካልሆነ የማን ልጅ ነው? ሕይወትስ ከሌለው ለምን እያደገ ይሔዳል? የውርጃ አራማጆች መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች ናቸው። በሰው ሕይወት ላይ የተደረጉ በርካታ ጥናቶች እና ምርምሮች የሰው ሕይወት ከፅንስ እንደሚጀምር አረጋግጠዋል።

www.zeorthodox.org

## 4. ውርጃ የሴቶችን መብት የሚጋፋ ድርጊት ነው፡-

ከላይ እንደተመለከትነው የውርጃ ደጋፊዎች ውርጃን የሴቶች የመብት ጥያቄ አድርገው ይከራከራሉ። ነገር ገን ውርጃን ሕጋዊ ያደረጉ ሰዎች ያልተረዱት እውነት ውርጃ የሴቶች መብት የሚከብርበት ሳይሆን የሴቶችን መብት የሚጋፋ ክፉ ድርጊት መሆኑን ነው። ምክንያቱም ሴቶች በማሕበረሰቡ ዘንድ የሚከበሩት በውርጃ ሳይሆን ለዓለም፣ ለሀገር፣ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቀምና ታሪክ የሚሠራ ልጅ በመውለዳቸው ነው። ሌላው ያልተረዱት እውነት ቢኖር በማሕፀን ውስጥ ለውርጃ የሚጋለጠው ፅንስ ወንድ ብቻ ሳይሆን ሴቶች ጭምር መሆናቸውን ነው። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በውርጃ ከሚሞቱት ሕፃናት ሃምሳ በመቶውን ቁጥር የያዙት ሴቶች መሆናቸውን ነው። ታዲያ ውርጃ የሴቶች የመብት ጥያቄ ከሆነ የሴቶች መብት መከበር አለበት የሚለው ክፍል በማሕፀን ውስጥ ያለችውን ሴት ሕፃን መብቷን አያከብርም ማለት ነው?

## 5. ሴቶች ውርጃን የሚፈጽሙባቸው ምክንያቶች፤

ሆን ተብሎ ለሚፈጸም ውርጃ ዋነኛ ምክንያቶች ከሆኑት መካከል፡-

5.1. ልጅ መውለድን አለመፈለግ

5.2. ይሉኝታ

5.3. የሚመጣውን ልጅ የማሳደግ አቅም ማጣት፣ በቂ መተደደሪያ ወይመ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ አለመኖር።

5.4. ከጋብቻ ውጪ፤ ሳያገቡ ቢሚከሠት ፅንስ ወይም ከትዳር ውጪ በመማገጥ ፅንስ ሲከሠት።

5.5. ሌሎች ልዩ ልዩ ምክንያቶች

## 6. ውርጃ በሴቶች ላይ የሚያሳድራቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች፤

ውርጃ በሕፃናት ላይ ከሚያደርሰው ሰብዓዊ የመኖር መብት ጥሰት በተጨማሪ በሴቶች ላይ ሥነ ልቡናዊ፣ አካላዊና መንፈሳዊ ቀውሶችን ያስከትላል።

### 6.1. ሥነ ልቡናዊ ቀውስ

www.zeorthodox.org

አንድ ሴት ውርጃን ከፈጸመች በኋላ ትልቅ የሥነ-ልቡና ቀውስ የሚገጥማት ሲሆን ሰላማዊና የተረጋጋ ኑሮዋን ስለሚረብሸው የዕለት ተዕለት ተግባሯን በስኬት እንዳታከናውን ያደርጋታል። መረበሽ፣ ድንጋጤ፣ የኀሊና ዕረፍት ማጣት፣ የእጦትና የኃዘን ስሜት፣ ጸጸትና የጥፋተኝነት ስሜት ይፈራረቅባታል። ከእነዚህ ሥነ-ልቡናዊ ቀውሶች ለመውጣትና ላለማስታወስ ሲሉ በተለያዩ ሱሶች የሚጠመዱም አሉ።

6.2. አካላዊ ቀውስ

ውርጃን ተከትሎ አንዲት ሴት የሚደርስባት ቀውስና የጤና ችግር የከፋ ነው። ይህም መካንነት፣ የወሲብ ፍላጎት መቀነስ፣ የጡት ነቀርሳ (ካንሰር)፣ለኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ የተዛባ የወር አበባ መከሠት፣ ወቅቱን ያልጠበቀ ምጥና ወሊድ በአጠቃላይ እርግዝናን ተከትሎ ለሚመጡ የተወሳሰቡ ችግሮች የተጋለጠች ትሆናለች። ከዚህ በተጨማሪም የማሕፀን መቀደድ፣ በበሽታ መያዝ፣ ውርጃን በሚፈጽሙ ሐኪሞች (የልምድ አዋላጆች) በሚፈጠር ስሕተት የራሷን ሕይወት እስከማጣት ትደርሳለች።

6.3. መንፈሳዊ ቀውስ፡-

እግዚአብሔር የሕይወት ምንጭ ነው። ሆን ተብሎ የሚፈጸም ውርጃን እግዚአብሔር ይጸየፋል፤ በድርጊቱ ፈጻሚዎችና ተባባሪዎች ላይም ይፈርዳል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውርጃ የተከለከለ ነው ተብሎ ቃል በቃል ባይጻፍም "አትግደል" የሚለው ሕግ ውርጃንም የሚጨምር መሆኑን መረዳት ይገባል። ውርጃ በአንድ ሰብአዊ ፍጡር ላይ ከተፀነሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚወለድበት ባለው ጊዜ ውስጥ በቀጥታ ሆን ተብሎ የሚፈጸም ግድያ ነው። ስለዚህ "አትግደል" የሚለውን የእግዚአብሔር ሕግ የሚቃወም ተግባር ከመሆኑም በላይ በሌላው የመኖር ሕልውና ውስጥ ጣልቃ በመግባት የመኖር መብቱን የሚጋፋ ድርጊት ነው። ስለዚህ ሆን ብለው ውርጃን የፈፀም ሰው እና ተባባሪዎቹ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርድ ይጠብቃቸዋል። (ዘፍ. ፱÷፮)

## ማጠቃለያ፡-

በዚህ ትምህርት ሆን ተብሎ የሚፈጸምን ውርጃ እግዚአብሔር እንደማይፈቅድ እና ውርጃ የሚያስከትላቸውን የተለያዩ ቀውሶች ተምራችኋል። በተጨማሪም በውርጃ የሴቶች መብት እንደማይከብር የተገነዘባችሁበት ጥሩ አጋጣሚ ነው። ስለዚህ ወጣቶች የሰው ሕይወት ክቡር መሆኑን አውቃችሁ ውርጃን አጥብቃችሁ በመቃወም እና ራሳችሁን ከዚህ ክፉ ግብር በመጠበቅ እግዚአብሔርን በሕይወታችሁ አክብሩ።

## ተግባር፡-

www.zeorthodox.org

- ☒ መምህሩ ወጣቶች በውርጃ እና በተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤያቸውን እና የዕውቀት አድማሳቸውን እንዲያሰፉ በጉዳዩ በቂ ልምድ ያላቸውን የማሕፀን እና የፅንስ እስፔሻሊስት ገለጻ እንዲያደርጉላቸው ይጋብዙላቸው።
- ☒ ወጣቶች የውርጃን ጎጂ ተጽዕኖዎች የሚያሳየውን ቪዲዮ (Video) እንዲመለከቱ ያድርጉ።

# ከሁሉ ጋር በሰላም መኖር

## ሠላሳ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ሰላም ያላቸውን ግንዛቤ በማዳበር የግጭት አፈታት ዘዴዎችን አውቀው በክፍል ውስጥ ያስረዳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከሰው ሁሉ ጋር ሰላም ኑሩ" ሮሜ ፲፪÷፲፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሮሜ. ፲፪÷፱-፳፩፣ ዮሐ ፳፬÷፳፯-፳፰

- ስለእርቅ እና ሰላም የተጻፉ መጻሕፍትን ወጣቶች እንዲያነቡ መምህሩ አስፈላጊውን ትብብር ያድርጉላቸው

## መግቢያ፡-

- ወጣቶች በሕይወት ለመኖር እና የዕለት ተዕለት ተግባራችንን ለማከናወን ሰላም አስፈላጊ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ? እንዴት?
- የተለያዩ ግጭቶች እና ጦርነቶች መንሥኤዎቻቸው ምን ይመስላችኋል?
- ግጭቶችን ለመፍታትና ሰላምን ለማስፈን ምን ዓይነት መንገዶችን ተጠቅማችሁ ታውቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### 1. ሰላም ምንድ ነው?

ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር ከማቀዳችን በፊት ስለ ሰላም ያለን ግንዛቤ ግልጽና ትክክለኛ መሆን አለበት፡፡ ሰላም የሚለው ቃል ዘወትር ከሰዎች ጋር ሰላምታ ስንለዋወጥ የሚነሣ እና የሚዘወተር ነው፡፡ ነገር ግን ሁላችንም ተመሳሳይ ግንዛቤ እንዲሁም አንድ ዓይነት የሰላም ትርጉም አለን ወይ የሚለውን ጥያቄ ስናነሣ፤ ሰዎች ስለ ሰላም የተለያየ ትርጉም እንዳላቸው እንገነዘባለን፡፡ ለአንዳንዶች ሰላም ማለት የጦርነት አለመኖር ሲሆን ሌሎች ደግሞ ሰላም የሚሆነው ጥሩ የተዝናኑና የተደሰቱ ዕለት ነው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ፤ ‹‹ምን ሰላም አለኝ አሜሪካን ሀገር ሳልሔድ፣ ሳላገባ፣ በቂ ገንዘብ ሳይኖረኝ? . . . ወዘተ›› ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ሰላም

www.zoorthodox.org

የሚሆነው ወይም ሰላም አለ ብለው የሚያምኑት ቁሳዊ ፍላጎቶቻቸው ሲሟሉ ብቻ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ሰላም በስምምነትና በአንድነት አብሮ መኖር ማለት ነው። ሰላም የዕረፍት ስሜት ነው። ሰላም የእግዚአብሔር መንግሥት እና የመንፈስ ፍሬ ነው። ሰላም በሕግና በሥርዓት መኖር ነው።

ጦርነት፣ ጥል፣ ጭቅጭቅ፣ መለያየት እና ክፍፍል አብሮ የመኖር ባህልን እንዲሁም ሰላምን የሚያደፈርሱ የሰላም ተቃራኒዎች ናቸው።

## 2. ሰላም እንዴት ይደፈርሳል?

2.1. ሃይማኖትን በትክክለኛው መንገድ ካለመረዳት፤ ዓለማችን በሃይማኖት ምክንያት የተቀሰቀሱ፣ የብዙ ንጹሐን ሰዎችን ደም ያፈሰሱ እና ብዙዎችን ለእልቂት የዳረጉ ጦርነቶችን አስተናግዳለች። ዛሬም ታሪክ ራሱን እየደገመ ሃያ አንደኛው መቶ ክፍል ዘመን በሃይማኖት አክራሪነት በሚቀሰቀሱ ጦርነቶች እና ግጭቶች የብዙ ሰዎች ሰላማዊ ኑሮ ሲናጋ ይታያል። ይሄም የብዙዎች ኑሮ በጭንቀትና በሰቀቀን እንዲሁም በፍርሀት የተከበበ እንዲሆን ከማድረጉ ባሻገር ብዙ ደም አፋሳሽ ጦርነቶችን በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች እየቀሰቀሰ ይገኛል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከላይ እንደተጠቀሰው፤ ሃይማኖትን በተመሳሳይ ሁኔታ በተዛባ መንገድ ተረድቶ ስለነበር ብዙዎችን ያሳድድ ነበር፤ ነገር ግን ደማስቆ ላይ እግዚአብሔር ወደ ትክከለኛው መንገድ አስገባው። የሐዋ. ፱÷፩-፲፰፤ የቆሮንጦስ ቤተ ክርስቲያን የክርስትና ሃይማኖት በደንብ ስላልገባቸው እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ እኔ የአጵሎስ፣ እኔ የክርስቶስ ነኝ እያሉ እርስ በርሳቸው ይጣሉና ይከፋፈሉ ነበር።

ይህን ድርጊታቸውን በመውቀስ እና በመገሠጽ ወደ ትክክለኛ የክርስትና ትምህርት እንዲመጡ ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ መክሯቸዋል። ፩ቆሮ ፩÷፲-፲፰ አይሁድ የአብርሃም ልጆች ነን እያሉ ነገር ግን አብርሃም እንደ አመነ የማያምኑ፤ አብርሃም በጎ ሥራ እንዲሠራ ለበጎ ነገር የማይተጉ፤ ሃይማኖትን በትክክለኛው መንገድ ያልተረዱ ስለነበሩ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መክሮአቸዋል። (ዮሐ ፰÷፳፩-፵፯) ስለዚህ ሃይማኖትን በትክክለኛው መንገድ ካለመረዳት እና በጭፍን ቅንነት እንዲሁም ለእግዚአብሔር ቀናተኛ ነኝ ከሚል ስሜታዊነት የተነሣ ሰላም ይደፈርሳል።

www.zeorthodox.org

2.2. **ሕግንና ሥርዓትን ባለማክበር፡-** ሕግ የሁላችንም የመኖር ዋስትና እንዲሁም ደኅንነት የሚረጋግጥበት ነው። ወንጀለኞች የሚቀጡበት ሕገ ወጦች የሚታረሙበት ሕግና ሥርዐት ከሌለ የእያንዳንዳችን የመኖር ዋስትና አደጋ ላይ ይወድቃል። ሕግ የማይከበርበት እና

ለሥርዐት ተገዢ ያልሆነ ሕዝብ ምንጊዜም ቢሆን ለዝርፊያ፣ ለጦርነት እንዲሁም ለግጭት የተጋለጠ ነው። ስለዚህ የእያንዳንዱ ኅብረተሰብ መብት እንዲከበር፣ የሁሉም ደኅንነት እና ጸጥታ እንዲረጋገጥ፣ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል በሕግና ለሥርዓት የሚገዛ፣ የሕግ የበላይነት የሚያምን፣ ፍትሕን ለማስፈን የሚጥር መሆን አለበት። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ጥቅመኞች እና ስስታሞች የሚቀሰቀሱ ግጭቶችን እና ጦርነቶችን የሕግ የበላይነትን በማስፈን መከላከል ይቻላል።

## 3. የተለያዩ ግጭቶችን የማስወገጂያ ዘዴዎች፤

የሰው ልጆች በመካከላቸው የሚፈጠረውን ጤናማ ያልሆነ የአለመግባባት ስሜት እንዲሁም የተለያዩ ግጭቶችን የሚፈቱበት ዘዴ እንደየ ሀገሩ እና እንደ ባህሉ የተለያየ ሲሆን በዚህ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘዴዎችን ለመመልከት እንሞክራለን።

### 3.1. ውይይት፡-

በግልና በሥራ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን በመነጋገር በተለይ በግልጽ መወያየት መፍታት ይቻላል። (ማቴ.፲፰÷፲፭-፳) ብዙ ጊዜ አንዱ የአንዱን ባህል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ሥነልቡና ወይም ፍላጎት ካለመረዳት አለመግባባት፣ ግጭት ወይም ጠብ ይመጣል። ከመረጃ እጥረትም ብዙ ሰዎች ለተለያዩ ግጭቶች ይጋለጣሉ። ስለዚህ በጠረጴዛ ዙሪያ በመቀመጥ በግልጽነት እና በቅንነት በመወያየት በግለሰቦች ወይም በሕዝብ መካከል የተከሠቱ ግጭቶችን እንዲሁም ችግሮችን መፍታት ይቻላል። አብርሃምና ሎጥ በመወያየት ችግሮቻቸውን ፈተዋል። (ዘፍ.፲፫÷፩-፲፰)

### 3.2. ሽምግልና፡-

በብዙ ሃይማኖቶች እና ባህሎች በዕድሜ የበለፀጉ ሰዎች ያካባቱት ሰፊ ልምድ እንዲሁም ጥበብ አላቸው ተብሎ ይታመናል። በዚህ የተነሣ በኅብረተሰቡ ልብ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያላቸው ሲሆን በብዙ ጉዳዮች ሽማግሌዎች ተጽዕኖ ፈጣሪዎች እና አስታራቂዎች ችግር ፈቺዎች ናቸው።

### 3.3. ይቅርታ፡-

www.zeorthodox.org

የበደሉንን ይቅር በማለት የበደልናቸውን ይቅርታ በመጠየቅ ግጭቶችን መፍታት ይቻላል። (ማቴ ፲፰÷፳፩፣ ማቴ ፭÷፳፩-፳፯)

### 3.4. በጸሎትና ለእግዚአብሔር በመተው፡-

እግዚአብሔር የሰላምና የፍቅር ምንጭ ነው። እውነተኛ ሰላም ከእርሱ ይገኛል። እርሱ

የሚሰጠን ሰላም ዓለም እንደሚሰጠን ሰላም አይደለም። ስለዚህ ዘወትር ስለ ሀገር፣ ስለ ዓለምና ስለ እያንዳንዳችን ሰላም ለመጸለይ እንዲሁም በቀልን ለእግዚአብሔር በመተው በአጠቃላይ ሰላምን ከሚያደፈርሱ ክፉ ተግባራት በመሸሽ ግጭቶችን መፍታት ይቻላል። እዚህ ጋር ልብ ልንለው የሚገባ ጉዳይ ግጭቶች ከመከሰታቸው በፊት የምንሰራቸው የሰላም ሥራዎች በኋላ ግጭቶች ከተከሰቱ በኋላ ከምንሠራው የእሳት አደጋ ሥራዎች የተሻሉ መሆናቸውን ነው።

## ማጠቃለያ፡-

ሰላም የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። ክርስቶስ የሰላም አለቃ እና ሰላምን ሰጪ ጌታ ነው። በዚህ ምክንያት እያንዳንዳችን የሰላም መልእክተኛ እና የሰላም አምባሳደር መሆን ይገባናል። ከሁሉም ጋር በሰላም እንድንኖርም ታዝዘናል። ክርስቲያኖች ከራሳቸው፣ ከፈጣሪ ጋር፣ ከወንድሞቻቸው እና ከተፈጥሮ ጋር በመታረቅ እውነተኛ ሰላም ያገኛሉ። ከምንም ነገር መጀመሪያ ለሰላም ቅድሚያ መስጠትን፣ ሰላምን መቀበልና መከተል የሁሉም ሰው ሓላፊነት ነው። አስተማማኝ ሰላም እንዲኖር ሁላችንም የሚገባንን አስተዋጽዖ ባላበረከትን ቁጥር ለሰላም መደፍረስም ተጠያቂዎች ነን። ስለዚህ በመተሳሰብና በመከባበር በመኖር፣ ግጭትን የማስወገድ ባህላችንን አዳብረን፤ የሰላም መልእክተኞች በመሆን፤ ሰላም በምድራችን እንዲሰፍን ተግተን መሥራት በተለይ ከወጣቶች ይጠበቃል።

## ተግባር፡-

- መምህሩ ወጣቶች ስለ ሰላም ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያዳብሩ እና የተለያዩ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ለማወቅ የሚያስችላቸውን ልምድ የሚቀስሙበት ዐውደ ጥናት ወይም የውይይት መድረክ ያዘጋጁላቸው።

www.zeorthodox.org

# አትፍረዱ

## ሠላሳ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለራሳቸው ማንነትና በሌሎች ላይ ስለመፍረድ ለይተው በማወቅ ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ" ማቴ. ፯÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፯÷፩-፫፣ ሮሜ. ፲፬÷፬፣ ዘፍ. ፲፰÷፳፫፣ ፩ ቆሮ. ፬÷፫

- ❖ መብራቱ ኪሮስ፣ ‹‹አትፍረድ››፣ ትርጉም፤ በአቡነ ሺኖዳ ሦስተኛ የተጻፈ መጽሐፍ
- ❖ "Don Not Judge" by Pope Shenouda III

### መግቢያ፡-

- ወጣቶች ስለ ራሳችሁ በቂ ግንዛቤና መረጃ አላችሁ?
- ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ ጠንካራና ደካማ ጎናችሁን በዝርዝር ጻፏቸው
- በሌሎች ላይ ፈርዳችሁ ታውቃላችሁ
- ስለ ሐሜት ያላችሁን ግንዛቤ ለመምህራችሁና ለጓደኞቻችሁ አስረዱ

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በሌሎች ላይ መፍረድ ብዙዎቻችን ለረጅም ጊዜ የተለማመድነው እና አብሮን የኖረ ባህላችን ሆኖአል፡፡ እግዚአብሔር የማይወደው ክፉ ተግባር እንደሆነና ትልቅ ኃጢአት መሆኑን አናስተውልም፡፡ በሌሎች ላይ መፍረድ ዘወትር የራሳችንን ድካምና ጉድለት እየመረመርን በሕይወታችን እድገትና መሻሻል እንዳይኖረን የሚያደርግ እንቅፋት ነው፡፡ ሁል ጊዜ የሌሎችን ነውር፣ ድካምና ኃጢአት እያነሱ መናገር ተገቢ አይደለም፡፡ ከዚያ ይልቅ ስለራሳችን ድካምና ጉድለት አውቀን ንስሓ መግባት፣ መሻሻልና መለወጥ እንደሚያስፈልገን፤ ክርስቶስ በራሳችን ላይ እንጂ በማንም ላይ እንዳንፈርድ አስተምሮናል፡፡ በእኛ ዓይን ውስጥ ምሰሶ እያለ የሌሎችን ጉድፍ መመልከት ስሕተት መሆኑንም አስረድቶናል፡፡ (ማቴ. ፯÷፩-፫)

www.zeorthodox.org

## 1. ሰዎችን እና ክፉ ሥራቸውን መለየት መቻል፡-

ዘወትር ደጋግመን የምንሠራው ስሕተት ሰዎችን እና ክፉ ሥራቸውን አንድ አድርገን መመልከታችን ነው፡፡ ትክክለኛው ምልከታ ግን፤ ኃጢአተኛውን ሰው ሳይሆን ኃጢአትን፣ ክፉ ሥራ የሠራውን ሰው ሳይሆን ክፉ ሥራውን፣ በክፉ ሐሳብ የሚያምጸውን ሰው ሳይሆን ክፉ ሐሳቡን መቃወም መጥላት እና ተግባራቸው ላይ መፍረድ፤ ከክፉ ሥራቸው ተቆጥበው ታርመው ወደ ንስሐ እንዲቀርቡ መምከር መርዳት ነው፡፡ ሰዎችን እና ክፉ ሥራቸውን ቀላቅለን የምናይበት ዓይናችን ተቀይሮ ክፉ ሥራን እና ክፉ ሰውን ለይተን ማየት ወደምንችልበት ብስለት ማደግ አለብን፡፡

### 2. በሌሎች ላይ ፈራጅ የሚያደርጉን ምክንያቶች፡-

በሌሎች ላይ ፈራጅ የሚያደርጉን ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም በዚህ ትምህርት ጥቂቶቹን ለማየት እንሞክራለን፡፡

### 2.1. ራስን በአግባቡ አለማወቅና አለመገንዘብ፡-

ብዙዎቻችን የራሳችንን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይተን ስለማናውቅ እና ስለ ራሳችን በቂ ግንዛቤ እንዲሁም መረጃ ስለሌለን ዘወትር ሌሎችን መኮነን ይቀናናል፡፡ ራሳችን እያመነዘርን፣ እየሰረቅን፣ እየዋሸን፣ ሌሎችን እያማን እና በወሬ ተጠምደን እየዋልን፤ እንዲህ የሚያደርጉትን ስንፈርድባቸው እንውላለን፡፡ ስለዚህ በሰዎች ላይ የተጠቆመውን ጣታችንን መልሰንና ዓይናችንን አንሥተን የራሳችንን የበደል የክፉ ሥራ ምሰሶ ማየት ግድ ይለናል፡፡

### 2.2. የፍቅር እጦት፡-

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ሰው ሰውን ሁሉ መውደድና መንከባከብ አለበት፡፡ ፍቅር ከአስቸጋሪ ሰዎች ጋር እንኳን መኖር የሚያስችለን ኃይል ነው፡፡ ክርስቲያኖች ጠላቶቻችንንም ጭምር እንድንወድ ታዘናል፡፡ (ማቴ. ፭÷፵፫-፵፰) ፍቅር ሰዎችን ከነ ድካማቸው እንድንወዳቸው እና እንድንሸከማቸው የሚያስችለን ጉልበት ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ፍቅር ብዙ ኃጢአትን እንደሚሸፍን አስተምሯል፡፡ (፩ጴጥ ፬÷፰) ስለዚህ ለሰው ያለን ፍቅር እየቀነሰ ሲመጣ ፈራጆችና ሐሜተኞች እንሆናለን ማለት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

### 2.3. ራስን ማጽደቅ፡-

ራስን ማጽደቅ ማለት እኛ ከሌሎች የተሻልን ነን በማለት፤ ራስን ከፍ አድርጎ የማየት ስሜት ነው፡፡ ይህ ስሜት ሥር እየሰደደ ከመጣ የራሳችንን ድካምና ኃጢአት ማየት የማንችልበት ደረጃ ላይ

ያደርሰናል፡፡ ይህ ደግሞ ነገሮችን በትክክል ተገንዝበን በማስተዋል ከመመርመር እና መልካሙን ከማድረግ ይልቅ፤ ራሳችንን በማጽደቅና ከፍ በማድረግ ከሌሎች ጋር እያነጻጸርን ፈራጆች እንሆናለን፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑት በቤተ መቅደስ ፈሪሳዊው እና ቀራጩ የጸለዩት ጸሎት ነው፡፡ ቀራጩ ስለራሱ ኃጢአት ብቻ እያሰበ ከእግዚአብሔር ምሕረትን ለማግኘት ሲጸልይ፤ ፈሪሳዊው ግን ራሱን ጻድቅና ከፍ አድርጎ ከቀራጩ ጋር እያነጻጸረ በእርሱም ላይ ይፈርድ ነበር፡፡ ራስን ማጽደቅ እውነተኛና ቅን ፈራጅ የሆነውን የጌታችንን ሥራ ቀምተን በትዕቢት ፈራጅ የሚያደርገን በመሆኑ ከዚህ ክፉ ተግባር እንጠበቅ፡፡ (ሉቃ. ፲፰÷፱-፲፬)

## ማጠቃለያ፡-

በሰዎች ላይ ሳይሆን በክፉ ምግባራቸው ላይ መፍረድ ተገቢውን ግሣጼ፣ ምክርና ቅጣት መስጠት በእግዚአብሔር የተፈቀደ ነው፡፡ ወላጆች ልጆቻቸው ሲያጠፉ እርምት መስጠት በእግዚአብሔር የተፈቀደ ነው፡፡ ወላጆች በልጆቻቸው ክፉ ምግባር ላይ፣ አባቶች ካህናት በንስሓ ልጆቻቸው ኃጢአት ላይ እንዲሁም ዳኞች በሕገ ወጥ ሥራዎች ላይ ይፈርዳሉ፣ ፍትሕን ያሰፍናሉ፡፡ ስለዚህ ወጣቶች ሰዎችን እና ክፉ ምግባራቸውን ለይታችሁ የምታዩበትን ጥበብ በመያዝ፤ ክፉ ሰዎችን ሳይሆን ክፉ ሐሳባቸውንና ተግባራቸውን እየተቃወማችሁ በቅንነት እና በክርስቶስ ፍቅር ከክፉ ምግባራቸው እንዲወጡ እርዷቸው እንጂ በማንም ላይ አተፍረዱ፡፡ የደከመውን ማበርታት፣ የሌሎችን ሸክም መሸከምን እና በሰዎች ተስፋ ሳትቆርጡ ራሳቸውን ወደ መልካም ምግባር የሚለውጡበትን ዕድል መስጠትን በሕይወታችሁ ተለማመዱ፡፡ (፩ጢሞ.፫÷፳፬፣ ገላቲያ.፮÷፩-፫) ከዚህ ቀደም በሌሎች ላይ በፈረዳችሁት ፍርድ እንዳይፈረድባችሁ ንስሓ ግቡ፤ ከዚህ በኋላም እንዳትፈተኑ ራሳችሁን ጠብቁ፡፡

## ተግባር፡-

- ወጣቶች ራሳቸውን የሚያዩበት የጽሞና ጊዜ እንዲኖራቸው እና በየዕለቱ ውሎአቸውን የሚመዝኑበት ልምድ እንዲያዳብሩ መምህሩ ከተግባራዊ ምሳሌዎች ጋር ይንገሯቸው፡፡
- ወጣቶች ራሳቸውን ማየት የሚያስችሏቸውን መንፈሳዊና ሥነ ልቡናዊ መንገደችን መምህሩ ይጠቁሟቸው፡፡
- የሚከተሉትን ዘዴዎች በመጠቀም ወጣቶች በሌሎች ላይ ከመፍረድ ራሳችሁን መጠበቅ ትችላላችሁ፡፡

www.zeorthodox.org

- ሌሎችን ማክበር፣ መውድድን እና ማመስገንን ልመዱ፡፡
- ሁል ጊዜ ስለሌሎች ጥሩ ነገር መናገርን ልመዱ፡፡
- ሐሜተኞችን ከማዳመጥ ራቁ፡፡
- የራሳችሁን የየዕለት እንቅስቃሴ መፈተሽ እና ድክመትና ጥንካሬያችሁን መመዘንን ተማሩ፡፡
- ወሬኞች የሚነግሩአችሁን ሁሉ አትመኑ፡፡
- ለደካሞች መጸለይን ልመዱ፡፡
- እውነታውን ሳትረዱ በስማ በለው ሰዎችን መጥላትን አስወግዱ፡፡

www.zeorthodox.org

# ክርስቲያንና የንጽሕና ሕይወት

## ሠላሳ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ክርስትና የንጽሕና ሕይወት መሆኑን ተገንዝበው ለ ግዚአብሔር ፈቃድ በመ ዘዝ ይኖራሉ፤ ለሌሎችም ያስረዳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፣** « ናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በ ናንተ ዘንድ ሊኖር በመንፈስ ንጂ በሥጋ አይደላችሁም፡፡ /ሮሜ ፰፥፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፪ ተሰሎ ፩፥፲፪፣ ፩ ቆሮ ፯፥፲፪-፳ ፣ ፩ ቆሮ ፯፥፩-፱ ገላትያ ፫፥፲፮-፳፮

## መግቢያ

- ወጣቶች ዓለማዊ ሆነው ከሚኖሩ ከማያምኑ ሰዎች ናንተን ልዩ የሚያደርግ ነገር አለ ብላችሁ ስባላችሁ? ምንድነው?
- በቅድስና ና በንጽሕና መኖር ለምን አስፈለገ?

## የሳምንቱ ትምህርት

ኛን ክርስቲያኖችን ዓለማዊ ሆነው ከሚኖሩ ሰዎች ልዩ የሚያደርገን የምንኖርበት ቤት፣ የምንበላው ምግብ፣ የምንለብሰው ልብስ. . . ወ.ዘ.ተ አይደለም፡፡ በዚህ ዓለም ክርስቲያኖች የምንኖርበት የተለየ ደሴት ወይም ካምፕ የለንም፤ የምንኖረው በዚህች ምድር ላይ ነው፡፡ የምንመገበው ሰዎች የሚመገቡትን የዚህን ዓለም ምግብ ንጂ ከሰማይ የሚወርድ የተለየ መና አይደለም፡፡ ልብሶቻችን ና ሌሎች ለመኖር የሚያስፈልጉን ነገሮች ሁሉ ከዚህ ዓለም የተገኙ ናቸው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በዚህ ምድር በሰዎች ላይ የሚሆነው ሁሉ በ ኛም ሕይወት ይሆናል፡፡ ን መማለን፣ ንሰደዳለን፣ ንራባለን፣ ንጠማለን፣ ደስ ሐዘን ያግጥመናል፣ ን መማለን፣ ንሞ ለን፡፡ ክርስቲያን ስለሆንን ብቻ ነዚህ ነገሮች አይመለከቱንም ልንል አንችልም፡፡ ክርስቲያኖችን ከዚህ ዓለም ሰዎች ልዩ የሚያደርገን በዚህ ዓለም የኖርን ዓለምን ና ምኞቷን አለመውደዳችን ና ከክፉ ተግባር ከ ጢአት መራቃችን ሲሆን፤ የንጽሕና ሕይወት በመኖር የሕይወት ልዩነት መፍጠራችን ከሌሎች ዓለማውያንና የማያምኑ ሰዎች ልዩ ያደርገናል፡፡

www.zeorthodox.org

### 1. የንጽሕና ሕይወት ምንድነው?

ክርስቲያኖች በነፍስም በሥጋም ንጹሕ ሆነው ንዲኖሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ የሥጋ ንጽሕና ማለት ሰውነ ችንን ከዝሙት ና ከርኩሰት በአጠቃላይ ሰውነ ችንን ሊያቆሽሹ ከሚችሉ

የ ጢአት ሥራዎች መጠበቅ ማለት ነው፡፡ የነፍስ ንጽሕና ደግሞ ነፍሳችን ዘወትር ለእግዚአብሔር ንድትገዛ ቃሉን በመስማት፣ በጾምና በጸሎት፣ በበጐ ነገሮች ሁሉ መትጋት፣ ነፍሳችንን ከ ጢአት መጠበቅ ነው፡፡ በተለይ ብዙ ወጣቶች የሚፈተኑበት የዝሙት ጢአት ስለሆነ ከዝሙት በመራቅ ና በመሸሽ የሥጋና የነፍስን ንጽሕናን መጠበቅ ይገባል፡፡

## 2. የድንግልና ሕይወት፡-

አንድ ወንድ ወይም ሴት ራሳቸውን ከዝሙት ጠብቀው ሌላ በንጽሕና የሚኖሩት ሕይወት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለአንድ ሰው ሁለት አማራጮች ንዳሉት ይናገራል፡፡ ይህም አንድ ክርስቲያን የድንግልና ሕይወት ወይም የጋብቻ ሕይወትን መርጦ ክርስቲያናዊ ሕይወቱን ንዲመራ ይመክራል፡፡ የድንግልና ሕይወትን ነቢዩ ኤልያስ፣ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ቅዱስ ጳውሎስና ሌሎቹም የኖሩት ሲሆን ለፈቃደ ነፍስ በመገዛት የበለጠ እግዚአብሔርን ና ሰዎችን ለማገልገል ሰዎች የሚመርጡት የሕይወት መንገድ ነው፡፡

## 3. የጋብቻ ሕይወት፡-

መጽሐፍ ቅዱስ አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ፣ አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት የሆነን ጋብቻ ይፈቅዳል፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ዕድሜው ለጋብቻ ሲደርስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቆ በሃይማኖት በክርስቲያናዊ ሕይወት ይምትመስለውን ና ሚስት የምትሆነውን ሴት ፈልጐ ያገባል፡፡ ቤተሰብ ይመሠር ል፣ ልጆችን ይወልዳል፤ በጋብቻ ሕይወቱም እግዚአብሔርን ያከብራል፡፡ ነገር ግን ከጋብቻ በፊት ና ከጋብቻ በኋላ የሚፈጸምን ዝሙት እግዚአብሔር የሚከለክል ሲሆን ንጹሕ የሆነውን የጋብቻ ሕይወት የሚያቆሽሽ ተግባርም ነው፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች ክርስትና የንጽሕና ሕይወት መሆኑን ከዚህ ትምህርት ተገንዝባችኋል፡፡ በዓለም ከሚኖሩ ሰዎች ልዩ የሚያደርጉአችሁን ነገሮችም አውቃችኋል፡፡ ስለዚህ በማያምኑ መካከል የኖራችሁ ናንተ ግን በ ግዚአብሔር በማመን፣በአመለካከት፣በሕይወት ና በኑሮአችሁ በመለየት ግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን የንጽሕና ሕይወት ለመኖር ትጉ፡፡ ዓለሙን ና ምኞቱን ሳይሆን ግዚአብሔርን የምትከተሉ ፈቃዱንም የም ደርጉ ሁኑ፡፡ /ኤፌ. ፭፥፩፣ ፩ዮሐ ፪፥፲፭-፲፯/

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- መምህሩ ወጣቶች በየዕለት ተዕለት ኑሮአቸው የንጽሕና ሕይወትን ንዲኖሩ የሚያስችሏቸውን ምሳሌዎች ከቅዱሳን ሕይወት ጋር ያዛመዱ ይንገሯቸው፡፡
- ወጣቶች ለዓለም ምኞት ሳይሆን ለ ግዚአብሔር ፈቃድ መ ዘዝ ንዴት ንደሚችሉ ያወያዩአቸው፡፡

# ክርስቲያንና ሥነ ልቡናዊ ጤንነቱ

## ሠላሳ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ክርስትና የተለያዩ ሥነ ልቡናዊ ፍላጐቶቻችንን በጥልቀት እንደሚያሟላ አውቀው በክፍል ውስጥ ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** ‹‹ፍጹም ፍቅር ፍርሐትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሐት የለም ፍርሐት ቅጣት አለውና የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም፡፡›› ፩ ዮሐ.፬፥፲፰-፲፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፩ዮሐ. ፬፥፯-፳፩፣ ፩ዮሐ ፫፥፩-፫ ፩ቆር፣ ፲፫፡፩-፰

### መግቢያ፡-

- ☒ ወጣቶች ሥነ ልቡናዊ ፍላጐቶቻችሁን ለይታችሁ ታውቃላችሁ?
- ☒ እነዚህን ሥነ ልቡናዊ ፍላጐቶች የሚያረካቸው ምንድነው?
- ☒ የአንድ ሰው ሥነ ልቡናዊ ፍላጐቶቹ ካልተሟሉለት ምን ሊሆን ይችላል?

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

አንድ ሰው ጤናማ ሥነ ልቡና አለው የሚባለው በተግባሩ፣ በሐሳቡና በስሜቱ መካከል ጤናማ የሆነ ውሕደት ሲኖር እና ሥነ ልቡናዊ ፍላጐቶቹ በትክክለኛ መንገድ ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ በፍላጐታችን እና በሐሳባችን መካከል ስምምነት ከሌለ ውስጣችን ስለሚረበሽ ጭንቀት፣ ፍርሐት፣ አለመረጋጋት እና በራስ አለመተማመን እንዲሰማን ያደርገናል፡፡

ክርስትና ሥነ ልቡናዊ ፍላጐቶቻችን ተሟልተው ሰላማዊ እና የተረጋጋ ሕይወት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ሰው ሥጋ ብቻ አይደለም፣ መንፈስም ነው፡፡ ለአንድ ሰው የሥጋ ፍላጐቶች ብቻ መሟላት ጤናማ ሥነ ልቡና እንዲኖረው አያስችለውም፤ መንፈሳዊ ፍላጐቶቹም መሟላት አለባቸው፡፡ በሥጋ እና በነፍስ መካከል ስምምነት እንዲኖርና የተረጋጋ ሕይወትን እንድንመራ ክርስትና ትልቁን ሚና ይጫወታል፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ የሰዎችን ጉድለት ይሞላል፡፡ /፪ቆሮ ፲፪፥፱፣ ሉቃ ፫፥፫/፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ሥነ ልቡናዊ ፍላጐቶቻችንን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

www.zeorthodox.org

## 1. የደኅንነት ስሜት እንዲሰማን መፈለግ፡-

ማንኛውም ሰው በሚኖርበት አካባቢ እና በሥራው ዋስትና እንዲኖረው እንዲሁም ደኅንነቱና ሰላሙ እንዲረጋገጥ ይፈልጋል፡፡ ክርስትና ስዎች በመዋደድና በመከባበር ከኖሩ ደኅንነነታቸውን እንዲሁም ሰላማቸውን ማረጋገጥ እንደሚችሉ ያስተምራል፡፡ በተለይ ነፍሳችን በእግዚአብሔር እንድትታመን እና ደኅንነት እንዲሰማት ያደርጋል፡፡ የእግዚአብሔር ሰላም ስለሚጠብቃት ነፍሳችን ከፍርሐት ነፃ ትሆናለች፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ በእስር ቤት ሆኖ ጥሩ እንቅልፍ የተኛውና ያልተጨነቀው ነፍሱ በእግዚአብሔር ትታመን ስለነበር ነው፡፡ (የሐዋ.ሥራ ፲፪÷፩-፲፪)

## 2. መወደድን መፈለግ፡-

ሁላችንም በሌሎች መወደድንና መፈቀርን እንፈልጋለን፡፡ በሌሎች እንደተወደድን ስናውቅ ውስጣችን በደስታ ይሞላል፣ የደኅንነት ስሜትም ይሰማናል፡፡ መንፈሳዊ ሕይወታችን ይህን የፍቅር ፍላጐታችንን ያሟላልናል፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ በእግዚአብሔር ስንታመን የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለሚፈስ የፍቅር ፍላጐታችን ሞልቶ ይተርፋል፤ ሌሎችንም ጭምር እናፈቅራለን፡፡ /ሮሜ ፭÷፭/

## 3. መመስገንን መፈለግ፡-

ከልጅነታችን ጀምሮ ለእያንዳንዱ እንቅስቃሴአችን የሌሎች አስተያየት፣ይሁንታ እና ምስጋና የማወቅና የመፈለግ ዝንባሌ አለን፡፡ አንዳንዶች የሌሎችን ምስጋና በጣም ከመፈለጋቸው የተነሣ በራስ መተማመናቸውን አጥተው በሌሎች ላይ ጥገኛ ሆነዋል፡፡ ሌሎች የሚያመሰግኗቸው፣ የሚያበረታቷቸው እና የሚያደንቋቸው ከሆነ በሕይወታቸው ሙሉ ሆነው የኖሩ ይመስላቸዋል፡፡ ሌሎች የማያመሰግኗቸውና የማያጨበጭቡላቸው ከሆነ ደግሞ በእንቅስቃሴያቸው ሁሉ ጉድለት ያለባቸው መስሎ ስለሚታያቸው በሕይወታቸው ሙሉ ሆነው የሚኖሩ አይመስላቸውም፡፡ ክርስቲያን ግን ይህ ፍላጐቱ በእግዚአብሔር ስለሚሟላ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አድርጎ ያምናል፡፡ የመንግሥቱ ወራሽ እንደሆነ ስለሚያምንም አምልኮውና ሥራው በሰዎች ምስጋና ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ ክርስቲያን ለምን እንደሚኖር? ማንን እንደሚያገለግል? ያውቃል፡፡

www.zeorthodox.org

## 4. ነጻነትን መፈለግ፡-

በዓለማችን ብዙ መሥዋዕትነት የተከፈለባቸው እልህ አስጨራሽ የነጻነት ትግሎች ተካሒደዋል፡፡ እነዚህ ትግሎች ሰው ለነጻነት ያለውን ከፍተኛ ፍላጐት እና የሚሰጠውን ዋጋ የምናይባቸው

መስታዎቶቻችን ናቸው፡፡ ማንኛውም ሰው ነጻ መሆን፣ በነጻነት መንቀሳቀስና መኖርን ይፈልጋል፡፡ ክርስትና እግዚአብሔር የሰው ልጅን በአምሳሉ ነጻ አድርጐ እንደፈጠረው ይሰብካል፡፡ እውነተኛ ነጻነትም በሕግና በሥርዓት መኖር ነው፡፡ ሰው ሕግን ሲተላለፍ ከሥርዓት ሲወጣና ኃጢአትን ሲያደርግ ነጻነቱን ስለሚያጣ የኃጢአት ባሪያ ይሆናል፡፡ (ዮሐ ፰፥፴፩-፴፮) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት ባርነት ነጻ እንዳወጣን በነጻነት እንድንኖር እንደፈቀደልን ክርስቲያኖች እናምናለን፡፡ /ሮሜ ፫-፮፣ ገላትያ ፫፥፩-፫፣ ሮሜ ፰፥፲፫-፲፮/

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች ሥነ-ልቡናዊ ፍላጐቶቻችሁ እንዴት ጤናማ በሆነ መንገድ መሟላት እንደሚችሉ እና በነጻነት መኖር ማለት በሕግና በሥርዓት መኖር ማለት እንደሆነ ከዚህ ትምህርት አውቃችኋል፡፡ ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ ጠንካራ በመሆን፣ በጸሎትና በበጐ ነገሮች በመትጋት የተረጋጋ እና ሰላማዊ የሆነ ኑሮን ለመኖር ትጉ፡፡

## ተግባር፡-

- መምህሩ ወጣቶች ሥነ-ልቡናዊ ፍላጐቶቻቸውን ከመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጋር አጣጥመው ሰላማዊ ኑሮን እንዴት መኖር እንደሚችሉ ተግባራዊ ልምዶችን እና ምሳሌዎችን በመጠቀም ያወያዩአቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# በዓላት(፩) - መግቢያ

## ሠላሳ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ በዓላት ምንነት፣ አከባበርና መንፈሳዊ በረከት አውቀው በጽሑፍ ያቀርባሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *" በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርሁ ፡፡ " ራእ.፩፥፲*

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ) ገጽ 106 - 122
- ‹‹በዓላት›› ምን? ለምን? እንዴት?፤(ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ)፣ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

## መግቢያ

**በዓል፡-** ማለት *" የደስታ፣ የዕረፍት ቀን በዓመት በወር በሳምንት የሚከበር፣ ያለፈ ነገር የሚታሰብበት ተዝካር፤ ሕዝብ ተሰባስቦ የበዓሉን ምስጢር እያሰበ ደስ ብሎትና አጊጦ.... የሚዘምርበት እልል የሚልበት ሽብሸባ ጭብጨባ የሚያደርግበት "* ነው፡፡ ሰዋስወ ግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ

በዓላት ከመደበኛ ሥራ ዐርፎ ለበዓሉ ይገባዋል የሚሉትን መልካም ነገር መንፈሳዊ ሥራ በመሥራት፤ እግዚአብሔርን በማመስገን፣ በማሕሌት፣ በምፅዋት፣ በጸሎት፣ ሊጎበኙ የሚገባቸውን አቅመ ደካሞች ረዳት ደጋፊ የሌላቸውን፣ በሽተኞችን እሥረኞችን በመጎብኘት፣ የተጣሉ በማስታረቅ የሚያሳልፉበት የሚከበሩበት ዕለት ነው፡፡

በዓላት ከሌሎቹ ቀናት የሚለዩበትም የዕረፍት ቀናት በመሆናቸው ነው፡፡ ለዚህም መሠረቱ የአይሁድ ሰንበት (ቀዳሚት ሰንበት) ናት፡፡ ‹‹ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸሙ፡፡ እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ፡፡ እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም፤ እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ ዐርፎአልና፡፡›› ዘፍ. ፪፥፩-፫፡፡

www.zeorthodox.org

በዓላት የመታሰቢያ ዕለታትም ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ለሠራው ድንቅ ሥራና በቅዱሳኑ አድሮ በቸርነቱ ለሠራው ሁሉ መታሰቢያ ይደረግለታል፡፡ ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ፤‹ ‹ለተአምራቱ

መታሰሲያ አደረገ፤›› ሲል፤መዝ.፻፲÷፬ እንደተናገረ፤ እግዚአብሔር ተአምራቱን ድንቅ ሥራውን በበዓላት እንዲታሰቡ አድርጓል፡፡

እግዚአብሔር ለሠራቸው ሥራዎችም ሆነ ለቅዱሳኑ ከሰጣቸው መታሰቢያዎች መካከል በዓላት መገለጫዎች ሆነው፤ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ እና የቅዱሳኑ ተጋድሎ የሚታሰቡበት ዕለታት ናቸው፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መታሰቢያ እንድናደርግ በወንጌል አዝዞናል፡፡ ‹‹ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፡፡›› ሉቃ.፳፪÷፲፱፡፡ ‹‹የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል፤›› መዝ.፻፲፮ ተብሎ በነቢዩ ዳዊትም ተጽፎአል፡፡

ቅዱስ ዳዊት የበዓላት ዕለታትን መታሰቢያነት፤ ‹‹እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት፤ ሐሴትን እናድርግ፣ በእርሷም ደስ ይበለን፤›› መዝ.፻፲፯÷፳፬ በማለት አጉልቶ ገልጾታል፡፡

- የበዓል ትርጉም ይህ ከሆነ፤ ብዙ ሰዎች ስለበዓላት ዓላማ እና አስፈላጊነት ላይ ጥርጥር አላቸው፡፡ ለምን ? እንዴት ? መከበር እንዳለባቸው የሚጠይቁም ብዙ ናቸው፡፡
- በዓላት በልማድ የሚከበሩ ወይም ቁጭ ብሎ መዋልን የወደደ ሰነፍ የፈጠራቸው አይደሉም፣ ምንጫቸው ሃይማኖት ነው፡፡
- በብሉይ ኪዳን ብዙ በዓላት ነበሩ፡፡ ከእነዚህ በዓላት ቀዳሚዋ፤ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፍጥረታትን ሁሉ ፈጥሮ ሲያርፍ የተጀመረችው ቀዳሚት ሰንበት የመጀመሪያዋ ስትሆን፤ በሙሴ ሕግ የተሰጡ በዓላትም ነበሩ፡፡ (ዘሌዋ.፳፫) ሁሉም በማኅበር የሚፈጸሙ አምልኮተ እግዚአብሔር ያሉባቸው ሲሆኑ የየራሳቸው ሥርዓት እና አከባበርም ነበራቸው፡፡ እነርሱም፡-

1. ቀዳሚቱ ***"ቀዳም ሰንበት"*** ዘፍ.፪÷፪-፫፣ዘሌ.፳፫÷፫-
2. በዓለ ፋሲካ፤ ዘጸ.፲፪÷፩-፳፣ ዘሌ.፳፫÷፭-፰ } ሁለቱ ተከታታይ በዓላት ስለሆኑ እንደ አንድ ይቆጠራሉ፡፡
3. የቂጣ በዓል፤ ዘሌ.፳፫÷፮
4. በዓለ መከር፤ ዘሌ.፳፫÷፲፭-፲፮
5. በዓለ መጥቅዕ (መለከቶች የሚነፉበት በዓል)፤ ዘሌ.፳፫÷፳፫-፳፭
6. የማስተሰረያ ቀን (በዓል)፤ ዘሌ.፳፫÷፳፮-፳፯
7. የዳስ በዓል (በዓለ መጸለት)፤ ዘሌ.፳፫÷፴፬-፴፮ ናቸው፡፡

ከባቢሎን ምርኮ በኋላም ሁለት በዓላትን ጨመሩ፡፡

8. ፋሪም፡፡ አስቴ. ፱÷፲፯
9. የመቅደስ መታደስ መታሰቢያ በዓል፤ዮሐ.፲÷፳፪

www.zeorthodox.org

- በአረማዊነት የሚኖሩት አሕዛብም በአካባቢያቸው አንድ ለውጥ ሲያዩ ብቻ ቶሎ መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር፡፡ ***"ነፋስ ሲነፍስ፣ የነፋስ አምላክ (ኤዎሎስ) ተቆጥቶናል፡፡ የፀሐይ ሙቀት ሲያይል የፀሐይ አምላክ (አጵሎስ) ተቆጥቶ ነው፡፡ ባሕር ስትታወክ የባሕር አምላክ (ፖሲዶን) ተቆጥቶ ነው "*** በማለት ካህናተ ጣዖቱ በዓል ያዘጋጁ መሥዋዕት ይሰው ነበር፡፡ በነዚህ ቀናት ሥራ ቢሠሩ በዓላት እንደሻሩ አይቆጥሩትም፡፡

አይሁድ እና አረማውያን ወደ ክርስትና ሲገቡ የበዓላትን መንፈሳዊነት ለመረዳት ከብዶአቸዋል፡፡

- በክርስትና በዓላት የሚከበሩት መንፈሳዊ ተግባራትን በመፈጸም እና ቀናቱን ለእግዚአብሔር በመቀደስ ነው፡፡ ለዚህም ነው በኦሪት "***የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ"*** ዘጸ.፳፥፰ የተባለው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም፤ ***"በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዶአል"*** ማቴ.፲፪፥፲፪ በማለት አከባበሩን አስተምሮናል፡፡ ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስም፤ **"በጌታ ቀን (በሰንበተ ክርስቲያን) በመንፈስ ነበርሁ"** ራእ.፩፥፲ በማለት የሰንበትን ልዕልና፣ አከባባር እና የፍጽምና ደረጃ አስተምሮአል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መንፈሳዊ ተግባራትን በመፈጸም መሆኑን አስተምሮአል፡፡
- ቅዱሳን ሐዋርያትም ልማድ መሰናክል እንዳይሆን ሁሉንም እንዳመሉ ተቀበሏቸው፡፡ ከአይሁድ ወደ ክርስትና የተመለሱት የክርስቶስን አዳኝነት አምነው ከተቀበሉና ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ በባህላቸው ያደርጉት የነበረውን ከማድረግ አልተከለከሉም፡፡ ለምሳሌ፡- በአይሁድነት ሳሉ ቅዳሜን ብቻ ያከብሩ ነበር፤ ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ግን ቅዳሜንም ፣ እሑድንም ያከብራሉ፡፡
- ግዝረትና የመሳሰለውም የብሉይ ኪዳን ትውፊት ከቤተ አይሁድ በተመለሱት ክርስቲያኖች ዘንድ እስከ አሁን ይሠራበታል፡፡ ከአረማዊነት የተመለሱት ደግሞ እንደዚሁ የክርስቶስን አዳኝነት አምነው ከተቀበሉና ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ልማደ አረማውያንን አልተውም፡፡ የቅዳሜን በዓልነት አያውቁም፣ ግዝረት የላቸውም፡፡
- ሊቃውንቱና መምህራኑ የረጅም ዘመናት ዕድሜ ያስቆጠረውን ልምድ ከማስተው ይልቅ በጣዖታቱ ተሰይሞ ይከበር የነበረውን ሁሉ በቅዱሳኑ ስም እየለወጡ እንዲያከብሩ አደረጉ፡፡ ለምሳሌ ፡- በጣዖት አምልኮ በነበሩበት ጊዜ ***"ፖሲዶን"*** የሚባለው ጣዖት የባሕር አምላክ ነበር፣ በክርስትና ዘመናቸው ግን ***"ኒኮላዎስ"*** የሚባለውን ቅዱስ የባሕር ጠባቂ ብለው በየዓመቱ ያከብሩታል፡፡ በ ***"ኦሪስ"*** ምትክ ዛሬ ቅዱስ ጊዮርጊስን የወታደሮች ጠባቂ ብለው በየዓመቱ ያከብራሉ፡፡
- በጠቅላላው አረማውያን ለእያንዳንዱ ድርጊት (ፍጥረት) አምላክ መድበውለት ስለነበር፤ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናቸው የሚከበሩት ቅዱሳን መላእክት ጻድቃን ሰማዕታት ሁሉ የአንዳንድ ነገር ጠባቂዎች እየተባሉ ተሰይመዋል፡፡

www.zeorthodox.org

ስለ በዓላት አጀማመር እና ሥርዓቶች የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ እና ትምህርት መሠረት አድርገን ለመግቢያ ያህል ከላይ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያሉትን በዓላት እና አከባበር እናያለን፡፡ በቅድሚያ በዓላቱን እንይ ፦

# ትምህርቱ

## በዓላት

- በቤተ ክርስቲያናችን በሳምንት፣ በወርኅ እና በዓመት የምናስባቸው እግዚአብሔር ሥራ የሠራባቸው ቀናት አሉ፡፡ ከዓመት እስከ ዓመት ባሉት ቀናት በሙሉ የሚታሰቡ የየራሳቸው በዓላትም አሉዋቸው፡፡ አንዳንዶቹ ቀናትም ከአንድ በላይ በዓላት ይታሰቡባቸዋል፡፡
- ከዚሁም ጋር ሊቃውንቱ **ለእመ ኮነ** እና **ወበዛቲ ዕለት** የሚሏቸው መታሰቢያዎች አሉ፡፡ ከሁለቱም ዕለታዊ፤ ሳምንታዊ፤ ወርኃዊ እና ዓመታዊ የምንላቸው በዓላት አሉ፡፡ ለመሆኑ ***ለእመ ኮነ*** እና ***ወበዛቲ ዕለት*** ማለትስ ምንድን ነው ?.....
- <u>ለእመ ኮነ</u>፡- የሚባሉት ቋሚ ቀን ሳይኖራቸው ከፍ እና ዝቅ እያሉ ፤ በበዓለት እና አጽዋማት ወቅት ሰንበታትን እና ወቅቶችን እየጠበቁ ይከበራሉ፡፡ በዚህ ወር፣ በዚህ ቀን በማለት ብቻ የማይወሰኑት እንደ ስብከት፤ ኖላዊ፤ ብርሃን፤ የዐቢይ ጾም፣ በዓለ ሃምሳ፣ ሰንበታት የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- <u>ወበዛቲ ዕለት</u>፡- የሚሏቸው ደግሞ በዚህ ወር፣ በዚህ ቀን፣ ተብለው ተወስነው የሚታሰቡትን ናቸው፡፡ ልደት፣ ጥምቀት፣ ወርኃዊ እና ዓመታዊ የቅዱሳን መታሰቢያዎች በዚህ ሥር ከሚካተቱት ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡
- እነዚህ ሁሉ በቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ግጻዌ ተሠርተዋል፡፡ ዐዋድያቱ (በሐሳበ ቀመር ያሉት) በየዓመቱ መጀመሪያ ቀን ይታወጃሉ፡፡ (መምህር በአዲስ ዓመት ስለሚታወጀው እና ዘየአርግ እና ይወርዱ ምን እንደሆነ? ተማሪዎች ጠይቀው እንዲመጡ እና እንዲያብራሩ፤ የቤት ሥራ እና የማብራርያ ጊዜ በክፍል ውስጥ ይስጥዋቸው፡፡)
- በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበዓላት ቀኖና የራሱ የሆነ መልክ አለው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ከሳምንት እስከ ዓመት ያሉትን እንመልከት፡፡

www.zeorthodox.org

## ሳምንታዊ በዓላት

- ከሁሉ በፊት ቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሜና እሑድን እንደ አንድ ቀን ታከብራለች፡፡
- የቅዳሜ መከበር በብሉይ ኪዳን የታዘዘ ሲሆን፣(ዘጸ.፳፥፯) እሑድ ደግሞ ጌታ ከሙታን ተለይቶ ስለተነሣባት ***"የጌታ ቀን"*** ተብላ በሐዲስ ኪዳን የከበረች ናት፡፡ (ራእ.፩፥፲)

## ወርኃዊ በዓላት

- ወሩን በሙሉ የሚታሰቡ የባለቤቱ የልዑል እግዚአብሔር እና ሥራ የሠራባቸው የቅዱሳን መታሰቢያዎች አሉ፡፡
- ከእነዚህም የጌታን በዓላት (በስድስት ኢየሱስ፣ በሰባት  ሥላሴ፣ በሃያ ሰባት መድኃኔ ዓለምን…..) በመወከል በየወሩ በሃያ ዘጠኝ ይከበራሉ፡፡
- የቅዱሳንን ሁሉ መታሰቢያ ማድረግ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸም ዘለዓለማዊ ትንቢት መዝ.፻፲፩ በመሆኑ እና የቅዱሳን መታሰቢያም ለበረከት ስለሆነ ምሳ.፲÷፯ የበጎ ትንቢት ፈጻሚዎች ለመሆን እና እግዚአብሔር ከቅዱሳን በረከት እንዲያሳትፈን በየወሩ እናስባቸዋለን፡፡ የሁሉንም ቅዱሳን እና የእመቤታችንን የተለያዩ በዓላት በመወከልም በቅድስተ ቅዱሳን በእመቤታችን ቅድስት ማርያም መታሰቢያ ቀን በየወሩ በ፳፩ ይከበራሉ፡፡
- የቅዱሳን መላእክት መታሰቢያንም በሊቀ መላእክት በቅዱስ ሚካኤል ዕለት በየወሩ በ፲፪ እናከብራለን፡፡
- ይህ ማለት ግን ከጌታችን በዓላት እንደ ፮ ኢየሱስ፣ ፯ ሥላሴ፤ ፳፯ መድኃኔዓለም፤ ከቅዱሳንም እንዲሁ የምናስባቸው በዓላት አይከበሩም ማለት አይደለም፡፡ በሦስቱ ዕለታት ግን ሁሉም በዋናነት ይታሰባሉ፡፡
- ከዚሁም ጋር በአጥቢያው ባለው ታቦት መታሰቢያ መሠረትም የአጥቢያው ምእመናን በክርስቶስ አምነው እና ተስፋ አድርገው ይህን ዓለም ያሸነፉትን ለማሰብ እና ከበረከታቸው ለመሳተፍ ቅዱስ ጊዮርጊስ ፣ አቡነ አረጋዊ ፣ ቅዱስ ዮሐንስ ሌሎቹም መታሰቢያቸው ባለበት ወርኃዊ እና ዓመታዊ በዓሎቻቸው ታስበው ይከበራሉ፡፡

## ዓመታዊ በዓላት

- ከላይ እንደተገለጠው ለእመ ኮነ እና ወበዛቲ ዕለት በሚለው የሚታሰቡት ናቸው፡፡
- እነዚህ በዓላት ፡-የጌታ ዐበይት በዓላት  እና የጌታ ንኡሳን በዓላት  በመባል ይታወቃሉ፡፡ ዓመታዊ የንግሥ በዓላት ብለን የምናከብራቸው ከላይ በተገለጠው ዝርዝር የሚካተቱ እና የማይካተቱ በዓላትም አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በዓለ መድኃኔዓለም ከጌታ ዓበይት በዓላት በአንዱ በስቅለት (በሰጊድ እና በሐዘን) ሲታሰብ መጋቢት ፳፯ ቀን ታቦት ወጥቶ ይነግሣል፡፡ ይከበራልም፡፡
- ሌላው ደግሞ እንደ ፍልሰታ ለማርያም፣የጥር ሥላሴ….. በዓመት የሚነግሡ ሆነው ሲከበሩ በዐበይት እና ንኡሳኑ አልተካተቱም፡፡ ነገር ግን መጽሐፈ ስንክሳር ያስባቸዋል፤ መጽሐፈ ግጻዌውም ያውጃቸዋል፡፡

www.zeorthodox.org

- ዓበይት እና ንኡሳን የጌታ በዓላት በተለየ ሁኔታ መከበራቸው፤ ግን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን እምነት ወይም ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓተ አምልኮዋን በሚገባ ያልተረዷት ክርስቶስን አታውቅም፣ አትሰብክምም ብለው ከሚተችዋት በላይ፤ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዌ እና የማዳን ሥራ የምትሰጠውን የላቀ ክብር ያመለክተናል፡፡
- ለመሆኑ እነዚህ የጌታ ዐበይት በዓላት እነማን ናቸው፡፡ ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም የሳምንት ሰው ይበለንና፣ በሚቀጥለው የትምህርት ክፍለ ጊዜ እናያቸዋለን፡፡

## ማጠቃለያ

- በዓላት ከእግዚአብሔር የተሰጡን የመንፈሳዊ በረከት መቀበያዎቻችን ናቸው ፡፡ በአግባቡ ስናከብራቸው እንጠቀምባቸዋለን፡፡
- ቤተ ክርስቲያን በሳምንት ሰንበታትን፤ እንዲሁም በወር እና በዓመት የምታስባቸው በዓላት በለእመ ኮነ (እንዱ በዓል በ…ቀን ከዋለ) በሚል ስሌት እና ታሪኩ በተፈጸመበት ዕለት የሚታሰቡ የሚከበሩ ናቸው፡፡
- ክርስቲያኖች እንደ አሕዛብ በፍርሐት እና አጋጣሚ፤ እንደ አይሁድ ደግሞ በፊደል ሳይሆን በመንፈስ የምናከብራቸው በዓላት የሥራ ፈትነት ምክንያት አይደሉም፡፡

## ተግባር

- ተማሪዎች በ፲፪ ቡድን ተከፍለው፤ በየወሩ ተመድበው ከአንድ እስከ ሠላሳ ባሉት ቀናት የየዕለቱን መታሰቢያዎች ከመጽሐፈ ስንክሳር ወይም ከመጽሐፈ ግጻዌ በመመልከት በሰንጠረዥ ያቅርቡ፡፡ መምህርም የጳጉሜን በሰንጠረዥ ያምጡላቸው፡፡
- እያንዳንዱ ቡድንም በደረሰው ወር ከሚከበሩት መካከል አንድ በዓል እየመረጠ ከአንድ ገጽ ያልበለጠ ታሪክ ያዘጋጅ፡፡
- ተማሪዎች የበዓላትን መንፈሳዊ ትርጉም ከመምህራን ተረዱ፤

www.zeorthodox.org

# በዓላት (፪) - ዐበይት የጌታ በዓላት

## ሠላሳ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ባለፈው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ሳምንት ስለ በዓላት ምንነት የጀመርነውን ትምህርት ስለ ጌታችን ዓበይት በዓላት አውቀው በዝርዝር ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት፤ሐሴትን እናድርግ በእርስዋም ደስ ይበለን፡፡"*** መዝ.፻፲፯(፻፲፰)፥፳፬

## መግቢያ

- ☒ በየወሩ የተከፋፈላችሁትን የቤት ሥራ ለእያንዳንዱ ቡድን አምስት ደቂቃ ብቻ ተሰጥቶት ስድስት ቡድኖች ብቻ በዚህ ሳምንት ያብራሩ፡፡ ቀሪዎቹ ቡድኖች ለሚቀጥለው ሳምንት ይዘጋጁ፡፡
- ☒ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት የጌታ በዓላት ዘጠኝ **ዐበይት በዓላት** እና ዘጠኝ **ንኡሳን በዓላት** ይባላሉ፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ስለእነዚህን በዓላት እንማራለን፡፡
- ☒ ባለፈው የትምህርት ክፍለ ጊዜ በብሉይ ኪዳን ስለሚታሰቡ በዓላት የተማርነውን ከልሱ፡፡ (ዐሥር ደቂቃዎች)
- ☒ ከእነዚህ በዓላትም በጌታ በዓላት ፍጻሜቸውን ያገኙትን የነቢያትን ትንቢት የያዘችው እውነተኛይቱ የክርስቶስ ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን ጌታዋን እንዴት ፍጹም በሆነ ክብር እንደምታስበው እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

www.zeorthodox.org

**፩ኛ. ብሥራት፡-** ጥንተ ዕለቱ መጋቢት ፳፱ ቀን ነው፡፡ ከልደት ጋር ለማክበር ተብሎም ታኅሣስ ፳፪ ይከበራል፡፡ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ክርስቶስን እንደምትወልድ ያበሠራት ዕለት ነው፡፡ በመንጸፈ ደይን ወድቆ ለነበረው የሰው ዘር ታላቅ የምሥራች የመጣበት ነውና የምሥራች ቀን (ብሥራት) ተብሏል፡፡

፪ኛ. **ልደት፡-** በትንቢተ ነቢያት የተነገረለት የሰውን ልጆች ጥንተ ተፈጥሮ የፈጠረ የእግዚአብሔር ልጅ አሁን ደግሞ በሐዲስ፣ ተፈጠሮ ለመፍጠር ማለት ሰውን ለማዳን ሰው ሁኖ የተወለደበት ዕለት ነው፡፡ ልደት በየዓመቱ የሚከበረው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ነው፡፡ በዘመነ ዮሐንስ ግን (የሉቃስ ጳጉሜን ስድስት ስለሆነች) ልደት ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ይሆናል፡፡

፫ኛ. **ጥምቀት፡-** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ፴ ዓመቱ የማዳን ሥራውን በጥምቀቱ ጀምሯል፡፡ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ እጅ ሲጠመቅ አብ በደመና ሁኖ ‹‹የምወደው የምወልደው ልጄ ይህ ነው›› ብሎ መስክሮለታል፡፡ መንፈስ ቅዱስም በጸዓዳ ርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀምጧል፡፡

- ይህ በዓል በዋዜማው ታቦታቱ ከየቤተ ክርስቲያናቸው ወጥተው በወንዝ ዳር (በሰው ሠራሽ የውኃ ግድብም ቢሆን) በዳስ በድንኳን ሆነው ያድራሉ፡፡ ሌሊት ስብሐተ እግዚአብሔር ደርሶ፣ ሥርዓተ ቅዳሴው ይፈጸማል፡፡
- ቤተ ክርስቲያን ጌታችን ለኛ ብሎ ያሳየውን ትሕትና ለመመስከር እና ለምእመናን የጌታን በረከተ ጥምቀት ለማስተላለፍ፤ በነጋታው ማለዳ በወንዝ (በግድቡ) ዳር ጸሎተ አኮቴት ተደርሶ አራቱም ወንጌላት ከተነበቡ በኋላ ውኃው ተባርኮ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይረጫል፡፡
- በበዓለ ጥምቀት የታቦታቱ ወደ ወንዝ መውረድ ጌታ በእደ ዮሐንስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ የመሔዱ ምሳሌ ነው፡፡ በመጽሐፈ ኢያሱ.፫፥፫ ***"የቃል ኪዳኑን ታቦት ካህናቱ ተሸክመውት ስታዩ ....ተከተሉት"*** በሚለው ቃል መሠረት ታቦታቱ ከመንበረ ክብራቸው ተነሥተው ስለ ክርስቶስ ማዳን እና ትሕትና እየመሰከሩ ሲባርኩን እኛም ተከትለን በክብር እናጅባቸዋለን፡፡
- በኦሪትዋ በዓለ መጸለት (የዳስ በዓል) አከባበር ድንኳን ተተክሎ ዳስ ተጋርዶ ይከበራል፡፡ የኦሪት የዳስ በዓል በጥምቀት ተተክቷል፡፡

፬ኛ. **ደብረ ታቦር፡-** ጌታችን በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን የገለጠበት ዕለት ነው፡፡ (ማቴ.፲፯፥፩-፰) ይህ በዓል በየዓመቱ ነሐሴ ፲፫ ቀን ይከበራል፡፡ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ምእመናንም -‹‹ቡሄ›› ይባላል፡፡

www.zeorthodox.org

፭ኛ. **ሆሣዕና፡-** ከትንሣኤ አንድ ሳምንት ቀድሞ በሚውለው እሑድ የሚከበር ነው፡፡ ታሪኩ በወንጌል እንደተመዘገበው፤ (ማቴ. ፳፩፥፩-፲፩) ጌታችን ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ሆሣዕና (ሆሣዕና ማለት መድኃኒት ማለት ነው) እያሉ ስላመሰገኑ ዕለቱ ተጠርቶበታል፡፡ ***"የፀበርት (የዘንባባ) እሑድም ይሉታል"*** ዘንባባ እየተባረከ ለሕዝቡ ይታደላል፤ ምእመናንም ዘንባባውን እየተቀበሉ እንደ መስቀል እየሠሩ በየቤታቸው፣ በጣታቸው እና በግንባራቸው ያደርጉታል፡፡

ከቅዳሴ በኋላ በቤተ ክርስቲያን በአራቱም ማዕዘናት አራቱ ወንጌላት ይነበባሉ። ሆሣዕና ሰርክ እስከ ትንሣኤ ያሉት ዕለታት የዓመተ ፍዳ መታሰቢያ (ሰሙነ ሕማማት) ስለሆኑ ጸሎተ ፍትሐት አይፈጸምባቸውም። ጸሎተ ፍትሐትና ጸሎተ አስተስርዮ የሚደረገው በዚህ የሆሣዕና በዓል ዕለት ነው ። በአክሱምና በአንዳንድ ቦታዎች በአህያ ሥርዓተ ዑደት ይፈጸማል፤

**፯ኛ ስቅለት** ፡-የስቅለት በዓል ለዓለም ቤዛ ሊሆን መድኃኔ ዓለም የተሰቀለበት ዕለት ነው። ከላይ እንደተገለጠው ከሆሣዕና ሰርክ ጀምሮ እስከ ትንሣኤ ያሉት ዕለታት የዓመተ ፍዳ መታሰቢያ ናቸው። በነዚህ ቀኖች አብዝቶ በመጾም፣ በስግደት፣ የጌታን መከራ ሞት የሚያስታውሱ ምንባባት ከቅዱሳት መጻሕፍት እየተነበቡ ይሰነብታሉ።

**ሐሙስ - ጸሎተ ሐሙስ** ይባላል፣ ጌታ በፍጹም ትሕትና የደቀ መዛሙርትን እግር ያጠበበት፣ ከሐዋርያት ጋር የመጨረሻዋን ራት የበላበት፣ ምስጢረ ቁርባንንም ያሳየበት ዕለት ነው። በዚህ ዕለት ካህናት የጌታችንን ምሳሌ በመከተል የምእመናንን እግር ያጥባሉ። ከጸሎተ ቅዳሴው በኋላ ምእመናን ወደየቤታቸው ሔደው ዳቦና ጉልባን ይበላሉ።

**ዓርብ ስቅለት** የጌታችን የስቅለቱ መታሰቢያ አኀበር ተሠርቶ፤ ስነ ስቅለቱን የሚመለከቱ ምንባባት እየተነበቡ ሲሰገድ ይዋላል ፣ ሰርክ ሲሆን ምእመናን ወደ ካህናት እየመጡ ። በወይራ ቅጠል እየተጠበጠቡ ቀን ሲሰግዱ ከዋሉት ሌላ ስግደት ይሰጣቸዋል። ጥብጣቤው የተግሣጽ ምሳሌ ነው። ዐሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ሠርሆተ ሕዝብ ይሆናል።

**፰ኛ. ትንሣኤ**፡- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን በመስቀል ተሰቅሎ ከሞተ በኋላ በሦስተኛው ቀን መግነዝ ፍቱልኝ፣ መቃብር ክፈቱልኝ፣ ሳይል ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት ዕለት ትንሣኤ ትባላለች። ይህች ዕለትም የኦሪቷን በዓለ ፋሲካ ተክታለች ማብራሪያውን እንደሚከተለው እናያለን።

- በዚያች እስራኤል ከባርነት ወጥተው የነጻነት ጉዞ ያደረጉባት ነበረች፤ በዚህችኛዋም(በሐዲስ ኪዳን) አዳም እና ልጆቹ ከሲኦል ባርነት ነጻ ወጥተው ገነት የገቡባት ናት።
- በዚያችኛዋ ፋሲካ ነውር የሌለበት በግ ታርዶ ሥጋውን ጠብሰው በልተውት ለነጻነት ጉዞ በረቱበት፤ ደሙንም የበሮቻቸውን ጉበን እና መቃን ቀብተውበት ሞት አለፈ። በዚህችኛዋ ፋሲካም በልቡ ተንኰል የሌለበት በአፉ ኃጢአት ያልተገኘበት ጌታችን አንድ እንኩዋን ስለ ኃጢአት የሚከስሰው ሳይኖር፤ መጥምቁ ዮሐንስ ***"የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ"*** (ዮሐ.፩፥፳፱) እንዳለው፤ ኃጢአታችንን አስወግዶ በደመ መኀተሙ ከዘላዓለም ሞት ያዳነን ፋሲካችን ክርስቶስ ተሠዋባት።
- ያኛው በግ ሲበላ ጥሬ እና ቅቅል ሳይሆን ከእሳት ጋር የተዋሐደ ጥብስ ነበር። በዚህኛው

www.zeorthodox.org

ፋሲካም ነፍስ የተለየው እሳተ መለኮት የተዋሐደውን፤ በመቃብር መፍረስ መበስበስ ያላገኘውን፤ሥጋውን በልተው ደሙንም ጠጥተውባት ምእመናነ ወንጌል የዘለዓለም ሕይወት አገኙባት። በዚህም *" ፋሲካችን ክርስቶስ "* ተባለ።፩ኛ ቆሮ.፭÷፯

ትንሣኤ ለክርስቲያኖች የድል ቀን ነው። የትንሣኤ በዓል ከሌሎች በዓላት ሁሉ በደመቀ አኳኋን ይከበራል፤ መንፈሳዊ ተመስጦም አለበት።

**በትንሣኤ ሳምንት በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ሰላምታ ልዩ ነው ፦**

- ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን ….. በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን
  (ክርስቶስ ከሙታን ተነሣ፤ በታላቅ ኃይል እና ሥልጣን)
- አሰሮ ለሰይጣን ….አግአዞ ለአዳም (ሠይጣንን አሰረው፤ አዳምን ነጻ አወጣው)
- ሰላም….እም ይዕዜሰ (ሰላም፤ ከአሁን በኋላ)
- ኮነ…..ፍሥሓ ወሰላም (ደስታ እና ሰላም ሆነ)

ከእሑድ ጀምሮ እስከ ዳግም ትንሣኤ ያሉት ዕለታት እንደ አንድ ቀን ይቆጠራሉ ፤ መዝሙሩም፣ ጸሎቱም አይለወጥም።

፰ኛ. ***ዕርገት*** ጌታ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ አርባ ቀን ለሐዋርያት እየተገለጠ ታይቷቸዋል። ትምህርትም አስተምሯቸዋል።የሐዋ.ሥ.፩÷፫ በአርባኛውም ቀን ከአርያም ኃይል እስኪያገኙ በኢየሩሳሌም ቆዩ ብሎአቸው ወደ ሰማይ ያረገበት ቀን ነው። ይህ በዓል በቤተ ክርስቲያን በጸሎት፣ በማሕሌት ይከበራል።

፱ኛ. **ጰራቅሊጦስ፡-** ጌታ ባረገ በዐርባኛው፣ በተነሣ በሃምሳኛው ቀን ለሐዋርያት በነገራቸው የተስፋ ቃል መሠረት መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው። ይህ በዓል፡-

- **በዓለ ጰራቅሊጦስ- የአጽናኙ በዓል** ይባላል። ጰራቅሊጦስ በጎን የሚቆም፣የሚረዳ፣ የሚያጽናና ማለት ነው።
- **"ጰንጠቆስጤ - ሃምሳኛ ቀን "**ተብሎም ይከበራል። ይህ በዓል በብሉይ ኪዳን የእሸት በዓል ነበር፤ ከፋሲካ ጀምረው ሃምሳውን ቀን በዓል አድርገው ይሰነብታሉ።
- በሃምሳኛይቱ ቀን በዓለ ሰዊትን (የእሸት በዓላቸውን ያከብራሉ።) በአራት እሥራኤላዊ ገበሬ ከዘራው ሁሉ በየዓይነቱ እሸቱን ቆርጦ ተሸክሞ ወደ ምኩራቡ ይመጣል። በቤተ መቅደስ የሚያገለግል ካህን ተቀብሎ ባርኮ የሚጠበሰው እየተጠበሰ፣ የሚታሸው እየታሸ በማኅበር አንድነት ይበላል። ይህም ***"ቀዳምያት"*** ይባላል።

www.zeorthodox.org

- ❖ ከማንኛውም በረከት የመጀመሪያውን በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ፤ ለእግዚአብሔር መስጠት እንደሚገባ ታዟልና ይኸው የሚፈጸምበት በዓል ነው፡፡
- ❖ በዓለ ፋሲካን ለማክበር ከዝርወት ተሰብስበው የሰነበቱ አይሁድ ሁሉ ወደ የመጠቡት የሚመለሱት ይህን በዓለ ሰዊትን ካከበሩ በኋላ ነው፡፡
- ❖ በጽርሐ ጽዮን መንፈስ ቅዱስ ለአንድ መቶ ሃያው ቤተሰብ እመቤታችን ባለችበት የተሰጣቸው በዚህች ዕለት ነበር፤ ከዝርወት የተሰበሰቡና በዚያውም የሚኖሩ አይሁድ የዳዊት ከተማ በነበረችው እና የዳዊት መቃብርም በሚገኝባት በደብረ ጽዮን መሲሕ ይመጣል ብለው ይጠብቁ ነበር፡፡ በዚች በደብረ ጽዮን በዓለ ሰዊትን ለማክበር ተሰብስበው እንዳሉ ሐዋርያት ደግሞ በዚሁ በደብረ ጽዮን በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ውስጥ ይጸልዩ ነበር፡፡
- ❖ ጌታ ባረገ በአሥረኛው ቀን ጧት መንፈስ ቅዱስ ወረደ ፤ ጌታ የነገራቸው የተስፋ ቃልም ተፈጸመ፡፡ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የሞቱና የትንሣኤው ምስክሮች ሆኑ፤ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በነሱ ላይ ሲያድር ለቤተ ክርስቲያን ጉዞ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ፡፡ ሊቀ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳለው ***"መንፈስ ቅዱስ ባይወርድላት ኖሮ የቤተ ክርስቲያን ሕልውና ኮስምኖ ቀጭጮ ይቀር ነበር፣ ስለዚህም በሚገባ አነጋገር ይህች ዕለት የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን ትባላለች፤"*** ሌሎችም ይህችን ዕለት ***የበዓላት ሁሉ እመቤት*** ይሏታል፡፡ የጰራቅሊጦስ በዓል በክርስቲያን ዓለም ሁሉ ከትንሣኤ በኋላ በሃምሳኛው ቀን ይከበራል፡፡ የትንሣኤው ቀለም እና የሃምሳ ቀን ፋሲካ የሚፈጸመው የጰራቅሊጦስ ዕለት ነው፡፡

## ማጠቃለያ

- ☙ ከእነዚህ ውስጥ ሆሣዕና፣ ስቅለት፣ ትንሣኤ፣ ዕርገትና ጰራቅሊጦስ በዓላት ዐዋድያት ስለሆኑ ወደላይ እና ወደታች ይወጣሉ ይወርዳሉ ዕለታቸው ግን አይፋለስም ፡፡ ማለትም በቀን አቆጣጠር መባቻ ሐመርን ተከትለው የሚውሉበት ቀን ከመጋቢት እስከ ሐምሌ ወራት ባሉት ቀናት ከፍ እና ዝቅ ቢሉም ፤ ሆሣዕና፣ ትንሣኤ፣ ጰራቅሊጦስ እሑድን፤ ስቅለት ዐርብን፤ ዕርገት ሐሙስን አይለቁም፡፡
- ☙ ሌሎቹ ፡- ፅንስ፣ ልደት፣ ደብረ ታቦር፣ ጥምቀት ግን ዐዋድያት አይደሉም፡፡ ዕለታቸው ግን የተፋለሰ ነውና ፤ ከሰኞ እስከ እሑድ ባሉት ቀናት ሊውሉ ይችላሉ፡፡
- ☙ የጌታችን ዓበይት በዓላት ዓለም የዳነባቸው ስለሆኑ የክርስቶስ አካሉ እና እንደራሴው ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ክብር ታስባቸዋለች፡፡

www.zeorthodox.org

- ቀድሞ ስለ ክርስቶስ ትንቢት በተነገረው፣ ምሳሌ በተመሰለው እና ተስፋ በተሰጠው መሠረትም አካሉ ክርስቶስ ዓለሙን አድኖአል፡፡ እነዚህ በዓላትም ትንቢት እና ምሳሌ ከብሉይ ያመጡ እና አካሉ መድረሱን የሚነግሩን ናቸው፡፡

## ተግባር

1. እነዚህን በዓላት ስናስብ የጌታችንን ፍቅር እና ውለታ እናስታውሳለን፡፡ የዚህ ሁሉ ተሳታፊ መሆንም አለብን፡፡
2. ‹‹*በአንዳንዶች ዘንድ ልማድ እንደሆነ በከንቱ አትመላለሱ*›› እንደተባልን፤ በዓላት የሚከበሩበትን ምክንያት እየተረዳን፣ የምንማረውን ትምህርት እና የምናገኘውን በረከት እያመንን ማክበር ይገባናል፡፡

www.zeorthodox.org

# በዓላት(፫)

## የጌታ ንዑሳን በዓላት፤ ሌሎች ዓመታዊ በዓላት እና አካባበራቸው

## ሠላሳ ዘጠነኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ተማሪዎች ስለ ጌታችን ንዑሳን በዓላት እና ሌሎች ዓመታዊ በዓላትን ምንነትና አከባበር ሥርዓት አውቀው ያስረዳሉ፡፡

### የሚጠና ጥቅስ፡-

- *" በጌታ ደስ ይበላችሁ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ፡፡"* ፊልጵ.፬፥፬
- *" በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ....የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ፡፡ "* ኢሳ.፶፮፥፭

### ምንባባት

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ) ገጽ 106 - 122

## መግቢያ

- ባለፈው የትምህርት ክፍል ጊዜ፤ ስለ ዘጠኙ ዓበይት በዓላት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እና መንፈሳዊ መሠረት የአከባበራቸውንም ሥርዓት አይተናል፡፡
- ከዘጠኙ ዐበይት በዓላት ሌላ ዘጠኝ ንኡሳን የጌታ በዓላት አሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዓመት ስለምናከብራቸው ዘመን መለወጫ እና የንግሥ በዓላትን በዛሬው ትምህርታችን እንመለከታለን፡፡
- የበዓላት አከባበራችንንም በዛሬው ትምህርታችን እንዳስሳለን፡፡

## ትምህርቱ

www.zeorthodox.org

### ሀ. ዘጠኙ ንዑሳን የጌታ በዓላት

1. **የመስቀል በዓል፡-** በየዓመቱ መስከረም ፲፯ ቀን በመላው ዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች የሚከያብሩት በዓል ነው፡፡ ምክንያቱም ንግሥት እሌኒ የጌታችንን መስቀል ለሦስት መቶ ዓመታት ከተቀበረበት ያወጣችበት ነው፡፡

2. **ስብከት፡-** ነቢያት ‹‹ይወርዳል ይወለዳል ያድነናል›› ብለው የሰበኩለት የእግዚአብሔር ልጅ እንደተወለደ ይዘመራል ፤ቅዱስ ያሬድም ለዚህ ሰሞን ባዘጋጀው መዝሙሩ፤ ከነቢያቱ ጋር ***“ወልደ መድኅነ ንሰብክ - አዳኝ የሆነውን ልጁን እንሰብካለን ”*** ይላል፡፡ የነቢያቱን ስብከት የሚያመለክቱ ምንባባትም ይነበባሉ፡፡ መዝ.፻፵፫÷፯

3. **ብርሃን፡-** ነቢያቱ ***“ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ - ብርሃንህን እና ጽድቅህን ላክልን”*** መዝ.፵፪÷፫ ብለው የተነበዩለት፤ ***“ ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር፡፡”*** ዮሐ.፩÷፱ ተብሎ ከልደቱ በፊት እንደ ዋዜማ የሚታሰብበት ሳምንት ነው፡፡ ያ ብርሃን “ ***በዓለም ነበረ ዓለሙም በእርሱ ሆነ ዓለሙም አላወቀውም፡፡”*** ዮሐ.፩÷፱-፲ ነበርና፤ ቤተ ክርስቲያን የማሳወቅ ሥራዋን ሳታቆም በንባብ አጉልታ፣በስብከት አስፍታ፣በልዕል ዜማም ***“ አቅዲሙ ነገረነ በኦሪት - አስቀድሞ በኦሪት ነገረን ”*** ትላለች፡፡

4. **ኖላዊ፡-** ነቢያት ትንቢት የተሰበከለት የዓለም ብርሃን፣ የነፍሳት ጠባቂ ቸር እረኛ እንጂ ከእርሱ በፊት እና በኋላ እንደመጡት ነጣቂ ተኩላ አይደለም፡፡ ለማለት በቤተ ክርስቲያናችን በመዝሙርና በጸሎት ሥርዓት ሳምንቱ ይታሰባል፡፡

**የሦስቱም (ስብከት፣ ብርሃን እና ኖላዊ) አከባበራቸውም በቤተ ክርስቲያን ቀለም(ምንባባት እና መዝሙራት) እንጂ ልዩ ሥርዓት የላቸውም፡፡**

5. **ግዝረት፡-** ይህ በዓል የሚውለው ጥር ስድስት ቀን ነው፤በሙሴ ሕግ እንደተጻፈ፡፡ ዘሌ.፲፪÷፫ ሕፃን ሲወለድ በስምንት ቀኑ ይገረዛል፡፡ይህን የሙሴን ሥርዓት ለመፈጸም ጌታ በተወለደ በስምንት ቀኑ ወደ ቤተ ግዝረት መሄዱ ይታሰባል፡፡

6. **ልደተ ስምዖን፡-** ጌታችን ሕግ መጽሐፋዊን መፈጸሙን የምናስብበት በዓል ነው፡፡ዕለቱም በተወለደ በአርባ ቀኑ የሚከበር ነው፡፡ ሉቃ.፪÷፳፪-፴፰፣ ዘሌ.፲፪፣ ዘጸ.፲፫÷፪

የእሥራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ የነበረው ስምዖን አረጋዊ የተባለ የእግዚአብሔር ሰው በኢየሩሳሌም ነበር፡፡ እሱም መሲሕን ሳያይ እንዳይሞት ከመንፈስ ቅዱስ ተረድቶት ነበርና፤ ጌታችንን አይቶ እግዚአብሔርን አመሰገነ፡፡ ስለጌታ እና ስለ እመቤታችንም ተነበየ፡፡

ጌታችን ወደ ቤተ መቅደስ የገባበትና በስምዖን ዕቅፍ የታየበት ዕለት በቤተ ክርስቲያን ይከበራል፡፡ ስምዖን ጌታን በታቀፈ ጊዜ ከእርጅናው መታደሱ ስለሚነገር በዓሉ የጌታ ሁኖ ሳለ ‹‹***ልደተ ስምዖን***›› እያልን እንጠራዋለን ፡፡ ሌሎቹ ***"የጌታ ወደ ቤተ መቅደስ መቅረብ"*** ይሉታል፡፡

www.zeorthodox.org

7. **ቃና ዘገሊላ፡-**ቃና በገሊላ የምትገኝ ቀበሌ ናት፤በዚች ቀበሌ ውስጥ ጌታ በሰርግ ቤት ተገኝቶ የመጀመሪያውን ተአምር፤ ውኃውን ወደ ወይን የለወጠበት ቀን ስለሆነ እናከብረዋልን፡፡

8. **ደብረ ዘይት** ወይራ የሞላበት ተራራ ማለት ነው፡፡ የሚገኘውም ከኢየሩሳሌም በስተ

ምሥራቅ ጥቂት ኪሎ ሜትሮች ራቅ ብሎ ነው፡፡ ጌታ ቀን በቤተ መቅደስ ሲያስተምር፤ደቀመዛርቱ የዳግም ምጽአቱን ምልክት በጠየቁት መሠረት የመምጣቱን ምልክት ያስተማረበት ቦታ ነው፡፡

- ❖ ይህ በዓል ከሌሎቹ ተለይቶ ወደ ፊት የሚሆነው የሚታሰብበት ሲሆን፤ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድም የዓቢይ ጾምን እኩሌታ እሑድ የጌታ ዳግም ምጽአት መታሰቢያ አድርጎ መዝሙሩን በዳግም ምጽአት ጽፏል፡፡
- ❖ በዚህ ቀን ጌታችን ሲመጣ ‹‹***ብራብ አብልታችሁኛል***›› የሚለውን በማሰብ ለሌላቸው በማካፈል ይታሰባል፡፡

9. **የመጋቢት መስቀል** የሚውለው መጋቢት ዐሥር ቀን ሲሆን፤ ንግሥት ዕሌኒ በመስከረም ወር ማስቆፈር ጀምራ መስቀሉ የወጣበት ነው፡፡

**ለ. ዐውደ ዓመት**

- ❖ በብሔራዊ ደረጃ የሚከበረው ይህ በዓል፤ በቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ዮሐንስ ይባላል፡፡ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር አዲስ ዓመት የሚጀመረው መስከረም አንድ(፩) ቀን ነው፡፡ በዓሉ፡- ርእሰ ዐውደ ዓመት፣ ቅዱስ ዮሐንስ፣ ዘመን መለወጫ፣ ዕንቁጣጣሽ የሚሉ መጠሪዎች አሉት፡፡
- ❖ ርእሰ ዐውደ ዓመት በዓመቱ ውስጥ የሚገኙ በዓላት ሁሉ ርእስ መሆኑን ለመግለጥ የተሰጠው ስያሜ ነው፡፡
- ❖ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ በዘመነ ብሉይ እና በዘመነ ሐዲስ መሸጋገሪያ የነበረ በመሆኑ የዘመናት ለውጥ በእርሱ ተሰይሞአል፡፡ ዘመን መለወጫ አዲሱን ዓመት፤ዕንቁጣጣሽ ደግሞ የአበቦችን ማሸብረቅ የሚያመለክት ስያሜ ነው፡፡
- ❖ በዘመነ ብሉይ በእኛ መስከረም እና ጥቅምት ወራት አካባቢ መለከቶች የሚነፉበት በዓል (በዓለ መጥቅዕ) ሲከበር፡፡ ዐዋጅ የሚነገርበት እና እህል የሚከማችበት በዓል ነበር፡፡ ዘኁል.፳፥፩-ፍጻሜ ምዕራፍ፤ ዘሌዋ.፳፫፥፳፫-፳፰
- ❖ በዘመነ ሐዲስም፤ የዘመነ ብሉይ መደምደሚያ የዘመነ ሐዲስ መንገድ ጠራጊ ዮሐንስ የጌታን መንገድ ጥረጉ የሚል ዐዋጅ እየነገረ መጣ፡፡ በቤተ ክርስቲያንም መምህራን በመስከረም ፩ ቀን ስለዓመቱ በዓላት እና አጽዋማት ያውጃሉ፤ ጸሎተ አስርቆት ያደርጋሉ፡፡ በዚህም የዘመኑን መለወጥ ያበሥራሉ፡፡
- ❖ ከዚህም ጋር አሮጌውን አሳልፎ አዲስ የተስፋ እና የሥራ ዘመን የሰጠንን የዘመናት ፈጣሪ እና ሰጪ እግዚአብሔርን እናመሰግንበታለን፡፡

www.zeorthodox.org

**ሐ. ዓመታዊ የንግሥ በዓላት**

- በቤተ ክርስቲያን በዓመታዊ በዓልነት የሚታሰቡ የንግሥ በዓላት አሉ፡፡ እነዚህም **" *እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ* "** ማቴ.፳፰÷፳ ያለን ጌታ ራሱ ተገልጦ እና በቅዱሳኑ አማካይነት የሠራቸው ድንቅ ሥራዎች የሚታሰቡባቸው በጌታችን እና በቅዱሳን ስም የሚከበሩ በዓላት ናቸው፡፡
- በቤቱ ስማቸው እንዲጠራ እና መታሰቢያቸው እንዲደረግ የፈቀደውም እርሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ***"በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ....የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ፡፡ "*** ኢሳ.፶፮÷፭
- በዚህ መሠረት በዓመት ፴፫ የእመቤታችን መታሰቢያ በዓላት፤ እንዲሁም የመላእክት፣የቅዱሳን አበው እና እማትም በዓላት አሉ፡፡ ታቦታቸው በተቀረጸበት ስማቸው በተሰየመበት ይከበራሉ፡፡

**መ. የበዓላት አከባበር**

- አንዳንዶች በዓላት ሥራ ፈት ያደርጋሉ ሲሉ ሌሎቹም በዓል ማክበር ተቀምጦ መዋል ይመስላቸዋል፡፡
- **የአይሁድ** ሊቃውንት ስለ ሰንበትም ሆነ ስለሌሎች በዓላት ክብር ብዙ ዓይነት አተረጓጎም ነበራቸው፡፡ ***"ሰንበትን አክብር"*** የሚለውን ቃል ለመፈጸም የጉልበት ሥራ መሥራት ቀርቶ መንቀሳቀስ አይፈቅዱም ነበር፡፡
- ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን፡-***"አይሁድ በዕለተ ሰንበት ወደ ሽንት ቤት እንኳን አይሄዱም ነበር"*** ይላል ፡፡ አከባበራቸው ***"ኢታንሥእ እደዊከ ወእገሪከ - እጅ እና እግርህን አታንሣ"*** ነውና አደጋ ቢደርስ ፣ ሰው ቢሞት፣ጦር ቢመጣ ሰንበት ከሆነ መንቀሳቀስ ክልክል ነው፡፡ ለምሳሌ በመቃብያን ዘመን ብዙ ሺሕ አይሁዳውያን በአንድ ቀን ያለቁት በሰንበት ነበር፡፡
- **አረማውያንም** አማልክቶቻቸው ብዙ እንደመሆናቸው ብዙ በዓላት አሏቸው፡፡ አከባበራቸውም እንደ አምልኮታቸው ከፍርሃት የመነጨ እንጂ መጽሐፋዊ ስላልሆነ በዘፈን፣ ዝሙትን በመፈጸም፣ ሰውነትን በመጥባት እና ለጣዖታት በመሠዋት ያከብራሉ፡፡ ስጦታ መለዋወጥ እና ግብዣም የክብረ በዓላቱ አካላት ናቸው፡፡
- ***"እጅ እና እግርህን አታንሣ"*** የሚል ትእዛዝ ያልነበራቸው ከአረማዊነት የተመለሱት ክርስቲያኖች በዓል የሚያከብሩት ሥራ ፈትቶ ተቀምጦ በመዋል አይደለም ፡፡ ለምሳሌ፡- በዓሉ የቅዱስ ጊዮርጊስ ከሆነ የጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባለበት ቅዳሴ ይቀደሳል ምእመናንም ያስቀድሳሉ ፣ ቅዱስ ቁርባን ይቀበላሉ፣ ከጸሎተ ቅዳሴው ፍጻሜ በኋላ በጊዮርጊስ ስም የተሰየሙት ከቤታቸው ተቀምጠው ወዳጅ ዘመዶቻቸው ***"የክርም ሰው ይበልህ"*** እያሉ

www.zeorthodox.org

የሚያመጡላቸውን ስጦታ ሲቀበሉ ሲመጸውቱ፣ ሲያስታርቁ መልካም ተግባራትን ሲያከናውኑ ይውላሉ፡፡

- ቤተ ክርስቲያን የበዓላት አከባበር እንደ አይሁድ በጫና እንደ አሕዛብ በገቢረ ኃጢአት እንዳይሆን ታስተምራለች፡፡ *"ኢይደልዎሙ ለክርስቲያን ከመ ያፅርዑ ተገብሮ በዕለተ ሰንበት ከመ አይሁድ፣ አላ ይትገበሩ በውእቱ ዕለት ከመ ክርስቲያን፡፡ ወለእመ ተረክቡ እምሕዝብ ንዘ ይገብሩ ግብረ አይሁድ ውእቶሙ ይከውኑ ስዱዳነ እምቅድመ ገጹ ለክርስቶስ፤ ክርስቲያን እንደ አይሁድ በዕለተ ሰንበት ተግባርን ማጉደል አይገባቸውም በዚያች ቀን እንደ ክርስቲያን ይሥሩ እንጂ፡፡ ከሕዝቡ ወገን የአይሁድን ሥራ ሲሠሩ ቢገኙ እነርሱ ከክርስቶስ ፊት የተለዩ ይሆናሉ ፡፡" " ወኢትትዓቀቡ ሰንበተ ከመ አይሁድ - እንደ አይሁድ ሰንበትን አትጠናቀቁ "* (ፍ.ነ. 19፡713)ሲል ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ያዝዘናል፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስም በቅዳሴው፤ *"ወዕረፍትሰ አኮ በሰኪብ ከመ ዘሀመ በደዌ ፣አላ በትጋሀ መዓልተ ወሌሊተ ከመ ንኩን ፍቁራኒሃ ለዛቲ ዕለት፤ ዕረፍት እንደታመመ በመተኛት ሳይሆን ቀን እና ሌሊት በመትጋት የዕለቲቱ ወዳጆች በመሆን ነው "* ይለናል፡፡
- ከዚህ ወጪ አያት ቅድመ አያቱ የሚያከብሩትን ልጁ የልጅ ልጁ የአባቴ፣ የአያቴ ታቦት ነው እያሉ በየወሩ ቢያከብሩ በግል ፍቅራቸው እንጂ የቤተ ክርስቲያን ውሳኔ አይደለም፡፡
- ቤተ ክርስቲያን በቀኖናዋ ሰፍራ ቆጥራ ያስተማረችው የጌታ፤የእመቤታችን ፤ የመላእክትና የቅዱሳን በዓላት የተወሰኑ ናቸው፡፡ ሁሉም በዓላት ሥራ በመተው ይከበሩ አልተባለም፤ ምክንያት እየፈጠሩ ተቀምጦ መዋልም የቤተ ክርስቲያን ትምህርት አይደለም፡፡
- በበዓላት ማናቸውንም ሥራ የማይሰሩ፡፡ ሌላው ቀርቶ በሰንበታት የተቀዳ ውኃ ፣ የተወቀጠ ቡና የማይጠጡ፣ ወንዝ የማይሻገሩ፣ የግብርናውንም ሆነ የባለሞያን ሥራ በቤት ውስጥ የሚሠራውንም ሥራ መሥራት (ቅጠል መበጠስ፣ መጽሐፍ መጻፍ፣ መደጎስ፣ ልብስ ማጠብ) በዓል እንደመሻር እየቆጠሩ ቁጭ ብለው የሚያሳልፉ ክርስቲያኖች አሉ፡፡ ይህ ሁሉ አይሁዳዊ ልማድን የያዘ የሕዝብ ልማድ እንጂ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት የተደነገገ አይደለም፡፡

www.zeorthodox.org

**በቤተ ክርስቲያን ትውፊት በዓላት የሚከበሩት፡- ዋዜማ ተቁሞ፣ሌሊት በማኅሌት፣ቀን በቅዳሴ** እና ታቦት ወጥቶ ነው ፡፡ ምእመናንም እንደሚከተለው ይሳተፋሉ፡፡

1. በንግሥ፤ ከዋዜማው ጀምሮ በማኅሌት ፤ በቅዳሴ ፤በታቦት ዑደት፤ በዓሉን የሚመለከት ቃለ እግዚአብሔር በማስተላለፍ ተከናውኖ በሰርሆተ ሕዝብ ይፈጸማል፡፡ በዚህም ምእመናን ይሳተፋሉ፤ ቡራኬ ይቀበላሉ፤ በቃለ እግዚአብሔር የነፍሳቸውን ስንቅ ይይዛሉ፡፡

2. **በምሥጋና፤** በመዝሙር ***"በዓል የሚያደርጉ ሰዎች የደስታና ምስጋና ቃል አሰሙ።"*** መዝ.፵፩(፵፪)፥፬ ተብሎ እንደተጻፈ፤ እግዚአብሔር በዕለቱ የሠራውን በማሰብ የሚቀርብ ምሥጋና አለ። ካህናቱ እና መዘምራኑ በቅዳሴ እና በቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማ ሲያመሰግኑ ምእመናን በእልልታ እና በሽብሸባ አምላካቸውን ከካህናቶቻቸው ጋር ያከብሩታል።

3. ***መልካም በማድረግ፤*** *መድኃኒታችን ኢየሱስ* ክርስቶስ ***"በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዶአል"*** ማቴ.፲፪፥፲፪ ሲል በቃሉ አስተምሮ በተግባር ድሆችን እየጎበኘ፣ ቅዱስ ቃሉን እያስተማረ፣ ሕሙማንን እየፈወሰ እንዳሳየን፤ በዓላት በባለቤቱ በእግዚአብሔር ወይም በሚታሰበው ቅዱስ ስም ምጽዋት በመስጠት፣ በማስታረቅ፣ የታመመን በመጠየቅ፣ የታሰረን በመጎብኘት ይከበራሉ።

4. **በጸሎት በማሰብ፤** በዕለቱ የሚታሰበውን በዓል ምክንያት በማድረግ የቻለ በቤተ ክርስቲያን የሚደረገውን የማኅበር ጸሎት፤ ያልቻለም ባለበት በማመስገን ምልጃን በመማጸን ያከብራል።

5. **በመዘከር፤** *ጌታ* ***"ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቼ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ ÷እውነት ዋጋው አያጠፋበትም " ማቴ.፲፥፵*** ባለን አማናዊ ቃል መሠረት በዕለቱ በሚታሰበው ቅዱስ(ት) ስም እንደአቅም ከጣሳ ውኃ ጀምሮ በመስጠት የቅዱሱ ወይም የበዓሉ መታሰቢያን በረከት ለማግኘት በመማጸን ይታሰባል።

6. በቅድሳት ሥዕላት ፊት መብራት በማብራት የእግዚአብሔርን የባሕርይ ብርሃንነት እና ቅዱሳን በተጋድሎ እና በጸጋ የደረሱበትን ብርሃንነት በማሰብ እና በመመስከር ይታሰባል።

## ማጠቃለያ

- ዘጠኙ ንዑሳን በዓላት፣ የንግሥ በዓላት እና ዘመን መለወጫ በቤተ ክርስቲያን እና በሀገር ደረጃ በዓመት የሚከበሩ በዓላት ናቸው።
- በዓላት መንፈሳዊ በረከት የምናገኝባቸው፣ ዕረፍተ ነፍስ የምናደርግባቸው፣ የደስታ እና የምሥጋና ቀናት ናቸው።
- አከባበራችንም እንደ በዓላቱ ቢለያይም በመንፈሳዊ ሥራዎች የሚታሰቡ ናቸው።

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- ተማሪዎች የበዓለ መስቀልን አከባበር ጠይቃችሁ የተረዳችሁትን በክፍል ውስጥ አብራሩ።
- ዘጠኙን ዐበይት እና ንዑሳን በዓላት አጥንታችሁ በቃላችሁ ያዙ።

# አባሪ ትምህርት

## በዓለ መጥቅዕ

በዘመን ብሉይ ሕዝበ እሥራኤል ከግብጽ ነጻ የወጡበትን ወር የመጀመሪያ ወር ብለው ያከብሩ ነበር። ይህንንም ወር አቢብ (ኒሳን) ይሉታል። በእኛ መጋቢት እና ሚያዚያ ወራት ላይ ይውላል። ከዚህ ወር ጀምሮ ያለውን ሰባተኛ ወር ኤሉል ወይም ኤታኒም (ቶስሪ) የተባሉት ወራት መሐል (በኦሪት ሰባተኛው ወር ተብሎአል) የእኛን መስከረም እና ጥቅምት ወራት እናገኛለን። በዚህ በሰባተኛው ወር አራት በዓላት እንዲያከብሩ ልዑል እግዚአብሔር ***"በሰባተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን ዕረፍት÷በመለከት ድምፅ መታሰቢያ÷የተቀደሰ ጉባኤ ይሁንላችሁ።"*** ብሎ ባዘዛቸው መሠረት የሚከበሩ እና የሐዲስ ኪዳን ምሳሌ ጥላ የሆኑ በዓላት ነበሩ። እነርሱም፦

1. ***መለከቶች የሚነፉበት ቀን (በዓለ መጥቅዕ)፦*** በወሩ የመጀመሪያው ቀን ነው፤ መለከት ዓዋጅ መንገሪያ እንደሆነ ለንስሐ የሚዘጋጁበት ወቅት ነበር። በምሥራቹ ዘመንም ዓዋጅ ነጋሪው መጥምቁ ዮሐንስ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ብሎ እየጮኸ በዮርዳኖስ ማዶ ጮኸ። ሉቃ.፫÷፩-፲፯፣ ማር.፩÷፩-፰

2. የማስተስረያ ቀን በወሩ በዐሥረኛው ቀን ራሳቸውን በማዋረድ ሰውነታቸውን በንስሐ የሚያስጨንቁበት እና የማስተስርያ ቁርባን የሚያቀርቡበት ቀን ነው። ዘኍ.፳፱÷፯-፲፩ ዮሐንስም ለሥጋ አስጨናቂ የሆነችውን ንስሐ ሕዝቡ እንዲገቡ አድርጎአል። ራስን በእግዚአብሔር ፊት ማዋረድንም አስተማሮአል። ማቴ.፫÷፩-፲፬

3. የዳስ በዓል በወሩ ከ፲፰-፳፩ኛው ቀናት። እህል ከተከማቸ በኋላ ለእግዚአብሔር በዳስ ውስጥ ለሰባት ቀናት ምሥጋና የሚቀርብበት በዓል ነው። ዳስ ጊዜያዊ ቤት ነው፣ በበረሐው ውስጥ የሚታረፍበት እና ምሥጋና የሚቀርብበት ነበር። ንስሐ የገቡ  ምእመናን ድንኳን በሆነው ምድራዊ መኖሪያቸው ያከማቹትን ለእግዚአብሔር ክብር ያውሉታል፤ በቤተ ክርስቲያን ጥላ ይኖራሉ። ፪ኛ.ቆሮ.፰÷፩-፰፣ ዘሌ.፳፫÷፴፫፣ዘኍ.፳፱÷፲፪

የተቀደሰ ጉባኤ በወሩ በሃያ ሁለተኛው ቀን፤ ***" በስምንተኛውም ቀን (ለዳስ በዓል መጀመሪያ) የተቀደሰ ጉባኤ ይሁንላችሁ÷.....ዋና ጉባኤ ነው። የተግባር ሥራ ሁሉ አታድርጉበት።"*** ዘሌ.፳፫÷፴፮ እንደተባለ፤ በስምንተኛው ሺሕ ጌታችን ሲመጣ የተቀደሰው ትንሣኤ ዘጉባኤ ይደረጋል። ያን ጊዜም ***"እንግዲያስ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶላቸዋል።"*** ዕብ.፬÷፱ የተባለውን እውነተኛውን ዕረፍት የመጠበቅ በዓል ነው።

www.zeorthodox.org

በጠቅላላው ወሩ በመለከት ዓዋጅ የሚጀመር፤ ስርየት በንስሐ የሚጠይቁበት እና እህል ከተከማቸ በኋላ ለሰባት ቀናት በድንኳን ውስጥ አምላካቸውን እያመሰገኑ ሰንብተው በስምንተኛው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ የሚያከብሩበት የረጅም ቀናት በዓል ወቅት ነበር፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህን በዓል ለማክበር ወጥቶ ነበር፡፡ ዮሐ.፯፥፪ እና ፲

ቤተ ክርስቲያንም የዘለዓለምን ዕረፍት እንድናገኝ ከጌታችን ምርጥ ዕቃ ጋር ሆና፤ ***"እንግዲህ እንደዚያ እንደ አለመታዘዝ ምሳሌ ማንም እንዳይወድቅ ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንትጋ፡፡"*** ዕብ.፬፥፲፪ ትለናለች፡፡

www.zeorthodox.org

# በዓለ ሃምሳ በወጣቶች ሕይወት

## አርባኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ከትምህርቱ በኋላ፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለይተውና በሕይወታችን እንዴት መቀበል እንደምንችል አውቀው በክፍል ውስጥ ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** ‹‹በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም፡፡›› /ሮሜ ፭፥፭/

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** የሐዋ.ሥራ ፪፥፩-፲፪፣ ገላትያ ፭፥፲፮-፳፮

### መግቢያ፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተነሣ በሃምሳኛው ቀን በዐረገ ደግሞ በዐሥረኛው ቀን ቅዱሳን ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን እንደ ተቀበሉ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ይነግረናል፡፡ ጌታ ሐዋርያት ኃይልን እስኪለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አስቀድሞ ነግሯቸው ነበር፡፡ "እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ፡፡" /ሉቃ ፳፬፥፵፱/ ቅዱሳን ሐዋርያት በእምነትና በጸሎት እየተጉ ጌታ የሚልክላቸውን አጽናኙን መንፈስ ይጠባበቁ ጀመር፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ ታማኝ ስለሆነ ጌታ እንደተናገረው አጽናኙ መንፈስ ወደ ሐዋርያት መጣ፣ ልዩ ልዩ ጸጋንም ተቀበሉ፡፡ መንፈስ ቅዱስም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ስለነበር ወንጌልን ሳይፈሩ ሰበኩ፣ብዙ ሕሙማንን ፈወሱ፣ ብዙ ድንቃድንቅ ተአምራትንም አደረጉ፡፡ በአገልግሎታቸውም እግዚአብሔርን እያከበሩ ብዙ ነፍሳትን ለክርስቶስ ማረኩ፡፡ በዚህ ትምህርት መንፈስ ቅዱስ ዛሬም በእኛ ሕይወት እንደሚሠራ እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

#### 1. ወጣቶች መንፈስ ቅዱስን አታሳዝኑ /አትቃወሙ/፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ክፉ ነገሮችን በመሥራት መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን እንደማይገባ በመልእክቱ ይመክረናል፡፡ "ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ

አታሳዝኑ፡፡" /ኤፌ ፬÷፴/ ኦርቶዶክሳዊያን ክርስቲያኖች ወንዶች በአርባ ቀን ሴቶች በሰማኒያ ቀን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ በጥምቀት ተቀብለናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ዘወትር ለጸሎትና ለምስጋና እንዲሁም ለበጐ ነገሮች እንድንተጋ ይረዳናል፡፡ የተለያዩ ስጦታዎችንም ይሰጠናል፡፡ ነገር ግን ለመንፈስ ቅዱስ የማንታዘዝና በገዛ ምኞታችን የምንመራ ስንሆን መንፈስ ቅዱስ ያዝናል፡፡ ክፉ ነገሮችን በማድረጋችንም በውስጣችን ያለውን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ እንቃወማለን፡፡ ኃጢአት ስንሠራ፣ ሐሰትን ስንናገር፣ ክፉ ቃል ስንናገር፣ ስንቆጣና ስንሳደብ በውስጣችን ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚያዝን ተረድተን ከእነዚህ ተግባራት ልንርቅ ይገባል፡፡

ወጣቶች እውነትን ከመከተል ሐሰትን ምርጫችሁ ስታደርጉ፣ ከፍቅር ጥላቻን፣ በጐ ቃልን ከመናገር ስድብን ስትከተሉ መንፈስ ቅዱስን እየተቃወማችሁ እንደሆነ ተገንዘቡ፡፡

## 2. መንፈስ ቅዱስን እንዴት እንቀበላለን?

መንፈስ ቅዱስን የምንቀበልባቸው የተለያዩ መንገዶች ቢኖሩም ዋና ዋናዎቹን በዚህ ትምህርት እንመለከታለን፡፡

### 2.1. በጸሎት፡-

ዘወትር በጸሎት በመትጋት እግዚአብሔር ቅዱስ መንፈሱን እንዲሰጠን እንጠይቃለን፡፡ ቅዱስ ዳዊት በጸሎት የእግዚአብሔርን መንፈስ ጠይቋል፡፡ "አቤቱ ንጹሕ ልቡና ፍጠርልኝ፤ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ፤ ከፊትህ አትጣለኝ፤ ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ፡፡" (መዝ. ፶/ ፶፩/÷፲-፲፩) ስለዚህ በጸሎት የእግዚአብሔርን መንፈስ ልንጠይቅና ልንቀበል ይገባናል፡፡

### 2.2. መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ፡-

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው ቅዱሳን ሰዎች የጻፉት መጽሐፍ ነው፡፡ ቃሉ የፈጣሪ ድምፅ በመሆኑ ስናነበው መንፈሱ ያድርብናል፣ በቃሉ ይወቅሰናል፣ በቃሉ ያድነናል፣ሕይወትም ይሰጠናል፡፡

### 2.3. ሥርዓተ አምልኮን ስንፈጽም፡-

www.zeorthodox.org

በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙትን ሥርዓተ አምልኮዎች ለምሳሌ ቅዳሴ ስናስቀድስ፣ ቅዱስ ቁርባን ስንቀበል፣ በጸሎትና በምስጋና ስንካፈል እግዚአብሔር ቅዱስ መንፈሱን ይሰጠናል፡፡

## 3. መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች

### 3.1. ለእግዚአብሔር ቃል እና ለሕጉ በመገዛት፡-

ክርስትና እንደ እግዚአብሔር ቃል መኖር ነው፡፡ እንደ ቃሉ መኖር ለመጽሐፍ ቅዱስ ሕግ መገዛትን፣ ለቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ተገዢ መሆንን እና ለንስሓ አባታችን ታዛዥ መሆንን ያጠቃልላል፡፡

### 3.2. ክርስቶስን በመውደድና በማፍቀር፡-

ለክርስቶስ ያለን ጥልቅ ፍቅር ዘወትር ከእርሱ ጋር በጸሎት በመነጋገር፣ በቃላችን እና በሥራችን ስሙን በመመስከር እንዲሁም ድሆችን በመውደድና በመንከባከብ ይገለጻል፡፡

### 3.3. ራሳችን በመግዛትና እኔነትን በመካድ፡-

ሐሳባችን፣ ስሜታችንና ተግባራችን በመግዛት እንዲሁም እኔነትን በመካድ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ራሳችንን እናዘጋጃለን፡፡

## 4. የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች

ለቤዛ ቀን የታተምንበት ቅዱስ መንፈስ እንዳለን እና በሕይወታችን እየሠራ እንደሆነ የምናውቀው በፍሬው ነው፡፡ ወጣቶች የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ከሆናችሁ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴያችሁ የመንፈሱ ፍሬ የሚታይ ሲሆን በተቃራኒው መንፈሱ ከሌላችሁ እንዲሁ በንግግራችሁ እና በሥራችሁ ይታወቃል፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ እንዳለ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትና የሌለበት ሰውም በተግባሩ ይታወቃል፡፡ (ማቴ ፯፥፲፮-፳) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የሥጋና የመንፈስ ሥራዎችን በመልእክቱ ላይ ዘርዝሯቸዋል፡፡ (ገላትያ ፭፥፲፮-፳፮) ስለዚህ የመንፈስ ፍሬዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

4.1. ፍቅር
4.2. ሰላም
4.3. ደስታ
4.4. እምነት
4.5. ትዕግሥት
4.6. ቸርነት
4.7. በጎነትና ልግስና
4.8. የዋህነት
4.9. ራስን መግዛት

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች በዚህ ትምህርት ሐዋርያት በሃምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ በእግዚአብሔር የተወደደ አገልግሎትም እንዳገለገሉ ተምራችኋል፡፡ እናንተም እግዚአብሔር የሚከብርበትን ሥራ እንድትሠሩ ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ ከሚያሳዝን ክፉ ተግባር በመራቅ የመንፈሱን ሥራ ለመሥራት ትጉ፤ በሕይወታችሁም የመንፈስን ፍሬ አፍሩ፡፡

## ተግባር፡-

- ወጣቶች በመንፈስ ፍሬዎች ላይ አንድ በአንድ እንዲወያዩ መምህሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡
- የክፍሉን ተማሪዎች በተለያዩ ምድቦች በመክፈል በመንፈስ ፍሬዎች ስያሜ እንዲጠሩ በማድረግ በቤተ ክርስቲያን የተለያዩ በጐ ሥራዎችን እንዲሠሩ ያድርጓቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ማሽኮርመምና መሽኮርመም

## አርባ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች እግዚአብሔር የሚፈቅደውን የወንድና የሴት ግንኙነት እንዲሁም የማሽኮርመም እና መሽኮርመምን ምንነት አውቀው ያብራራሉ፤ ራሳቸውንም ይጠብቃሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ፤ በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርን፣ ሰላምን አጥብቀህ ተከተል፡፡" ፪ጢሞ. ፪፥፳፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፴፱፥፩-፲፪፣ ዘፍ. ፳፱፥ ፱-፴

### መግቢያ፡-

ወጣቶች የወጣትነት ዕድሜ በሕይወታችን ውስጥ ወሳኝ ዕድሜ ነው፡፡ በወጣትነት ዕድሜያችን የተለያዩ አካላዊ ለውጦች ይከሠታሉ፡፡ ከእነዚህ ለውጦች መካከል ወጣቶች በተቃራኒ ጾታ መሳብ፣ ለመወደድና አድናቆትን ለማግኘት ልዩ ጥረት ማድረግ ይገኙበታል፡፡ ይህ ክሥተት ገደብ ካልተበጀለት እና ወጣቶች ራሳቸውን መግዛት ካልቻሉ ወደ አልተፈለገ ምግባር ሊመራቸው ይችላል፡፡ በተለይ በዚህ ዘመን ወጣቶች ከተለያየ አቅጣጫ በሚደርስባቸው ተፅዕኖ እና አካባቢያቸውን ለመምሰል ሲሉ በመሽኮርመምና በማሽኮርመም ሕይወት ውስጥ ገብተው ይገኛሉ፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

#### 1. ክርስቲያናዊ ያልሆነ ማሽኮርመምና መሽኮርመም

- ጊዜያዊ ደስታ ለማግኘትና ስሜትን ለማርካት ከተቃራኒ ጾታ ጋር የሚመሠረት ጊዜያዊ ግንኙነት ነው፡፡
- በፍጥነት ወደ ወሲባዊ ግንኙነት የሚያመራ ነው፡፡
- ዘላቂ ዓላማ እና ሓላፊነት የሌለበት ግንኙነት ነው፡፡
- በጊዜያዊ የሥጋ ጥቅምና ፍላጎት ላይ ብቻ የሚመሠረት ነው…. ወ.ዘ.ተ፡፡

www.zeorthodox.org

## 2. ክርስቲያናዊ ያልሆነ ማሽኮርመም አደጋዎች

- የተቃራኒ ጾታ አካላዊ ማንነት ወይም ውጫዊ ውበት ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ፡፡
- ተቃራኒ ጾታን የስሜት ማብረጃ እና መጠቀሚያ እቃ አድርጎ ማሰብ፡፡
- ሌሎችን ለመሳብ እና ጎልተን ለመታየት በምናደርገው ጥረት ሥርዓት ያጣ አለባበስን ስለምናዘወትር ለተለያዩ ጾታዊ ትንኮሳዎች መጋለጥ፡፡
- ለትምህርታችን ትኩረት ማጣት እና በውጤት መቀነስ፡፡
- ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ቸልተኛ መሆን፡፡

## 3. በሐሳብ (በልብ) ማመንዘር

ማንኛውም ተግባር የሚጀምረው ከሐሳብና ከምኞት ነው፡፡ ምኞት እያደር ወደ ኃጢአት የሚያድግ የኃጢአት ፅንስ ነው፡፡ /ያዕ. ፩÷፲፬-፲፭/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ምኞት የአመንዝራነት ፅንስ መሆኑን አጽንዖት ሰጥቶ አስተምሯል፡፡ ይህ የብዙ ወጣቶች ችግርም ነው፤ ብዙ ወጣቶች ራሳቸውን ሥጋዊ ፈቃድን ከመፈጸም ቢቆጥቡም ዘወትር በወሲባዊ ሐሳብና ምኞት ተጠምደው ይገኛሉ፡፡ /ምሳል ፮÷፳፭ ፣ማቴ. ፭÷፳፰/

## 4. ወሲባዊ ምኞቶችን እንዴት መዋጋት እንችላለን?

- የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ፤
- ሕገ እግዚአብሔርን በማክበርና በመጠበቅ፤
- ጓደኞቻችንን በጥንቃቄ በመምረጥ፤
- በጸሎትና በጾም እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ፤
- በመንፈሳዊ አገልግሎት በመትጋት፤
- ራሳችንን በመግዛት፤
- ስሜታችንን ከሚቀሰቅሱ ነገሮች በመራቅ፤
- ንስሐ በመግባት…. ወ.ዘ.ተ፡፡

www.zeorthodox.org

## 5. ክርስቲያናዊ ማሽኮርመምና መሽኮርመም፡-

ክርስቲያናዊ ማሽኮርመምን የሚገልጹ ታሪኮች በመጽሐፍ ቅዱስ እናገኛለን፡፡ የያዕቆብና የራሔል ታሪክ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ /ዘፍ. ፳፰÷፩-፪፣ ዘፍ. ፳፱÷፳፩/ ክርስቲያናዊ ማሽኮርመም፡-

- ዓላማው ወደ ጋብቻ ለማምራት ነው፡፡
- የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመጠየቅ የሚጀመርና ወደ ፍጻሜ የሚያመራ ነው፡፡

- በቅድመ ጋብቻ ግንኙነት ወቅት ሥጋዊ መፈቃቀድ አይኖርም።
- ሁሉም ነገር በንስሓ አባት ምክርና በቤተሰብ ፈቃድ የሚፈጸም ነው።

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች ክርስቲናዊ ካልሆነ ማሽኮርመምና መሽኮርመም ራሳችሁን ጠብቁ። ሁሉም ነገር በጊዜው እንደሚሆን አውቃችሁ የእግዚአብሔርን ጊዜ በእምነትና በትዕግሥት ጠብቁ።

## ተግባር፡-

- ወጣቶች የዝሙት ስሜት ሲፈታተናችሁ መጸለይን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን ተለማመዱ።
- ውሎአችሁን፣ የምትሰሙትንና የምታዩትን በተለይ ሥጋዊ ፍላቶታችሁን ከሚቀሰቅሱ ፊልሞችና መጻሕፍት ራቁ።

www.zeorthodox.org

# ወጣትነት እና ቤተሰባዊ ሕይወት

## አርባ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ከቤተሰባቸው ጋር መልካምና ጤናማ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚያስችሏቸውን ነጥቦች ተገንዝበው በክፍል ውስጥ ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በወንድማማች መዋደድ እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ፡፡" ሮሜ. ፲፪፥፲

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

☒ Bishop Mussa; Youth and family life.

☒ ዲ/ን አካለ ወልድ ተሰማ፤ ወጣትነት እና ቤተሰባዊ ሕይወት፤

### መግቢያ፡-

❖ ወጣቶች ከቤተሰባችሁ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ጤናማ ነው? ካልሆነ በምን ምክንያት?

❖ ብዙ ጊዜ ከወላጆቻችሁ ጋር የሚያጋጫችሁ ነገር ምንድነው?

❖ ከቤተሰብ ጋር በመኖራችሁ የሚሰማችሁ ስሜት ምንድነው?

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቤተሰብ የተከበረ ማኅበራዊ ነው፡፡ አንድ ቤተሰብ ባልና ሚስትን፣ ልጆችን እንዲሁም ሌሎች በአንድ ጣሪያ ሥር የሚኖሩትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነገር ነው፡፡ ቤተሰብ የሀገር፣ የቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ የሰው ልጅ መሠረት ነው፡፡ ይህም ማለት ቤተሰብ ካለ ሀገር፣ ሕዝብ፣ ቤተ ክርስቲያን.... ወ.ዘ.ተ አለ ማለት እንችላለን፡፡ ነገር ግን ቤተሰብ ከሌለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሉም፡፡ በዚህ የተነሣ መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተሰባዊ ሕይወት ትልቅ ክብር እንድንሰጥ ቤተሰባችንን ከሚፈብሹ ክፉ ተግባራት እንድንርቅ ይመክረናል፡፡ ቤተሰብ መንፈሳዊ አንድነት ያለበት፤ ፍቅር፣ መተሳሰብና መቻቻል የሚታይበት፤ እኔ የሚል መንፈስ ሳይሆን እኛ የሚል ቋንቋ የሚነገርበት የኅብረት እና የጋራ ኑሮ ነው፡፡

1. **የቤተሰብ አስፈላጊነት፡-**

ሀ. ቤተሰብ የፍቅር ትምህርት ቤት ነው፡፡

ለ. ብዙ ተባዙ የሚለው አምላካዊ ቃል የሚፈጸምበት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ሐ. የመኖር ዋስትናችን የሚረጋገጥበት ነው፡፡

መ. በሥነ-ምግባርና በሃይማኖት የምንቀረጽበት ነው፡፡

ሠ. ለሌላ መኖርን፣ መካፈልንና መተሳሰብን የምንማርበት ነው… ወ.ዘ.ተ፡፡

2. ወጣቶችን ከቤተሰባቸው ጋር የሚያጋጫቸው ምንድነው?

በተለይ በወጣትነት ዕድሜ ብዙ ወጣቶች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሲጣሉ አንዳንዶች ከቤት ወጥተው ሲኮበልሉ ይስተዋላል፡፡ ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም በዚህ ትምህርት ወጣቶችን የሚመለከቱ ምክንያቶችን ብቻ እናያለን፡፡

ሀ. ለቤተሰብ ሕግና ሥርዓት አለመገዛት፤ በትምህርት ደካማ መሆን፤

ለ. ቤተሰብ የሚሰጠንን ሓላፊነት በታማኝነት አለመወጣት፤

ሐ. በተለያዩ አጉል ሱሶች መያዝ፤ አልኮል መጠጥ፣አደንዛዥ ዕፅ ወዘተ ማዘውተር፤

መ. ያልተጠበቀ እና ከጋብቻ ውጪ የሆነ እርግዝና፤

ሠ. የቤተሰብን ገንዘብ አልባሌ ለሆኑ ነገሮች ማጥፋት፤

ረ. የተለያዩ ቤተሰብን የሚያሳዝኑና ቅር የሚያሰኙ ተግባራትን ማከናወን.. ወ.ዘ.ተ፡፡

## ማጠቃለያ

ወጣቶች ከቤተሰባችሁ ጋር እንድትኖሩ ዕድል ስለሰጣችሁ በመጀመሪያ እግዚአብሔርን ማመስገን አለባችሁ፡፡ በዚህ ትምህርት የቤተሰብን አስፈላጊነት እና ከቤተሰብ ጋር በስምምነት መኖር የሚሰጠውን ዘርፈ ብዙ ጥቅም ተምራችኋል፡፡ የክርስቲያን ቤተሰብ ማለት "ትንሿ ቤተ ክርስቲያን" ማለት ነው፡፡ (ፊል. ፩÷፪) ስለዚህ ወጣቶች ከቤተሰባችሁ ጠንካራ ሠራተኛነትን፣ መልካም ሥነ ምግባርን፣ ሃይማኖትን፣ ፍቅርና መተሳሰብን ተምራችሁ ወደ ፊት ከእግዚአብሔር ጋር ለምትመሠርቱት ቤተሰብ ራሳችሁን አዘጋጁ፡፡ ቤተሰባችሁን ከሚያሳዝን እንዲሁም የቤተሰቡን ሰላም ከሚያውክ ተግባር ሁሉ ራሳችሁን ጠብቁ፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- ወጣቶች ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመኖራቸው ያገኙትን በጎ ነገር ለጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ መምህሩ ይፍቀዱላቸው፡፡
- ለብቻቸው በጎዳና ላይ የሚኖሩ ወጣቶች ከቤተሰብ ጋር ባለመኖራቸው የሚገጥሟቸውን በርካታ ችግሮች መምህሩ ይግለጹላቸው፡፡
- ወጣቶች በቤተሰብ ውስጥ ስለአላቸው ሚና እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡

# ራስን ማክበር (Self Respect)

## አርባ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓለማ፡-** ወጣቶች ራሳቸውን የሚያከብሩበትን፣ የሚቀበሉበትን እና በራስ የመተማመን ችሎታቸውን የሚያዳብሩባቸውን መንገዶች አውቀው ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ” ፩ቆሮ. ፮÷፳

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ቆሮ.፮÷፲፫-፳፣ መዝ.፴፰(፴፱)÷፱፣ መዝ. ፺፬÷፫፣ መዝ. ፻፴፰(፻፴፱) ÷፲፬፣ ዘፍ. ፩÷፳፮-፳፯

### መግቢያ፡-

- ወጣቶች ስለ ራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት (ሥዕል) ምን ይመስላል?
- በማንነታችሁ እንዲሁም በተፈጥሮአችሁ ደስተኛ ናችሁ?
- ስለ ውበታችሁስ ተጨንቃችሁ ታውቃላችሁ?
- ራሳችሁን ምን ያህል ትወዳላችሁ?
- መስታወት ፊት ቆማችሁ በቀን ውስጥ ምን ያህል ጊዜ ታጠፋላችሁ?
- ራሳችሁን ከሌሎች ጋር ታወዳድራላችሁ?

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

መጽሐፍ ቅዱስ ሰው በእግዚአብሔር አርአያ እና አምሳል የተፈጠረ ክቡር እንደሆነ ይመሰክራል፡፡ ሰው ግን ብዙ ጊዜ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንዲሁም በተለያዩ ተጽዕኖዎች ይህን ክብሩን ሲዘነጋ እና የማይገባውን ሥራ ሲሠራ ይታያል፡፡ መዝሙረኛው ዳዊት ይህን ሲገልጽ በመዝሙሩ፤ “ሰው ክቡር ሆኖ ሳለ አላወቀም፤ እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ፡፡” ብሏል፡፡ /መዝ. ፵፰/ ፵፱/÷፲፪/ ስለዚህ እግዚአብሔር እንዳከበረን ተገንዝበን ስለራሳችን በጎ አመለካከት ሊኖረን ይገባል፡፡

www.zoorthodox.org

#### 1. ለራሳችን ጥሩ የሆነ አመለካከት ካለን፡-

- ለሕይወት ትርጉም እንሰጣለን፤
- በተፈጥሮአችን ደስተኞች እንሆናለን፤

- ለሌሎች ተፈላጊዎች እንደሆንና እኛም ሌሎች እንደሚያስፈልጉን እናምናለን፤
- በሚገጥሙን ችግሮች ሳንማረር እና ተስፋ ሳንቆርጥ ነገ የተሻለ እንደሚሆን እናስባለን፤
- በጎ ነገሮችን የማሰብና ደስተኛ የመሆን እድላችን ሰፊ ነው…ወ.ዘ.ተ፡፡

2. ለራሳችን ጥሩ የሆነ አመለካከት ከሌለን፡-
   - ሕይወታችን ትርጉም ስለሚያጣ ተስፋ እንቆርጣለን፤ መኖርን እንጠላለን፤
   - ራሳችንን የማንጠቅምና የማናስፈልግ አድርገን እናያለን፤
   - ራሳችንን አስቀያሚ አድርገን ስለምንመለከት ራሳችንን እንጠላለን፤
   - በሌሎች ተወዳጆች እንዳልሆንና ፈላጊ እንደሌለን እናስባለን፤
   - በራሳችን ውበትና ተፈጥሮ ስለማንረካ ብዙ ጊዜ ከሰዎች ማረጋገጫ ለማግኘትና፤ ራሳችንን ከሌሎች ጋር በማነጻጸር እንጠመዳለን… ወ.ዘ.ተ፡፡

## 3. ራስን ማክበር በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ

ሰው የእግዚአብሔር ፍጡር እንደሆነ የሚናገረው መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አርአያ እና አምሳል ስለተፈጠረ እግዚአብሔር የሰጠውን ክብርና ማዕረግ በመጽሐፍ ቅዱስ ተዘርዝሮ እናነባለን፡፡ “እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር… እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፡፡” (ዘፍ. ፩÷፳፯)

በእግዚአብሔር አርአያ እና አምሳል መፈጠራችንን አምነንና ተቀብለን ራሳችንን ማክበር የሁላችንም ሓላፊነት ነው፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን በእግዚአብሔር ውብ ሆኖ እንደተፈጠረ ሲመሰክር፡- “እኔ ጥቁር ነኝ፤ ነገር ግን ውብ ነኝ” ብሏል፡፡ /መኃልየ መኃልይ ፩÷፭/ መዝሙረኛው ዳዊትም ክብሩን ስላወቀ ስለ ተፈጥሮው እግዚአብሔርን “ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ፤ *ሥራህ ድንቅ ነው ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች”* (*መዝ.፻፴፰(፻፴፱)÷፲፬*) በማለት አመሰግኗል፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ሰው ሆኖ በመምጣቱ እና የእኛን ሥጋ በመልበሱ፤ ሰው የከበረ ፍጡር መሆኑን በሥጋዊው አስተማረን፡፡ ፈሪሳውያንም ለሰው የተዛባ አመለካከት ስለነበራቸው እና ሰውን ከሰንበት አሳንሰው ያዩ ስለነበር የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ እንደሆነም አስተማረ፡፡ (ማቴ. ፲፪÷፩-፲፭) ባልንጀራችንን እንደራሳችን እንድንወድ ታዘናል፡፡ ነገር ግን ባልንጀራችንን እንደራሳችን መውደድ ማለት እንዴት እንደሆነ ለብዙዎቻችን ግልጽ አይደለም፡፡ ራሱን ያልወደደ፣ ያላከበረ፣ ጤንነቱን፣ ንጽሕናውን የማይንከባከብ፣ ለሕይወቱ ዋጋ የማይሰጥና ራሱን ያልተቀበለ ሰው ሌላውን ሊያፈቅር፣ ሊንከባከብ፣ ስለሌላው ጤንነት እና ንጽሕና ለማሰብ ለመጨነቅ ስለማይችል ጌታችን፤ ‹‹ባልንጀራችሁን እንደራሳችሁ ውደዱ›› አለ፡፡ ሰውነቱን ያከበረ

www.zeorthodox.org

ሰው ሌላውን ሰው ያከብራል፡፡ ራሱን የተቀበለ ሰው ሌላውን ለመቀበል አይከብደውም፤ በራሱ የሚተማመን ሰው ሌላውን ለማመን በሌላው ላይ እምነት ለመጣል አይከብደውም፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች እግዚአብሔር የሰውነታችን ፈጣሪና ወዳጅ ነው፡፡ ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነው፡፡ (፩ቆሮ. ፫÷፲፮) እግዚአብሔር የሰውነታችን ወዳጅ መሆኑን፤ አንደኛ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ፤ ሁለተኛ ሰውነታችንን ከተለያየ በሽታዎች በማዳኑና በመፈወሱ፤ ሦስተኛ ሥጋችንን ከሞት በማንሣቱ ሰውነታችንን ምን ያህል እንዳከበረው እና ለእኛ ያለውን ፍቅር አሳይቶናል፡፡ ስለዚህ ወጣቶች እግዚአብሔር ያከበረውንና የወደደውን ማንነታችሁን አትጥሉ፤ ይልቁንም ራሳችሁን በማክበር፣ በመውደድና በራሳችሁ በመተማመን እግዚአብሔርን በኑሮአችሁ አክብሩ፡፡

## ተግባር፡-

- ➔ ወጣቶች ራስን በማክበርና በትሕትና መካከል ያለውን ልዩነት እንዲገነዘቡ መምህሩ በምሳሌ ያብራሩላቸው፡፡
- ➔ ወጣቶች በራስ መተማመናቸውን የሚያዳብሩባቸውን ልዩ ልዩ ዘዴዎች ይንገሯቸው፡፡
- ➔ ወጣቶች ማንነታቸውን ተገንዝበው ራሳቸውን በማከበርና በመቀበል በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ስለሚያዳብሩባቸው መንገዶች ያወቁትን በክፍል ውስጥ እንዲያብራሩ ያድርጓቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ከተቃራኒ ጾታ ጋር መቀላቀል

## አርባ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ለተቃራኒ ጾታ ያላቸው አመለካከት በበጎነት እና በአክብሮት ላይ የተመሠረተ ሆኖ ራሳቸውንም ከክፉ ምኞት የሚጠብቁበትን መሠታዊ ነጥቦች ተገንዝበው በክፍል ውስጥ ያስረዳሉ፤ ይወያያሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በማንም ላይ ፈጥነህ እጅህን አትጫን፤ በሌሎችም ኃጢአት አትተባበር፤ ራስህን በንጽሕና ጠብቅ፡፡" ፩ጢሞ. ፭÷፳፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መምህሩ ወጣቶች ከተቃራኒ ጾታ ጋር ጤናማ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚያግዙ መጻሕፍትን እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

### መግቢያ፡-

- ወንዶች ሴቶችን እንዴት ነው የምትመለከቷቸው? ሴቶችም እንዲሁ?
- ስለ ሴቶች በጎ ነገር አላችሁ? ሴቶችስ ስለ ወንዶች ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?
- ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያላችሁን ግንኙነት እንዴት ታዩታላችሁ?

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

በዚህ ዘመን ከተቃራኒ ጾታ ጋር የምንገናኝባቸው ዕድሎችና አጋጣሚዎች በጣም ብዙ ናቸው፡፡ በቀድሞው ዘመን ሴቶች በአብዛኛው በባህልና በሃይማኖት ሰበብ ከቤት ይውሉ ስለነበር ከቅርብ ዘመዶቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ባለፈ ከሌላ ሰው ጋር የመገናኘት አጋጣሚው አልነበረም፡፡ ከኢንዱስትሪው ዘመን በኋላ ግን ይህ ታሪክ ቀስ በቀስ እየተቀየረ ዛሬ ያለንበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል፡፡ ከኢንዱስትሪው መስፋፋት ጋር በተያያዘ ከተሞች በመቀርቀራቸውና ሰዎች በጋራ መኖር በመጀመራቸው፣ ሴቶች ለሥራና ለትምህርት ከቤት መውጣት ጀመሩ፡፡ የተለያዩ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በመገንባታቸው ከተቃራኒ ጾታ ጋር የመገናኘቱን ዕድል የዚያኑ ያህል ሰፊ አድርጎታል፡፡ ስለዚህ ዕለት ዕለት በትምህርት ቤት፣ በትራንስፖርት፣ በሥራ ቦታ፣ በመዝናኛ ቦታዎችና በቤተ ክርስቲያን… ወ.ዘ.ተ ሴቶች ከወንዶች ጋር ወንዶች ደግሞ ከሴቶች ጋር እንገናኛለን፡፡ ይህን አጋጣሚ ለበጎ ነገሮች ወይም ለኃጢአት ሥራዎች መጠቀም የእኛ ምርጫና ሓላፊነት ጭምር ነው፡፡

www.zoorthodox.org

❖ **ከተቃራኒ ጾታ ጋር እንዴት ጤናማ ግንኙነት ሊኖረን ይችላል?**

ከተቃራኒ ጾታም ሆነ በአጠቃላይ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ጤናማ የሚሆነው ለግንኙነታችን በምንሰጠው ክብርና በጎ አመለካከት ነው፡፡ ለሰዎች የምንሰጠው ክብር፣ ጥንቃቄ እና በጎ ዕይታችን ለግንኙነታችን ጤናማ መሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ወንዶች ሴቶችን እንዴት ነው የምትመለከቷቸው? ሴቶችን ለምንድነው የምትፈልጓቸው? ሴቶችስ ወንዶችን እንዴት ትመለከቷቸዋላችሁ? ወንዶች ለምን ያስፈልጓችኋል? እነዚህን ጥያቄዎች ቆም ብለን ማሰብ እና በጥልቀት መመርመር ያስፈልገናል፡፡ ወንዶች ስለ ሴቶች ሊኖራችሁ የሚገባ ጤናማ አመለካከት፤ ሴቶች እናት፣ እኅት፣ ጓደኛ፣ ሚስት፣ የሥራና የትግል አጋር መሆናቸውን በማመንና በመቀበል ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡ ሴቶችም ስለወንዶች ሊኖራችሁ የሚገባው በጎ አመለካከት፤ ወንዶች አባት፣ ወንድም፣ ባል፣ ጓደኛ፣ የሥራና የልማት አጋር ናቸው ብሎ በማመንና በመቀበል ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡ ሴቶችን ዝቅ አድርጎ የወንዶች ስሜት ማብረጃ እንደሆኑ ማሰብ ትልቅ ስህተት ነው፡፡ ስለዚህ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ጤናማ ግንኙነት እንዲኖረን የሚከተሉትን ሦስት ነገሮች ማጤን ግድ ይላል፡፡

ሀ. እንደ እግዚአብሔር ቃል በመኖር፤

ለ. ዓላማችንን ባለመዘንጋት፤

ሐ. ቁጥብ በመሆንና ግንኙነታችንን በመወሰን፤

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች በዚህ ትምህርት ለተቃራኒ ጾታ ሊኖራችሁ ስለሚገባው በጎ አመለካከት እንዲሁም ግንኙነታችሁ ጤናማ እንዲሆን ለማድረግ የሚገባችሁን ጥንቃቄ ተገንዝባችኋል፡፡ ስለዚህ ከተቃራኒ ጾታ ጋር የሚኖራችሁን አጋጣሚ ለኃጢአት ሥራ በማዋል ግንኙነታችሁ እንዳይበላሽ ራሳችሁን ጠብቁ፡፡ ያገኛችሁትን ነጻነትና አጋጣሚ ሌሎችን ለማባለግ ከመጠቀም ተከልከሉ፡፡ እንደ ዮሴፍ በተለያዩ አጋጣሚዎች ከተቃራኒ ጾታ የሚቀርቡላችሁን የዝሙት እና የኃጢአት ግብዣዎች በዓላማችሁ በመጽናት እንቢ ማለት እና መሸሽን ተማሩ፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- መምህሩ ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ከተቃራኒ ጾታ ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ ጤናማ የአገልግሎት ሕይወት አፅንኦት ሰጥቶ ይንገሯቸው፡፡
- ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን እያሳበባችሁ አልባሌ ቦታ እንዳትገኙ እግዚአብሔርን እና ቤተሰቦቻችሁን እንዳታሳዝኑ ራሳችሁን ጠብቁ፡፡
- በቤተ ክርስቲያን እያሳበቡ ክፉ ሥራ ከሚሠሩ ጓደኞች ራቁ፡፡
- መምህር፤ ወጣቶች ከተቃራኒ ጾታ ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ ጤናማ ግንኙነት እና ራሳቸውን ከክፉ ምኞትና ሥራ ስለመጠበቅ ዋና ዋና ነጥቦችን በማንሣት በክፍል ውስጥ እንዲገልጹና እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

www.zeorthodox.org

# ጊዜን በአግባቡ መጠቀም

## አርባ አምስትኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ጊዜ ምንነት ዋጋ እንዲሁም ጊዜያቸውን በአግባቡ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ተገንዝበው በክፍል ውስጥ ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከሰማይ በታች ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው" መክብብ. ፫÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መክብብ ፫÷፩-፱ (ዮሐ ፱÷፬) ኤፌ ፭÷፲፯-፲፯

### መግቢያ፡-

- ወጣቶች ስለ ጊዜ ምንነት እና ዋጋ ያላችሁ ግንዛቤ ምን ያህል ነው?
- ጊዜያችሁን በአግባቡ ትጠቀማላችሁ?
- አብዛኛው ጊዜያችሁ የሚባክነው በምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አንዳንድ ሰዎች ውድ ጊዜያቸውን በዋዛ ፈዛዛ ሲያባክኑ ይስተዋላል፡፡ ሌሎች ደግሞ "ጊዜው እንዲሔድልኝ" በሚል ሐሳብ ካርታ ሲጫወቱ፣ መጠጥ ሲጠጡና ጫት ሲቅሙ… ወ.ዘ.ተ ይውላሉ፡፡ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበት በጎ ሥራ ስለሌላቸው ቀኑ እንዲመሽላቸው ጊዜው እንዲሔድ ወይም በእነርሱ አባባል "ጊዜ ለመግደል" በተለያዩ ሱሶች ተጠምደው ለራሳቸው፣ ለሀገራቸውና ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም መልካም ነገር ሳይሠሩበት ዘመናቸው ያልፋል፡፡

### 1. ጊዜ ምንድነው?

ጊዜ በዚህ ምድር የምንኖረውን ኑሮ እና ሥራችንን በሰዓት፣ በቀን፣ በሳምንት፣ በወር እና በዓመት መለኪያ፣መመዘኛና መሥፈሪያ ነው፡፡ እግዚአብሔር በጊዜ የማይለካ ከጊዜ ውጪ ሲሆን ከሰማይ በታች ለፈጠረው የሰው ልጅ ግን ጊዜን ሰጥቷል፡፡ ስለዚህ ሁላችንም በቀን ውስጥ እኩል ሃያ አራት ሰዓት አለን፣ ዘመናችንም የተሠፈረ እና የተለካ ነው፡፡ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ወይም በስንፍና ማባከን የእኛ ምርጫ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም ጊዜ እንዳለውና ጊዜ የከበረ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ ይመክረናል፡፡

www.zeorthodox.org

### 2. የጊዜ ባሕርያት፡-

የጊዜ ባሕርያት የሚከተሉት ናቸው፡፡

2.1. ወደፊት በፍጥነት መጓዙ፤ ጊዜ ማንንም ቆሞ አይጠብቅም፡፡

2.2. አንዴ ካለፈ አይመለስም፤ ጊዜን ወደ ኋላ ማጠንጠን አይቻልም፡፡

2.3. በምንም ገንዘብ ወይም ዋጋ የማይተመን ውድ መሆኑ፤ ጊዜ ወርቅ ነው፡፡

የተሳካለትና ያልተሳካለት ሰው በማለት ለይቶ እግዚአብሔር አልፈጠረም፡፡ ለስኬታማ ሰዎችም እግዚአብሔር ጭማሪ ሰዓት ሰጥቶ አያውቅም፡፡ ሰዎችን ስኬታማ ያደረጋቸው ለሁሉም እኩል እንደተሰጠ ሁሉ ለእነርሱም የተሰጣቸውን ጊዜን በአግባቡ በመጠቀማቸው ነው፡፡

## 3. ጊዜን በአግባቡ እንዳንጠቀም የሚያደርጉን ነገሮች፡-

3.1 የጊዜን ምንነት እና ዋና አለማወቅ፤

3.2 ጊዜ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን አለመገንዘብ፤

3.3 ጊዜን መርገም (መስደብ)፤

3.4 ሥራን ለነገ ማለት፤

3.5. ማድረግ ያሉብንን ነገሮች ለይተን እና በቅደም ተከተል አድርገን እንደየአስፈላጊነታቸው ቅድሚያ በመስጠት በመርሐግብር ወይም ፕሮግራም አውጥተን ሥራችንን በወቅቱ አለማከናወን፡፡

3.6. በሕይወት ቅድሚያ የምንሰጣቸውን ነገሮችን አለማወቅ… ወ.ዘ.ተ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች ከዚህ ትምህርት ጊዜ ውድና የከበረ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን ተገንዝባችኋል፡፡ ጊዜን በዋዛ ፈዛዛ ማባከን ሕይወትን ማባከን ነው፡፡ ጊዜን መግደል ራስን መግደል ነው፡፡ ሰነፎች ብዙ ጊዜ እንደማይመቻቸውና ጊዜ እንደሌላቸው ያወራሉ፡፡ ችግሩ የጊዜ አለመኖር ሳይሆን ጊዜን በአግባቡ መጠቀም አለመቻላቸው ነው፡፡ ስለዚህ ወጣቶች እግዚአብሔር በሰጣችሁ ዕድል ለመጠቀም እና በዘመናችሁ ቁም ነገር ለመሥራት የጊዜ አጠቃቀም ባህላችሁን ቀይሩ፣ ስለ ጊዜ ያላችሁን አመለካከትም ለውጡ፡፡ በጊዜና በዕቅድ በፕሮግራም መመራትን ልመዱ፡፡

## ተግባር፡-

www.zeorthodox.org

- መምህሩ ወጣቶች ስለ ጊዜ ያላቸው ግንዛቤ እንዲሰፋ እና ጊዜያቸውን በአግባቡ መጠቀም የሚችሉበትን ዘዴ እንዲያውቁ በጉዳዩ ጥሩ መረጃ የሚሰጡ መጻሕፍትን እንዲያነቡ ይጠቁሙአቸው፡፡
- ጊዜያቸውን በምን እንደሚያሳልፉ የጊዜ አጠቃቀማቸውን በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻቸው እንዲነግሩና ልምድ እዲለዋወጡ ያድርጓቸው፡፡

# ሞርሞኒዝም

## አርባ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የሞርሞኖች አስተምህሮ ኑፋቄ መሆኑን ተገንዝበው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችን በመጥቀስ በክፍል ውስጥ ዘርዝረው ያስረዳሉ፤ ራሳቸውንም ከክህደት ትምህርት ይጠብቃሉ።

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እነሆም በቶሎ እመጣለሁ የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁዕ ነው።" ራእይ.፳፪÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ዮሐ ፬÷፩-፯ (ገላትያ ፩÷፩-፱) ዕብ. ፲፫÷፯-፱

## መግቢያ፡-

- ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የምታውቋቸውን መናፍቃን እና የክህደት አስተምህሮዎቻቸውን ዘርዝሩ
- ለብዙ ሰዎች የክህደት አስተምህሮ መነሻ የሆናቸው ነገር ምንድ ነው?
- ከሐሰት ትምህርቶች እንዴት ራሳችሁን ትጠብቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### 1. ሞርሞንስ

ይህ እምነት በመጀመሪያ በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተወለደውና ያደገው በአሜሪካን ሀገር ጆሴፍ ስሚዝ በሚባል ሰው ነው። ይህ ሰው በዓለማዊም ሆነ በመንፈሳዊ ትምህርት በቂ ዕውቀት ያልነበረው ቢሆንም ራሱን ነቢይ በማድረግ እግዚአብሔር እውነተኛውን ክርስትና እንዲመሠርት እንዲላከው መስበክ ጀመረ። በ1820 እ.ኤ.አ ጆሴፍ ስሚዝ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን አለመግባባትና ከሦስት ዓመት በኋላም ሞሮኒ የሚባል መልአክ እንደተገለጠለት ይናገራል። በጥንት ዘመን በሰሜን አሜሪካ በሚኖሩ ሰዎች የተጻፉ ጽሑፎችን የያዙ የወርቅ ሳህኖች የተቀበሩበትን ስፍራ እንዳሳየው እና የእነዚህን ጽሑፎች ተርጉሞ በ1830 እ.ኤ.አ የሞርሞንስን መጽሐፍ ሊጽፍ እንደቻለ ይገልጻል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሞርሞንስ የኋለኛው ዘመን ቅዱሳን እየተባሉ የሚጠሩ ሲሆን ወደ 2.5 ሚሊዮን የሚጠጉ ተከታዮችም አሉዋቸው።

www.zeorthodox.org

## 2. የሞርሞንስ መጽሐፍ

የጆሴፍ ስሚዝ ተከታዮች የሞርሞንስን መጽሐፍ ዐሥራ አምስት መጻሕፍትን የያዘ ትልቅ መጽሐፍ እንደሆነ ይናገራሉ። ይህ መጽሐፍ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከመካከለኛው ምሥራቅ ተሰደው በአሜሪካ መኖር ስለጀመሩ የጥንት ሰዎች ይናገራል። እነዚህ ሰዎች አይሁዶች እንደነበሩና በጫካ ይኖሩ ለነበሩት ሕንዶች መገኛ እንደሆኑም ይገልጻል። እነዚህ ሰዎች ጥበበኞች የነበሩ ሲሆን ጆሴፍ ስሚዝ የሕንፃ ጥበብን እንዳፈለቁ ከተሞችንም መገንባት የጀመሩት እነርሱ እንደሆኑ ተናግሯል። በኋላም ኢየሱስ እንደጎበኛቸው ያትታል። ኢየሱስ እነዚህን ሰዎች በጎበኛቸው ጊዜ ያስተማረው ትምህርት ሞርሞን በተባለው ነቢይ በወርቅ ሳህን ላይ እንደተጻፈ የሞርሞን ተከታዮች ይመሰክራሉ። በአጠቃላይ ሞርሞንስ የጆሴፍ ስሚዝን መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል የሚቀበሉ ሲሆን፤ ጆሴፍ ስሚዝ እንደሙሴ ቅዱስ ነው እንዲያውም ኢየሱስን ይስተካከለዋል፤ ሲሉ ይደመጣሉ።

## 3. የሞርሞንስ የክህደት ትምህርቶች

- ምስጢረ ሥላሴን አይቀበሉም።
- ሁሉም ሰው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከመወለዳችንም በፊት እንደነበርን ያስተምራሉ።
- ገና ያልተወለዱ ነፍሳት እስኪወለዱና ሰው እስኪሆኑ መላእክት ሆነው እግዚአብሔርን እያገለገሉ ነው ይላሉ።
- ሰው ከሞተ በኋላ የመጨረሻውን ፍርድ በገነት ሆኖ እንደሚጠብቅ፣ ሙታን በገነት ውስጥ ኃጢአታቸውን የመናዘዝ እንዲሁም ንስሓ የመግባት ሁለተኛ ዕድል እንዳላቸው በመጨረሻም ቅዱሳን እንደሚሆኑ ያስተምራሉ።
- በገነት ውስጥ ያሉ ነፍሳት የእነርሱ ቤተ ክርስቲያን አባል እንዲሆኑ ለመርዳት ሞርሞንስ የሙታን ጥምቀት አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ።

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች ሰዎች ለገዛ ምኞታቸው እውነተኛውን ቃል እንደሚያጣምሙና እንደገዛ ፍላጎታቸው መጽሐፍ ቅዱሱን እንደሚተረጉሙ ተገንዝባችሁ እናንተ ግን በእውነተኛ እምነታችሁ እስከ መጨረሻው ድረስ በመጽናት በሃይማኖት ቆሙ ጎልምሱ። በሃይማኖት በመጽናት ራሳችሁን ከክህደት ትምርቶች ጠብቁ።

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- ወጣቶች የክርስቶስን አምላክነት እና ምስጢረ ሥላሴን የሚገልጹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ፈልጉና ተወያዩባቸው።
- የሞርሞንስ አስተምህሮ ከመጽሐፍ ቅዱስ የራቀ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎችን በመዘርዘር አስረዱ።

# የሕይወት አጋሬን እንዴት ልምረጥ?

## አርባ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ፍቅር ግንኙነት በቂ ግንዛቤ አግኝተው በትክክል የሕይወት አጋራቸውን የሚመርጡበትን ጊዜና ሁኔታ አውቀው ያብራራሉ።

**በቃል በሚጠና ጥቅስ፡-** "በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።"

፩ዮሐ ፫÷፲፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ቆሮ ፯÷፩-፲፯/፩ቆሮ. ፲፫÷፩-፲፫/ዘፍ. ፳፬÷፩-፷፯/ዘፍ. ፪÷፲፰-፳፭

- መምህሩ ወጣቶች ስለ ተቃራኒ ጾታ ሊኖራቸው የሚገባውን በቂ ልምድ እንዲቀስሙ ስለዚህ ጉዳይ የተጻፉ ጥሩ ጥሩ መጻሕፍትን መርጠውላቸው እንዲያነቡ ይጠቁማቸው።

## መግቢያ፡-

- ወጣቶች ፍቅርን እንዴት ነው የምትረዱት?
- ፍቅር ይዞአችሁ ያውቃል?
- የፍቅር ጓደኛ ለምን እንዳስፈለጋችሁ ምክንያታችሁን በግልፅ አስቀምጡ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

"ፍቅር ይዞኛል" "አፍቅሬአለሁ" ማለት በብዙ ወጣቶች ዘንድ የተለመደ ነገር ነው። ወጣትነት ወንዶች ሴቶችን ሴቶችም ወንዶችን ለፍቅር የሚመርጡበት ዕድሜ ነው። በወጣትነት ዘመን በተቃራኒ ጾታ መሳብ፣ የራስን ሰው ለማግኘት ጊዜ ወስዶ ማሰብና መጨነቅ የተለመደ ክስተት ነው። መፈላለግ ተፈጥሮአዊ ቢሆንም ሁሉም ለቁም ነገር ነው ለማለት ግን አያስደፍርም። በዚህ የተነሣ ወጣቶች ተቃራኒ ጾታን ለጓደኝነት የሚመርጡባቸውን ምክንያቶች በሚገባ ማወቅ አስፈላጊያቸው ነው። የተወሰኑትን ምክንያቶች በዚህ ትምህርት ለማየት እንሞክራለን።

www.zeorthodox.org

### 1. ወጣቶች የተቃራኒ ጾታ ጓደኛ የሚይዙባቸው ምክንያቶች

ሀ. ጓደኛ የለውም (የላትም) እንዳይባሉ፣

ለ. ሌሎች ሲይዙ በማየት፣

ሐ. ለሩካቤ ሥጋ ፍላጎት (ለዝሙት) (፪ ሳሙ ፲፫÷፲፩)፣

መ. በፍቅር ስለወደቁ (ዘፍ. ፴፬፥፫)፤

ሠ. የትዳር ጓደኛ ፈልገው (ዚፍ. ፳፱፥፩፰)፤

ረ. ለቁሳዊ ጥቅም ብለው (መሳ. ፲፮፥፭)

ሰ. በፉክክር ስሜት፣ ሌሎችም ለማናደድ ሲፈልጉ … ወ.ዘ.ተ፡፡

2. የሕይወት አጋርን የምንመርጥባቸው ደረጃዎች፡-

ወጣቶች የፍቅር ጓደኛ መፈለጋችሁ ኃጢአት ሳይሆን ተፈጥሮአዊ እና ጤናማ ስሜት ነው፡፡ ነገር ግን ይህን የተቀደሰ ፍላጎት ያለ ጊዜው፣ በተሳሳተ ምርጫ እና ጤናማ ባልሆነ ፍላጎት እንዳናበላሸው ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡ ስለዚህ የሚከተሉትን መመዘኛዎችና ደረጃዎችን ማጤን ትክክለኛ ውሳኔ እንድንወስን ያስችለናል፡፡ እንዲሁም ያለጊዜው ባደረግነው ያልተገባ ግንኙት ወይም በተሳሳተ ምርጫችን እንዳንጸጸት ያደርገናል፡፡

2.1. **አካላዊ ብቃት** (Physical Maturity)፡-

ወንዶች ለአቅመ አዳም ሴቶች ለአቅመ ሔዋን መድረሳችንን፤ ሰውነታችን ሌላ ሰውን ለመቀበል የተዘጋጀ መሆኑን ማወቅ አለብን፡፡

2.2. **መንፈሳዊ ብስለት** (Spiritual Maturity)፡-

በመንፈሳዊ ሕይወት ጠንካራ መሆናችንን እንዲሁም ከአንድ ክርስቲያን የሚጠበቅ መንፈሳዊ ብስለት እንዳለን ለማረጋገጥ ራሳችንን ማየት ተገቢ ነው፡፡ በሕይወታችን ወይም በኑሮአችን ሁሉ እግዚአብሔርን እንደምናስቀድም፣ የጸሎት ሕይወታችን ምን እንደሚመስል፣ መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብና ለቃሉ ያለንን ፍቅር፣ የመንፈሳዊ ሕይወታችንን ጥንካሬ … ወ.ዘ.ተ ያጠቃልላል፡፡

2.3. **የኢኮኖሚ ብቃት** /Economical Maturity/

ፍቅር ሓላፊነት እና ተጠያቂነት ያለበት ግንኙነት ነው፡፡ ገንዘብ ለዚህ ዓለም ኑሮ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ስለዚህ ከራሳችን አልፈን ሌላ ሰው ማኖር እንዲሁም መንከባከብ የሚያስችል አቅም አለኝ ወይ ብለን ራሳችንን መፈተሽ አለብን፡፡ ለመተዳደሪያ የሚሆን በቂ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ አለን ወይ? የሚለውን ጥያቄ በአስተማማኝ ሁኔታ መመለስ ይገባናል፡፡

www.zeorthodox.org

2.4. **የሥነ ልቡና ዝግጅት** /Psychological Maturity/

አንድን ሰው ለማፍቀር ከመነሣታችን በፊት ሥነ ልቡናዊ ዝግጅት ማድረግ አለብን፡፡ ፍላጎታችንን መመርመር፣ ሌላ ሰውን ለመቀበል የመንፈስ ዝግጅት ማድረግ፣ በስሜት ሳይሆን በእርጋታና በሰከነ መንፈስ ምርጫችንን ማጤንን አስፈላጊ ነው፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች የሕይወት አጋራችሁን ስትመርጡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች ማሟላታችሁን አረጋግጡ፡፡ ፍቅር የከበረ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን ተገንዝባችሁ በስሜታዊነት የፍቅር ጓደኛ ከመምረጥና በኋላ ከመጸጸት ራሳችሁን ጠብቁ፡፡ ከክፉ የጎልማሳነት (የወጣትነት) ምኞት በመራቅና በመሸሽ እያንዳንዱን ጉዞአችሁን በእግዚአብሔር ቃል እየመረመራችሁ እና ፈቃዱን እየጠየቃችሁ በመንፈስ የምትመሩ ሁኑ፡፡

## ተግባር፡-

- ➔ መምህሩ ወጣቶች ትክክለኛ የፍቅር ጓደኛ የሚመርጡበትን ጊዜ እና ሁኔታ እንዲያውቁ እንዲሁም ብዙ ጊዜ ወጣቶች የሚፈጽሟቸውን ስሕተቶች በግልጽ በመንገር ራሳቸውን ከስሜታዊነት እንዲጠብቁ ይንገሩአቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# እምነትና ትዕግሥት

## አርባ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የእምነትን፣ትዕግሥትን እና ጽናትን ምንነት በመገንዘብ በመንፈሳዊ ሕይወት የሚገኘውን ድልና በረከት አውቀው ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “በመታገሣችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ፡፡” ሉቃ. ፳፩÷፲፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**ዕብ. ፲፩÷ ፩-፫ /ዕብ. ፲፪÷፩-፫ / ኢዮ. ፪÷፯-፲ / ፩ጴጥ. ፩÷፳-፯

### መግቢያ፡-

- መምህር ከትምህርት በፊት እምነትና ትዕግሥት በሕይወታችን ያላቸውን ጠቀሜታ ወጣቶች እንዲወያዩበት ያድርጓቸው፡፡
- ወጣቶች በትዕግሥት ጠብቃችሁ ያገኛችሁት መልካም ነገር ምንድነው?
- ባለመታገሣችሁ በችኮላ ሠርታችሁት በኋላ ያስቆጫችሁ ነገርስ ምንድነው?
- በእምነትና በጥርጣሬ በምታደርጓቸው ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት አስተውላችሁ ታውቃላችሁ?

### የሳምንት ትምህርት፡-

#### 1. እምነት ምንድነው?

የእምነት መሠረቱ የሰው ልጅ የምርምር ውጤት አይደለም፡፡ የእምነት መሠረቱ እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡ እግዚአብሔር ራሱን በፍጥረታቱ፣ በመልእተኞቹና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ገልጧል፡፡ ለዚህ መገለጥ እኛ የምንሰጠው ተግባራዊ ምላሽ ‹‹እምነት›› ይባላል፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ ታማኝ አምላክ ነው፡፡ በመሆኑም በፍጹም ልብ ተቀብሎ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ ማረፍ እምነት ይባላል፡፡ (ቲቶ. ፫÷፰፣ ፪ጢሞ. ፪ጢሞ. ፪÷፲፫) እግዚአብሔር በሰጠው የተስፋ ቃል መተማመንና መደገፍ እምነት ነው፡፡ ስለዚህ እምነት የእግዚአብሔርን መልእክት መታዘዝ ነው፡፡ (ሉቃ. ፩÷፴፰) እምነት ዛሬ ላይ ሆነን ነገን በተስፋ የምናይበት የመንፈስ ዓይናችን ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን እንደፈጠረ ይህ የሚታየው ዓለም ከማይታየው እንደሆነ የምናስተውለውም በእምነት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

(ዕብ. ፲፩÷፩-፫) እምነት ለመንፈሳዊ ሕይወት ጉልበታችን ሲሆን እግዚአብሔርንም ደስ የምናሰኝበት ነገር ነው፡፡ (ዕብ. ፲፩÷፮)

## 2. ትዕግሥት ምንድነው?

ትዕግሥት የመንፈስ ፍሬ፣ በሚገጥሙን የተለያዩ ፈተኛዎችና ችግሮች ጽናትን፣ መቻልንና ብርታትን የሚሰጠን የመንፈስ ጉልበት እና ጥንካሬ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጧል፡፡ (ገላትያ. ፭÷፳፪፣ ኢያሱ ፲፬÷፲፩፣ ሮሜ ፭÷፫-፬) ትዕግሥተኛ ሰው ለረጅም ጊዜ በመከራ ይጸናል፣ ተስፋ ያደርጋል፣ ምሕረትንም ያያል፡፡ እግዚአብሔር ለሰዎች ብዙ ትዕግሥት አሳይቷል፡፡ (ሮሜ ፪÷፬፣ ፩ጴጥ. ፫÷፳) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን የመስቀልን መከራ እንዲሁም ሞትን ታግሷል፡፡ (ዕብ ፲፪÷፳፩) ስለዚህ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ምንም ነገር እንደሌለ በመተማመን እና በትዕግሥት የጸሎታችንን መልስ እንጠብቃለን፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በእምነትና በትዕግሥት ሆነው በመከራ የጸኑ፣ በሕይወት የገጠማቸውን ፈተና የታገሡ ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎችን እናያለን፡፡ ለምሳሌ ዮሴፍ የወንድሞቹን ጥላቻ፣ ከቤተሰቡ ተለይቶ በባዕድ ሀገር መኖርን፣ የጲጥፋራን ሚስት የሐሰት ክስንና እስር ቤትን በእምነት በመታገሡ በመጨረሻ እግዚአብሔር የትዕግሥቱን መልካም ፍሬ አብልቶታል፡፡ ኢዮብም ሀብቱን ሲያጣ፣ ልጆቹ ሲሞቱበት፣ የሕመሙን ስቃይ፣ የሚስቱንና የጓደኞቹን ነቀፋ ሁሉ በእምነት ታግሷል፡፡ እግዚአብሔርም እንደገና ኢዮብን ባርኮታል፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች አንዳንድ ጊዜ ከሚገጥማችሁ ችግርና መከራ የተነሣ እግዚአብሔር ለጸሎታችሁ መልስ ለመስጠት የዘገየ መስሎ ሊሰማችሁ ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ለጥያቄአችን መልስ ለመስጠት የሚዘገየው እምነታችን እና ትዕግሥታችንን ለመፈተን፣ ክብሩ እዲገለጥ እንዲሁም እግዚአብሔር ትክክለኛውን ጊዜ አዋቂ ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህ በሕይወታችሁ በሚገጥሟችሁ ችግሮች ሳትደናገጡ እና ተስፋ ሳትቆርጡ በእምነትና በትዕግሥት ሆናችሁ የእግዚአብሔርን መልስ ጠብቁ፡፡ ቢዘገይም ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይመጣል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- ወጣቶች እምነታችሁን እና ትዕግሥታችሁን የሚፈታተን ችግር ሲገጥማችሁ በመጽሐፍ ቅዱስ የእነ ኢዮብን፣ የአብርሃምንና የዮሴፍን... ወ.ዘ.ተ የሌሎችንም ቅዱሳን ታሪክ በማንበብ እነርሱን ያበረታ አምላክ ጉልበት እንዲሆናችሁ ጸልዩ፡፡

# ባለ ራእይ ወጣት

## አርባ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ራእይ ምንነት አውቀው በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻቸው ያስረዳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ" ት/ኢዮኤል ፪÷፳፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ት.ኢዮ. ፪÷፳፰-፴፪፣ የሐዋ/ሥራ ፪÷፲፯-፳፣ ዘፍ. ፲፪÷፩

## መግቢያ፡-

- ወጣቶች ራእያችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ወጣቶች ታስታውሱ እንደሆነ ልጆች ሆናችሁ ምን መሆን ትፈልጋለህ? ምን መሆን ትፈልጊያለሽ? ተብለን ስንጠየቅ የብዙዎቻችን መልስ ኢንጂነር፣ ፓይለት፣ ዶክተር… ወ.ዘ.ተ ነበር፡፡ አሁንስ ምን መሆን እንደምትፈልጉ ታውቃላችሁ? በሕይወታችሁ እውን ልታደርጉትና ልታሳኩት የምትፈልጉት ነገር ምንድነው? ወጣቶች ራእይ ሊኖራችሁ ይገባል፡፡ ለወጣቶች የሚያስፈልገው ራእይ ነው፡፡ ራእይ የሌለበት ጉብዝና ከንቱ ነው፡፡ ራእይ የሌለበት ትምህርት ከንቱ ዕውቀት ነው፡፡ መኪና ኃይል(ጉልበት) አለው፤ ኃይሉን ወይም ጉልበቱን ጠቃሚ የሚያደርገው ግን መሪው ነው፡፡ ለትልቁ መኪና መልካም መድረሻ ፍጻሜውን የሚወስንለት መሪው እንጂ ኃይሉ(ጉልበቱ) ብቻ አይደለም፡፡ ልክ እንደዚሁ ሁሉ ወጣቶች ጥሩ የመማር ፍላጎት፣ ብዙ ዕውቀትና ጥሩ መረዳት ቢኖራችሁ ራእይ ግን ከሌላችሁ ዕውቀታችሁን እንዴት መጠቀም እንዳለባችሁ በተለይም መድረሻችሁን ስለማታውቁ መንገድ ላይ ትቀራላችሁ፡፡ ስለዚህ ለምን እንደምትኖሩ? ለምን እደምትማሩ? ወደፊት ምን መሆን እንደምትፈልጉ? ግልጽ የሆነ ዓላማ እና ራእይ ሊኖራችሁ ይገባል፡፡

www.zeorthodox.org

### 1. ራእይ ምንድነው?

ራእይ ምንም በማይታይበት ስፍራ ላይ የሚታየን ክቡር ነገር ነው፡፡ ራእይ በእግዚአብሔር ይጀመራል፤ በእግዚአብሔር ይከናወናል፤ በእግዚአብሔር ይፈጸማል፡፡ ራእይ በመቻላችን ወይም ዛሬ

ባለን ማንነት ላይ አይደገፍም፡፡ እንዲያውም በማንችለው ነገር ላይ እግዚአብሔር እንደሚያስችለን እናይበታለን፡፡ ራእይ ከሕልም የተለየ ሆኖ እግዚአብሔርን ለሚያውቁና የእግዚአብሔር መንፈስ ላደረባቸው የሚሰጥ ነገር ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ራእይ የታያቸው ነቢያት ብዙ ሲሆኑ በተለይ ሕዝቅኤልና ዳንኤል ብዙ ራእይ አይተዋል፡፡ በሐዲስ ኪዳንም የእግዚአብሔር ፈቃድ ለዘካርያስ፣ ለሐናንያ፣ ለቆርኒልዮስ፣ ለጴጥሮስ፣ ለጳውሎስና ለዮሐንስ በራእይ ተገልጦአል፡፡ (ሉቃ.፩፥፳፪፣ የሐዋ.ሥራ ፱፥፲፣ ፲፥፫፣ ፲፥፱-፲፯፣ ፲፩፥፭፣ ፲፰፥፱፣ ራእ. ፩፥፲፯-፲፱፣ ፬፥፲፩) እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው ራእይ እንዲኖረው ይፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ራእይ የሌለው ትውልድ ወይም ሕዝብ መድረሻውን የማያውቅ መረን ስለሚሆን ነው፡፡ ትልቁ የሕይወት ምስጢር ያለው በማየት ውስጥ ሲሆን ይህም ራእይ ነው፡፡ እግር ዓይን ወደ አየበት ይራመዳል፡፡ መሪ መሆን የሚችለው ቀድሞ ያየ ሰው ነው፣ ምክንያቱም መሪነት ሹመት ሳይሆን የማየት (ባለራእይ) የመሆን ጉዳይ ነው፡፡ ራእይ ሁሉን ሰው እንደጠቃሚው እንደ ለውጥ አጋሩ ያየዋል፡፡

## 2. የባለ ራእይ ባሕርይ

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ዮሴፍ ባለ ራእይ ወጣት ነበረ፡፡ /ዘፍ. ፴፯፥፩-፲፩/ ዮሴፍ በወጣትነት ዕድሜው በጉብዝናው ወራት በአሥራ ሰባት ዓመቱ ከእግዚአብሔር ራእይን ተቀበለ፡፡ የራእይን ምንነትና ባሕርይ በዮሴፍ ሕይወት እንመለከታለን፡፡ ሁሉም ነገር የራሱ የሆነ ሥነ ምግባር አለው፡፡ አንድ መምህር በማስተማር ሥራው ውጤታማ ለመሆን የአስተማሪነት ሥነ ምግባሮችን ማክበር አለበት፡፡ ያለ ሥነ ምግባር ካሰቡት ግብ መድረስ አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ሥነ ምግባር ከሌለን ሥራችንን በተቀላጠፈ ሁኔታ በአግባቡ ለማከናወን አንችልም፡፡ ስለዚህ ባለ ራእይ ከሌሎች የሚለይበት የሚከተሉት መመዘኛዎች አሉት፡፡

### 2.1. ባለ ራእይ አርቆ ተመልካች ነው፡፡

እግዚአብሔር ዮሴፍ የሆነውን ሳይሆን ወደ ፊት የሚሆነውን ስላየለት ራእይ ሰጠው፡፡ ባለ ራእይ ዓይኑ በፍጹም ልቡ የሚያምነው እና ተስፋ የሚያደርግበት የእግዚአብሔር ዓይን ስለሆነ ዛሬ የሆነውን ሳይሆን ነገ የሚሆነውን ያያል፡፡

### 2.2. ባለ ራእይ እምነቱን በእግዚአብሔር አድርጎ ራሱን ለሌሎች የሰጠ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

### 2.3. ባለ ራእይ ሓላፊነት ይሰማዋል፡፡

### 2.4. ባለ ራእይ ጉዳቱን አይቆጥርም፤ ለመሥዋዕትነት የተዘጋጀ ነው፡፡

ዮሴፍ ጉዳቱን አልቆጠረም፤ በዚህ የተነሣ ወንድሞቹ ሲጨክኑበት፣ በሐሰት ሲከሰስና ወደ እስር ቤት በግፍ ሲወርድ ጉዳቶቹን እየቆጠረ አላጉረመረመም፡፡ ዮሴፍ የዛሬ ጉዳቱን ሳይሆን ነገ የሚሆነውን እየተመለከተ ጸና ታገሰም፡፡ ሙሴ የፈርዖንን ቤተመንግሥት የተወው ባለ ራእይ ስለነበረ ነው፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች በዚህ ትምህርት የሚያስፈልጋችሁ ኃይል ሳይሆን ራእይ እንደሆነ ተምራችኋል። ራእይ የሌለበት ጉብዝና ከንቱ ጉብዝና መሆኑን፤ ራእይ የሌለው ዕውቀትም ከንቱ መሆኑን ተገንዝባችኋል። ስለዚህ ዛሬ ካላችሁ አቅምና ችሎታ በላይ እግዚአብሔር ባለ ዓላማ ሲያደርጋችሁ የሚኖራችሁ አቅም እንደሚበልጥ አውቃችሁ በራእይ ማደግን እና መኖርን ተማሩ።

## ተግባር፡-

- መምህሩ ወጣቶች ስለ ራእይ ያላቸውን ግንዛቤ የበለጠ የሚያስፋፉበትን ሥልጠናዎችን እንዲገኙ ያድርጓቸው።
- መምህር ወጣቶች ስለ ራእይ ምንነትና ባሕርይ የተገነዘቡትን በክፍል ውስጥ እንዲገልጹና እንዲወያዩበት ያድርጉ።
- ወጣቶች እግዚአብሔር ራእይ እንዲሰጣችሁ በጸሎት ጠይቁት።
- ወጣቶች የባለ ራእይ ሰዎችን ሕይወት ታሪክ ዘወትር እንዲያነቡ መምህሩ ጥሩ ጥሩ መጽሐፍትን ይጠቁማቸው።

www.zeorthodox.org

# የእግዚአብሔርን መንግሥት መገንባት

## ሃምሳኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለወጣቶች ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እና በእግዚአብሔር የእነርሱን ሱታፌ ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** ‹‹መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ፡፡›› /ማቴ.፲÷፯-፰/

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፫÷፩-፲፪፣ ራእ. ፳፩

### መግቢያ፡-

አዳምና ሔዋን በኃጢአት ወድቀው ከገነት ከተባረሩ በኋላ በሰይጣን መንግሥት እና ግዛት ሥር ወደቁ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞታችንን በሞቱ ሽሮ የባርነታችንን ቀንበር ሰባብሮ ነጻ እስኪያወጣን ድረስ ሰው ሁሉ በሰይጣን ግዛት ውስጥ የኃጢአት ባሪያ ሆኖ ይኖር ነበር፡፡ በክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት የእግዚአብሔር መንግሥት ተመሠረተ፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎችን ለእግዚአብሔር መንግሥት የንስሓ ጥምቀት እያጠመቀ ያዘጋጅ ነበር፡፡ (ማር. ፩÷፩-፱) መጥምቁ ዮሐንስ አልፎ ከተሰጠ በኋላ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከና፤ ዘመኑ ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ፤ እያለ ወደ ገሊላ መጣ፡፡ (ማር. ፩÷፲፬-፲፭)

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

#### 1. የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ

የእግዚአብሔር መንግሥት እግዚአብሔር የሚነግሥበት መንግሥት ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚከብርበት አምልኮ፣ አገልግሎትና እርሱ የሚገዛው ሕይወት የእግዚአብሔር መንግሥት ይባላል፡፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚገዛ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ ክርስቶስ ባለበት የእግዚአብሔር መንግሥት አለ፡፡ በዚህ መሠረት “የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናት፡፡” (ሉቃ. ፲፯÷፳፩) ብሎ ክርስቶስ አስተማረ፡፡ ስለዚህ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲገቡ በጥምቀት ዳግመኛ መወለድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ (ዮሐ. ፫÷ ፫-፭) ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር የእግዚአብሔር መንግሥት ናት፡፡ ኢየሱስ በዚህ ምድር ሳለ መንግሥቱ ነበረ፣ አሁንም አለ፡፡ በመጨረሻም መንግሥቱ ይገለጣል፡፡ በመንግሥቱ እውነተኞችና ሐሰተኞች ለጊዜው አንድ ላይ ይኖራሉ፤ በዓለም መጨረሻ ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ ግን ይለያሉ፡፡ (ማቴ. ፲፫÷፳፬-፴፣ ፲፫÷፴፮-፵፫)

www.zeorthodox.org

## 2. ልባችን የእግዚአብሔር መንግሥት ዙፋን ነው

የሰማዩ መንግሥት የሚጀምረው በዚህ ምድር ክርስቶስን በልባችን ስናነግሠው ነው። ክርስቶስ በልባችን ሊነግሥ ዘወትር ልባችንን ያንኳኳል። /ራዕ. ፫÷፳ ጌታ "ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ ዓይኖችህም መንገዴን ይውደዱ" ምሳሌ ፳፫÷፳፮ ይላል። ነገር ግን ክርስቶስ የተለየ ንጉሥ ነው። ክርስቶስን የተለየ ንጉሥ የሚያደርገው በመንግሥቱ ማንንም ስለማያስገድድ እና በፍቅር ስለሚገዛ ነው።

## 3. የሰማዩን መንግሥት ለመገንባት የእኛ ተሳትፎ (ሱታፌ) ምንድነው?

የእግዚአብሔርን መንግሥት ከመገንባታችን በፊት መንግሥቱ ከምን እንደሆነ ማወቅ አለብን። በዮሐንስ ራእይ የእግዚአብሔር መንግሥት ምን እንደሆነ እና ከምን እንደሚገነባ በግልጽ ተቀምጧል። "እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱም ጋር ያድራል፤ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል።" (ራእይ ፳፩÷፫-፬) ከዚህ ቅዱስ ቃል እንደምንረዳው የእግዚአብሔር መንግሥት የተገነባው በሰዎች ነው። ስለዚህ ሌሎች ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አምጥተናል? ብለን ራሳችንን ልንጠይቅና የእኛ መዳን ብቻ ሳይሆን የሌሎች መዳንም ሊያስጨንቀን ይገባል።

የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመገንባት ጠንካራ ሠራተኛ መሆንን፣ በዓላማ መጽናትን እንዲሁም ትልቅ መሥዋዕትነትን ይጠይቃል። ለሰዎች ሳንሰለች ስለ ክርስቶስ መመስከርን፣ ጊዜያችንን ለማስተማርና ለማገልገል መስጠትን፣ ያለንን ለሌሎች ማካፈልንና የሥጋ ምኞታችንን መተውን ሁሉ ያጠቃልላል። ቅዱሳን ሐዋርያት የክርስቶስን መንግሥት ለመገንባትና ለማስፋት ያላቸውን ሁሉ ሰጥተዋል። የቤተ ክርስቲያን ጌጦች የሆኑ ቅዱሳንም ዓለምን ንቀው ያገለገሉትና ዋጋ የከፈሉት የክርስቶስን መንግሥት ለመገንባት ነው። ስለዚህ ወጣቶች የክርስቶስን ሥራ በመሥራት መምጣቱን ልትጠባበቁ ያስፈልጋል።

## ማጠቃለያ፡-

ወጣቶች ዕለት ዕለት በኑሮአቸው ክርስቶስን በመግለጽ ወንጌልን በመስበክ ለመንግሥቱ ብዙ ሰዎችን ልታመጡ እንደሚገባ በዚህ ትምህርት ተረድታችኋል። ስለዚህ በኑሮአችሁ ክርስቶስን በመምሰል ለሰዎች እውነትን፣ ፍቅርንና ሰላምን በመስበክ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲገቡ መሪ ሁኑ፤ ራሳችሁን ለሌሎች መሰናክል ከመሆን ጠብቁ።

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- ወጣቶች ከትምህርቱ ያገኙትን ግንዛቤ መነሻ በማድረግ፤ እንዴት የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደሚያስፋፉ ውይይት እንዲያደርጉ መምህሩ እገዛ ያድርጉላቸው።

# ዋቢ መጻሕፍት

- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም።
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኝኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም።
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፪፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም።
- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም።
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም
- ኀሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም
- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም።

www.zeorthodox.org

- ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
- H.G. Bishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.
- በጠቅላይ ቤተ ክህነት። 2000 ዓ.ም። የኢትዮ. ኦርቶ.ተዋ. ቤ.ክ ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም። አዲስ አበባ ፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፥ ዶ/ር )። 2000። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግዕዝ ቋንቋ ። አዲስ አበባ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ
- የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። 1996 ዓ.ም። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ። ንግድ ማተሚያ ቤት።
- ጎርጎርዮስ(ብፁዕ አቡነ)። 1996 ዓ.ም። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ። አዲስ አበባ። ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።
- መሐሪ ትርፌ (በሊቀ ሊቃውንት)። 19 ዓ.ም። የጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው። አዲስ አበባ።
- ዳንኤል ተሾመ። 19 ዓ.ም። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችና የትርጉም ስልቶች። አ.አ
- Pulpet ; 19 A.D; Bible commentary The Epistle of paul to the ROMAN;
-


www.zeorthodox.org


-Tadros Yakob Malaty (Father); 2007-2008 A.D; The Epistle of Saint Paul to the Romans; Alexandria,Egypt.
- መብራቱ ኪሮስ (ዲያቆን)። አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ። የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ያልታተመ መማሪያ።

- ጎርጎርዮስ (በብፁዕ አቡነ):: 1981 ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ:: አዲስ አበባ::
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር ):: 2001:: የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ 1ኛ እና 2ኛ:: አዲስ አበባ::
- Lule Melaku (Asst. Professor); 2010; History of the Ethi. Orthodox Tewahido Church; A.A ; Elleni p.p.plc.
- ሰሎሞን መላኩ(ዲያቆን):: 2001ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት:: አዲስ አበባ:: ባናዊ ማተሚያ::
- Syrian Sunday school curriculum.
- Introduction to Coptic orthodox Church ; Father Tadros Y Malaty
- Ian Gillman,Hans-Joachim Klimkeit ; Christian in asia before 1500 ;
- ዜና ሐዋርያት
- ገድለ ቅድስት አርሴማ
- ሺኖዳ(ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ) ቅንዓት
- የኢትዮፕያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ.ክ ፤ ስንክሳር ፤ በትንሳኤ ዘጉባዔ ማተሚያ
- ያሬጋል አበጋዝ (ዲ/ን):: ቅዱስ ዩሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ ፤ አዲስ አበባ
- በጌታቸው ኃይሌ(ፕሮፌሰር):: 1997 ዓ.ም:: የአባ ባሕርይ ድርሰቶች
- ዳንኤል ክብረት(ዲ/ን):: 1998ዓ.ም:: የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች:: አዲስ አበባ:: ሜጋ ማተሚያ ቤት::
- .........:: አዋልድ መጻሕፍት:: ሐመረ ተዋሕዶ::
- Douglas J.D and Tenney M.c (1987) New International BIBLE DICTIONARY. ZONDERVAN'S.Grand Rapids,MICHIGAN USA
- Holy Trinity College.(2004) Patrology፡ Holy Trinity College module/ unpublished./
- Malaty T.Y( Father)Patrology ;

www.zeorthodox.org

- Malaty T.Y( Father).(199). Tradition and Orthodoxy. Alexandria .Egypt.
- ማኅበረ ቅዱሳን፡፡ 2004 ዓ.ም፡፡ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ የማዕረግ ቃል ማተሚያ ቤት፡፡
- ነገረ ማርያም
- Shenoda - Pope (1999). The Holy virgin Saint Mary. Cairo,Egypt.
- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡ (1988) ወንጌል ቅዱስ ትርጓሜ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
- የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት መማሪያ ፤ ካናዳ
- ሺኖዳ ሰው ምንድነው ፤ በብጹዕ ወቅዱስ ፤
- ክርስቲያን አንትሮፖሎጂ
- ሺኖዳ (ብጹዕ ወቅዱስ ፤ አቡነ)፡፡ መንፈሳዊው ሰው
- John Mark (Father). 19 . Ascending the heights ; A lay man guide to the ladder of divine ascent
- አበራ (በሊቀ ጉባዔ ፤ አባ)፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን፡፡
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 200 ዓ.ም፡፡ መሸኮርመምና ማሸኮርመም፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ ቅድመ ጋብቻ፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ተስፋ ገብረ ሥላሴ፡፡ 1988፡፡ መጽሕፍተ መነኮሳት፡፡ አዲስ አበባ
- ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት፡፡
- ጥዑመ ልሳን፡፡() ያሬድና ዜማው፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- ሙሳ (ሊቀ ጳጳስ)፡፡ ወጣትነትና የቅድስና ኑሮ፡፡ በመምህር ወንድወሰን ሶርሳ የተተረጎመ፡፡


www.zeorthodox.org